በተለያዩ ሰዎች ስፖንሰር የተደረገ እና ባለበት ሁኔታ ለማሰራጨት የተፈቀደ።

ፀኛ እትም (PDF)

2015 ኢት.አ.

ፊያት መገበያያ

እና

ወለድ

FIAT CURRENCY AND INTEREST



ዓ ብ ዱ ል ቃ ዲ ር ኑ ረ ዲ ን

ፊያት መገበያያ እና ወለድ

(FIAT CURRENCY & INTEREST)

ዓብዱልቃዲር ኑረዲን አህመድ

MSc in Accounting and Finance,

MBA

ኤዲተር፡ ኸውለት አህመድ በሺር

PHD Cndt, Islamic Banking and Finance,

Certified Shari'ah Finance Advisor and Auditor (CSAA)

MBA, CMA

የሸፋን ዲዛይን፡ ራህማ ሁሴን ዓብደላህ

MSc in Computer Science

© መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው።

Citation: Abdulkadir Nureddin (2022); Fiat Money and Interest (in Amharic Language); 7th Edition; 3S Printing, Addis Ababa, Ethiopia.

የመጽሐፉ ISBN: 978-99944-72-09-3o

አድራሻ፡-

Email: izzmak@yahoo.com

ለ8ኛ እትም የተሻሻለ፤

ዘመን፡ 2015 ኢ.አ.

አዲስ አበባ

ኢትዮጵያ

بِسْمِ اللهِ الرَّحْمٰنِ الرَّحِيْمِ



****

ከሰዎች ተመሲጋኞች

- ኸውለት አህመድ በሺር መጽሐፉን ኤዲት በማድረግ በሕትመት ሒደቶች ላይ በመተባበር
- ራህማ ዐብደላህ የዝግጅት ሒደት ላይ በመተባበር
- የመጀመሪያው ልጄ ዒዘልኢስላም ዐብዱልቃዲር እርማት ላይ በማገዝ

ታላቅ ምስጋና ለስፖንሰሮች

ሸይኽ አህመድ መሐመድ	በPDF እንዲለቀቅ ሐሳብ አቅርቦ የ100 መጽሐፍ ስፖንሰር
ዐብዱራህማን	የሸይኽ አህመድ ጓደኛና የ100 የከፈለ
መሐመድ ሳኒ	የ100 መጽሐፍ መጀመሪያ በፌስቡክ ቃል በመግባት
ራፋኤል አበቢል	የመጀመሪያው ከፋይ
ዐብዱራህማን ሰማን	በመክፈልም በማስተባበርም
InLine Trading PLC	የ200 መጻሕፍት ከፍተኛ ስፖንሰር እና **የጎደለውን የሞላ**
አብሬት ፕሮ	
ኸይራት መሐመድ	
ሸይኽ ኑሩ ጀማል ሲራጅ	
ወሊድ ዐሊ	
መሐመድ አስመላ	
በክሪ ድሬ	
ኸድር መሐመድዓለሙ	
አንተነህ ዘውዱ	
መሐመድ ሙሳ	
ዑመር መሐመድ እንድሪስ	
አይነታው አህመድ	
ማሕሙድ ሙኽታር	
ዓብዱልፈታህ አሚን	
ኤሊያስ ደነቀ	
ዒዘዲን ኑርሰቦ	
መሐመድ ዓለሙ	
ቃሲም መሐመድ	
ዑስማን አህመድ	
ሀሰን ኢብራሂም	
ብሩክ ካሳሁን ኃይሌ	
ሰይድ ዩኑስ ጎንደር	
ዐብዱዲን ሷቢር	
ሀምዲያ ነጋሽ ሱሩር	
አቡኻሊድ ኸይረዲን	
ዐብዱራህማን ኸይረዲን	
ጂብሪል ኸድር ዐብደላህ	
አህመዲን ሁሴን	
በድሪ ሰማን	
ጉተማ ሀይደር አባገሮ	
ያሚን አሚን ሰማን	
ካሚል ሰይድ ዐሊ	
ሀሰን ዐሊ እና የአባቱ ስም ዘይን የሚለው የሚታይ	
ብር ልከው ግን ስማቸውን ማውጣት ላልቻልኩና እንዲጻፍ ላልፈለጉ፣ ለመላክ አስበው ላልተሳካላቸውና በዱዓና በመልካም ምኞት ላገዙ ሁሉ ምስጋናዬ ይድረስልኝ።	
ከእነዚህ ውስጥ በአካል የማውቃቸው ከሦስት አይበልጡም።	

ቁልፍ ቃላት

- ✓ **ፈያት፡-** የወረቀት ወይም የቁጥር ገንዘብ
- ✓ **የተፈጥሮ ገንዘብ፡-** የወርቅ ወይም የብር ማዕድናትና የንብረት በንብረት ልውውጥ (ገንዘብ በኢስላም)
- ✓ **ወለድ፡-** አራጣ እና ወለድ በትርጉም ቢለያዩም በዚህ መጽሐፍ እንደ ተለዋዋጭ ቃላት ጥቅም ላይ ውለዋል
- ✓ **ኒክሰን ሾክ፡-** ገንዘብ በወርቅ ደጋፊነት መታተም የቀረበት የፕሬዝዳንት ኒክሰን ዓለም አቀፍ ንዝረት
- ✓ **“ኢስላማዊ ባንክ”፡-** ሙሉ ለሙሉ ከ “ወለድ ነጻ” የባንክ አገልግሎት ሊሰጡ የተቋቋሙ ባንኮች እና በመደበኛ ባንኮች ከ“ወለድ ነጻ” መስኮቶችን ይጨምራል።
- ✓ **ሴኩላሪዝም፡-** የተለያዩ አከራካሪ ትርጉሞች ቢኖሩትም “አንድ መንግሥታዊ ኃይማኖት እና/ወይም ኃይማኖታዊ መንግሥት የሌለበት ሥርዓት ማለት ነው።

****

ምሕጻረ ቃላት

- ✓ ﷺ፡ ሶለ኏ሁ ዓለይሂ ወሰለም (ሶላትና ሰላም በነቢዩ ላይ ይስፈን)
- ✓ **ረ.ዐ.፡** ረዲየ኏ሁ ዐንሁ (አላህ መልካም ሥራውን ይወደድለ(ላ)ት))
- ✓ **ኢ.ኢ.፡** የኢትዮጵያ አቆጣጠር ማለት ሲሆን ኢ.አ. ያልተባለባቸው ቦታዎች ያሉ የዘመን አቆጣጠሮች በሙሉ እንደ አውሮፓዊያን ዘመን አቆጣጠር ናቸው።

اللَّهُمَّ صَلِّ عَلَىٰ سَيِّدِنَا مُحَمَّدٍ وَعَلَىٰ آلِهِ وَصَحْبِهِ وَسَلِّمْ

ማውጫ

ምዕራፍ አንድ..... 5

ገንዘብ ምንድን ነው? 5

1.1. ትርጓሜ (Definitions).....8

1.2. የገንዘብ ዓይነቶች 17

1.2.1. የእሴት ወይም የዓይነት ገንዘብ በኢስላም.....26

1.2.2. የቁጥር ገንዘቦች (Non-Commodity Moneys).....47

1.2.3. ሲለካም ሲቀመጥም ዋጋ አለመኖር..... 117

1.2.4. የአራጣ ኢኮኖሚን ለማሳለጥ የተፈጠረ ስለመሆኑ..... 121

1.2.5. አስገዳጅ መሆኑ..... 123

1.2.6. ዘካን እንደ ምሳሌ..... 125

1.3. የዓይነትና የፊያት መገበያያ ንጽጽር 131

1.4. ግሽበት (INFLATION) እና መዋዠቅ (FLUCTUATION)..... 135

ምዕራፍ ሁለት 141

የሀገራችን ተግባራዊ ዕውነታዎች 141

2.1. የማሕበር ሱቆች..... 142

2.2. የኮንዶሚኒየም ወይም የመኖሪያ ቤቶች ዕድሎች..... 143

2.3. ኢንቨስትመንነት..... 146

2.4. የገንዘብ ኖት ሕትመትና የዜጎች የጋራ በጀት መሆኑ..... 153

2.5. ከገንዘብ ተቋማት ውጭ መበዳደር አለመቻሉ..... 160

2.6. ከገንዘብ ተቋማት ውጭ መንቀሳቀስና ማከማቸት አለመቻሉ 161

ምዕራፍ ሦስት..... 163

መውጫ መንገዶች..... 163

3.1. ችግሩን እና ደረጃውን ማወቅ..... 163

3.2. በሒደት እንጂ በአብዮት እንደማይፈታ..... 199

3.3. ያለውን ሲስተም መጠቀም..... 200

3.4. የባንክ ወለድን (interest) ለባንኮች አለመተው..... 205

3.5. ኮንቬንሽናል (መደበኛ) የፋይናንስ ኢንደስትሪዎችን መጠቀምና ባለቤት መሆን..... 207

3.6. የግብርና ልማት ባንክ እና ኢንቨስትመንት ባንክ..... 210

3.7. በወርቅ ሒሳብ ማስላት፣ መመዘንና መበዳደር..... 215

3.8. ኢስላማዊ የገበያ ሥርዓት መተግበር..... 219

3.9. “ኢስላማዊ ባንክ” ማቋቋም?..... 225

ምዕራፍ አራት 293

ኃላፊነት መስጠት..... 293

የፊያት መገበያያና የሸሪዓ አቋም 293

ይድረስ ለዑለማእ (ሊቃውንት) እና ኡመራእ (አስተዳዳሪዎች) 300

ኤፒሎግ፡- የእጅ ሥራ ትምህርት እና ፋይናንሻል ኢምፔሪያሊዝም 303

መግቢያ

ይህ መጽሐፍ ከወረቀት ገንዘብና ወለድ መጽሐፍ በኋላ ፈያት ገንዘብና ወለድ በሚል ሰም ለሰባት ጊዜ ያህል ታትሞ ተደራሽነቱን ለማስፋት ከማተሚያ ቤት ውጭ በኢነተርኔት እንዲለቀቅ ተሻሽሎ የተዘጋጀና እንደ ስምንተኛ እትም ሊወሰድ የሚችል ነው። በመጽሐፉ የገንዘብና የወለድን ምንነት ከሳይንስና ከኢስላማዊ ኃይማኖት መጻሕፍት ተወስዶና አሁን ያለንበትን የፋይናንስና ኢኮኖሚ አሠራር የተፈተሸበት ነው።

በአራት ምዕራፎች የተከፋፈለ ሲሆነ ምዕራፍ አንድ ስለ ገንዘብ ምንነትና ታሪኮች፣ ምዕራፍ ሁለት ስለ ሀገራችን ነባራዊ ሁኔታዎች፣ ምዕራፍ ሦስት መውጫ መንገዶችና ምዕራፍ አራት ለኢስላም ሊቃውንት ጥሪ የቀረበበት ነው። ታሪኩንና ወቅቱን ከማስረዳት ጋር የአስልምና ኃይማኖታዊ መጻሕፍት አንቀጾችን እንደ ቋሚና የማይለወጡ ሕግጋት ተወስደው ዘመኑን ከሕግጋቱ ጋር ለመተርጎም ተሞክሯል።

ሪባ (ወለድ፣ አራጣ) ክልክል መሆኑ ማንም ያውቃል። አስተማሪም አይሻም። ሀላልና ሀራም (ፍቁድና ውጉዝ) ግልጽ ስለሆኑ የተለየ ዕውቀት አይፈልጉም። ኃይማኖትም አይገድባቸውም። በተፈጥሮ ይታወቃሉ። ሪባም አንዱ ስለሆነ ሀራምነቱ በሚታወቅ ነገር "ሀላል ነው አይደለም" ውስጥ አንገባም። ሆኖም ግን የምንጠቀማቸው ነገሮች የትኞቹ ሪባ ናቸው? የትኞቹ አይደሉም? የሚለው ላይ እናተኩራለን። አሁን ያለንበት ሥርዓቱ መሰረቱ ሪባ ነው። መሠረቱን ዘንግተን ቅርንጫፍ ላይ እንዳንክር ይህ መጽሐፍ ግንዛቤ ያስጨብጠናል።

ሀላል እና ሀራም የመበየን ብቸኛ ባለሙብት አላህ ነው። የሰዎች ስብስብ ሀራምን ሀላል አያደርግም። ሪባ መሠረቱ ክልክል በመሆኑ በየትኛውም ጊዜና ቦታ ፍቁድ አይሆንም። መቸገር ክልክላትን ፍቁድ አያደርግም። ከክልክልነታቸው ጋር ለችግር መሻገሪያ ይሆኑ ይሆናል እንጂ ቦታና ሁኔታ ክልክልነታቸውን አይሸረውም። የአሳማ ክልክልነትን (ሀራምነትን)፤ ረሃብ ፍቁድ (ሀላል) አያደርገውም። በረሃብ ከመሞት ለመሻገር አማራጭ ማጣት (ዶሩራ) ይሆን ይሆናል እንጂ ፍቁድ ምግብ አይሆንም። ግዴታነቱም ረሃብ ሊገድለው በደረሰ ሰው ላይ ይገደባል። ሪባም ቢሆን በተመሳሳዩ፤ ችግር ሀላል አያደርገውም። **(ዐብዱልቃዲር ሀጅ ኑረዲን አህመድ)**

ምዕራፍ አንድ

ገንዘብ ምንድን ነው?

ምዕራፉን **በአራት** ነጥቦች ከፍለን እናየዋለን።

1. **የገንዘብ ትርጓሜ**
2. **ገንዘብ በኢስላም (የእሴት ገንዘብ)፡- ማሟላት ያለበት አራት ነገሮች**
   - 2.1. በተፈጥሮው ምሉዕ መሆን (ለምሳሌ ወርቅ)
   - 2.2. ከነጃሳ (እርኩስ) ነገር መጽዳት (የአሳማ ቆዳ፣ ሲጋራ፣ ወዘተ. ያልሆነ)
   - 2.3. የማይጎዳ (ሲቀመጥ የማይቀንስ ወይም የማይጋሸብ)
   - 2.4. የማይገደዱበት
3. **ፈያት (የወረቀት/ቁጥር ገንዘብ)**
   - ታሪኮቹ
     - ✓ ቀደምት ታሪኮች
     - ✓ የ21ኛው ክፍለ ዘመን መሠረታዊ ለውጦች
   - መገለጫዎቹ
     - ✓ ገንዘቡ በተፈጥሮው አራጣ (ወለድ) መሆኑ
     - ✓ ሲለካም ሲቀመጥም ዋጋ የሌለው መሆን
     - ✓ የአራጣ ኢኮኖሚን ለማገልገል የተፈጠረ መሆኑ
     - ✓ አስገዳጅ ገንዘብ መሆኑ
     - ✓ ዘካ ላይ ለሚነሱ ጥያቄዎች
4. **የዓይነትና የወረቀት (ፈያት) ንጽጽር**

መንደርደሪያ

ገንዘብ የግብይት ቋንቋ ነው። ገንዘብ የግብይት ማዕከላዊ መዘውር ነው። “ገንዘብ” የሚለውን ቃል ስንሰማ “ዱንያ” ማለትም ይህኛው ዓለም የማለት ያህል ይደርሳል። ስለዚህ ምንነቱን ማወቅ አጠቃቀሙን ከማወቅም ሊልቅ ይችላል። ይህ ሆኖ ሳለ “የገንዘብ ምንነትና ታሪካዊ አመጣጥ” በጣም የተዘነጋ ጉዳይ ነው ማለት ይቻላል። ከየት ተነስቶ የት ደርሷል የሚለውን ካየን የወደፊት አካሄዱንም ለመገመት ይረዳናል። ምክንያቱም አሁን እየተጠቀምንበት ያለው ገንዘብ አሁንም ወደሌላ ውስብስብ የገንዘብ ሥርዓት እየተቀየረ ነውና። በምዕራፉ ገንዘብን በሁለት ከፍለን እናየዋለን። ሦስተኛው ነጥብ የተጨመረው ሁለቱን ገንዘቦች ለማነጻጸር ነው። የመጽሐፉ ዋነኛ ትኩረት አሁን ያለውን የወረቀት መገበያያ ምንነት ማሳወቅ እንጂ ድሮ የነበረውን ታሪካዊ ገንዘብ ለመተረክ አይደለም። ስለወረቀት መገበያያ ስናወራ ወደ ወረቀትነት/ቁጥርነት የተቀየረበትን ታሪክ ማየታችን የግድ ብቻ ሳይሆን ወሳኙም ክፍል ነው። ለዚህ መነሻችን ደግሞ የዓይነት (እሴት) ገንዘብ ነው። ጉዳዩን “በአንድ እንጨት ሁለት ወፍ ማዳን” (ከመግደል ማዳን) ዓይነት ነገር አድርገነው ከተፈጥሮም ከኢስላምም ሕግጋት አኳያ ማየቱ ደግሞ የተሻለ ነው። ምክንያቱም ኢስላምም እነዚሁ የተፈጥሮ ወይም የእሴት ወይም የዓይነት ገንዘቦችን ተቀብሎ አጽድቆአቸዋል። በመሆኑም መሠረታዊ የኢስላም የአምልኮ ምሰሶ የሆነው ዘካ የተመሠረተውም በእነዚሁ በዓይነት /እሴት፣ንብረት፣ የተፈጥሮ/ ገንዘቦች ላይ ነው። ከዚህም በተጨማሪ በኢስላማዊ ሕግጋት ውስጥ ሰፊ ቦታ የተሰጣቸው እንደነ ውርስ፣ ከጋብቻና ፍቺ ጋር የተያያዙ ገንዘቦች እንዲሁም የግብይት ማካሄጃ፣ የሀብት ማጠራቀሚያዎች እና ወለድ በእነዚሁ ገንዘቦች መሠረት የተደነገጉ ናቸው።

እዚህ ጋር አንድ ማስገንዘቢያ ማንሳቱ አስፈላጊ ነው። የተፈጥሮ ገንዘቦችን ኢስላማዊ ገንዘብ" ከምንል "ገንዘብ በኢስላም" ብንል የተሻለ አገላለጽ ነው። ምክንያቱም ከኢስላማዊ አስተዳደርና እምነት ውጭ ያለው እምነትም አስተዳደርም የተጠቀማቸውና እየተጠቀማቸው ያሉ ገንዘቦች ናቸው። የወረቀት መገበያያን የፈጠሩና የሚቆጣጠሩ ሀገራትና ሥልጣኔዎችም ጭምር ዛሬም ድረስ ሙሉ ለሙሉ ትተዋቸዋል ማለት አይቻልም። የቀድሞው ገንዘብ ከሰፊው ሕዝብ የግብይት ሥርዓት ቢወገድም ለተለያዩ የመንግሥታዊ አገልግሎቶች ዛሬም ድረስ ያገለግላል። ሙስሊም የሆነም ያልሆነም ሰው የጋራ መጠቀሚያ በመሆናቸው፣ ንግድ ከሙስሊምም ሙስሊም ካልሆነውም ጋር መነገድ ሀላል (ፍቁድ) በመሆኑ የኢስላም የገንዘብ ሕግጋት ከሌሎች እምነትና ሕግጋት ጋር ሳይጋጩ ለዘመናት ኖረዋል። በመሆኑም የኢስላም ብቸኛ ንብረት ናቸው የሚያስብል ነገር የላቸውም። ታዲያ እኒሁ የተፈጥሮ ማለትም የወርቅ፣ የብርና መሰል ማዕድናት ገንዘቦች እምነቱ እንደ ፍቁድ (ሀላል) ገንዘብነት ሲቀበላቸው የራሱ ሕግጋት አስቀምጦላቸዋል። ስለዚህ ሕጉን ነው ኢስላማዊ የምንለው እንጂ ገንዘቡን አይደለም። ብዙም ሳንርቅ እዚሁ ከስር ትርጉም ላይ ብቻ ብናይ እንኳ "ስለ ዕውነተኛው ገንዘብ" የኢስላማዊው አተረጓጎምና የመደበኛው የኢኮኖሚክስ አተረጓጎም ልዩነት ያላቸው ሆነው አናገኛቸውም። ለጋራ ግንዛቤ ያህል የሚከተሉትን ትርጉሞችን እንይ።

ማሳሰቢያ፡- ይህ PDF ከዚህ መጽሐፍ ቀጥሎ ከታተመው መ-ገንዘብ መጽሐፍ በኋላ ማሻሻያ ስለተደረገበት አንዳንደ ቦታ ላይ "በመ-ገንዘብ መጽሐፍ ተዳሷል" የሚል ነገር ሊገጥማችሁ ይችላል። ፍላጎቱ ያለው ሰው ለተጨማሪ ማብራሪያ እንዲጠቀመው ከማሰብ ነው።

1.1. ትርጓሜ (Definitions)

(ትርጉሞቹ ከመ-ገንዘብ መጽሐፍ የተወሰዱ ናቸው)[1]

ሀ. አጠቃላይ ትርጉም[2]

ገንዘብ ረጅም ታሪክ ያለውና በሁሉም ማኅበረሰብ ውስጥ ጥቅም ላይ የሚውል በመሆኑ፤ ከዘመን ዘመንና ከቦታ ቦታ የተለያዩ ትርጉሞች ተሰጥተውታል። ረቂቅ እና የማይጨበጥ ባሕሪይ ከሚጨበጥ ዕቃ ጋር ስለተጋመዱበት፤ በትክክል ይህ ነው ብሎ ለመደምደም ያዳግታል። የተለያዩ ጸሐፍት ስለገንዘብ ያስቀመጡትን ትርጉሞችን እንመልከት።

- *ገንዘብ ማለት አጠቃላይ ወይም ዓለማቀፋዊ ተቀባይነት ያለው እና በኦፊሴል ደረጃ በማዕድን (ብረታ ብረት) ሣንቲም የሆነ (የታተመ) የመገበያያ ቋንቋ ነው።*[3]

- *ገንዘብ ማለት ማንኛውም ዕቃ ወይም መረጋገጥ የሚችል መዝገብ (VERIFIABLE RECORD) ሆኖ ለዕቃና አገልግሎት ክፍያ ተቀባይነት ያለው እና በተለይ ለአንድ ሀገር መንግሥት ዕዳ መክፈያ መሣሪያ ነው*[4]*።*

[1] ይህ ለፒ.ዲ.ኤፍ. የተዘጋጀው ጽሑፍ ውሱን ቦታዎች ላይ ከዚህኛው መጽሐፍ በኋላ ከታተመው "መ_ገንዘብ" መጽሐፍ ላይ የተወሰዱ አሉ።

[2] Stefano Battilossi, Youssef Cassis, Kazuhiko Yago; Handbook of the History of Money and Currency; Origins of Money and Interest: Palatial Credit, Not Barter, ISBN 978-981-13-0595-5 (አብዛኞቹ ትርጉሞች ብዙ የጥናት መጻሕፍት ከያዘው ከዚህ ጥራዝ ውስጥ ይገኛል።

[3] Money: ሜሪየም ዌብስተር መዝገበ ቃላት

[4] Mishkin Frederic S., The Economics of Money, Banking and Financial Markets, 4th edition, Pearson, 2011, Page 43

- *ገንዘብ ማለት የነገሮች (ዕቃዎች) እና የአገልግሎቶች ባለቤትነትን በነጻና በፈቃደኝነት ማስተላለፊያ የሆነ ኢኮኖሚያዊ መሣሪያ ነው።*[5]
- *አሪስጣጣሊስ እንደጻፈው፡- ገንዘብ ማለት የሁሉም ነገር ማነጻጸሪያ ነው። ይህም የሆነው ነገሮችን በገንዘብ እስከተለካ ድረስ ነው*[6]*። በዚህም ገንዘብ ነባራዊ ዓለምን በረቂቅ ቁጥር የምናየይዝበት ካርታ (Map) በመሆኑ የተወሳሰበውን የዕቃዎችና የአገልግሎቶቸን ምንነት በመመተር ለማመሳከርና ለማገናዘብ ይረዳል*[7]*።*

- *"ገንዘብ የሚባለው የተወሰነና የተረጋገጠ ዋጋ ያለው ሲሆን ዋጋውም የማይጨምርም የማይቀንስም መሆን አለበት። ያ ገንዘብ የተሰኘው ነገር የሚዋዥቅ ከሆነ ሌሎች የሚቀንሱና የሚጨምሩ ንግድና ዕቃዎችን ልንለካበት አንችልም።"*[8]

[5] Sergio Focardi; Economics in the Real World: Money What It Is, How It's Created, Who Gets It, and Why It Matters-Routledge (2018). Park Square, Milton Park, Abingdon, Oxon OX14 4RN and by Routledge ISBN: 978-1-138-22894-8 (hbk)

[6] Aristotle, Nicomachean Ethics, Book V, trans. W. D. Ross (Kitchener, Ont.: Batoche, 1999), 80.

[7] David Orrell and Roman Chlupatý; The evolution of money; New York Columbia University Press; 2016; Page 45; ISBN 978-0-231-54167-1

[8] (ኢብኑል ቀይም፣ ዒላሙል ሙወቂዒን፣ 2/137-138)

ለ. ቴክኒካዊ ትርጉም፡- ገንዘብ እና/ወይም መገበያያ

- **ገንዘብ (Money)**፡- የሚዳሰስም ይሁን የማይዳሰስ የሀብትና ንብረት ጥቅል ስም ወይም ጥቅል ሲስተም ሲሆን ዋነኛ መገለጫው ለዋጋ ማስቀመጫነት (Store of value) ማገልገሉ ነው። ምሳሌ፡- ወርቅ፣ ብር፣ ጥራጥሬዎች፣ ነዳጅ ሊጠቀሱ ይችላሉ።[9]

- **መገበያያ (Currency)**፡- "ኩሬሬ" ከሚል የላቲን ቃል የመጣ ሲሆን "በራሪ፣ ፈሳሽ" የሚል ትርጉም አለው። ከሰው ወደ ሰው ሳያቋርጥ በመብረሩ ነው። በዘመኑ አሠራር በሉዓላዊ ሀገር ስም በወረቀት ወይም በብረት የታተመ በራሪ መገበያያ ነው።[10] ዋነኛ ባሕሪው ማገበያየት እንጂ ማስቀመጥ አይደለም። ምሳሌ፡- ፊያት ኖት

በእርግጥ አንዱ የገንዘብ ዓይነት አንዱ "Money" አንዱ "Currency" ሆኖ የሚመጣበት አጋጣሚ አለ። በአጠቃላይ "Money (ገንዘብ)" ስንል የዓይነት ወይም የንብረት ወይም የእሴት ሲሆን፤ "Currency (መገበያያ)" ደግሞ የቁጥር ገንዘቦችን ያመለክታል። የዓይነት ገንዘብ ለማገበያየት ከዋለ "Currency" ሆኖ ሊመጣ ይችላል። በእንግሊዝኛ የዕለት ተዕለት ንግግር ውስጥ "Money" እና "Currency" የሚባሉ ቃላት እናገኛለን። አማርኛው ላይ ሁለቱንም ገንዘብ እያልን ስንጠቀማቸው ቢታይም ቴክኒካዊ ትርጉማቸው ግን ይለያያል። እላይ

[9] Investopedia.com (በፋይናንስ ዘርፍ ሁነኛ ድረ-ገጽ)
[10] Etymonline ዲክሽነሪ

የመዝገበ ቃላትና የአገባብ አተረጓጎሞችን አይተናል። ቀጥለን በትግበራ ደረጃ ያሉትን ትርጉሞችን እናያለን።

ሐ. ተግባራዊ (Functional) ትርጉም

(ሀ) በዚህኛው ክፍል የቀረበው ወደ ፋይናንስና ኢኮኖሚ የተጠጋ አተረጓጎም ሲሆን በአገልግሎት መሠረት ከፋፍለን ለማየት ይመቸናል። በዚህ ዘርፍ የተጻፉ መጻሕፍት ገንዘብን በሦስት ተግባራት ይከፋፍሉታል። በአራትም በአምስትም የከፈሉ የተለያዩ ጸሐፍት አሉ። (ከ40 በላይ መጻሕፍትና ጥናቶች የተጠናቀሩበትና ከስር በግርጌ ማስታወሻ የተጠቆመውን "Handbook of the History of Money and Currency" እንድታነቡት ጸሐፊው ይመክራል)[11]።

በነዚህ መጻሕፍት ገንዘብን በሦስት ተግባራት ይከፍሉታል።

1. ለዋጋ ማስቀመጫነት (Store of value)፡- ቀልጠፍ ያለና አንድ ወጥ የዋጋ ማስቀመጫ ሲሆን ይህም የመግዛት ኃይልን ያጠራቅማል፣ ዋጋን ጨምቆ ያስቀምጣል፣ ረጅም ጊዜ ሲቀመጥ እንዳይበላሽም ያደርጋል።

(ጥሬ ወርቅና ጥሬ ጠገራ ብር ይህንን ማሟላት ሲችሉ ፊያት መገበያያ ግን አያሟላም። ምክንያቱም በዋለ ባደረ ቁጥር ስለሚጋሸብ ለዋጋ ማቆያነት አያገለግልም።)

[11] Stefano Battilossi, Youssef Cassis, Kazuhiko Yago, Handbook of the History of Money and Currency; Origins of Money and Interest: Palatial Credit, Not Barter, ISBN 978-981-13-0595-5 Page 51

2. ለኪ መሆኑ (Measure value)፡- ምርትና አገልግሎቶችን ይለካል። ለዚህም ወርቅና ብር ለረጅም ዓመታት ሰፊ ቅቡልነት ይዘው አገልግለዋል[12]።

(ጥሬ ጠገራ ብርና ጥሬ ወርቅ ሌላ እሴትን መለካት ሲችሉ፤ ፊያት መገበያያ ግን እራሱ በሌሎች እሴቶች ይለካል እንጂ ሌሎችን መለካት አይችልም። ምክንያቱም የትናንትናና የዛሬ ፊያት እኩል ዋጋ የላቸውም። ወርቅ ሰንት ሪያል ገባ? ሰንዴ ሰንት ሺሊንግ ገባ? እንላለን እንጂ ዩሮ ሰንት ሰንዴ ገባ? ዶላር ሰንት ወርቅ ገባ አይባልም። ፊያት ሰለሚዋዥቅ ሌላ እሴትን መለካት አይችልም።)

3. አገበያይና ተከፋፋይ መሆኑ (Transaction value & divisibility)፡- የመክፈልና የመከፋፈል ባሕሪይ ስላለው ለውስብስብ ክፍያዎች በክፍልፋይ እየሰነጣጠቁና እያከፋፈሉ ለመክፈል ይረዳል። ይህም የሚሆነው የምንከፋፍለው ነገር ጥራቱና ደረጃው ከታወቀ በኋላ ነው።

(ፊያት ወደ ክፍልፋይ ቁጥሮች መከፋፈል ይችላል። የሚያሟላው ይህንን ነው። ማገበያየት ላይ ግን እዚያው በዚያው (On spot) ሲሆን ነው። ግን ሲያድር ከትናንትናው ጋር እኩል ሰላልሆነ ዛሬ የምንገበያየው በዛሬው የፊያት ዋጋ ነው። ጥሬ ወርቅና ጥሬ ጠገራ ብር ከማገበያየት አልፈው እስከ አንድ ግራም ድረስ መከፋፈል ይችላሉ።

[12] Stefano Battilossi, Youssef Cassis, Kazuhiko Yago; Handbook of the History of Money and Currency; Origins of Money and Interest: Palatial Credit, Not Barter, ISBN 978-981-13-0595-5 Page 51

(ለ) ከሌሎች ጸሐፊዎችም ተመሳሳይ አከፋፈል እናገኛለን። ከስር የተጠቀሰው የኢኮኖሚክስ ትርጉም ከላይኛው ጋር ተመሳሳይ አከፋፈል አስቀምጧል። ለማጠናከር ተጨምሯል።

በኢኮኖሚክስ ገንዘብ ማለት ሲቀመጥ ዋጋ ያለው (A store of value) ንብረት ሆኖ ለግብይት በአጠቃላይ ተቀባይነት ያለው ሲሆን በመርህ ደረጃ በቀጥታ ንብረት የሚገዛበት ነው። "የውሊታ አለብኝ ማስታወሻ" (IOU NOTE) ወይም የልውውጥ ቢል እንደ መገበያያ መሣሪያ ሊያገለግል ይችላል እንጂ ገንዘብ ልንለው አንችልም። ሆኖም ግን በአጠቃላይ ለመገበያያ መሣሪያ የምንጠቀምባቸው ነገሮች የክፍያ መገልገያዎች ተብለው ይጠራሉ። ስለዚህ ገንዘብ ሙሉ ለሙሉ "ቶሎ ተመንዛሪ የሆነ ንብረት (Liquid asset)" ነው። አንድ ንብረት ቶሎ ተመንዛሪ ነው ስንል እራሱን በቀጥታ፣ ወዲያው፣ ያለምንም ተጨማሪ ወጪ ወይም ያለገደብ ክፍያ ሲፈጸምበት ነው[13]*።*

እላይ በኢኮኖሚክስና ፋይናንስ ለአብነት የተጠቀሱት በዘርፉ የሚገኙ ሌሎች ጸሐፍት ገንዘብን በተለያየ አቀራረብ ቢገልጹትም ትርጉማቸው ግን ተቀራራቢ ነው። በመሆኑም ከላይኛው ትርጉም በመነሳት በፋይናንስና ኢኮኖሚክሱ ገንዘብ ሦስት ዋና ዋና ባሕሪያት አሉት የሚል ጭብጥ እናገኛለን። እነሱም፡-

1) መገበያያና ክፍያ መፈጸሚያ [As a currency] ይህኛው በሁለት ተከፍሎ መገበያያን ለብቻ ክፍያ መፈጸሚያን ለብቻው ሊታይ ይችላል።
2) የንብረት (asset)፣ የዕዳ (liability) እና የሀብት (capital) መለኪያ [As a measurement]

[13]C.Groth (2012), Macroeconomics, University of Copenhagen, Page 579

3) ሲቀመጥ ዋጋ ያለው [As a store] የሚሉት ፍሬ ነገሮችን እንወስዳለን[14]።

ያለፉት ትርጉሞች ከመደበኛው ትምሕርት መጻሕፍት የሚገኙ የፋይናንስና የኢኮኖሚክስ ትርጉሞች ሲሆኑ ቀጣይ የኢስላም ኃይማኖት ያስቀመጣቸው አተረጓጎሞችን ከተለያዩ መጽሐፎች ተጨምቀው ቀርበዋል።

መ. ኢስላማዊ አተረጓጎም

ገንዘብ ማለት ንብረት (እሴት) ነው። ግብይት የሚካሄደውም ንብረትን በንብረት በመለወጥ ነው። ለዚህም በራሳቸው ዋጋ የሆኑ፣ መቆየት የሚችሉ፣ በስፍር ወይም በሚዛን የሚታወቁ እና የሚያገበያዩ፣ እርኩስነት (ነጃሳ የሌላቸው)፣ ለማይምም ጭምር ግልጽ ሆነው ለማጭበርበር ብዙም የማይመቹ የሆኑ ናቸው። ለግብይትና ልውውጥ ከማዕድንና ከምግብ ዓይነቶች ውስጥ ስድስት ተለይተዋል። እነርሱም፡- ወርቅ፣ ብር፣ ስንዴ፣ ገብስ፣ ተምር እና ጨው ናቸው። የግብይት ዕቃ ወይም አገልግሎት (Goods and services) ልኩ በማይታወቅ ወይም በማያመች ሁኔታ ላይ ከስድስቱ ውስጥ የወርቅና የብር ማዕድናትን እንደ መለኪያም፣ እንደ መገበያያም፣ እንደ ሀብት ማስቀመጫም እንጠቀማለን።

ሆኖም ግን በእነዚህ ብቻ ተገበያዩ የሚባል ገንዘብ የለም። በቁርጥ ቢወሰኑ ኖሮ ግዴታ ይሆንና ገንዘብ አምልኮ ወይም የጅነት/ጀህነም መለያ ይሆን ነበር። ግብይት ያለ አስገዳጅ በውዴታ ብቻ ነው። ከቁርአንና ከሀዲስ በመነሳት በተዋቀሩ በኢስላማዊ ሕግጋት (ፊቅሕ) ውስጥ ስድስቱ ገንዘቦች "አምዋለ-ሪበዊያህ" ይሰኛሉ። ትርጉሙም "አራጣ አምጪ" ወይም አራጣ በቀጥታ የሚመለከታቸው ገንዘቦች እንደማለት ነው።

[14] C. Groth Lecture Notes in Macroeconomics, (mimeo),2012,

ምክንያቱም አራጣና ንግድ ተቆራኝተው ይከሰታሉ። አራጣው ክልክል ሲሆን ንግዱ ፍቁድ ነው። ወርቅና ብር አራቱንም በመጠቅለል የሌሎች ግብይቶችም ማሳለጫ ናቸው። እነዚህ የተመረጡት ከዘመን ዘመን፣ ከቦታ ቦታ በእኩል ስለሚመመዘኑ፣ ስለሚመዝኑ፣ ስለሚስሰፈሩና ስለሚሰፍሩ፣ ለመካትም ይሁን ለመልለካት የማይዋዥቁ ስለሆኑ ነው። ገንዘብ እንደዚያ መሆን አለበት።

በቁርአንና በነቢያችን (ﷺ) ሀዲስ ገንዘብ የሚታወቅ ስም አለው። ዲናር፣ ዲርሀም፣ ወሪቅ (የተሰነተመ)፤ የሚሉ ስሞች አሉት። ስፍር እና ልኬት ማለትም “ሚኪያል” እና “ሚዛን” ይታወቃል። በሁሉም የዓየር ሁኔታ፣ ቦታና ድንበር ሳይገድበው፣ ወቅት ሳያስረጀው መኖር አለበት። ለዚህ ምቹዎቹ ወርቅና ብር ናቸው። ከዚህኛው ዓለም አልፎ የጀነት (ገነት) ዓለምም ድረስ ንብረቶች ናቸው። ስለገንዘብ አተረጓጎም ከኢስላማዊ ሊቃውንት መጻሕፍት የየትኛውም ዓለም፣ የምሥራቁም ይሁኑ የምዕራቡ፣ የዓረቡም ይሁን የአጀሙ (አረብ ያልሆኑት) ብንወስድ በትርጉም ላይ ልዩነት የላቸውም።

“ገንዘብ የሚባለው የተወሰነና የተረጋገጠ ዋጋ ያለው ሲሆን ዋጋውም የማይጨምርም የማይቀንስም መሆን አለበት። ያ ገንዘብ የተሰኘው ነገር የሚዋዥቅ ከሆነ ሌሎች የሚቀንሱና የሚጨምሩ ንግድና ዕቃዎችን ልንለካበት አንችልም።” (ኢብኑል ቀይም፣ ዒላሙል ሙወቂዒን፣ 2/137-138)

ማጠቃለያ፡- ትርጉሞቹ ገንዘብ በኢስላማዊውም በምዕራባዊውም ተቀራራቢ ትርጉም እንዳላቸው ያስገነዝቡናል። ሆኖም ግን አሁን እጃችን ላይ ያለው ገንዘብ ከትርጉሞቹ ጋር አንድ ነው ወይ? ብለን ብንጠይቅ ግን በጣም እንደተራራቁ እንደርስበታለን። ምክንያቱም ገንዘብ ወይም የገንዘብ ሲስተም በዘመናት ሒደት ብዙ


ዑደቶችና አዳዲስ ለውጦችን አስመዝግቧል። በተፈጥሮ ወይም በኢስላም “ገንዘብ” ተብሎ የሚታወቀው ገንዘብ እና አሁን ያለው ገንዘብ “እንቆቅልሽ” በሚባል ሁኔታ ከተጨባጭ ገንዘብነት ወደ ማይጨበጥ እና ከአየር ወደ ደቀቀና ወደ ረቀቀ መገበያያነት፤ በአንዳንድ ጸሐፍት ዘንድ “ቅዠት” ወደሚያሰኝ ነገር ተቀይሮአል።

በትርጉምና አተረጓጎም ደረጃ እንኳንስ በሙስሊም ሊቃውንት መካከል ልዩነት ሊኖረው ቀርቶ የኢስላማዊው አተረጓጎምና የዓለማዊው (የምዕራብ) ዘመነኛ ትምህርት አተረጓጎም ጋር ተቀራራቢ ነው። የኢስላማዊው የገንዘብ አተረጓጎምን ለንጽጽር ማቅረባችን፤ ከመሠረቱ ምን ያህል እንደራቅንና ከወለድና ከገንዘብ ተቋማት ጋር በተያያዘ የምናደርገው ክርክር የት ሜዳ ላይ እንዳለ ለማስተዋል ይረዳናል። በዚህ ክፍለ ዘመን በሙስሊም ሊቃውንት ስም የተሰራጩ ገንዘብ ነክ ሀይማኖታዊ ብያኔዎቻችን (ፈትዋዎቻችን) ሲታዩ ከዕውነታው በጣም የተራራቁና ምእመኑን ቅኝ ግዛት ስር የሚከቱ ናቸው ያስብላሉ። በተሳሳተ መሠረት ተነስተን ከመፍረዳችን በፊት ጉዳዩን በሚገባ ማወቅ የግድ ነው። ምክንያቱም “ሰው የመጣው ከዝንጀሮ ነው” ብለን ተቀብለን የምንሠራው ጥናትም ይሁን ብይን ውጤቱ ከእንስሳነት ወይም ከዝንጀሮአዊነት ብዙም አይርቅም። መሠረቱ ከተሳሳተ ውጤቱም የተሳሳተ ይሆናል። እላይ ትርጉሞቹን አይተናል። ቀጥለን ዓይነቶቹን እናያለን።

1.2. የገንዘብ ዓይነቶች

(ይህኛውም ንዑስ ክፍል ከመ-ገንዘብ መጽሐፍ የተወሰደ ነው)

ገንዘብ የረቂቅና የተጨባጭ ነገሮች ድምር ነው። በዚህም ገንዘብ ረቂቅ እና የማይጨበጥ አድርገው የወሰዱ እንዳሉ ሁሉ፤ በተቃራኒው ሙሉ ለሙሉ ቁስና ተዳሳሽ አድርገው የወሰዱም አሉ። የተለያዩ ጸሐፍት የተለያየ ዓይነትና ክፍፍል ቢያስቀምጡም አማካዩን ወስደን፤ (1) የዓይነት/የተፈጥሮ/የእሴት ገንዘብ እና (2) የቁጥር ገንዘብ በሚል **<u>በሁለት</u>** ከፍለናቸዋል።



አጭር ማብራሪያና ምሳሌ

- **የዓይነት / የተፈጥሮ / የእሴት ገንዘብ (Commodity Money)**

  የሚዳሰስ፣ የሚታይና ዕውነተኛ የሚባለው ገንዘብ ወይም ንብረት ነው። ምሳሌ፡- ወርቅ፣ ብር፣ መዳብ፣ እህል፣ ሲጋራ፣ መጠጥ ሊጠቀሱ ይችላሉ። መጠጥና ሲጋራ ጦር ሜዳና እስር ቤት አካባቢ እንደ ገንዘብ ስለሚያገለግሉ ነው። ግን ኢስላማዊው የገንዘብ ሥርዓት ከገንዘብነት ያስወግዳቸዋል። ገንዘብ በኢስላም እዚህ ስር ይመጣል። የገንዘቡ ዓይነት ከግሽበት ነጻ ነው። የዓይነት (እሴት) ገንዘብ ማለትም commodity money አሁን ባለንበት የዓለምም ይሁን የሀገራችን ሁኔታ ለሁሉም ሰው ተግባራዊ ለማድረግ በጣም አዳጋች ነው። ሥራ ላይ የሉም ማለት ግን አይቻልም። በደንብ እየተሠራባቸው ነው። በተለይ በመንግሥት ደረጃ አሁንም ድረስ አሉ። የደረጃ ጉዳይ ካልሆነ በስተቀር በወርቅ ዛሬም ግብይት ይካሄዳል። ሕዝብ ግን ፊያቶቹን ማለትም የወረቀቶቹን ይጠቀማል።

- **የቁጥር ገንዘብ (Non-Commodity Money)**

  ✓ **የፊያት መገበያያ (Fiat Currency)**፡- በአጭሩ የብሔራዊ ባንክ ወይም ማዕከላዊ ባንክ የገንዘብ ኖት ይሰኛል። መንግሥት በብሔራዊ ባንክ በኩል ያለ ምንም ደጋፊ ንብረት በወረቀት ወይም ብረታ ብረት እንደሳንቲም የሚያትመው ገንዘብ ወይም መንግሥታዊ የኮምፒውተር ዲጂታል መገበያያ ነው። ፊያት የሚለው ቃል በላቲን ቋንቋ "ይሁን፣ ይደረግ" እንደማለት ሲሆን "የፊት ገጽታ ወይም ፊት ለፊት" የሚል ትርጉምም አለው። ሁለቱም አተረጓጎሞች የቁጥር ወይም ወረቀት መገበያያ ባሕሪያት ናቸው። ቃሉ ለገንዘብ በተወራራሽ ትርጉምነት

ሲሰጥ “የአዋጅ ገንዘብ፣ ሕጋዊ ገንዘብ፣ አስገዳጅ ገንዘብ፣ የፊት ለፊት ገንዘብ፣ የይሁን ገንዘብ፣ የውክልና ገንዘብ” እያልንም ልንተነትን እንችላለን።[15] በአሁን ወቅት የምንጠቀምበት የወረቀት ወይም የቁጥር ገንዘብ ፊት ለፊቱ ላይ ካለው ቁጥር በስተቀር ውስጡ ምንም ዋጋ የሌለው በመሆኑና ያለንብረት ተያዥነት ስለሚታተም ነው ፊያት የሚባለው። በዚህ ጽሑፍ “ፊያት” ስንል መንግሥታዊ የብሔራዊ ባንክ የግብይት ኖት ወይም የቁጥር (ዲጂታል) ገንዘብ ማለታችን ነው።

- ✓ **ተወካይ መገበያያ (Representative Currency)፡-** ከጀርባው የሆነ ንብረት የያዘ ወረቀት ሲሆን ከመንግሥት ፊያት መገበያያ የሚለየው የንብረት ድጋፍ ስላለው ነው። ለምሳሌ፡- የአክሲዮን ሰርተፊኬት፣ የድርጅቶች ዲጂታል ቶከን እና መሰል ወረቀቶች ናቸው። (የፊያትን ክፍተት ተክቶ የሚሠራ ሲሆን፤ ለብቻው ሌላ መጽሐፍ የሚያስጽፍ ነው።

- ✓ **ፊጁሻሪ መገበያያ (Fiduciary Currency)፡- በባንኮች ለድርጅቶች** ታትመው የሚሰጡና በድርጅቶች ፈራሚነት ገንዘብን ወክለው የሚሠሩ ናቸው። ፊያት ገንዘቦች መንግሥት የሚፈርማቸውና ባለቤትነታቸው እጁ ላይ በያዛቸው ሰው የተገደበ ሲሆን ፊጁሻሪ ገንዘቦች ግን አብዛኛው ጊዜ ለተጻፈለት ግለሰብ ወይም ድርጅት ብቻ የሚያገለግሉ ናቸው። ለዚህ “ቼክ” ጥሩ ምሳሌ ነው።

[15]Gregory N. Mankiw (2014), Principles of Economics, University of N Gregory, Page 220.

- ✓ **የንግድ ባንኮች ገንዘቦች (Commercial bank Currency)፡-** እንደ ብሔራዊ ባንክ በሕትመት ሳይሆን በንግድ ባንኮች ብድሮችና መጠባበቂያ ተቀማጭነት የሚፈጠሩ ገንዘቦች ናቸው። Fractional reserves በአማርኛው "ክፍልፋይ መጠባበቂያ" ተቀማጮች የሚለው ሊቀርበው ይችላል። ይህኛው በዝውውር ላይ ያለው ድርሻ ከአስር ዘጠኝ እጅ ያህል ይገዘፋል። በኢትዮጵያ የ2015 በጀት ዓመት እስከ 93% የሚያደርስ መመሪያ ወጥቶለት ነበር። የፊያት ድርሻ በአማካይ 10% ሲሆን የንግድ ባንኮች በብድር የሚፈጠረው ገንዘብ ግን 90% ይሆናል። ዝርዝሩ ከስር ይመጣል።

- ✓ **ክሪፕቶከረንሲ (Cryptocurrency)፡** ያልተማከሉ (Decentralized) የክሪፕቶከረንሲ ተጠቃሚ ግለሰቦችን ምስጢራዊ የሒሳብ ቋት (encrypted ledger)ን በብሎክቼይኖች አሰናስሎ ግብይት የመፈጸም ወይም የማስተላለፍ ዘዴ ነው። **ይህንን ግን ገንዘብ ነው ብሎ ለመውሰድ ያዳግታል።**

የኮምፒውተርና የፋይናንስ ቃላት ጥምር ሲሆን፤ ክሪፕቶከረንሲን ለማወቅ እያንዳንዱን ተያያዥ ቃልና ሐረግ ለያይቶ ማየት ያስፈልጋል።

- ክሪፕቶ (Crypto)፡- ከግሪክኛ "kryptós' ከሚል ቃል የተወሰደ ሲሆን ትርጉሙም ምሥጢራዊ ወይም ድብቅ ማለት ነው ።
- ኢንክሪፕትድ (Encrypted)፡- ወደ ምስጢራዊ ኮድ የተቀየረ ማለት ነው። ከዋልታ ዋልታ፣ ወይም ከአንዱ ጫፍ እስከ

ሌላው ጫፍ፣ ወይም ከመነሻ እስከ መድረሻ ድረስ መልዕክት ሲተላለፍ ያልተፈቀደለት ሰው የማይገባበት፣ የማይጠልፈውና የማይሰብረው እንደማለት ነው። ምሳሌ በአሁን ዘመን ላይ “Whatsapp” ተብሎ የሚጠራው የኢንተርኔት የማኅበራዊ ሚዲያን ስንከፍተው “End to End Encrypted” የሚል ጽሑፍ እናገኛለን። ከጫፍ እስከ ጫፍ የተመሰጠረ የሚል ትርጉም ይሰጠናል። በሁለት እና ከዚያም በላይ በሆኑ መረጃ ተለዋዋጮች መካከል ሦስተኛ አካል ሰብሮ የማይገባበት እንደማለት ነው። ሰነድ በፖስታ ስንልክ ከላኪ ወደ ተቀባይ ሲሄድ፤ አድራሽ መልዕክተኛው እንዳይከፍተው በሰም እናሸገዋለን። ኢንክሪፕትድ ማለት ያልተፈለገ ወገን የማይገባበት ሲሆን በአጭር ትርጓሜ “የይለፍ ቃሉ (Passwords)” ከዕቃው (Hardware) ጋር የተቆራኘ ጥብቅ ልውውጥ እንደማለት ነው።

- ግራፊ (Graphy)፡- ግራፍ ከሚል የመጣ ሲሆን በስዕል ወይም በገጸ-ምስል (ቪዥን) የአንድን ነገር ምንነት መግለጽ። በሒሳብ ደግሞ ግራፍ ሲሳል የ“X” እና የ“Y”ን ነጥቦች እንደምናገኘው ኮምፒውተርም ላይ የተለያዩ የግኙኝነት ዋልታዎችን ወይም ብሎኮችን ወይም አንጓዎችን ማገናኘት ነው።
- ክሪፕቶግራፊ (Cryptography)፡- በምሥጢራዊ የኮምፒውተር ቋንቋ ከጫፍ እስከ ጫፍ ግንኙነት ማለት ነው።
- የሒሳብ ሌጀር (Accounts Ledger)፡- ይህኛው ደግሞ የኮምፒውተር ሳይሆን የሒሳብ (አካውንቲንግ) ቋንቋ ነው።

ሌጀር በአማርኛ ቋት ተብሎ ተተርጉሟል። በሒሳብ የጥሬ ገንዘብ ቋት፣ የተሰብሳቢ ገንዘብ ቋት፣ ለሽያጭ የቀረበ ዕቃ ቋት፣ የቋሚ ዕቃ ቋት፣ የብድር ቋት፣ የገቢ ቋት፣ የወጪ ቋት፣ ወዘተ. እየተባለ ለአመዘጋገብ እና ልየታ እንዲመች በእንደየዓይነቱ እና እንደየአስፈላጊነቱ ደግሞ በንዑስ ቋት ይከፋፈላል።

- ብሎክቼይን (Blockchain)፡- ብሎክ እና ቼይን የሚሉ የሁለት ቃላት ጥምር ሲሆን በተለያዩ ኮምፒውተሮች የሚገኝን የሒሳብ ቋት (Ledger) በክሪፕቶ (ምስጢራዊ ዘዴ) እርስበእርስ ማሰናሰል ማለት ነው። ብሎክን ልክ እንደ ብሎኬት ወይም ጡብ ወስደን፤ ቼይንን ደግሞ ልክ እንደ ሰንሰለት ወይም ሲሚንቶ ብንወስደው ብሎኬቱን ከብሎኬት ጋር በሰንሰለት ወይም ሲሚንቶ ማሰናሰል ወይም ማያያዝ ማለት ነው። ወይም በባቡር ፉርጎ ልንመስለው እንችላለን። አንዱ ፉርጎ ሲሞላ ሌላ ፉርጉ ወይም ተሳቢ እናስራለን። የአንዱ ፉርጎ ታርጋ (ሰሌዳ) ቁጥር እና የጎን ቁጥር ይለያያል። በዚህ ቴክኖሎጂ አንድ ልውውጥ (Transaction) ወይም የልውውጦች ጥርቅም አንዱ በአንዱ እየተነባበረና እየተቆለፈ በሲስተሙ ውስጥ ባሉ ኮምፒውተሮች ውስጥ በቅጂ (Copy) ይቀመጣል። ለመቀየር፣ ለመሰረዝና ለመስረቅ አይመችም። ክሪፕቶከረንሲ እና ብሎክ ቼይን የተለያዩ ነገሮች ሲሆኑ እዚህ ለመዘርዘር የመጽሐፉ ይዘት አይፈቅድም።


- አልጎሪዝም (Algorithm)፦ አንድን ችግር ለማፍታታትና ወደ ውጤት ለመድረስ የሚቀመር ትዕዛዝ ነው። በምናውቀው በምግብ ምሳሌ ብንወስድ፤ ወጥ ለመስራት ድስት ውስጥ የምንከታቸው ምጥኖች፣ ሒደቱና ውጤቱ በምግብ ቋንቋ "ሪሲፒ" ይባላል። በኮምፒውተርም አንድን ውጤት ለማግኘት የምንከታቸው የስሌት ቅመሞች "አልጎሪዝም" በመባል ይታወቃል።
- ዲጂታል ማይኒንግ (Digital Mining)፦ የኮምፒውተር አልጎሪዝሞችን በመጠቀም የክፍያ ሌጀሮችን ፈጥኖ ማጣራትና በማጽደቅ ምሥጢራዊ ኮድ ሰጥቶ አዲስ ብሎክ በመጨመር የሚካሄድ ምናባዊ የማዕድን ቁፋሮ ነው።
- ከረንሲ (Currency)፦ የፋይናንስ ቋንቋ ሲሆን ቀጥተኛ ትርጉሙ መገበያያ ማለት ነው።
- ሳንቲም (Coin)፦ የፊያት ኖቶችና ሳንቲሞች አንድን ሀገር ተመርኩዘው የሚፈጠሩ እንደሆኑት ሁሉ የክሪፕቶከረንሲ ሳንቲሞች ደግሞ አንድን ብሎክቼይን ሲስተም ተመርኩዘው የሚፈጠሩ ምናባዊ ሳንቲሞች ማለት ነው። የፊያት ሳንቲሞች የክሪፕቶ ሳንቲሞችን ሊገዙ ሲችሉ፤ የክሪፕቶ ሳንቲሞች ግን የፊያት ሳንቲሞች ሊገዙ አይችሉም። ወደ ፊያት (ባንክ ኖት) ሳንቲምነት የሚቀየሩት በሦስተኛ ወገን በኩል ነው። የክሪፕቶ ሳንቲሙን የሚፈልግ ሰው ሲኖር በልዋጩ የባንክ ሳንቲም ሰጥቶ ሊሸጥለት ይችላል።

- ቶከን (Token)፡- አንድን ድርጅት ተመርኩዘው የሚመጡ “ነጥቦች” ወይም “ቦኖዎች” ናቸው። ለምሳሌ የለስላሳ ቆርኪ ተፍቆ የሚገኝ ዕጣ፣ ለደንበኝነት የሚሰጥ የነጻ ዕቃ ወይም አገልግሎት መውሰጃ ነጥብ፣ አየር መንገድ ብዙ ለመጓዝ የሚሰጠው “ማይል”፣ ወዘተ ሊሆን ይችላል። ያ ቦኖ ከፈቀደልን ድርጅት ውጭ መጠቀም አይቻልም። ሌላ ድርጅት ሊያውቀው አይችልም። በቶከን የባንክም ይሁን የክሪፕቶ ሳንቲም መግዛት አይቻልም። ሆኖም ግን በግል ስምምነት ለሚያውቀን ሰው አሳልፈን ሰጥተን የባንክ ሳንቲም ልንቀበል እንችላለን።
- ክሪፕቶከረንሲ (Cryptocurrency)፡ ያልተማከሉ (Decentralized) የክሪፕቶከረንሲ ተጠቃሚ ግለሰቦችን ምስጢራዊ የሒሳብ ቋት (encrypted ledger)ን በብሎክቼይኖች አሰናስሎ ግብይት የመፈጸም ወይም የማስተላለፍ ዘዴ ነው። በአጠቃላይ በዲጂታል ወይም የኮምፒውተር ውስጥ ዓለም ምናባዊ ባንክና ምናባዊ የወርቅ ቁፋሮ የሚካሄድበት ከፊያት ዓለም ይበልጥ የቀጠነና የተወሳሰበ ነው።[16]

[16] ስለክሪፕቶከረንሲ እና ብሎክቼይን ቴክኖሎጂ መ-ገንዘብ በሚለውና ከዚህ በኋላ በታተመው መጽሐፍ ውስጥ በስፋት ተዳሷል።

በዚህ መጽሐፍ የምናተኩርባቸው

በዚህ መጽሐፍ ገንዘብን እሴት፣ ፊያትና ክሬዲት በሚል ተከፍሏል። የገንዘብ ዕደገትና ሒደት ከእነዚህ ላይወጣ ይችላል። በመጀመሪያ እሴት ወይም ዓይነት ነበር። ከዚያ ወደ ፊያት ወይም ወደ ብሔራዊ ባንክ ኖት ተቀየረ። የብሔራዊ ባንክ ኖት የንግድ ባንክ ብድሮችን ፈጠረ። እሴት እራሱን የቻለ ሲሆን ፊያትና ክሬዲት ግን በአንድ ጠቅልሎ በሁለት ቡድን ማየት ይመቻል። በዝውውር ደረጃ የብሔራዊ ባንክ ፊያት ኖት በአማካይ 10% ሲይዝ የንግድ ባንኮች ክሬዲቶች 90% ያህል ይይዛሉ። እሴት ግን በአብዛኛው ከዝውውር ውጭ ሆኖ ለክምችት ብቻ የሚውል በመሆኑ ለመገመት አይመችም። ሁሉም ተቀላቅለው ስለሚሄዱ ድንበራቸውና ጸባያቸውን ማወቅ ያስፈልጋል።[17]



اللَّهُمَّ صَلِّ عَلَىٰ سَيِّدِنَا مُحَمَّدٍ وَ عَلَىٰ آلِهِ وَصَحْبِهِ وَسَلِّمْ

[17] ከተጠቀሱት ውስጥ በተለይ የእሴት ገንዘብ ከዚህ መጽሐፍ ቀጥሎ በታተመው በመ-ገንዘብ መጽሐፍ ከኃይማኖታዊ አሳቤ ውጭ በጥልቀት ተዳሰዋል። በዚህ መጽሐፍ ግን ከኢስላም ሕግጋት ጋር አገናዝበን እናያቸዋለን።

1

1.2.1. የእሴት ወይም የዓይነት ገንዘብ በኢስላም

የዚህ ንዑስ ርዕስ ነጥቦች

ኢስላማዊ የገንዘብ አተረጓጎም አራት ነገሮች ማሟላት ይጠበቅበታል።

ሀ. በተፈጥሮው ምሉዕ የሆነ ንብረት መሆን፣

- ምሉዕነት ከሸሪዓ አኳያ
  - ✓ Measure value (ሚክያል/ሚዛን)
  - ✓ Transaction value (አገበያይ)
  - ✓ Store value (ተቀማጭ)
- ስታንዳርድ የገንዘብ መስፈሪያ ከጥንት እስከ ዛሬ
- የዲናርና ዲርሀም ስፍርና ልኩ

ለ. ከነጃሳ (እርኩስ) ነገር የጠራ መሆን፣

ሐ. ከመጉዳት የጸዳ መሆን እና

መ. ገንዘቡ የማያስገድድ መሆን ናቸው። (ALMUNAWWAR 2013)

ማስታወሻ፡- ይህ ብቸኛ የሸሪዓው የገንዘብ መለኪያ መንገድ ሳይሆን የተለያዩ ሊቃውንት ከቁርአን እና ከነቢያችን ﷺ ሀዲሶች በማውጣጣት ለመማሪያነት ያስቀመጡትን በመውሰድ ነው።

ሀ. ውስጡም ውጪውም ምሉዕ የሆነ ንብረት መሆን

ለምሉዕ ገንዘብነት ሦስት ነገሮች መሟላት ይኖርባቸዋል።

ሀ) የሚሰፈር ወይም የሚመዘን እና የሚለኩበት (Measure value),

ለ) የሚያገበያይ (Transaction value),

ሐ) ለረጅም ጊዜ የሚቆይ (Store value) ሊኖረው ይገባል።

ይህኛው ከላይ ከጠቀስነው የኢኮኖሚክስ ትርጉሞች ጋር ተመሳሳይነት አለው። ከቁርአን ጥቂት አንቀጾችን ወስደን **ሦስቱንም ጸባዮችን** ማግኘት እንችላለን።

ከሴቶች፣ ከወንዶች ልጆችም፣ ከወርቅና ከብር ከተከማቹ ገንዘቦችም፣ ከተሰማሩ ፈረሶችም፣ ከግመል ከከብትና ከፍየልም፣ ከአዝመራም የሾኑ ፍላጎቶችን ለሰዎች ተሸለመ። ይህ ሁሉ የቅርቢቱ ዓለም መጠቀሚያ ነው። አላህም እርሱ ዘንድ መልካም መመለሻ (ገነት) አለ። (ቁርአን 3፡14)

"... ሰፍርንና ሚዛንን ሙሉ። ሰዎችንም አንዳቾቻቸውን (ገንዘባቸውን) አታጉዱሉባቸው። በምድርም ውስጥ ከተበጀች በኋላ አታበላሹ ... ቁርአን 7፡85

"(ዩሱፍን) በርካሽ ዋጋም በሚቆጠሩ ዲርሃሞች ሸጡት። በእርሱም ከቸልተኞች ነበሩ"። (ቁርአን 12፡20)

«ከመጽሐፉ ሰዎችም በብዙ ገንዘብ (ቂንጣር) ብታምነው ወዳንተ የሚመልስ ሰው አለለ። ከእነሱም በአንድ ዲናር እንኳ ብታምነው፤ ሁል ጊዜ በርሱ የምትጠባበቅ ካልኾንክ በስተቀር የማይመልስ ሰው አለለ። «ይህ በመሃይማን (በምናደርገው) በእኛ

ላይ ምንም መንገድ የለብንም» ስለሚሉ ነው። እነርሱ ኢየወቁም በአላህ ላይ ውሸትን ይናገራሉ። (ቁርአን 3:75)

"እንዲሁም በመካከላቸው እንዲጠያየቁ ቀሰቀስናቸው። ከእነሱ አንድ ተናጋሪ ምን ያህል ቆያችሁ አለ። አንድ ቀን ወይም የቀንን ከፊል ቆየን አለ። ጌታችሁ የቆያችሁትን ጊዜ ልክ ዐዋቂ ነው። ከዚህችም ብራችሁ ጋር (ቢወሪቂኩም) አንዳችሁን ወደ ከተማይቱ ላኩ። ከምግቦቿ የትኛዋ ንጹሕ መሆኗን ይመልከት። ከእርሱም (ከንጹሑ) ምግብን ያምጣላችሁ። ቀስም ይበል። በእናንተም አንድንም ሰው ኢያሳውቅ አሉ"። (ቁርአን 18:19)

"ግድግዳውማ በከተማይቱ ውስጥ የነበሩ የሁለት የቲሞች ወጣቶች ነበር። በሥሩም ለእነርሱ የሾነ (የተቀበረ) ድልብ ነበረ። አባታቸውም መልካም ሰው ነበር። ጌታህም ለአካለ መጠን እንዲደርሱና ከጌታህ ችሮታ ድልባቸውን እንዲያወጡ ፈቀደ። በፈቃዴ አልሠራሁትም። ይህ በእርሱ መታገስን ያልቻልከው ነገር ፍች ነው (አለው)"። ቁርአን 18:82

ኡባዳ ኢብን ሷሚት (ረ.ዐ.) እንዳስተላለፈው ነቢያችን ﷺ ሲሉ እንደሰማሁት ወርቅ በወርቅ ይከፈላል፣ ብርም በብር ይከፈላል፣ ስንዴም በስንዴ ይከፈላል፣ ተምርም በተምር ይከፈላል፣ ጨውም በጨው ይከፈላል፤ ተመሳሳይ ለተመሳሳይ፣ እኩል ለእኩል፤ ክፍያዎች ደግሞ እጅ በእጅ ናቸው። ዓይነታቸው (የዕቃዎቹ)[18] የተለያየ ጊዜ እንዳመቻችሁ ሽጡዋቸው። ክፍያው እጅ በእጅ እስከሆነ ድረስ።

[18] ዓይነታቸው የተለያየ ሲባል ወርቅ በብር፣ ስንዴ በገብስ፣ ብር በጨው ወዘተ እንደማለት ነው።።

በአቡሰዒድ አል ኹድሪይ (ረ.ዐ.) የሀዲስ ሰነድ በኩል ተመሳሳይ ዘገባ ኖሮ "... (በእነዚህ ዕቃዎች) ጭማሪ ያደረገም፣ ጭማሪ የጠየቀም ሁለቱም በአራጣ ተገበያይቷል። ተቀባይም ከፋይም እኩል ተጠያቂ ናቸው" የሚል ዓረፍተነገር አለው።

(ኢማም ሙስሊም ሀዲስ ቁጥር 3853 እና 3854)

በተመሳሳይ አወራር *"ዲናርም በዲናር ይከፈላል፣ ዲርሀምም በዲርሀም ይከፈላል ..."* የሚሉ ሀዲሶች አሉ።

ከስም አኳያ፡- ዲናር (የወርቅ ሳንቲም) እና ዲርሀም (የብር ሳንቲም) በእነዚሁ የቁርአን አንቀጾች ውስጥ እናገኛቸዋለን። ከስድስቱ ገንዘቦች ውስጥ በተለይ ሁለቱ (ወርቅና ብር) ያገበያያሉ፣ ይለካሉ፣ ይመዘናሉ፣ ይሰፈራሉ፣ ንብረት ማስቀመጫ ናቸው። ለዚህም የቁርአን ተንታኞች ጋር የሚከተሉትን እናገኛለን።

"እነርሱ (ወርቅና ብር) የግብይት መለኪያ ናቸው። ... የሀብትና የንብረት መጠን በግልጽ በማይታወቅበት ጊዜ ለመዳኘት (ለመለካት) እንጠቀምባቸዋለን"። (ቃዲ አቡበክር ኢብኑል ዓረቢ፣ አህካሙል ቁርአን፣ 3/1064)

"ሁሉንም ነገር በእነርሱ (በወርቅና ብር ማዕድናት) ይለካሉ። (አልሰርኻሲ፣ አልመብሱጥ፣ 2/193)

"ሀብት በሁለቱ ይለካል። እነርሱን (ለመጠቀም) ባይፈለጉ እንኳ ነገሮችን ይለካሉ" (አልሰርኻሲ፣ አልመብሱጥ፣ 3/20)

“በመሆኑም እነርሱ (ወርቅና ብር) የእያንዳንዱ ግዢና ሽያጭ መሠረቶች (መለኪያዎች) ሲሆኑ ሀብትና ትርፍም በእነርሱ ነው የሚታወቀው” (አልሺራዚ፣ አልሙሀዘብ 1/325)

“ገንዘብ የሚባለው የተወሰነና የተረጋገጠ ዋጋ ያለው ሲሆን ዋጋውም የማይጨምርም የማይቀንስም መሆን አለበት። ያ ገንዘብ የተሰኘው ነገር የሚዋዥቅ ከሆነ ሌሎች የሚቀንሱና የሚጨምሩ ንግድና ዕቃዎችን ልንለካበት አንችልም።” (ኢብኑል ቀይም፣ ዒላሙል ሙወቂዒን፣ 2/137-138)

ተሰፋሪ፣ ተመዛኝና መዛኝ (Measure value)፡- በቁርአን አንቀጾቹ ውስጥ “ሚዛን” የሚለው ለወርቅና ብር ሳንቲሞች ሲሆን ስፍር ወይም “ሚክያል” የሚለው ደግሞ እህሎችን ለማለት ነው። ዲርሀም እና ዲናር የሚቆጠሩ ገንዘቦች እንደሆኑ ተመልክቷል። ከአንድ ዲናር ተነስተን “ቂንጧር” እና ከዚያም በላይ የሰፋ ገንዘብ ድረስ መመዘን እንችላለን። ኩንታል የምንለው “ቂንጧር” ከሚል ቃል የመጣ ነው። መዝነን እና ቆጥረን ለግብይት ስናውለው መልሶ ሌላን ነገር ይመዝናል። ገንዘቦቹ በራሳቸው ምሉዕ ንብረት ናቸው። ለተለያዩ ሥራዎች ለግብዓትነት ይውላሉ። ጌጣጌጥ መሆን ይችላሉ። ወርቅና ብር እስከ ቅንጣትና ግራም ድረስ እየተከፋሉ ይለካሉ።

የሚያገበያይ (Transaction value)፡- ከአንቀጾቹ እንደምናየው የተሰነተሙ ወርቅና ብር ማዕድናት (እንደ ወሪቅ ያሉ) ለግዥ ውለዋል። የበሰለ ምግብ ተገዝቶባቸዋል። በሽያጭ ከሄድን ከዕቃ አልፎ ባሪያ ሳይቀር ተሸጦባቸዋል። ወደ አገልግሎት ስንመጣ በሌላ የቁርአን አንቀጽ ደመወዝ (ኡጅራ/Wage) የተከፈለበት ሁኔታም አለ።

ለረጅም ጊዜ የሚቆይ (Store value)፡- ገንዘብ ማለት የሚከማች ነው። በእህል ከሄድን ብንዘራቸው ጨምረው ይበቅላሉ። በተለያዩ የማቆያ ዘዴዎች በጎተራ ይቀመጣሉ። አንዳንድ እህሎች በተቀመጡ ቁጥር የጥራት ደረጃቸው ይጨምራል። ወደ ወርቅና ብር ስንመጣ የዋሻዎቹ ሰዎች ከተኙበት ተዓምራዊ እንቅልፍ ከሦስት መቶ ዓመታት በኋላ ከዋሻ ወጥተው በማያውቁት ክፍለዘመንና መንግሥት የታተሙ ሳንቲሞቻቸውን "ወሪቅ" ተጠቅመው ምግብ ገዝተዋል። በዚያው በቁርአን 18ኛው በዋሻው ምዕራፍ በሌላ አንቀጽ ላይ ከምድር በላይ ሳይሆን ጭራሽ መሬት ሥር ለረጅም ዓመታት በአባት ተቀብረው ለልጅ የተዋረሱ ገንዘቦችም አሉ።

ወርቅና ብር የትኛውንም ዓይነት የአየር ጸባይ ይችላሉ። እሳት ይበልጥ ያጸዳቸዋል። ቅዝቃዜ ደግሞ አያዝጋቸውም። ብል ወይም ባክቴሪያ አያጠቃቸውም። ከጥቅም በኋላ ዳግም ተመልሰው መጠቀም ይቻላል። ለምሳሌ ኮምፒውተሮቻችን ወይም ስልኮቻችን ውስጥ ሳይቀር ወርቆች አሉ። ኮምፒውተሩ አገልግሎት ቢያቆም እና ብናቃጥለው ወርቁን አጣርተን ልናወጣው እንችላለን። አቃጥሎ የማውጫው ዋጋው የሚያዋጣ ከሆነ። ከአሁኑ ገንዘብ ጋር ለማመሳከር ያህል፤ አሁን ገንዘብ ተብሎ በልማድ የተወሰደው ከአየር የቀጠነ የኮምፒውተር ውስጥ ቁጥር (ፊያት) ነው። ኮምፒውተሩ መብራት ካጣ ቁጥሩ አይኖርም። ወይም የማይጨበጥና በማንኛውም ወቅት የሚለዋወጥ ነው። ወርቅ ግን ኮምፒውተሩ ቢቃጠል እንኳ ነጥሮ የሚቀር ንብረት ነው።

በልኬትም፣ በስፍርም ይሁን በቁጥር የተገለጸው ነገር ውስጡ ከያዘው ተፈጥሮአዊ ቁስ ጋር እኩል መሆን አለበት። ይህንን ነጥብ ኢስላማዊ ብቻ ሳይሆን በተፈጥሮ የሰው ልጅ የሚቀበለው ነው። ከኢስላም ውጭ ያሉ ኢኮኖሚስቶችም የሚያነሱት ሐቅ መሆኑን በቀደሙት ገጾች አይተናል። *"ገንዘብ ሰንል ውስጡም*

ጭምር ገንዘብ የሆነ (Intrinsic value or inherent value) ያለው መሆን አለበት"።[19] በሌላ አነጋገር ለምሳሌ የወርቅ ሳንቲም ገጽ ላይ የተጻፈው ቁጥር ከወርቁ ክብደትና ጥራት ጋር እኩል መሆን አለበት ማለታችን ነው። ይህንን ለማብራራት ለምሳሌ አንድ ዲናር 4.25 ግራም ንጹሕ ወርቅ ነው ከተባለ፤ አንድ ዲናር ተብሎ የተጻፈበት ሳንቲም ስንመዝነው 4.25 ግራም መመዘን አለበት ማለት ነው። አንድ ኪሎ የተባለ ወርቅ፣ ገብስ፣ ስንዴ፣ ወዘተ ስንመዝናቸው አንድ ኪሎ መምጣት አለባቸው። የስንዴ ጆንያ ውስጥ አንድ ኪሎ ስንዴ ጨምረን መቶ ኪሎ ብለን መጻፍ እንደማንችለው ሁሉ አንድ ዲናር 4.25 ወርቅ ነው ካልን ስንመዝነውም ያንኑ ልክ መስጠት አለበት። አንድን ዲናር በወረቀት ወክለን "ዲናር" ወይም "ወርቅ" አንለውም። ወርቅና ወረቀት የተለያዩ በመሆናቸው ወረቀትን በወረቀት፤ ወርቅን በወርቅ እንጂ ባልሆነው ነገር መወከል ተፈጥሮአዊ አይደለም። አንድ ዲናርን እላዩ ላይ "ዜሮዎችን" በመደርደር ብቻ ሚሊዮን ዲናር ልንለው አንችልም። ይህንን ማንም አይቀበለውም። በወርቅ ሚዛን ስንመዝነው 4.25 ግራም ብሎ እያነበበ አንድ ሚሊዮን ዲናር ነው ብለን ይዘን አንሄድም። ይህ ሁኔታ የፊያት (ወረቀት) ገንዘቦች ዋነኛ ባሕሪይ ነው።

[19] O'Sullivan, Arthur; Steven M. Sheffrin (2003), Economics: Principles in Action, Upper Saddle River, New Jersey, Pearson Prentice Hall, Page 246.

ስታንዳርድ የገንዘብ መለኪያ/መስፈሪያ ከጥንት እስከ ዛሬ

አንድ ግራም →	15.43 ፍሬ ስንዴ/ገብስ
አንድ ፍሬ ስንዴ →	0.065 ግራም (ለማቅለል ተጠጋግቶ)
7,000 ስንዴ በአቩዋዲፑዋ (Avoirdupois) →	455 ግራም ወይም አንድ ፓውንድ
በማጠጋጋት 15.43 ስንዴ X በ 0.065 ግራም ≅ 1 ግራም 15,432 ስንዴ ≅ 1 **ኪሎ ግራም**	

በዝርዝር ለማየት

በየትኛውም ማኅበረሰብ ገንዘቦች የሚታዩና የሚዳሰሱ ሆነው በተለይ ማዕድናትና የምግብ እህሎች ነበሩ። ለዚህም እንደየሀገሩ በስፍርና በልኬት ሲግባቡ ኖረዋል። በየትኛውም ሥልጣኔ ወይም እምነት የገንዘቦችም ይሁኑ ሌሎች ክብደቶች፣ የልኬት መነሻቸው የገብስ ወይም ስንዴ ዘር ነው። የኢስላማዊ የገንዘብ ነክ ጉዳዮችና የዘካ (ምጽዋት) መለኪያ መነሻዎችም የስንዴ (ገብስ) ዘር ክብደቶች ናቸው። ለአብነት የእንግሊዝ ባሕላዊ መለኪያ ብንወስድ የእህል ዘሮችን ለክብደት መለኪያነት ይጠቀም ነበር። በሒሳብ ትምህርት ውስጥ የምናውቃቸው "የትሮይ፣ የአቩዋዲፑዋ እና የአፖቴካሪስ" መለኪያዎች መነሻቸው የስንዴ (ገብስ) እና መሰል ጥራጥሬዎች

ናቸው።[20],[21],[22], ሦስቱም (የትሮይ፣ አቩዋዲፑዋ እና አፖቴካሪስ) ዘዴዎች የተለያዩ የስንዴ ቁጥሮችን ለመለኪያነት ይጠቀማሉ። ትሮይና አፖቴካሪስ የሚጠቀሙት የስንዴ ዘሮች ብዛት ተቀራራቢ ናቸው። የትሮይ ፓውንድ 5,760 የስንዴ ዘር ማለትም (373.24 ግራም ወይም 12 ወቄት) ገደማ ነው። አንድ የትሮይ ወቄት (Ounce ወይም oz ወይም toz) 480 የስንዴ ዘር ክብደት ነው። ስለዚህ አንድ የትሮይ ፓውንድ ማለት 12 ወቄት ማለት ነው። 12 በ480 ሲባዛ 5,760 የስንዴ ዘር ክብደት መጣ ማለት ነው።

በፓውንድ አለካክ ብዙ ዕውቅና ያለው የአቩዋዲፖዋ አሠራር 7,000 የስንዴ ዘሮችን ለልኬት ይጠቀማል። ስለዚህ ላለማወዛገብ ከሦስቱ አቩዋዲፑዋን ብቻ እንመልከት። ምክንያቱም ይህኛው የዓለም አቀፍ የፓውንድ መለኪያ ነው። ቃሉ ፈረንሳይኛ ሲሆን "ኤቩዋ ዲ ፑዋ (Avoirdupois)" ማለት "ዕቃ መለኪያ" ወይም "ሚዛን" ማለት ነው። በአቩዋዲፑዋ አንድ ፓውንድ ሲባል ሰባት ሺህ የስንዴ (ገብስ) ዘር ማለት ነው። የሚከተለውን እና ከወረቀት በፊት የነበረው የፓውንድ ልኬት እንመልከት።

አንድ የስንዴ (ገብስ) ዘር 0.065 ግራም ተደርጎ ተወስዶአል። መነሻውም ለአንድ ግራም 15.43236 የስንዴ (ገብስ) ዘር በመመደቡ ነው። እዚህ ጋር ያሉት

[20]Rowlett, Russ (13 September 2001), How Many? A Dictionary of Units of Measurement, Chappel Hill, North Carolina: University of North Carolina at Chapel Hill, Grain (1-3)

[21]Ridgeway, William (1889). "Metrological Notes: III, Had The People of Pre-Historic Mycenae a Weigh Standards? The Journal of Hellenic Studies, London: The Council for the Society for the Promotion of Hellenic Studies 10: 90-97.

[22]Zupko, Ronald Edward (1977), British Weighs & Measures: A History from Antiquity to the Sixteenth Century, University Of Wisconsin Press, Page 11.

ሁለቱን ቁጥሮች (0.065X15.43236) ብታባዟቸው ውጤቱ 1.00 ይመጣል። አንድ ግራም ተባለ ማለት ነው። አሁን አንድ ግራም የምንለው በማቀራረብ (approximately) 15 ፍሬ ስንዴ ማለታችን ነው።

በአሹዋዲፑዋ መለኪያ 7,000 (ሰባት ሺህ) የስንዴ ዘር ማለት በማጠጋጋት 455 ግራም (0.455 ኪሎ ግራም) ገደማ ነው። ፓውንድ ስተርሊንግ ወደ ኋላ ታሪኩ ሄደን ስናይ ፓውንድ መለኪያ (Unit of measure) ሲሆን ስተርሊንግ ደግሞ የብር ማዕድን ነው። ስለዚህ አንድ ፓውንድ ማለት 7,000 ዘር የሚሆን ስንዴ ወይም 0.455 ኪሎ ግራም ስተርሊንግ ወይም የብር ማዕድን ነው ማለት ነው።

በዚህ ሒሳብ አንድ ግራም 15.4324 የስንዴ (ገብስ) ዘር ከሆነ በአንድ ኪሎ ግራም ማለትም በአንድ ሺህ ግራም ውስጥ አስራ አምስት ሺህ አራት መቶ ሠላሳ ሁለት የስንዴ (ገብስ) ዘር አለ ማለት ነው። በገንዘብ ሲተመን ወደ ሁለት ፓውንድ ስተርሊንግ (ብር) ገደማ ማለት ነው። ለአንድ ፓውንድ እንደ ነዋሪው ስምምነት የተለያየ (ተቀራራቢ) የስንዴ ዘር ለልኬትነት አገልግለዋል። ጨምረን ከጠቀስናቸው ከትሮይና አፖቴካሪስ ዘዴዎች ውጭ እንደየነዋሪና ሥልጣኔው ሌሎችም አለካኮች ይኖራሉ። እዚህ ጋር መርሳት የሌለብን የብር “ቅንጣትና” የስንዴ ዘር እኩል ናቸው ማለት ሳይሆን ተፈጥሮን መሠረት ያደረገ የልኬት መነሻ ለማመላከት ነው። እንግዲህ በኋላ ላይ በስፋት በምንዳስሰው ሁኔታ ይህንን ንብረት መሠረት ያደረጉ ንብረቶችን ነው እላይ በገለጽናቸው ወረቀቶች የተተኩት።

የአለካክ መነሻ ባለመረዳት ብዙ ሰው አንድ ዶላርና አንድ ስተርሊንግ፣ አንድ ዩዋንና አንድ ዲናር እኩል ናቸው ብሎ ስህተት ሊፈጽም ይችላል። አንድ ፓውንድ የ7,000 ራስ የስንዴ ዘር እንደሚመዝን አይተናል። ይህ ማለት ወደ ግማሽ ኪሎ

ግራም ለመድረስ ትንሽ የቀረው ማለት ነው። ዲናር ደግሞ ወርቅ ሲሆን በ71.43 (በደፈናው በ72) ራስ የስንዴ ዘር ነው (ዝርዝሩ ከሥር ይመጣል)።

አንድ ዲናርና አንድ ስተርሊንግ እኩል ናቸው ካልን 7,000 የስንዴ ዘር ከ72 የስንዴ ዘር ጋር እኩል ነው እንደማለት ሊሆን ነው። ይህ ደግሞ ስህተት ነው። ችግሩ የአሁን ገንዘቦች የድሮ ገንዘቦችን ስም ይዘው መጥተው እያጭበረበሩ ናቸው እንጂ ለወረቀት ወረቀትማ የዚምባቡዌም የግብጽም የእንግሊዝም ገንዘብ ያው ተመሳሳይ ወረቀቶች ናቸው።

በዓይነት ቢለካ እንኳ አለካኩ ሜትሪክን በሜትሪክ፣ ፓውንድን በፓውንድ ነው ማድረግ ያለብን። በዚህ መሠረት "ይህንን ያህል ግራም የቻይና ሪሚምቢ (መዳብ) ከዚህ ያህል ግራም የእንግሊዝ ስተርሊንግ (ብር) ጋር እኩል ነው፤ ወይም ይህንን ያህል ግራም ዲናር (ወርቅ) ከዚህን ያህል ግራም ስተርሊንግ (ብር) ጋር እኩል ነው" ማለት ነው ያለብን። አንዱ የብር ማዕድን ሆኖ በፓውንድ እየተለካ ሌላው የወርቅ ማዕድን ሆኖ በሜትሪክ አለካክ እየተለካ እኩል ናቸው ማለት ሎጂካዊ አይደለም።

የኢትዮጵያ ገንዘብ "**ብር**" ይባላል። ብር ሲባል መነሻው የብር ማዕድን ስለሆነ ነው። የኢትዮጵያ «ብር» እና የእንግሊዝ «ስተርሊንግ» ለማለካት (ሁለቱም ብር ስለሆኑ) በፓውንድ ወይም በሜትሪክ መለካት አለባቸው። የብር ማዕድን ያው ብር ስለሆነ እና ዓለም አቀፍም በመሆኑ የእንግሊዝ የኢትዮጵያ የሚባል አይኖረውም። አንድ ፓውንድ የሚመዝን የኢትዮጵያ ብር አንድ ፓውንድ ከሚመዝነው የእንግሊዝ ስተርሊንግ (ብር) ጋር እኩል ነው። አንድ ኪሎ የኢትዮጵያ መዳብ አንድ ኪሎ ከሚመዝነው የቻይና ሪሚምቢ (መዳብ) ጋር እኩል ነው። በመደበኛ ሒሳብ አንድና አንድ የትም እኩል ናቸው። ልዩነት የሚመጣው የዓይነትና ጥራት ላይ ብቻ ነው።

እርሱን በተመለከተ ኢስላማዊ ሕግ ያስቀመጠው አለ። በዚህ በተሻሻለው እትም ተዳሷል።

ባለንበት ዘመን ብሩም ሆነ ወርቁ ከወረቀቶቹ ጀርባ ባለመኖራቸው ብዙም አያሳስብ ይሆናል። ግን በወረቀቱም ቢሆን ሌላ አደናጋሪ ነገር አለው። ይህ መጽሐፍ መጀመሪያ እየተጻፈ በነበረበት በ2017 መጨረሻ አንድ የኢትዮጵያ ብር በ59 የጣሊያን ሊራ እና በ4 የጃፓን የን ይመነዘራል። ኢትዮጵያ ከጣሊያንና ጃፓን በእድገት በልጣ ሳይሆን የመለኪያ መነሻ መለያየት አንዱ መለያያ ነው ተብሎ ይታሰባል። በዚሁ ወቅት አንድ የኢትዮጵያ ብር በ0.035 የአሜሪካ ዶላር ይመነዘራል። የተደበላለቀ እና የተወሳሰበ ነገር ያስመሰለው በዓይነት ይጠራባቸው የነበሩ የገንዘብ ስሞች እና የተለያዩ የመለኪያ ስሞች እንደ አንድ በመውሰድ ወደ ፊያት (የወረቀት መገበያያ) ሲመጡም ተያይዘው በመምጣታቸው ወይም ስለገንዘብ ምንነት መጠየቅ በመተዋችን ነው።

ወረቀቶች የወርቆችን እና ብሮችን ስም ይዘው ነው እያገለገሉ ያሉት። ወርቅ እና ወረቀት ደግሞ እኩል አይደሉም። እንደምናውቃቸው ወረቀቶቹ እላያቸው ላይ የተመቸ የመሪ፣ የመልክዓምድር፣ የአራዊትና የአዕዋፋት ፎቶ እየተለጠፈባቸውና ቁጥር እየተጻፈባቸው "እንዲህ ያለ ገንዘብ ነው" እየተባሉ ገበያ ተወስደው ዕቃ ይገዛባቸዋል። ከጀርባው ያሉ ሌሎች ኢኮኖሚያዊ ቀመሮች በወረቀት መወከል ለማጭበርበር በር ስለሚከፍቱ የእምነቱ ሕግጋት ከመነሻው ዘግቶአቸዋል። በአሁኑ ወቅት የምናያቸው የዓለም ሀብት በሙሉ እስኪባል ድረስ በጥቂት ሰዎች እጅ መውደቃቸውና አብዛኛው ደሀ መሆኑ ለምን እንዴት ብለን ሳንጠይቅ አንቀርም። እንግዲህ ከምክንያቶቹ ዋነኛው የገንዘብ ፍልስፍና ነው።

ወደ ተፈጥሮአዊ ገንዘቦች ማለትም ውስጥና ውጪያቸው አንድ የሆነ ገንዘብ እንደ ገንዘብ ብንጠቀም የኢኮኖሚክስ እሳቦቶች (assumptions) እና እራሱ ኢኮኖሚክስም ይከስማሉ። ልክ እንደ ወርቁ ስንዴንም ሆነ ገብስን እንደ ገንዘብ ከወሰድናቸው "ልካቸው" በጥራታቸውና በክብደታቸው (ልኬታቸው) ይወሰናል እንጂ አንድ ኩንታል ስንዴን "ሦስት ሺህ ኩንታል ስንዴ ነህ" አንለውም። ስንዴው ውስጡም ውጪውም ገንዘብነት አሟልቶአልና ገንዘብ መሆን ይችላል። አንድ ኪሎ የያዘ ወይም የስንዴ ፎቶ ያለበት ጆንያ ወይም ፌስታል እላዩ ላይ ሚሊዮን ኪሎ ስንዴ ተብሎ ቢጻፍ የወረቀት መገበያያ ሆነ ማለት ነው።

የዲናር እና ዲርሀም ስፍርና ልክ

በአጭሩ፡-

አንድ ዲናር ⟶	4.25 ግራም ወርቅ ⟶	71.43 ፍሬ ስንዴ/ገብስ
አንድ ዲርሀም ⟶	2.975 ግራም ብር ⟶	50 የስንዴ/ገብስ ፍሬ

በዝርዝር ለማየት

ወደ ኢስላማዊ የገንዘብ እሳቤ ዳግም እንመለስና በነቢያችን (ﷺ) ዘመን ገንዘብ የሚባለው ዕቃን በዕቃ ልውውጥ ሲሆን ከዚህም በተጨማሪ ልኬታቸው በግልጽ የማይታወቁ ነገሮች ላይ የወርቅና ብር ማዕድናት እንደ መለኪያና መገበያያ አገልግለዋል። በቀጣይ ትውልዶችም ከቁርአንና ሀዲስ በመነሳት ወርቅ (ዲናር) እና ብር (ዲርሀም) ተመራጭ መገበያያዎች ነበሩ።

ፓውንድ ላይ እንዳየነው የዲናርና ዲርሀም ገንዘቦችም መነሻቸው የስንዴ (ገብስ) ዘሮች ናቸው። እነዚህ ጥራጥሬዎች ከምሥራቅ እስከ ምዕራብ የሚመረቱ፣ የሚታወቁና ለምግብነት የሚያገለግሉ ሲሆኑ፤ ከወርቅና ብር ይልቅ ማንም ሰው ሳይወዛገብ ያውቃቸዋል። ከሕጻን እስከ አዋቂ እንዲሁም ለእንስሳም ጭምር ለምግብነት ይውላሉ። ወርቅና ብር በሌሉበት ጊዜ፣ ሁኔታና ቦታ እንደ ግብይት ቋንቋ ማገልገል ይችላሉ። ክብደታቸው በተፈጥሮ የሚብበጁ ስለሆኑ ብዙም ለውዝግብ ክፍት አይደሉም። እንደ ወረቀት መገበያያም "ነህ በቃ ነህ" የምንላቸው ሳይሆኑ ለመመረት ጉልበት፣ ጊዜ እና ንብረት ይፈልጋሉ። ማንም እየተነሳ የሚጨምራቸውና የሚቀንሳቸው ሳይሆኑ ጊዜ ተወስዶ የሚመረቱ ናቸው።

ዲናር እንደየሀገርና ዘመን፤ ጥራቱ በአማካይ ከባለ ሀያ እስከ ሀያ ካራት ሆኖ ከ4 ግራም እስከ 4.5 ግራም ወርቅ ነው። በእያንዳንዱ ዲናር ላይ ትክክለኛ ደረጃውና ግራሙ ይጻፋል። በ7ኛው ክፍለ ዘመን ከላይኛው ናይል (አባይ) እስከ ባዛንታይን ድረስ የነበረው የዲናር ልክ ባለ ሀያ ካራት ጥራት የሆነ 4 ግራም ወርቅ ነበር።[23]

አማካይ የነበረውንና በኸሊፋው ዑመር ኢብኑል ኸጧብ (ረ.ዐ.) ዘመን "የተሠነተመው" (ሣንቲም ያስደረገው) የሚባለው የዲናር-ዲርሀም ልኬቶችን ቀጥለን እናያለን። እላይ ባየነው በፓውንድ ሲስተምም (ትሮይ፣ አቮዋዲፑዋና አፖቴካሪስ) ጭምር አንድ የስንዴ (ገብስ) ዘር 0.065 ግራም ቢሆንም ቅሉ፤ በተለይ ለከበሩ ማዕድናት የስንዴውን የግራም ምዘና ዝቅ ይደረግ ነበር። ምክንያቱም ማዕድናቱ አፈር ሊኖራው ስለሚችል ነው። በዚህም መሠረት የዲናር መለኪያ የምንወስደው የስንዴ (ገብስ) ክብደት በአማካይ 0.06 ግራም ገደማ ነው። በደማስቆ ሙዚየም የሚገኘው

[23] Porteous, John (1969), "The Imperial Foundations". Coins In History: A Survey Of Coinage From The Reform Of Diocletian To The Latin Monetary Union, Weindenfeld and Nicolson, Pages 14.

በዐመዊይ ሥርወ-መንግሥት በኸሊፋ ዓብዱል ማሊክ ኢብን መርዋን ዘመን (በ79 ሂጅሪያ/በ700 እ.ኤ.አ.) በሶሪያ በደማስቆ "የተሠነተመው" (ሣንቲም ያስደረገው) 22 ካራት (ማለትም ባለ 917 ጥራት የተሰኘው) የሆነ ወርቅ ሲሆን ክብደቱ 4.25 ግራም ነበር[24]። ጥራቱ 999.9 ወይም 24 ካራት ወርቅ የተደረገባቸውም ታሪኮች አሉ።

ወርቅ ከ14 ካራት እስከ 24 ካራት እንዳለው እንሰማለን። ከአፈር ወይም ሌሎች ማዕድናት ቅልቅል (ግግር) ስለሚሆን የንጽሕና ጥራቱን የምንለካበት ሲስተም ነው። ለምሳሌ 14 ካራት የሚባለው ጥራቱ ከ58.3% እስከ 62.5% የሆነ ሲሆን ከፐርሰንቱ በመነሳት 58.3% ወይም በደፈናው 583 ይባላል። ልክ እንደዚሁ 22 ካራት የሚባለውም 91.66% እስከ 95.83% ሲሆን በደፈናው 916 ወይም 917 ይባላል። 24 ካራት ወይም 999.9 የሚባለው ደግሞ 99.99% የሆነው ነው።

ዋናው ግን ዲናሩ ላይ ጥራቱና ክብደቱ እላዩ ላይ ከሚገለጸው ጽሑፍ ጋር መግጠም አለበት። ዲርሀም ደግሞ በአማካይ 2.975 ግራም ንጹሕ ብር ሲሆን ይህ ደግሞ ከሀምሳ የገብስ ዘር ጋር እኩል ነው። የተለያዩ ሀገሮች ከዚሁ ጋር የሚቀራረብ ክብደት ተጠቅመዋል። ለአብነት በግብጽ 3.088 ግራም ወይም 47.661 የትሮይ ጥራጥሬ ዘር ተጠቅመዋል[25]። **በዚህ ጽሑፍ ዲናር ስንል 71.43 የገብስ (ስንዴ) ዘር ወይም 4.25 ግራም ንጹሕ ወርቅ ሲሆን ዲርሀም ካልን 50 የገብስ (ስንዴ) ወይም 2.975 ግራም ንጹሕ ብር ነው።**

[24] Johnson, Marion (1968), "The Nineteenth – Century Gold 'Mithqal' in West and North Africa", The Journal of African History, Cambridge University Press, 9 (4): 547-569

[25] Oxford English Dictionary, 1st edition, dirhem.

የዲናርና ዲርሀም ንጽጽር፡- የኡመር ኢብኑል ኸጣብ (ረ.ዐ.) የዲናር እና ዲርሀም "ስታንዳርድ ሬሾ ወይም መዶኛ"፡-

- 7 ዲናር (7 ሚስቃል) ወርቅ ክብደት ከ10 ዲርሀም (ብር) ጋር እኩል ነበር። አንድ ወቄት (Ounce) ማለት ነው።
- ይህም ማለት 7 x 4.25 ወርቅ ክብደት = ከ 10 x2.975 ግራም ብር ክብደት ጋር እኩል ነው ማለት ነው።
- በክብደት ደረጃ እንጂ በምንዛሪ ደረጃ ማለት አይደለም። የሰባት ዲናር ክብደት እና የአስር ዲርሀም ክብደት እኩል 29.75 ግራም ነው ለማለት ነው።
- በስንዴ ዘር በዲናር ቦታ 7 ሲባዛ በ71.43 እኩል ይሆናል በዲርሀም ቦታ 10 ሲባዛ በ50 ስንዴ ማለት ነው። በሁለቱም ከሄድን አምስት መቶ የስንዴ ዘር ይመጣሉ።
- አሁንም በሌላ አነጋገር አንድ ሚዛን ላይ 500 የስንዴ (ገብስ) ዘር አስቀምጠን ዲናሮችንና ዲርሀሞችን በሌላ ሚዛን ክንፍ ላይ አስቀምጠን መመዘን እንችላለን። 500 የስንዴ ዘር ክብደት ማለት 7 ዲናር ወይም 10 ዲርሀም ማለት ነው።
- የድሮ ሀኪሞች መድኃኒት የሚያዙት የስንዴ (ገብስ) ዘሮችን ሚዛን ላይ እያስቀመጡ በመመዘን ነበር።

ውስጡም ውጪውም ገንዘብ የሆነ ማለት ተጠቃሚው ባለቤትነቱ ተረጋገጠለት ማለት ነው። ስንዴ ያለው ሰው የአሜሪካ መንግሥት ያጋሸበዋል ብሎ አይሰጋም። ሲሻው ለምግብነት ይጠቀምበታል። ሲሻው በወርቅ ወይም በጨፍ ይቀይረዋል። ሲሻው አስቀምጦ ይዘራዋል። በኢስላምም በተፈጥሮም አንድ ገንዘብ፤ ገንዘብ ነው ለማለት ውስጡም ጭምር ጠቃሚ የሆነ ነገር ሊይዝ ይገባል።

ወደ ወርቅ ብንመለስ መጭበርበር አይኖርም ወይ? ሊባል ይችላል። ለአንድ ወር በወርቅ ንግድ ውስጥ ብንቆይ ገና ሳንፈትሸው በዓይን እይታ ማወቅ እንችላለን። ሲስተሙ ሲኖር የፍተሻና የማስተላለፊያ ተቋማት ይኖራሉ። ልክ ለባንኮች ወረቀት እንደምንሰጠው ለባንክ ወርቅ ሰጥተን ሌላ ቅርንጫፍ ላይ መውሰድ እንችላለን። ወደዚያ ስንመለስ ብዙ ነገሮች ስለሚቀያየሩ ሲስተሙ ምቹ ይደረጋል። ችግሩ የመጣው ከሲስተሙ በመራቃችን ነው።

ስለዚህ ገንዘቡ ውስጡም ውጪውም ምሉዕ መሆን ተቀዳሚ መሠረት ነው። ይህንን መሠረት የጣሰ ነገር በተፈጥሮአዊም በምዕራባዊም አተረጓጎም ከገንዘብነት ይወጣል። የወረቀት መገበያያ ዓይነቱም ስፋቱም ብዙ ስለሆነ ሌላ የፋይናንስና የኢኮኖሚክስ ውስብስብ ትርጉም ውስጥ ይወድቃል። ብዙ ጽንሰ ሐሳቦች ስላሉት ከመጽሐፉ ፍሰት ውጭ ይወስደናልና እዚሁ እንግታው።

ለ. ከነጂሳ (እርኩስ) ነገር የጠራ መሆን

ይህም ሁሉም ሰው ሳይጠየፈው እንዲጠቀምበት ለማስቻል ነው። ለምሳሌ፡- የአሳማ ቆዳ፣ ኩበት ለመገበያያ አያገለግሉም። አስካሪ እና አደንዛዥ ነገሮች ወትሮም ክልክል ስለሆኑ ከግብይት ብቻ ሳይሆን ከገበያም ውጭ ናቸው። በእስር ቤቶችና ጦር ሜዳ አካባቢ ሲጋራና መጠጥ እንደ ግብይት መሣሪያነት ያገለገሉባቸው የታሪክ አጋጣሚዎች ነበሩ። ይህ ግን በኢስላማዊ ሕግ የገንዘብ ደንቦችን ስለማያሟላ መገበያያ ልንለው አንችልም።

በገጠር ኩበት ሳይበላሽ ለረጅም ጊዜ ይቆያል። ሆኖም ኩበት እንደ ግብይት መሣሪያነት አያገለግልም። **ይህንን የሚያነብ ሰው በዲጂታል ዘመን ወደ ኩበት መለስከን ሊል ይችላል። ነገር ግን ኮምፒዩተር ላይ ከተጻፈ ባዶ ቁጥር አንድ ቅርጫት ኩበት ይሻላል።**

ገንዘብ ማለት ንብረት ማለት ስለሆነ ለሰው ልጅ የሚያገለግል ዕቃ በሙሉ እንደ ገንዘብ ይቆጠራል። በዚህኛው አገባብ ኩበት ገንዘብ ወይም ንብረት ሊሆን ይችላል። ነገር ግን ለመገበያያነት አይሆንም። ይህ የምናውቀው ነገር ስለሆነ ነው ለምሳሌነት የመጣው። በተጨማሪም አስካሪና መርዛማ ነገሮች እዚህ ስር ይጠቃለላሉ።

ነጃሳ በሁለት ነገር ሊመጣ ይችላል። አንደኛው ዕቃው ወይም ነገሩ በራሱ ነጃሳ ሊሆን ይችላል። ለምሳሌ ዓይነ ምድር፣ የአሳማ ወይም ከርከሮ ተዋጽኦ በራሱ ነጃሳ ነው። ሁለተኛው ድርጊቱ ወይም ሥራው ነጃሳ ሊያደርገው ይችላል። ለምሳሌ ሀሺሽ፣ ጫት፣ የቁማርና የጥንቆላ መሳሪያዎች፣ ብቅል ወይም ገብስ ቢነኩ ነጃሳነት የላቸውም። ገብስ ለምግብነት ያገለግላል። ጌሾ በራሱ ምንም እርክሰት አይኖርበትም። ግን ከተምር አደገኛ መጠጥ ሊዘጋጅ ይችላል። ስለዚህ ገብስም ይሁን ጌሾ ለመጠጥ ቤት ማድረስ ነጃሳ ይሆናል። ወለድም ከወሰድን ነጃሳ ነው ማለት ነው። ግብይት ሁሉ ፍቁድ ሲሆን ወለድ የተቀላቀለበት ጊዜ ይነጀሳል።

ሐ. ከመጉዳት የጸዳ መሆን

በኢስላማዊ መሠረታዊ ሕግጋት (ቀዋኢደል ፊቅሂያ) "መጉዳት" ማለት የንብረት መለኪያው ጊዜ ሲያልፍ ዋጋ የሚያጣ ከሆነ እንደ ገንዘብ ሆኖ አያገለግልም። ምክንያቱም ገንዘብ የሚባለው የትኛውም ዘመን ድረስ ቢቀመጥ መጠኑም ዋጋውም የማይለውጥ ነው። ይህ ሲሆን ነው ማዕከላዊ መገበያያ የሚሆነው። በተለይ የያዘው ሰው በማያውቅበት ሁኔታ የሚጋሸብ ከሆነ እንኳን ሌላውን ሊለካ ቀርቶ ለራሱ መለኪያ ይፈልጋል (ALMUNAWWAR 2013)።

ወርቅና ብርን ስንወስድ ዜግነት፣ ቋንቋ፣ ጊዜ፣ ቦታና የአየር ንብረት አይገድባቸውም። ሙቀት ቢጨመርባቸው ይበልጥ ይጸዳሉ። በቅዝቃዜ ወይም

እርጥበት አይዝጉም። እስከ ጀነት ድረስ ያገለግላሉ። ቢቀበሩ ለልጅ ልጅ ይዋረሳሉ። በቁርአን እና ሀዲስ በርካታ ታሪኮች አሉ። ልክና ልኬታቸው ከዘመን ዘመን እና ከቦታ ቦታ ያው ነው። የወረቀት/ቁጥር ገንዘብ ግን እራሱን ችሎ ስለማይቆም እነርሱን ተገን አድርጎ ነው የሚተመነው። ወርቅ ስንት ዶላር ገባ? ስንዴ ስንት ዶላር ገባ እንላለን እንጂ ዶላር ስንት ወርቅ ወይም ስንዴ ገባ እንልም። ምክንያቱም ፊያቱ (ወረቀቱ) ይዋሸቃልና።

ለምሳሌ ስማቸው ኩባያ የሆኑ ብዙ ኩባያዎች አሉ። ኩባያ ሁሉ እኩል አይደለም። አንድ ሊትር ሲለካበት የነበረ ኩባያ እያደረ የሚያንስ ከሆነ ስሙ "ኩባያ" ስለተባለ ብቻ ፈሳሽም ይሁን ጥራጥሬ ልንለካበት አንችልም። ፕላስቲክ ሥራ ላይ ከዋለ ጊዜ ጀምሮ ገጠር ላይ በፕላስቲክ ጆግ ወይም የፕላስቲክ ኩባያ እህል መለካት ልምድ ሆኖ ነበር። ነገር ግን አንዳንድ አጭበርባሪዎች ጆጉን ወይም ኩባያውን በጋለ ምጣድ ላይ በማስቀመጥ ያሳጥሩታል። ሳይታወቅባቸው ለተወሰኑ ጊዜያትም ሲገለገሉበት ቆይተዋል። ከጊዜ በኋላ ግን እናቶች የገዙትን እህል እቤትም ካመጡት በኋላ ሲለኩት እኩል አልመጣ አላቸው። ቢቸግራቸው የየራሳቸውን ጆግና ኩባያ ገበያ ይዘው መውጣት ጀምረው ነበር። በዚሁ ምሳሌ መሠረት እየዋለ እያደረ ከእሳት ወይም ከምስጥና ነቀዝ በረቀቀ ነገር የሚበላ ገንዘብ እላዩ ላይ ቁጥር ስለተጻፈበት ብቻ ያንኑ የአምናና ሀቻምና ገንዘብ ነው ማለት ሎጂካዊ አይደለም። አሁን እጃችን ላይ ያለው ገንዘብ ዓይን በዓይን አስገድዶ ማጉደል ያለበት ነው። ስለገንዘብ ማጉደል ቁርአን ውስጥ የሚከተለውን አንቀጽ እናገኛለን።

*"ወደ መድየንም (ምድያን) ወንድማቸውን ሹዓይብን (ላክን)፤ አላቸው፡- ወገኖቼ ሆይ አላህን ተገዙ። ከእርሱ በቀር ምንም አምላክ የላችሁም። ከጌታችሁ ዘንድ ግልጽ ማስረጃ በእርግጥ መጥታላችኋለች። **ሰፍርንና ሚዛንን ሙሉ። ሰዎችንም***

አንዳቾቻውን (ገንዘቦቻቸውን) አታጉዱሉባቸው። በምድርም ውሰጥ ከተበጀች በኋላ አታበላሹ። ይህ ምእመናን እንደሆናችሁ ለናንተ የተሻለ ነው።" ቁርአን 7:85

የወረቀት/ቁጥር ገንዘብ ለማስቀመጥ አስተማማኝ አይደለም። በቀላሉ ለማምታታት ይመቻል። የኮምፒውተር ቁጥሮች ወይም የማሽን ሕትመቶች ስለሆኑ ‹‹ዜሮ›› እየጨመሩና እየቀነሱ ለማጭወት ምቹ ናቸው።

ይህንን ንዑስ ርዕስ ስናጠቃልለው ገንዘብ ለመለኪያነት ለማገልገል ለረጅም ጊዜ ባለበት የሚገኝ፣ የማይለዋወጥ ወይም የማይዋዥቅ መሆን ይገባዋል። መለዋወጡን እያወቅን ምንም እንዳላወቀ ሆነን የሰው ገንዘብ ስንበላ ወይም እኛም በሌላው ስንበላ (በሁለቱም መንገድ) ከአላህም ከሕሊናም ዳኝነት ማምለጥ የምንችለው አይደለም።

መ. የማያስገድድ ገንዘብ መሆን

በንግድ ላይ ምንም ዕቃ ወይም ንብረት በስምምነት ካልሆነ በስተቀር በአንዱ ወገን አስገዳጅነት በሌላው ወገን ላይ ሊጫን አይገባውም። ሰዎች ተስማምተውበት ካልሆነ በስተቀር ቁሳዊ ንብረት የሆኑት ወርቅና ብር እንኳ የተጫኑ ገንዘቦች ሊሆኑ አይገባም። ይህን የሚለው የገንዘብን ምንነት የሚበይነው የኢስላማዊው ዲን(ሃይማኖት) መጽሐፍ ነው። የጸሐፊው ፈጠራ አይደለም። ሊቃውንትም በዚህ ይስማማሉ። ተገበያዮቹ የሚስማሙበት ነገር ውስጣዊ ዋጋ ያለው፣ ነጻሳ ያልሆነና የማይዋዥቅ ከሆነ ሰዎች ያለማንም አስገዳጅነት ሊገበያዩበት ይችላሉ። አስገዳጅነት ካለው ገንዘብ ልንለው አንችልም። የዚህ ሕግ መነሻ የሆነውን የቁርአኑን አንቀጽ እንመልከት፡-

*"እናንተ ያመናችሁ ሆይ! ገንዘቦቻችሁን በመካከላችሁ ያለ አግባብ አትብሉ። **ግን ከእናንተ <u>በመዋደድ</u> የሆነችውን ንግድ (ብሉ)**። ነፍሶቻችሁንም አትግደሉ። አላህ ለናንተ አዛኝ ነውና።" ቁርአን 4:29*

አላህ ንግድን ከመሠረቱ ጀምሮ ፈቅዶት፤ በተፈቀደው ንግድ ላይ ግን አራጣን እርም አድርጎት ሲያበቃ በቁርአን 2:275 ላይ "...*ግን መሸጥን አላህ ፈቅዷል። አራጣንም እርም አድርጓል ...*" አለንና ንግዶች ወይም ልውውጦች ግን መካሄድ ያለባቸው በተገበያዮቹ መልካም ፈቃድ ላይ ብቻ እንዲሆን ከዚህ ከፍ ብሎ በተጠቀሰው አንቀጽ ደነገገልን።

የፊያት ኖት ላይ "ላምጪው እንዲከፈል ሕግ ያስገድዳል" የሚል ዓረፍተነገር የገንዘቡን ገንዘብነት ጥያቄ ውስጥ ይከተዋል። የሰው ልጅ ለገንዘብ ልዩ እና ብርቱ ፍቅር አለው። ማስገደድ አይፈልግም። ግዴታ ካለ ነገር አለ ማለት ነው።

ስለዚህ ኢስላማዊ የገንዘቦች ሕግጋት ተፈጥሮአዊም ናቸው። ሌሎች እምነቶች ዘንድ ከዚህ የተለየ ወይም የራቀ ላይኖራቸው ይችላል። ምክንያቱም የዓለማዊው ትርጓሜ ሳይቀር ከኢስላማዊው ጋር በጣም ተቀራራቢ ነውና። እስልምና የአኗኗር ሥርዓትም ነው የሚያስብለው አንዱም ይኸው በመሠረታዊ የሕይወት ጉዳይ ላይ ለሰው ልጅ ፍትሃዊ ብይንን በማስቀመጡም ጭምር ነው። እንግዲህ እነዚህ የዓይነት ገንዘቦች ባለቤታቸው አላህ ነው። ለሙስሊሙም ሙስሊም ላልሆነውም እንደፈለገ ይቸራቸዋል። የሚገኙት ደግሞ በልፋት እንጂ በማጭበርበርና በመጉዳት አይደለም። የተፈጥሮ ገንዘብ ከኢስላማዊ ዕይታ በኩል ይህንን ይመስላል። ጸሐፊው የተጠቀመው የተወሰኑ ሊቃውንት ዕይታ መሆኑን ልብ ይሏል። በዚህኛው አተያይ መሠረት ገንዘብን ስንለካ የተጠቀሱት አራቱ መስፈርቶች መሟላታቸውን አንዘንጋ።

1.2.2. የቁጥር ገንዘቦች (Non-Commodity Moneys)

- **የፊያት መገበያያ**
  - ✓ **መግቢያ**
  - ✓ **የፊያት መገበያያ ታሪኮች**
    1. ቀደምት ታሪክ (ከቻይና እስከ አውሮፓ)
    2. የ21ኛው ክፍለ ዘመን ታሪካዊ ለውጦች
       - የብሬተን ዉድስ ስምምነት (1944)
       - የዓለም ባንክ መቋቋም
       - የአይ.ኤም.ኤፍ. መመሥረት
       - የኒክሰን ሾክ (1971 ገንዘብ "ፊያት" የተደረገበት ዕለት)
       - ድኅረ ኒክሰን ሾክ
- **የንግድ ባንክ ገንዘቦች (ክሬዲት)**
- **የፊያት መገበያያ መለያዎቹ (Characteristics)**
  - ✓ ግልጽ አራጣ መሆኑ (ሦስት ደረጃዎች አሉት)
    - በተቀመጠ ወርቅ ልክ "Promisory Note" ሲታተም
    - የተቀመጠው ወርቅ 1971 ላይ በምዕራባዊያን ሲካድ
    - ወርቅ ያልደገፈው ፊያት ጥቅም ላይ ሲውል
  - ✓ የአራጣ ኢኮኖሚ ማሳለጫ መሆኑን
  - ✓ ሲለካ ውስጡ ዋጋ የሌለው፣ ሲቀመጥም የሚቀንስ
  - ✓ አስገዳጅ ገንዘብ መሆኑ
  - ✓ ኢስላማዊ ዘካን እንደ ምሳሌ

2

1.2.2.1. የፊያት መገበያያዎች

ሀ. መግቢያ፡- ፊያት/ክሬዲት፣ ሲኞሬዥ፣ የመግዛት ኃይል

(መግቢያው ከመ-ገንዘብ መጽሐፍ የተወሰደ)

ፊያት (FIAT) እና ክሬዲት (Credit)

ፊያት በላቲን ጥሬ ትርጉሙ “ይሁን፣ ይደረግ” የሚል ትርጉም ይዟል። የገንዘብ አገባቡ ያለምንም ተያዥ ወይም ልውውጥ በብቸኝነት የሚታተምና በገጹ የተገለጸው የቢል ዋጋ ላምጪው መልሰህ ክፈለኝ የማይባል ሕጋዊ ዕዳ ነው። በወረቀቱ ገጽ ላይ 50፣ 100፣ 1,000 ተጽፎ ታትሞ ቢወጣ አሳታሚው በተጻፈው አሃዝ ልክም ይሁን በታች፤ ወርቅ ወይም ሌላ ነገር ክፈለኝ ብሎ መጠየቅ አይቻልም። በፋይናንስ “Irredeemable” ይባላል። የማይለወጥ ወይም የማይቀየር ወይም የማይወራረድ የሚለው ይቀርበዋል። ይህንን ሙቢት የያዘው መንግሥት ወይም ግለሰብ ወይም “ሲኞር” ሲሆን፤ ለራሱ ግን በማንኛውም ወቅት ማወራረድና ወደ ንብረት መመንዘር ይችላል። በመቶ ብር የተለፋበት እሴት በአንድ ግራም ወረቀት ወይም በኮምፒውተር ቁጥር ጠቅልሎ የመያዝ “የመግዛት” አቅም አለው። ፊያትና ክሬዲት የማይነጣጠሉ ቢሆኑም ለአንባቢ ግንዛቤ ብቻ ነው ተነጣጥለው የተቀመጡት።

ክሬዲት ከላቲን “ክሬዴሬ”

በእርግጥ ዝውውር ላይ ካለው ገንዘብ በብሔራዊ ባንክ የሚታተመው (Printed Fiat) ፊያት 10% ሲይዝ በንግድ ባንኮች የሚፈጠረው (Created credit) 90% ይይዛል።

ሲኞሬዥ (Seigniorage)

የፈረንሳይኛ ጥሬ ትርጉሙ “የጌታ መብት፣ ጌትነት፣ አለቅነት” እንደማለት ሲሆን ይህንን ቦታ የያዙት መንግሥታትና ማዕከላዊ ባንኮች ናቸው። በእኛ ሀገር “ገዥ” ነው የሚባሉት። ሲኞርነታቸው ገንዘቦችን የማተምና ልዩነቱን የመጠየቅ መብት ያላቸው ብቸኛ ተቋማት ናቸው። የአሜሪካውና የተወሰኑ የአውሮፓ ሀገራት ሲኞሮች ግለሰቦች ሲሆኑ የተቀሩት ዓለማት ግን የመንግሥት ተቋማት ናቸው። የፊያት ኖትና የብረት ሳንቲም ማተሚያና መቅረጫ ዋጋ ከኖቱ የገጽ ዋጋ ያለው ልዩነት ሲኞሬዥ ይሰኛል። የመቶ ብር ኖትን ለማተም 2 ብር ቢፈጅ ሲኞሬገዮ 98 ብር ነው ማለት ነው። ሲኞር በ2 ብር 98 ብር ያገኛል።

የመግዛት ኃይል (Purchasing Power)

የመግዛት ኃይል ማለት አንድ ግለሰብ ወይም ቡድን በያዘው ገንዘብ ሊገዛው የሚችለው ምርት ወይም አገልግሎት መጠን ማለት ነው። የመግዛት ኃይልን ሊወስኑ ከሚችሉ ነገሮች ውስጥ የገቢ ደረጃ፣ ግሽበት፣ ታክስና የምንዛሪ ጉልበት ሊጠቀሱ ይችላሉ። የመግዛት ኃይል ሕዋዉን (Universe) ከሚገዛ የቁጥር ኃይል ጋር ከተያያዘ ቆይቷል። ሕዋው የሚግባባው በቁጥር ነው[26]። ጨረቃ፣ ጸሐይ፣ መሬት፣ ከዋክብትና አጠቃላይ የሕዋው አካላት በሙሉ የሚንቀሳቀሱት በቁጥር ነው። አላህ ፈጥሮና ቆጥሮ እርስበእርስ በቁጥር ያናግራቸዋል። በፍጡርም ስንመጣ ቁጥር ያለው የመግዛት ኃይል አለው። የቁጥር ኃይል የመግዛት ኃይልን ያጎናጽፋል። የቁጥሩን ኃይል በብቸኝነት ይዘው የሚቆጣጠሩት ሲኞሮች ዓለምን በቁጥር ገንዘብ የመግዛት ኃይል ይዘዋል። ለሎሌዎች ያንን ኃይል እየቆረሱ ይሰጣሉ። ላልታዘዛቸው ክፍል

[26] David Park (2007), The Grand Contraption: The World as Myth, Number, and Chance, Princeton University Press ISBN: 9780691130538

ኃይል ያሳጡታል። የመግዛት አቅሙ ለሲኾሮቹ ባለው ታዛዥነት ይወሰናል። ኃያል ገንዘቦች “Hard currencies” ሲባሉ የሌሎች የቅኝ ተገዢዎች መገበያያዎች “Soft currencies” ይሰኛሉ። አቅመቢሶቹ የሚለኩት በኃያሉ መገበያያ ወይም በአሜሪካን ዶላር ነው። (እንዴት ኃያል እንደሆነ በቀጣይ የምናየው ይሆናል)። ሲኾሮቹ እንደ አምላክ “ልዕለ ኃያል” ሲባሉ መግዣውን “ገንዘብ ሁን” ይሉታል። “ይሆናልም”።

ሲኾሮች አምላካዊ ባሕሪይ ይዘዋል። ቅዱስ መጽሐፉ “ፊያት” ነው። መቅደሱ ባንክ ሲሆን ሸይኾቹና ቀሳውስቱ የባንክ ሠራተኞች ናቸው። የብሔራዊ ባንክ ሊቀ ጳጳስ ወይም ሙፍቲ አለው። የቅድስና ስሙም “ገዥ፣ ሲኾር” ይባላል። ትዕዛዙን የሚያሳልጡ ዲያቆናት፣ ፓስተሮችና ኡስታዞች ማለትም የንግድ ባንኮች ሠራተኞች አሉ። ሌሎች ምእመናን ነጋ ጠባ ወደ አምልኮ ቤቱ (ባንክ) ይመላለሳሉ። ስለት (ዲፖዚት) ያስገባሉ። ካፒታሊስቶች ንብረት አስይዘው “የቁጥር ኃይል” ይዘው ሄደው ንብረት ይገዛሉ። መጽሐፉ ቅድስና ስላነሰው ባደረ ቁጥር የመግዛት ኃይሉ እየቀነሰና እየረከሰ ይሄዳል። በአሁን ወቅት ከቅዱስ መጻሕፍትነት ወደ እርኩስ መጻሕፍትነት ተንደርድሯል።

ፊያት በሲኾር መንግሥት (“አምላክ”) “ይህንን ያህል ግዛ” ተብሎ ቁጥር ይሰጠዋል እንጂ እንደ እሴት ገንዘብ እራሱን በራሱ መወሰን፣ መተመን፣ መመዘንና ዋጋ መስጠት አይችልም። ፊያት በሌላ ይወሰናል እንጂ ሌሎችን መወሰንም ይሁን መለካት አይችልም። በተደጋጋሚ እንደጠየቅነው 100 ብር ስንት ነው? 50 ብር ስንት ነው? ቢባል መልስ አይኖርም። ተመሳሳይ ወረቀት ላይ የተጻፉ ቁጥሮች ናቸው። ውስጡ ባለው የመግዛት ኃይል እና የተቀበልንበት ጊዜ ነው። 100 የተጻፈበት ቦኖ (ኖት) ተቀብለን እንደሁ፤ አምላኩ መንግሥት ላምጪው እንዲከፈል ስለሚያስገድድ በዚያ ልክ እና በዕለቱ ባለው ጉልበት እንገዛበትና የተረከብነውን ምርት ይዘን ፊያቱ

ለሌላ ሰው እናቀብለዋለን። የቁጥሩ ኃይል እንደ መንፈስ በሰዎች መካከል ይዘዋወራል። ያስማማል፣ ያዋጋል። የዛሬ 100 ብር ኖት ጉልበቱ የዛሬ ብቻ ነው። ያለፈው ወር የተቀበልነው 100 ብር ዞሮ ተዟዙሮ እኛ ጋር ሲመጣ ተዳክሞ እናገኘዋለን። በእርግጥ ሳይዞር ቢቀመጥም ያው ነው። ባደረ ቁጥር ይደክማል። በተቃራኒው ወርቅና እህሎች ተመዝነው፣ ተሰፍረውና በራሳቸው ታምነው ስንቀበላቸው፣ የፊያት መገበያያ ግን መንግሥታትን ነው የምናምነው። የእሴት እምነት እራሱ ገንዘቡ ላይ ሲኖር የፊያት እምነት ግን መንግሥታት ላይ የተቀመጠ ነው። የዓለም ፊያቶች ተጠቃለው በአሜሪካ ወሳኝነትና ታማኝነት ላይ ተደምድመዋል። የአሜሪካ መንግሥትና ኩባንያዎች የሌሎች ሀገራትን ፊያቶችን እስከመወሰን ደርሰዋል።

እዚህ ጋር ልናነሳው የሚገባው፣ የዓለም የቢዝነስ ሥርዓት በፈጠረው ፍትጊያ ተጎጂ የሆነው የጎብረተሰብ ክፍል አለ። ይኸውም በተለይ በወለድ ምክንያት የጠራ መረጃ ሳይኖረው እየተሰቃየ ያለው ሙስሊሙ ጎብረተሰብ ነው። የነገሮችን ዕውነታ ተገንዝቦ፣ በሰኪዩላር መንግሥታት የሚወጡ ፖሊሲዎች ላይ ብሎም ፖሊሲዎቹ ከመውጣታቸው በፊትም ሆነ በኋላ የሀገራችን ሙስሊም ሊቃውንት አቅጣጫ ሲያሳዩ አይታዩም። በሁኔታዎች የሚወናበደው የንግዱ ማኅበረሰብ ባልተረዳው ፖሊሲ ‹የእውር ድንበሩን› ሲጓዝ ከብዙ ነገሮች ጋር ሲላተም ይታያል። ሙስሊም ሊቃውንት በዕውቀት ላይ የተመሠረተና ለሀገርም ዕድገት ጭምር የሚሞች ኢስላማዊ ብይን ለማዘጋጀት እንዲችሉ የመነሻ መረጃ ለማቅረብ እንወዳለን። በዚህም መሠረት በቅድሚያ ፊያት ከየት ተነሳ የትስ ደረሰ የሚለውን ታሪክ ለማየት እንሞክር።

የፊያት ኖት ይዘቱና ልኬቱ


ምሳሌ 1፡- በ “The Officail RED BOOK, a Guide Book of United States Paper Money” ውስጥ የአሜሪካን የወረቀት ዶላር፡

ልኬቱ፡- **ርዝመት** 156 ሚሊ ሜትር እና **ስፋት** 66 ሚሊ ሜትር

ሰሪቱ፡- 75% ጥጥ እና 25% ሊነን

ክብደቱ፡- በአማካይ 1 ግራም

አማካይ የዝውውር ዕድሜ፡- 5.8 ዓመት ነው።



ምሳሌ 2፡- በ “Bank of England “Take a Closer Look” Booklet (PDF) እና በ “Mandy Barrow, Project Britain, 2013” መረጃ መሠረት የእንግሊዝ የፓውንድ ስተርሊንግ **ወረቀት**፤ ልኬቱ 149 ሚሊ ሜትር በ 80 ሚሊ ሜትር ወረቀት ነው። ፓውንድ ሌሎች ነገሮቹ ከዶላር ጋር ተቀራራቢ በመሆኑ መደጋገሙ አያስፈልግም።

ለ. የፊያት መገበያያ ታሪኮች

ይህንን ክፍል በሁለት ከፍለን እናየዋለን። **አንደኛው** የፊያት መገበያያ ተጀምሮበታል ተብሎ የሚታመንበት ዘመን በግርድፉና በአጭሩ ስናይ **ሁለተኛው** ደግሞ የዘመናችን የፊያት ለውጦችና ወሳኝ ክስተቶችን እናያለን።

1. ቀዳማይ ታሪክን በጨረፍታ

የወረቀት መገበያያ በቻይና በ11ኛው ክፍለ ዘመን እንደተጀመረ[27] የሚያስረዱ የታሪክ ዘገባዎች አሉ። ገንዘቡ በዚሁ ሀገር በ14ኛው ክፍለ ዘመን **በዩዋን** እና በ15ኛው ክፍለ ዘመን ደግሞ **በሚንግ** ሥርወ መንግሥታት ዘመን በስፋት ጥቅም ላይ ውሎአል።[28] አሁን ያለው የቻይና ገንዘብ "ዩዋን / ሪሚምቢ" እንደሚሰኝ ይታወቃል። "ዩዋን" ማለት "የሪሚምቢ" መለኪያ ነው። ለምሳሌ የእንግሊዝ ገንዘብ "ፓውንድ ስተርሊንግ" የሚባል ሲሆን "ስተርሊንግ" ማለት ከብር ማዕድን የተሠራ ገንዘብ ማለት ነው። የዚህ ገንዘብ መለኪያው ደግሞ "ፓውንድ" ነው። ልክ እንደዚሁ "ሪሚምቢ" የቻይና የመዳብ ገንዘብ ሲሆን መለኪያው ደግሞ "ዩዋን" ይባላል። በወረቀት የተወከለው የቻይናው ሪሚምቢ በ13ኛው ክፍለ ዘመን በአውሮፓዊ ሀገር አሳሹ በማርኮ ፖሎ አማካይነት ወደ አውሮፓ እንደገባ ይገመታል።[29]

በአውሮፓ የስፔይን አንደሉሲያን ከነስሪድ ኢሚሬት ወደ ካቶሊኮች በወደቀችበት ወቅት (1482-1492) የወረቀት መገበያያ ጥቅም ላይ ውሏል። በእርግጥ

[27] Selgin, George (2003), "Adaptive Learning and the Transition of Fiat Money", The Economic Journal, 113 (484)

[28] Von Glahn, Richard (1996), Foundation of Fortune: Money and Monetary Policy in China, 1000-1700, Berkeley; University of California.

[29] David Milesm; Andrew Scott (2005), Macroeconomics: Understanding the Wealth of Nations, John Wiley & Sons, Pate 273

የስፔይን አንደሉስ "ሙስሊም የጨርቃ ጨርቅ ሲራራ ነጋዴዎች" የወረቀት መገበያያን ይጠቀሙ እንደነበር የሚገልጹ ታሪኮችም ተገኝቷል። የወረቀት መገበያያ ዘዴዎቹ እየረቀቁ ወደ ሌሎች የአውሮፓና አሜሪካ ሀገራትም ተስፋፍቶአል።[30] በእንግሊዝ በ19ኛው እና በአሜሪካ ደግሞ በ20ኛው ክፍለ ዘመን በተደራጁ ባንኮች መሠራት ቀጠለ። በ21ኛ ክፍለ ዘመን ወረቀቱ ከወርቅ ደጋፊነት ወደ ለየለት ፊያትነት (ወርቅ አልባነት) ተቀየረ። አሁን ያለው ገንዘብ ከዚያን ጊዜ የጀመረ እድገቱን ዛሬ ላይ አጠናቋል ማለት ይቻላል። ምክንያቱም ፊያት ምን ማለት እንደሆነና እንዴት እንዳወናበደን ሳናውቅ፣ ኑሮአችንም ሳይቀየር ሰምተናቸው የማናውቃቸውና ፊያትን ሊተኩ የሚችሉ የገንዘብ ዓይነቶች ብቅ ማለት ጀምረዋል። እነዚህ ደግሞ ከፊያትም በላይ የተወሳሰቡና ለመረዳት አዳጋች የሆኑ ናቸው።

ገንዘቦቹ ፊያትን ይተኩ አይተኩ ገና ሙከራ ላይ ናቸው። ስለዚህ እኛ ፊያት ሳይገባን እና መሠረቱን እንኳ ባላወቅነው ነገር ሀላል-ሀራም እያልን ስንወዛገብ ከምዕተ ዓመታት በላይ ቆይተናል። ሌሎች "ኮምፒዩተር ወለድ" የሆኑ ገንዘቦችን ለመረዳት ምን ያህል ጊዜ እንደሚበቃን አልታወቀም። አንዳንድ አዲሶቹን ገንዘቦችን ወይም ገንዘብ መሳዮችን ለመረዳት ከፋይናንስ ባለሙያነትም በላይ የኮምፒዩተር ዕውቀትም የሚጠይቁ ናቸው። ለዚህ ምሳሌ ክሪፕቶከረንሲን መጥቀስ ይቻላል። ይህንን ለማወቅ ግን ቢያንስ ፊያትን ጠንቅቀን ማወቅ የግድ ይለናል። ምክንያቱም ፊያት በየጓዳው ስለገባ ለመቀየር የትውልዶች ዕድሜ ይፈልጋልና። የአሁኑን ገንዘብ ምንነት ስናውቅ ቀጣይ ገንዘቦች ምን እንደሆኑ ለማወቅ ይረዳናል። ስለዚህ ቀጥለን ፊያት በ21ኛው ክፍለ ዘመን እንዴት እንዳደገ እናያለን።

[30]Foster Ralph (2010), Fiat Paper Money – The History and Evolution of Our Currency; Berkeley, California, Foster Publishing, Page 59

2. የ21ኛው ክፍለ ዘመን የፊያት መገበያያ ወሳኝ የታሪክ ሒደቶች

በዚህኛው ክፍለ ዘመን ገንዘብ ላይ በጣም ታላቅ ታሪካዊ ለውጦች ተካሂደውበታል። ይህንን ክፍል ስናነብ የወረቀት ገንዘቦችን የወሰኑ ክስተቶችን እናገኛለን። እነዚህ ታሪካዊ ክስተቶች "ሥራቸው" በደንብ ወደ መሬት ጠልቆ ነክሶ ይዞአል። በአሁኑ ሰዓት የዓለምን ገንዘብ እየወሰኑ ያሉት በዚህ ስር የምናያቸው ክስተቶች ናቸው። ከዋና ዋና ክስተቶች ውስጥ፡-

- "የብሬተን ውድስ" ስምምነት፣
- የዓለም ባንክና
- የዓለም አቀፉ የገንዘብ ተቋም (ፈንድ)
- የኒክሰን ሾክ ወይም "ንዝረት" (ኦገስት 15/ 1971)
- ከ1971 በኋላ የተፈጠሩ ጥቂት ክስተቶችን እናያለን።

▪ የብሬተን ውድስ ስምምነት

የብሪተን ውድስ ስምምነት የሚባለው *"የተባበሩት መንግሥታት የገንዘብና የፋይናንስ ኮንፈረንስ"* የሚሰኝ ሲሆን ከጁላይ 1-22 /1944 በአሜሪካ በኒው ሀምሻየር በማውንት ብሬተን ዉድስ ውስጥ በማውንት ዋሽንግተን ሆቴል አሜሪካ፣ ካናዳ፣ ምዕራብ አውሮፓ፣ አውስትራሊያና ጃፓን ተሰብስበው የተፈራረሙት ስምምነት ነው። ኮንፈረንሱ የ2ኛው የዓለም ጦርነት ማብቃትን ተከትሎ የተካሄደ ነው። ኮንፈረንሱ ድንገት የተካሄደ ሳይሆን ከአንደኛው የዓለም ጦርነት (1914) ከፈነዳበት ጊዜ ጀምሮ ሲጠዝ የነበረና *"የዓለም አቀፍ ገንዘብ ምን መምሰል እንዳለበት"*

ሲመከርበት የኖረ ነው[31]። እንግዲህ የብሬተን ውድስ ኮንፈረንስ በተጠቀሰው ሆቴል የሁለተኛው የዓለም ጦርነት ላይ የነበሩ 44 አጋር ሀገራት 730 ተወካዮችን ልከው ተሳትፈዋል። የሶቪየት ኅብረት ልዑካን በስብሰባው ቢገኙም ስምምነቱን ለማጽደቅ አልፈለጉም ነበር። ቢሆንም ሌሎች ሀገራትን በመጨመር በ1945 ሙሉ ለሙሉ ጸደቀ[32]። ኢትዮጵያም ስምምነቱን አጽድቃ የቀዳማዊ አጼ ኃይለ ሥላሴ ፎቶ ያለበት የወረቀት ብር ኖት (ፊያት) በዚሁ ዓመት በአሜሪካ ፊላዴልፊያ ውስጥ ለመታተም በቅቶአል (የዚህኛው ዝርዝር በሌላ ርዕስ ስር ይመጣል)።

በስብሰባው ኢትዮጵያን ወክለው የተሳተፉት፡-[33]

- **ሊቀመንበር፡-** በወቅቱ በአሜሪካ የኢትዮጵያ አምባሳደር የነበሩና ከዚህ ቀደም ከ1942-1943 ምክትል የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር የነበሩት ብላታ ኤፍሬም ተወልደ መድኅን (1894 የተወለዱ)፣
- **ተጨማሪ ልዑክ፡-** የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ገዥ የነበሩት አሜሪካዊው ጆርጅ አልበርት ብሎወርስ ሲሆኑ ከዚያ በፊት የስዑድ ዐረቢያ የገንዘብ ባለሥልጣን ሆነው ሠርተዋል።
- **ለጸሐፊነት፡-** ሄለን ዊላርድ

[31]Ravenhill, John (2005), Global Political Economy, Oxford University Press, Page 328

[32]Edward S. Manson and Robert E. Asher, "The World Bank Since Bretton Woods: The Origins, Policies, Operations and Impacts of the International Bank for Reconstruction" Washington DC: Brooking Institution, 1973, Page 29.

[33] Kurt Schuler and Mark Bernkopf, Who Was at B retton Wood s?, Center for Financial Stability Paper in Finacial History, New York, 2014, Page 9

- **ተጨማሪ ሠራተኛ፡-** ሁግ አር. ቼዝ ነበሩ። በወቅቱ ባንኮቻችን የውጭ ስለነበሩ የተማሩ የውጭ ሰዎችን ቀጥረን እናሠራ ነበር።

ስምምነቱ አሁን እጃችን ላይ ያለውን ገንዘብ የአሁኑን ይዘት እንዲይዝ መስመር ያበጀ ሲሆን አብዛኞቹ የዓለም ሀገራት "የአጠቃላይ ቅኝ ግዛት" የወደቁበት ስምምነት ነው ማለት ይቻላል። በኮንፈረንሱ የመጀመሪያ ተሳታፊ ሀገራት በአሁን ወቅት የዓለምን ኢኮኖሚ የሚያሽከረክሩ ሀገራት መሆናቸውን ማየቱ በቂ ነው።

በስምምነቱ ወቅት በመካከላቸው ስላሉ ገንዘቦችና ምንዛሪ፣ የዓለም አቀፍ ንግድና የግብይት ሥርዓት እንዲሁም ሌሎች ሀገሮች ለስምምነቱ ተገዢ የሚሆኑበት፣ የመከላከልና የመቆጣጠሪያ መንገዶችም ጭምር ተወስኖበታል። ለወሳኞቹ በእርግጥ ታላቅ ስኬት አቀዳጅቶአቸዋል። በእነርሱ አቅጣጫ ካየነው ግኝቱ የ21ኛው ክፍለ ዘመን ታላቅ ግኝት ለመሆኑ ምንም አይካድም። ለሌላው ግን ታላቅ ስቃይ እንደሆነ በደሀው ብዛት ማየት ይቻላል። ሚዛኑ የሞላ ጊዜ በሌላ ሲስተም መቀየሩ አይቀርም። ምክንያቱም እምነትም ዘርም የማይለይ ዓለም አቀፍ ጉዳይ በመሆኑ እያንዳንዱ ክስተት እያንዳንዱ ቤት ድረስ ያንኳኳልና። ከኢስላም ሕግጋት አኳያ ብለን አነሳነው እንጂ ሙስሊም ያልሆነውም ጎብረተሰብ የሚጋራው ጉዳይ ነው።

የስምምነቱን ሒደት ለማየት በአሜሪካ የውጭ ጉዳይ መሥሪያ ቤት መዛግብት (Website Archive) ውስጥ ያለውን እንመልከት።

በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ወቅት የእንግሊዙ ጠቅላይ ሚኒስትር ዊኒስተን ቸርቺልና የአሜሪካው የውጭ ጉዳይ ጸሐፊ ኮርዴል ሁል "ለዓለም ኢድገት ነጻ ንግድ ብቻው በቂ አይደለም። ባይሆን ዓለም አቀፍ ሰላምም ወሳኝ ነው" በሚል ተነጋግረው ከስምምነት ላይ ይደርሳሉ። ጉዳዩ ድንገት የታሰበ ሳይሆን ከ1930ዎቹ ጀምሮ እያነሱ

የሚጥሉት ሃሳብ ነበር። በዚህ ጊዜ እንደ አዲስ እንዲያነሱት ያነሳሳቸውም የሚከተሉትን ለመግታት ነበር። እነሱም ታላላቅ የኢኮኖሚ ቀውሶችን፣ የከፍተኛ ታሪፍ (ቀረጥ) ተግዳሮቶችን፣ ተጻራሪ ገንዘቦች የሚፈጥሩባቸው ግሽበቶችንና ሌሎች የንግድ "ንፍቀ-ክልሎች" (ብሎኮች) የሚያሳድሩት ተጽዕኖዎችን ታግሎ፤ የተረጋጋ ዓለም አቀፍ ሰላምን መፍጠር ነበር።

የመጀመሪያውን ድራፍት ፍራንክሊን ሩዝቬልትና ዊኒስተን ቸርቺል በኦገስት 1941 አዘጋጅተውታል። የቻርተሩ አራተኛ ክፍልን ከወሰድን እንግሊዝና አሜሪካ ለእድገታቸው የሚበጃቸውን ንግድና የዓለም ጥሬ ዕቃዎች ያለችግር የሚያገኙበትን ካርታ ስለወበታል።

በፌብሩዋሪ 1942 ሁለቱም ሀገራት ጉዳዩን በደንብ አጠንክረው በየግላቸው ረቂቅ አዘጋጅተው መክረውበታል። ከ1942 እስከ 1944 ከሁለቱም ሀገራት ኤክስፐርቶች ተውጣጥተው ወደ አንድ አቅጣጫ ደረሱ። በዚህም በ21 ኤፕሪል 1944 ላይ International Monetary Fund (IMF) የሚቋቋምበትን ስምምነት ይፋ አደረጉ። ይህ ስምምነት የብሬተን ዉድስ ስብሰባ ዋነኛ አጀንዳ ሆነ። (አስፈጻሚነቱን) ወደ ተባበሩት መንግሥታት ለማምጣት በጁላይ 1944 የብሬተን ውድስ ስብሰባ ተካሄደ። በዚሁ ወቅት "የሁለተኛው የዓለም ጦርነት የመልሶ ግንባታ ባንክ" በኋላ ላይ የዓለም ባንክ የሆነው ባንክ ተቋቋመ። ሁለቱም ተቋማት በ27 ዲሴምበር 1945 ሕጋዊ የአስፈጻሚነት ሰውነት አግኝተው አሜሪካም የማስፈጸሙን ሥራ በይፋ ተረከበች። ስምምነቱ ለሦስት አስርታት ገደማ ከሠራ በኋላ ዶላርን በወርቅ መቀየር በ1971 በኒክሰን ሾክ ወቅት ቆመ። በፌብሩዋሪ እና ማርች 1973 ዋና ዋና የሚባሉ የኢንዱስትሪ ሀገራት አዲሱን የምንዛሪ ሒደት ተለማመዱት።

አዲሱን የዓለም የገንዘብ ሥርዓት እንዲያሳልጡ International Monetary Fund (የዓለም አቀፍ የገንዘብ ተቋም) እና International Bank for Reconstruction and Development የአሁኑ የዓለም ባንክ ሲቋቋሙ ሁለቱም 29 አባል ሀገራት ይዘው የነበረ ሲሆን አሁን ላይ 189 ሀገራት በአባልነት ተካተዋል።

ነገሩን በይበልጥ ወደ ውስጥ ገብተን ወሳኝና አንኳር ነጥብ ለማንሳት ያህል **ወርቅ በወቄት 35 ዶላር ሒሳብ እንዲሆንና የአሜሪካ ዶላር ደግሞ "የሪዘርቭ (መጠባበቂያ) ገንዘብ" እንዲሆን** የሚለው የስምምነቱ መሠረታዊና ውጤት ነው። ይህ ማለት ዶላር በተዘዋዋሪ መንገድ ወርቅ መሰብሰቢያ ሆነ ማለት ነው ወደሚል ድምዳሜ ሊያመራን ይችላል። የማንክደው ሐቅ ግን የዓለም አቀፍ የገንዘብ እና ንግድ ሒደት አሜሪካ እንድትቆጣጠረው ዳኝነት ችሮአታል። በተጨማሪም አሜሪካ የዓለምን ሁለት ሦስተኛ ወርቅ የመቆጣጠር መብቶችን አመቻችቶላታል።

ሌሎች ሀገሮች ወደስምምነቱ በውድም በሁኔታዎች አስገዳጅነትም ተስበዋል። እንደሚታወቀው የሉአላዊ ሀገራት መሪዎች የየዜጎቻቸው ወኪሎች ናቸው። ሁሉንም ሀገራት ማለትም በወቅቱ የተገኙትም ሆኑ ኋላ ላይ የተካተቱ በሙሉ የ1944ቱ የብሪተን ዉድስን ስምምነት በውድም፣ በግድም ባለመረዳትም ተቀብለዋል። በእነርሱ ስር እኛ ተራ የዓለም ዜጎችም ስምምነቱን ሳንጠየቅ በግድ ተቀብለነዋል ማለት ነው። ሌሎቻችን ከመንግሥቶቻችን ውጭ መሆን ስለማንችል ነው። ጉዳዩ ጊዜው ደርሶና ተጽዕኖ ፈጣሪ መሪዎች ተፈጥረው፣ የዓለምን ማኅበረሰብ አስተባብረው ካልቀየሩት በስተቀር እንዳለ ይቀጥላል። እኛም እንደ ኢትዮጵያዊ ከዚህ ስምምነት ማምለጥ አንችልም። ምክንያቱም መንግሥቶቻችን ሌላው ሀገር እንደፈረመው ፈርመውታል። እንደ ሙስሊም ደግሞ ከእምነታችን ጋር እንዴት ይሄዳል የሚለውን ማየትና ከሐገራችን የገንዘብ ሥርዓትና ፖሊሲዎች ጋር

ተስማምተን በሀገራዊ ልማቶችና ኢንቨስትመንቶች ላይ እንዴት እንሳተፋለን የሚለው ቀዳሚ ጉዳይ ነው።

ዛሬ "በፊያት አልገበያይም" ማለት ልክ "ምግብ አልመገብም" እንደማለት ነው። የዚህ ርዕስ ዓላማ አሜሪካንን ማስጠላት ሳይሆን በየግላችን ኑሮአችን ላይ እየወሰነ ያለውን ገንዘብ ዕውነታውን ተረድተን የኑሮአችንን አቅጣጫ እንድናስተካከል በማሰብ ነው። ስለዚህ ምን እናድርግ የሚለው ከዑለሞቻችንም (ሊቃውንት) ባሻገር የየግለሰቡም የመንግሥታችንም ጭምር ኃላፊነት ነው።

▪ የዓለም ባንክ መቋቋም

የዓለም ባንክ የተሰኘው ተቋም በ1944 በአሜሪካ ዋሽንግተን ከተማ የተቋቋመና የብሬተን ዉድስ ስምምነት ውጤት ሲሆን ስምምነቱን ለማሳለጥ የተቋቋመ (የተጠናከረ) ባንክ ነው።[34] በአሁኑ ወቅት ባንኩ 189 አባል ሀገራት ያሉት ሲሆን በሥሩ አምስት ድርጅቶች አሉት። አምስቱ ድርጅቶች

(1) International Bank for Reconstruction and Development,

(2) The International Development Association,

(3) The International Finance Corporation,

(4) The Multilateral Investment Guarantee Agency,

[34]Goldman, Michael (2005), Imperial Nature: The World Bank and Struggles for Social Justice in the Age of Globalaization; New Haven, Page 52

(5) The International Centre for Settlement of Investment Disputes" የተሰኙ ግዙፍ ድርጅቶች ናቸው። International Bank for Reconstruction and Development የሚባለው የመጀመሪያውና የዓለም ባንክን የወለደ እናት ባንክ ነው። ሌሎቹ አራቱ ድርጅቶች በኋላ የተዳበሉና የአሁኑን የዓለም ባንክ የፈጠሩ ቡድኖች (ግሩፖች) ናቸው።

የድርጅቱ ተልዕኮ (ከድረ-ገጹ የተወሰደ) "To end extreme poverty and to promote shared prosperity" በግርድፉ ሲተረጎም "አስከፊ ድህነትን ማጥፋት እና የጋራ ብልጽግናን ማፋጠን" ይላል። ሆኖም ግን የአስከፊ ድህነት መንስኤ እንደሆነ (በተለይ ሙስሊም ያልሆኑ) በርካታ ጸሐፍት በተለያየ ጊዜ ተችተውታል። ከድርጅቱ ሥራዎች ውስጥ ዋናው ለደሀ ሀገራት ብድር ማቅረብ ነው። ብድሩ ዞሮ ዞሮ በወለድ እና በፊያት መገበያያ በመሆኑ ሀገራቱ ከድህነት እና ባርነት የሚወጡበት መንገድ አስቸጋሪ ነው ማለት ይቻላል። ደሀ የተባሉ ሀገራት የተፈጥሮ ሀብት ጉድለት ኖሮባቸው ሳይሆን ሀብቶቻቸው በዚህና መሰል ባንኮች በመያዣነት (Collateral) ከመወሰዱም በላይ ፊያት (ባዶ ወረቀት) አምጥተው የተፈጥሮ ሀብት፣ የተማረ የሰው ኃይል ማጋዝ እና የመንግሥታት አስተዳደራዊ መዋቅሮች ላይ ጫና ሲያሳድሩ ይታያሉ። ብዙ ሀገራት የባንኩ ባለዕዳ በመሆናቸው መውጫ መንገዱ ርቆባቸዋል።

▪ የዓለም አቀፍ የገንዘብ ተቋም (I.M.F.)

ይህ ተቋም በብሬቶን ውድስ ስምምነት መሠረት በ1944 ሲቋቋም ዋና ሥራው በአባል ሀገራት መካከል የሚካሄድ የንግድ፣ የገንዘብ ዝውውሮችና ክፍያዎችን (Balance of Payments) መቆጣጠር ነበር። 189 አባል ሀገራት ሲኖሩት ከዲሴምበር 27/1945 ጀምሮ ሙሉ ለሙሉ ወደ ተግባራዊ ሥራው ገብቶአል። ስምምነቱ 31 አንቀጾችን የያዘ ሲሆን በተለያዩ ጊዜያት እንደ ሁኔታው ተሻሽለዋል። ድርጅቱ ከዓለም

ባንክ ጋር ጎን ለጎን ሆኖ ይሠራል። አሁን ባለው የድርጅቱ መተዳደሪያ አንቀጾች ውስጥ አንቀጽ አንድ ላይ ስድስት ዓላማዎች ሰፍረዋል። ከስድስቱ ዝርዝር አንቀጾች ውስጥ ፡-

ሀ. በቋሚ ድርጅቶች በኩል (ባንኮች ሊሆኑ ይችላሉ) የዓለም አቀፍ የገንዘብ ትብብር ማድረግ

ለ. የዓለም አቀፍ ንግድ እና የተመጣጠነ እድገትን ማፋጠን

ሐ. ምንዛሪን መቆጣጠርና ሌሎች ተወዳዳሪ ምንዛሪዎችን መከላከል

መ. የተለያዩ ተመጋጋቢ የክፍያ ሲስተሞችን ማቀላጠፍና በአባል ሀገራት መካከል የሚካሄዱ የንግድ ልውውጦች ላይ የውጭ ምንዛሪ ችግሮችን መቅረፍ

ሠ. በአባል ሀገራት መካከል የፈንድ ዕጥረት እንዳይኖር መተማመኛ መፍጠርና የክፍያ ልዩነቶቹን ማስተካከል

ረ. በተጠቀሱ ዓላማዎች አማካይነት የክፍያ የማስተካከያ ጊዜዎችን ማሳጠርና ሚዛኖችን ማስጠበቅ

የዓለም አቀፍ የገንዘብ ተቋም ዋና ሥራው ከገንዘብ አቅራቢነት ይልቅ ተቆጣጣሪነት ላይ ያመዝናል። የብሬተን ውድስን ስምምነት ተጻራሪዎች ከመጡ ዓለም አቀፍ ጦርነት ሊያስነሳም ይችላል። በአንቀጾቹ ላይ በሜይ 31/1968 ማሻሻያ ተደርጎባቸው እንዳበቁ፤ በ1971 “የኒክሰን ሾክ” የተባለውና የብሬተን ውድስን ስምምነቶችን የተጣረሰ ከስተት ተወለደ። ይህም የዓለም ገንዘብን ወደለየለት ፊያትነት ቀየረ።

▪ የኒክሰን ሾክ ወይም "ንዝረት" (ኦገስት 15/ 1971)

በ1971 እሁድ ኦገስት 15ኛው ቀን ላይ ገንዘብ ወደ ወረቀትነት የተቀየረበት ታሪካዊ ቀን ነበር። ቀደም ባሉት ገጾች የወረቀት መገበያያ ከ11ኛው ክፍለ ዘመን ጀምሮ እንደነበር አይተናል። እነዚያኞቹ ቢያንስ ደጋፊ ወርቅ ወይም ብር ወይም መዳብ ነበራቸው። **<u>ዕሁድ ኦገስት 15/ 1971 (ነሐሴ 9/1963) ግን የመለያ ቀን ሆነ።</u>** አጠቃላይ ስለገንዘብ ስናወራም ይሁን ስንወያይ እንዲሁም ፈትዋዎች (ብይኖች) እና ጥናቶችን ስናነብ ይህንን ዕለት ወርቅና ወረቀት የተለያዩበት ወይም ፍቺ የፈጸሙበት "የመለያ ዕለት (የውሙል ፉርቃን)" አድርገን መውሰድ ያስፈልጋል። ምክንያቱም ከዚህኛው ዕለት በፊትም የወረቀት ገንዘቦች ነበሩ። የወረቀት መገበያያን የተመለከቱ ብዙ መጻሕፍት እና ፈትዋዎችም (ታይማኖታዊ ብይኖችም) ተላልፈዋል። ቀኖቹን ሳናይ ስለወረቀት መገበያያ ያወራሉ ብለን በደፈናው ብንጠቀማቸው ይህንን ክስተት ስለማያውቁት የተሳሳተ ድምዳሜ ላይ ያደርሱናል።

ወደ ንዝረቱ ስንመለስ ፕሬዝዳንት ሪቻርድ ኒክሰን የ1944ቱን የብሬተን ዉድስን ስምምነት የሚጻረር ነገር ውስጥ ለምን ገባ ካልን ቀጣዩን እውነታ እናገኛለን። በብሬተን ዉድስ ስምምነት ላይ የአሜሪካ ዶላር የዓለም አቀፍ ሪዘርቭ ገንዘብ ሆኖአል። ስለዚህ ዶላር ማለት "ለምን ከየት" ተብሎ የማይጠየቅ "ታማኝ" ገንዘብ በመሆኑ አሜሪካ ዶላር እያተመች ዕቃ መሰብሰብ ያዘች። ያ ሁሉ "ያለ ወርቅ ማስያዣ" የተበተነውን ዶላር ተይዞ ቢመጣ ግን አሜሪካ ወርቅ መክፈል አትችልም ነበር። የሆነው ግን ይኸው ነው። በማስያዣ ለታተሙ ዶላሮች የተቀመጠው ወርቅም "አለ ወይስ የለም" የሚለውም ገና ያልደረስንበት ጉዳይ ነው። በትክክል ወርቅ አስቀምጠው ዶላር ያሳተሙ ሀገራትም ወርቆቻቸውን ማግኘት አልቻሉም። በመሆኑም ወርቆቹ አለመኖራቸው ወይም ከተቀመጠው ወርቅ በላይ ወረቀት መታተሙ አሜሪካንን ወደዚህኛው ክስተት አምጥቶአታል።

የብሬተን ስምምነት ማለትም *“ወርቅ እያስቀመጡ ዶላር ማተም”* የሚለው ባለበት ሁኔታ በባዶ ሜዳ ብዙ ወረቀት ማተም ማለት ብዙ ወርቅ ማጣት ነው። በባዶ የተሰደደው ወረቀት ተሰብስቦ ቢመጣ ማለት *“ተንጋለው ቢተፉ ተመልሶ ባፉ”* እንደሚባለው ነው። ለዚህም ነው እኮ ቢያንስ ወርቅ እያስቀመጡ ወረቀት ቢታተም ኖሮ መንግሥት ወረቀት ለማተም አይቀብጥም ነበር የሚባለው። ያኔ አሜሪካኖች ግን ክህደታቸውን ተማምነው አተሙ ወይም ክስተቱ ወደ ክህደት አመጣቸው። መካዳቸው አግባብ ነው ወይስ አይደለም ሌላ ርዕስ ነው። የሚገርመው ከብሬተን ዉድስ ስምምነት በፊት በ1933 የአሜሪካ ፕሬዝዳንት ሩዝቬልት የሀገር ውስጥ የዶላር በወርቅ መቀየርን አስቁሞ ነበር። ምክንያቱ ደግሞ መንግሥት እንጂ ግለሰብ ወርቅ መጠየቅ አይችልም በሚል! ይህንኑ አሠራር ነው ወደ ዓለም ማኅበረሰብ የተዛወረው። የ1971ዱ የዓለም አቀፍ ክህደት በመሆኑና የዓለምን ገበያን በማናጋቱ የተነሳ ነው “Nixon shock”[35] ማለትም “የኒክሰን ንዝረት” የሚል ስያሜ የተሰጠው።

ቢያንስ ለሩብ ምዕተ ዓመታት ያህል ከዓለም ሕዝብ ላይ ወርቅ ተሰብስቦበታል። በብዙ ሕትመቷ ምክንያት ግን አሜሪካ ዶላር ለሚያመጣ ሀገር ወርቅ መሸጥ (መመለስ) ከብዶአታል። በብሬተን ስምምነቱ መሠረት እሠራለሁ ስትል ደግሞ ልክ እኛን የዋጋ ግሽበት ናላችንን እንደሚያዞረው አሜሪካንንም የዋጋ ግሽበት ናላዋን አዞረው። ብዙ ወጪ በለመዱ ዜጎቿ ላይ ጫና ፈጠረ። በወቅቱ ስዊዘርላንድ፣ እንግሊዝ፣ ጀርመንና ፈረንሳይ ኢኮኖሚያቸው ከፍተኛ የሆነ እድገት እያሳየ ነበር። በጁላይ 1971 ስዊዘርላንድ የ50 ሚሊዮን ዶላር ወርቅ ጠየቀች። ሁኔታው ስላላማራት በአግስት 9/1971 ከብሬተን ዉድስ ስምምነት መውጣቷን

[35] Andrea Wong. “The Untold Story Behind Saudi Arabia’s 41-Years U.S. Debt Secret”, Bloomberg.

አወጀች።[36] ፈረንሳይም በተደጋጋሚ እየወተወተች ነበር። በመጀመሪያ ዙር ጥያቄዋ ብቻ የ19 ሚሊዮን ዶላር ወርቅ ይጫንልኝ አለች። ጀርመንም በተሻሻለው ኢኮኖሚዋ ምክንያት ብዙ ወርቅ ጠየቀች። ሀገራት ወርቄን፣ ጨርቄን ማለት ቀጠሉ።

በመሆኑም ዓርብ ኦገስት 13/1971 (ነሀሴ 7/1963 ኢ.አ.) ከሰዓት በኋላ ፕሬዝዳንት ኒክሰን ከ12 የኋይት ሀውስና የመንግሥት ግምጃ ቤት ኃላፊዎች ጋር በመሆን ምስጢራዊ ስብሰባ አካሂደው ሦስት ውሳኔዎችን በዓለም ሕዝብ ላይም ጭምር ወሰኑ። ውሳኔውን ዕሁድ ምሽት ኦገስት 15/1971 በቴሌቪዥን ተሰራጨ።

1. የአሜሪካ 61ኛውን የግምጃ ቤት ዋና ጸሐፊውና የቴክሳስ ገዥ የነበረውን ጆን ቦውደን ኮናሊ ከዋና ጸሐፊነት በማገድ *"ዶላርን በወርቅ መቀየሪያ መሰኮት"* ተዘጋ። ማንኛውም የውጭ ሀገር መንግሥት ዶላር አምጥቶ በወርቅ መቀየር አይችልም ተባለ።

2. የመንግሥት ትዕዛዝ ቁጥር 11615 "የዋጋ፣ የኪራይና የደመወዝ ማረጋጊያ" ተፈርሞ ማክሰኞ ኦገስት 17/1971 ታተመ።

3. አሜሪካዊው የሀገሩን ዕቃ እንዲጠቀምና የውጭ ሀገር ምርቶችን ለመቀነስ በገቢ እቃዎች ላይ የ10 በመቶ ሱር ታክስ ተጣለ።

ከፕሬዝዳንት ሪቻርድ ኒክሰን የቴሌቪዥን ንግግር ውስጥ፡-[37],[38]

[36]Baltensberger Ernst, Der Schweizer Franken (2013), Neue Zurcher Zeitung Verlag, Pages 111, 268

[37]Lowenstein, Roger; "The Nixon Shock"; Bloomberg BusinessWeek Magazine. 4 August 2011

[38]Nixon, Richard. "Address to the Nations Outlining a New Economic Policy: The Challenge of Peace". The American Presidency Project.

የአሜሪካ ዶላር የዓለም የገንዘብ ማረጋጊያነት ሚናውን እኛው መጠበቅ አለብን። ባለፉት ሰባት ዓመታት በዓመት በአማካይ አንድ የገንዘብ ቀውስ ይከሰታል።

ዋና ጸሐፊ ሚስተር ኮናሊ በጊዜያዊነት ከሥራቸው ታግደዋል። ዶላርን በወርቅ ወይም በሌሎች የማከማቻ ንብረቶች መቀየር ከእንግዲህ አይቻልም። ምናልባት መቀየር የሚቻለው የገንዘብ መረጋጋታችንን የሚያስተማምን እና የአሜሪካንን ጥቅም የሚያስጠብቅ ከሆነ ብቻ ነው።

አሁን ይህ ጉዳይ ምንድን ነው ከተባለ በጣም ቴክኒካል ነው። ምንድን ነው ካላችሁኝ (ዶላርን) በየወቅቱ ግሽበቱን ማስተካከል የሚለውን ድምጽ እስከነአካቴው መዝጋትና ማሳረፍ ነው።

የውጭ መኪና መግዛት ከፈለጋችሁ ወይም ውጭ ሀገር መሄድ ከፈለጋችሁ፣ የገቢያው ሁኔታ ዶላራችን ሊገዛው የሚችለው ነገር መጠነኛ ቅናሽ ሊያሳይብን ይችላል። ነገር ግን ይህንን ሁሉ ቁጥር ያለው አሜሪካዊ የአሜሪካ ምርቶችን ከተጠቀመ የነገው ዶላራችሁ የዛሬው ዶላር ጋር እኩል ይሆናል። ይህንን ስታደርጉ፣ በሌላም ዓለም ዶላር የተረጋጋ ይሆናል።

ወርቅ አስቀማጭም ወረቀት አታሚም ዋነኞቹ የምዕራብ ካፒታሊስቶች ስለነበሩ "በኒክሰን ንዝረት" በዓለም አቀፍ ደረጃ ቃል ኪዳን መፍረስ **ትልቁ የዓለም ክህደት** ልንለው እንችላለን። ዶላርን በወርቅ የመለወጥ ሥርዓት ማለትም የታተሙ ዶላሮችን ከዝውውር ሰብስቦ ይዞ ለመጣ የተቀመጠውን ወርቅ መመለስ (redeemability) ስምምነት በአንድ ወገን አፍራሽነት ፈረሰ። እስቲ ማፍረሳቸው ልክ ነው እንበል። ምክንያቱም የሆነ ሀገር ከባዶ ሜዳ (እራሳቸው ያተሙትም ቢሆን) ወረቀት (ዶላር) ይዞ አሜሪካ ሄዶ ያስቀመጥኩትን "ወርቅ ስጡኝ" ማለት

አያስተማምንም አይደል? ታዲያ ዛሬ እነሱስ ከባዶ ሜዳ ጭራሽ የራሳችን ያልሆነ ወረቀት አምጥተው ያላስቀመጡትን ወርቅና ንብረት ስንሰጣቸው እንዴት ፍትሐዊ ይሆናል? እየሆነ ያለው ግን እንግዲህ ይኸው ነው። ይህ ባዶ ወቀሳ ሳይሆን መራር ዕውነታ ነው። በዚህ ላይ ነው "ወለድ፣ ሀላል፣ ሀራም፣ ወዘተ እየተባባልን ምእመናን ለምእመናን የምንወዘጋገበውና የምንወጋገዘው። ፕሬዝዳንት ኒከሰን *"ግሸበቱን ማስተካከል የሚለውን ድምጽ"* ተገላግለውት ይሆናል። ነገር ግን በየዓለማት በሚገኙ በተለይ የተፈጥሮ ሀብት ሳያጡ ፈያትና መሰል ፍልስፍናዎች ባቆረቆዛቸው ሕዝቦች ዘንድ ግን በድምጽ ማጉሊያ እየጮኸ ነው።

እንግዲህ በተጠቀሱት ሒደቶች የዓለም መንግስታትም ሕዝቦቻቸውን በመወከል ስምምነቱን ፈርመዋል። ሕዝቡም መንግሥታ(ቶቹን) አምኖ ተቀብሎአል። እንደሚታወቀው ከስር የሚተዳደረው አብዛኛው የተማረውም ያልተማረውም እላይ ምን እንደሚካሄድ አያውቅም። በቃ "በይሆናል" እና "በይመስለኛል" ይመሻል ይነጋል። ድሕነትና የኑሮ ውድነቱ ግን እየከፋ ይቀጥላል። የአይኤምኤፍ አስተዳዳሪ ሆኖ የሚሾመው ከላይ የሚቆጣጠረው በኢኮኖሚ የበላይ የሆነ ሀገር ነው። በመሆኑም የአሜሪካ መንግሥት በአይኤም ኤፍ (የዓለም አቀፍ የገንዘብ ፈንድ ወይም ድርጅት) እና በዓለም ባንክ አማካይነት፤ ከዚያም በየሀገራት ወኪል መንግሥታት በኩል የእያንዳንዱ የዓለም ነዋሪ "ኪስ ያወልቃል" ብንል ቢያንስ እንጂ አይበዛም። ምዕራባዊያን ቁጥር ያበድሩንና ንብረት ይወስዳሉ። የሚገርመው ደግሞ ዛሬም አበዳሪ የምንላቸው፤ ትናንት የዓለም ሕዝብን የካዱቱ መሆናቸው ነው።

የዚህ መጽሐፍ አዘጋጅ በኒክሰን ንዝረት ወቅት አልተወለደም። በብሬተን ስምምነት ወቅት ደግሞ አባቱም አልተወለደም። ስለዚህ ወላጆቻችንም ጭምር የዓይነት ገንዘብን የተመለከተ ተግባራዊ ዕውቀት ስለሌላቸው፤ በእኛ ወቅት ደግሞ

በጣም በጦዘበት ወቅት ስለተወለድን ብዙዎቻችን ፊያት የተፈጥሮ ገንዘብ መስሎናል። ይህንን ስናነብ ብዙ ጥያቄዎች አእምሮአችንን ቢያጨናንቁ ሊገርመን አይገባም።

ይህንን ክስተት ቁርአን እንደሚከተለው ያስጠነቅቃል። አንቀጹ በቀጥታ ስለብሪተን ውድስና ኒክሰን ሾክ የሚያወራ እንጂ ከታሪኩ 1400 ዓመታት በፊት የተላለፈ መልዕክት አይመስልም።

«ከመጽሐፉ ሰዎችም በብዙ ገንዘብ ብታምነው ወዳንተ የሚመልስ ሰው አለለ። ከእነሱም በአንድ ዲናር እንኳ ብታምነው፤ ሁል ጊዜ በርሱ የምትጠባበቅ ካልሾንክ በስተቀር የማይመልስ ሰው አለለ። «ይህ በመሃይማን (በምናደርገው) በእኛ ላይ ምንም መንገድ የለብንም» ስለሚሉ ነው። እነርሱ ሏየወቁም በአላህ ላይ ውሸትን ይናገራሉ። (ቁርአን 3:75)

በዚህ አንቀጽ የመጽሐፉ ሰዎች ውስጥ እንደማንኛውም ሰው በኩንታል (ቂንጣር) ሙሉ ወርቅ (ገንዘብ) የሚታመን እንዳለ ሁሉ በአንድ ዲናር እንኳ የማይታመን አለ። ምክንያቱም የመሃይማን (መንጋዎች ሕዝቦች፤ በአይሁዶች አነጋገር ቂል ዐረቦች) ገንዘብ ብንበላ አምላክ ፈቅዶልናል ብለው ስለሚያምኑ ነው። ዋናው ነጥብም እምነቱ ጋር ነው። ስለዚህ እነርሱ ዘንድ ወርቅ ስታስቀምጡ ተጠባበቁዋቸው እያለን ነው። ለመንጋው ወረቀት እየሰጡ ወርቁን ከሰበሰቡ እና ካላመዱት በኋላ ካዱት። የዚህ ዘመን የቁርአን ተንታኝ ቢመጣ ከኒክሰን ሾክ በላይ ይህንን አንቀጽ የሚተነትንለት አያገኝም።

▪ ከ1971 በኋላ

በኒክሰን ንዝረት ምክንያት ዶላር በውጭ ሀገራት ዋጋ አጣ። ከሁለት ዓመታት በኋላ በኦክቶበር 1973 ላይ የስዑዲው ንጉሥ ፈይሰል የዓረብ-እስራኤል የስድስቱ ቀን ጦርነትን በዋናነት በደገፉ ሀገራት ላይ የነዳጅ ማዕቀብ ጣለ።[39] ይህ ዓመት "የመጀመሪያው የነዳጅ ቀውስ" በመባል ይታወቃል። በአሜሪካው የውጭ ጉዳይ ዋና ጸሐፊ በሄነሪ ኪሲንጀርና በስዑዲው ንጉሥ ፈይሰል መካከል ለዘጠኝ ወራት የፈጀ ድርድር ተካሂዶ ከነዳጅ ላኪ ሀገራት ዋነኛይቱን ስዑዲ ዓረቢያ ተነጥላ ማርች 1974 ላይ ነዳጅን በዶላር ለመሸጥ ተስማማች። በስምምነቱም ነዳጅ ከ3 ዶላር ወደ 12 ዶላር በበርሜል አደገ። ዶላር ከወርቅ ድጋፍ ወደ ነዳጅ ድጋፍ አድጎ **"ፔትሮ-ዶላር"** ተፈጠረ። ሌላ ዓይነት ገንዘብ ተፈጠረ ማለት ነው። ጉዳዩ ይበልጥ ያወሳሰበው በወቅቱ በአጠቃላይ በሙስሊሙ ዘንድ የተሻለ ተሰሚነት የነበረውን የስዑዲው ንጉሥ ፈይሰል አሜሪካ ይኖር በነበረና የግማሽ ወንድሙ ልጅ በሆነው በአልጋ ወራሽ ፈይሰል ቢን ሙሳዒድ "በዕጅ አዙር ሊሆን ይችላል" በ1975 ተገደለ። የንጉሥ ፈይሰል ገዳይ አልጋ ወራሽ ፈይሰል ቢን ሙሳዒድ እዚያው ስዑዲ ውስጥ በስቅላት ተቀጣ[40]። ከንጉሡ ሞት በኋላ ግን መካና መዲናን የሚቆጣጠሩት ነገሥታት ለሙስሊሙ ለውጥ የሚያመጣ ነገር ማለትም ፊያትን በማስረዳት ላይ ብዙም አልሠሩም።

በሁለተኛውና የ1979ኙ የነዳጅ ቀውስ የሚባለው በኢራን በአያቱላህ ኹመይኒ መሪነት ኢስላማዊ አብዮት ተነሳ። ዓለመል ኢስላም የሱኒ ሺዓ ውጥረት ውስጥ ወደቀ። በዚያ በኩል ውጥረቱን ለማባባስ የኢራቁ ሰዳም ሁሴንን በማስታጠቅ የሱኒ-

[39]Smith, Charless (2006), Palestine and the Arab-Israel Conflict, New York: Bedford, Page 329.

[40]James Wynbrandt (2010), "A Brief History of Saudi Arabia, Infobase Publishing, Page 236.

ሺዓ ጦርነት ተባባሰ። (መረጃዎቹ በርካታ ስለሆኑ፣ መጥቀስም ለርዕሳችን አስፈላጊ ባለመሆኑና ከርዕሳችንም ጋር ስለማይሄድ በመካከለኛው ምስራቅ የነበረውን ሁኔታ በጥቅል እንደሚከተለው ተሰባስበዋል)።

የኢራን ኢራቅ ጦርነት ከ1980 እስከ 1988 (ስምንት ዓመታትን) ፈጀ። በሁለቱም ብዙ ሰው ተገደለ። በኢራን በኩል ከሁለት መቶ ሺህ እስከ ስድስት መቶ ሺህ ሰው ሲገደል በኢራቅም ከሁለት መቶ ሀምሳ ሺህ እስከ አምስት መቶ ሺህ ሰው ተገድሎአል። እያንዳንዱ ሀገር ከስድስት መቶ ቢሊዮን ዶላር በላይ ወጪ አድርጎአል። ኢራንን ሲደግፉ የነበሩ ሀገራት ሶሪያ፣ ቻይና፣ ሰሜን ኮሪያ፣ ሊቢያና አሜሪካ ሲሆኑ ኢራቅን ሲደግፉ የነበሩት ሶቪየት ኅብረት፣ ቻይና፣ ፈረንሳይ፣ እንግሊዝ፣ ሳውዲ ዓረቢያ፣ ኩዌት፣ ዮርዳኖስና አሜሪካ ነበሩ። አሜሪካና ቻይና በሁለቱም በኩል ሲደግፉ ነበር። ልክ ይህኛው ሲያበቃ ሳዳም ጦሩን ከኢራን አስወጥቶ ደጋፊው የነበረችዋ ኩዌትን አጠቃልላለሁ ብሎ ወረረ። ኩዌቶች "አሜሪካ ሆይ ድረሽ" አሉ። አሜሪካኖች ኩዌት ገቡ። ስዑዲ ኢራቅን ተጻርራ ከአሜሪካ ጎን ሆነች። ጦርነቱ ከኢራን-ኢራቅ ወደ ሌሎች ሀገራት ተዛመተ። በሁኔታው የተበሳጩ ሰዎች ይሁኑ ሌላ በማናውቀው ምክንያት የአሜሪካ "የመስከረም 11/2011 የሽብር" ጥቃት መጣ፤ ሌላ ወረራ፣ ሌላ ምስቅልቅል። እሱ ሲያበቃ የዓረብ አብዮት ተነሳ። ይህ ሁሉ ችግር ነዳጅን በፊያት (ዶላር) የመሸጥ ያለ መሸጥ ችግር አንዱ አካል ነው። ነዳጃችንን በወረቀት አንሸጥም ያሉትን ለምሳሌ የኢራቁ መሪ ሳዳም ሁሰይን በሰላጤው ጦርነት እና የሊቢያው መሪ ሙአመር ገዛፊ "በዓረብ አብዮት" በአሰቃቂና በአዋራጅ ሁኔታ ተገደሉ።

የ1979ኙ የኢራኑ አብዮት በተነሳበት ዓመት ላይ የስዑዲ "ሀይአ ኪባረል ዑለማእ" እና የኩዌት የዑለማ ምክር ቤት የወረቀት መገበያያ መጠቀም እንደሚቻል

ብይን (ፈትዋ) ሰጥተዋል (ALMUNAWWAR 2013)። ይህ ፈትዋ ብዙም ሳይፈተሽ እስካሁን ድረስ ዘልቆአል። በሺዓው በኩል ፊያት ላይ የተሰጡ ፈትዋዎች ቢኖሩም ሱኒው ዓለም ግን ቢመራመርባቸውም እንኳ ከመደርደሪያ ወጥተው የነ1979ኙን የስዑዲና ኩዌት ዑለሞችን ፈትዋ ሊከልሱ አልቻሉም። ከዚያ በኋላ በሱኒው ዓለም በወረቀት መገበያያ ላይ ይህ ነው የሚባል ስር ነቀል ፈትዋ ባለመሰጠቱ፤ የከፋ ጉዳት አስከትሎአል። አሁንም ቢሆን በተለይ የኃይማኖት ሊቃውንት ከፍተኛ ትኩረት ሊሰጡት ይገባል።

ዓለመል ኢስላም ከመካና መዲና ሊቃውንት ብይን እንዲወርድለት በጉጉት እየተጠባበቀ ነው። ያ አካባቢ ግን በራሱ ጉዳይ ውስጥ ተዘፍቋል። የያኔው ፈትዋ (ሀይማኖታዊ ብይኑ) ዓለመል ኢስላምን ወደ ሚሰቀጥጥ ቀውስ እንደከተተው በገሀድ እያየነው ነው። ከነ97ነ ወዲህ ብዙ ታላላቅ ከስተቶች ተካሂደዋል። በቅትቡ እንኳ የዓለምን የፋይናንስና ኢኮኖሚ ሒደት የቀየሩ እንደ ኮቪድ -19 ዓለም አቀፍ ወረርሽኝ በሽታ እና የራሺያ ዩክሬይን ጦርነቶች አሉ። በኮቪድ - 19 ወቅት አሜሪካ በዐርባ አመታት ያላተመችውን ዶላር በአንድ ዓመት አትማለች። ይህ ግሽበት ለዓለም ሁሉ ተሰራጭቶ ብዙ ሀገራት ፈተና ውስጥ ገብተዋል። የእነዚህም ዝርዝሮች እንደተለመደው በመ-ገንዘብ መጽሐፍ ነው የምናገናቸው። ከላይ የብሔራዊ ባንክን ፊያት አይተናል። ቀጥለን የዚሁ ተቀጥላ የሆነው የንግድ ባንኮች ገንዘቦች እንዴት እንደሚፈጠሩ እናያለን። **በድጋሚ ለማስታወስ ያህል ፈትዋና መጻሕፍት ስናገኝ ከኒክሰን ንዝረት በፊት ወይስ በኋላ ብለን እንየው።**

اللَّهُمَّ صَلِّ عَلَىٰ سَيِّدِنَا مُحَمَّدٍ وَعَلَىٰ آلِهِ وَصَحْبِهِ وَسَلِّمْ

3

1.2.2.2. የንግድ ባንክ ገንዘቦች (ክሬዲትስ)

የንግድ ባንኮች ገንዘቦች እንደ ብሔራዊ ባንክ በሕትመት ሳይሆን ተቀማጭ ገንዘቦችን በማበደር እና መጠባበቂያ ተቀማጭ በመያዝ የሚፈጠሩ ገንዘቦች ናቸው። Fractional reserves በአማርኛው "ክፍልፋይ መጠባበቂያ" ተቀማጮች የሚለው ሊቀርበው ይችላል። እላይ ያየነውና ፊያት የተሰኘው በብሔራዊ ባንክ በኩል የታተመ (Printed) ገንዘብ ሲሆን ሕትመቱ ገደብ አለው። በንግድ ባንኮች በብድር መልኩ የሚፈጠር (Created money) ገንዘብ ግን ያለገደብ ይቀጥላል። የተቆጣጣሪ ብሔራዊ ባንኮች ቁጥጥር የለበትም ማለት ሳይሆን ብድር እስካለ ድረስ የገንዘብ ፈጠራው ይቀጥላል። በአጭር አገላለጽ ብሔራዊ ባንኮች በዓመት የተገደበ ገንዘብ ሊያትሙ ወይም ሲተርፍም ሊያቃጥሉ ወይም በተለያዩ መንገዶች መልሰው ዝውውሩን ሊቀንሱት ይችላሉ። ንግድ ባንኮች ግን ብሔራዊ ባንክ ባተመው ገንዘብ ላይ ተመርኩዘው ሌላ ገንዘብ ይፈጥራሉ። ይህም ተበዳሪ እስካለ ድረስ የሚቀጥል ነው። እንዴት እንደሚፈጠር ማየቱ የተሻለ ግንዛቤን ይፈጥራል።

ምሳሌ፡-

(1) እርስዎ አንድ ሚሊዮን ብር የሚያወጣ ወርቅ ብሔራዊ ባንክ አስቀምጠው የወረቀት መገበያያ (ፊያት) ተቀበሉ እንበል። የብሔራዊ ባንኩ በአንድ ልውውጥ አብቅቷል።

(2) አንድ ሚሊዮን ብርዎን የብሔራዊ ባንክ ሕግ በሚያዘው መሠረት ወደ አንዱ ንግድ ባንክ አምጥተው ያስቀምጡታል። ስለዚህ ገንዘቡን አምጥተው ያስቀመጡበት ንግድ ባንክ የእርስዎ ባለዕዳ ነው። ብሔራዊ ባንክ ለንግድ ባንክ በሰጠው የማበደር ስነሥርዓት መሠረት 10% ለመጠባበቂያ ይይዝና

ዘጠኝ መቶ ሺህ ብሩን ያበድረዋል። የእርስዎ ገንዘብ “የመግዛት ኃይል” በብድር ወደ ሌላ ሰው ዞረ ማለት ነው።

(3) ባንኩ ሲያበድረው ከዘጠኝ መቶ ሺህ ብር በላይ ንብረት (Collateral) ይዞ ነው። ተበዳሪው ባለዕዳ ይሆንና ንግድ ባንክ አየር ላይ ባለሀብት ሆነ ማለት ነው። አሁን ባለው አሠራር ገንዘብ ከባንክ ማውጣት ገደብ ስላለው እንቅስቃሴዎች ባንክ ለባንክ ወይም ሒሳብ ለሒሳብ ነው የሚዘዋወሩት።

(4) ዘጠኝ መቶ ሺህ ብር የተበደረው ሰው ብሩን ከንግድ ባንክ አያወጣውም። እዚያው እያለ ዕቃ ወደገዛው ሰው ሒሳብ ውስጥ ያስገባዋል ወይም ለብድር ከተፈቀደለት ፊያት ወረቀት ወጭ አድርጎ ይዞ ሔዶ ይከፍለዋል።

(5) ባለሱቁ ደግሞ የሸጠበትን ዘጠኝ መቶ ሺህ ብሩን ተቀብሎ በተራው እዚያው ንግድ ባንክ ወስዶ ያስቀምጠዋል።

(6) ንግድ ባንኩ ከባለሱቁ የተቀበለውን 900,000 ብር በብሔራዊ ባንክ መመሪያ መሠረት 10% ለመጠባበቂያ ያስቀምጥና ቀሪውን ያበድረዋል። ባንኩ በሁለተኛው ጊዜ ስምንት መቶ ሺህ ብር ቢያበድር እስካሁን 1,700,000 ብር አበድሯል ማለት ነው። 800,000 ብር የተበደረው ሰውዬ ከአንድ ወይም ከአምስት ቦታ ዕቃ ይገዛበታል።


(7) ዕቃ የሸጡ ሰዎች እቤት ማስቀመጥ ስለማይችሉ ንግድ ባንኮ አምጥተው ያስቀምጣሉ። ንግድ ባንክ እስካሁን ስንት ብር በቁጠባ አገኘ? ከባለ ወርቋ 1,000,000 ብር፣ ከሁለተኛው ባለሱቅ 900,000 ብር፣ ከዚህኛው ባለሱቆች 800,000 ብር በድምሩ 2,700,000 ብር ተቀብሏል። እስከዚህኛው ዙር ከ1,000,000 ብር በላይ ካዝና ውስጥ አለ።

(8) ንግድ ባንክ በዚህኛው በሦስተኛው ዙር 700,000 ብር አበደረ እንበል። ሦስተኛው ተበዳሪ የተበደረውን ብር ለሆነ ገበሬ ከፈለው።

(9) ገበሬውም ንግድ ባንክ ነው ይዞ የሚመጣው። ንግድ ባንክ እስካሁን 3,400,000 ብር በቁጠባ አግኝቷል።

(10) እንዲህ እየቀጠለ በመቶኛው ትራንዛክሽን ላይ፤ ንግድ ባንክ በ1,000,000 ብር ተቀማጭ በድምሩ ዘጠኝ ሚሊዮን ብር ያበድራል ወይም ይፈጥራል። መጀመሪያ ከብሔራዊ ባንክ ወደ ንግድ ባንክ 1,000,000 ብር ይዞ የመጣው (ችዋ) ሰው ሒሳብ፤ ዙራ ተዟዙራ መጠባበቂያ ትሟላለች። ይህ በአንድ መስመር ብቻ የተሠራ የንግድ ባንክ አሠራር ነው። ላለማወዛገብ ሌሎች ፈቃጅና ከልካይ ሕጎች በምሳሌው አልተካተቱም። (ብሮቹ ወደ ሙሉ ቁጥር ተጠጋግተዋል)።

ከስር ያለውን ስዕል ስትመለከቱ ይበልጥ ግልጽ ይሆናል። ንግድ ባንኩ አንድ ሚሊዮን ብሩን እየገመሰና እያገላበጠ በማበደር ብቻ የማይታተም ገንዘብ አየር ላይ ይፈጥራል። ይህ ክፍልፋይ መጠባበቂያ (Fractional Reserve) ይሰኛል።



እ.ኤ.አ. በ2020/2021 ወይም በኢት.አ. በ2013 በጀት ዓመት የኢትዮጵያ ልማት ባንክን ሳይጨምር የ17 ንግድ ባንኮች የገንዘብ ገቢ (deposits) ብር አንድ ነጥብ ሦስት ስድስት ትሪሊዮን (ብር 1,357,538,940,000) ሲሆን ያበደሩት (financing) ደግሞ ብር አንድ ነጥብ ሦስት አምስት ሦስት ትሪሊዮን (ብር 1,285,389,164) ነው። በመቶኛ ሲሰላ 95% አበድረዋል። የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ከሰበሰበው ውስጥ 96% በማደር ቀዳሚ ሥፍራ ይዟል።[41] በዚያው ዓመት የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የሪዘርቭ

[41] ከዚህ ቀጣይ ባለው መ-ገንዘብ በሚለው መጽሐፍ በዝርዝር ተቀምጧል።

መመሪያ 10% የነበረ ቢሆንም ከመመሪያው አልፈው አበድረዋል። የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ በመመሪያ ቁጥር SBB/84/2022 የንግድ ባንኮች የመጠባበቂያ ገንዘብ ከ10 ፐርሰንት ወደ 7 ፐርሰንት አውርዶታል። ስለዚህ ንግድ ባንኮች ከሰበሰቡት ገንዘብ ውስጥ 93 ፐርሰንቱን ማበደር ይችላሉ ማለት ነው።

በ1998 የካናዳ ባንክ ባሳተመው ሪፖርት የካናዳ በንኮች ያላቸው ሀብት እና ካዝናቸው ውስጥ ያለው ገንዘብ ሲነጻጸር 1፡358 ማለትም 1 ዶላር ጥሬ ገንዘብ ለ358 ዶላር ሀብት ነበር። ባንክ ውስጥ 358 ዶላር ኖሮት ላውጣ ብሎ የሚሄድ ሰው ሊያገኝ የሚችለው 1 ዶላር ብቻ ነው። 357 ዶላሩ እየተራባ ወጥቷል[42]። ሁሉም ሰው መጥቶ ገንዘቤን አምጡ ቢል ማግኘት አይችልም። ይህ እኮ ወረቀት (ፊያት) ሆኖም ማለት ነው።

የንግድ ባንኮች የፍራክሽናል ሪዘርቭ ጥቅሞች

- ያለምንም የሕትመት ወጭ ገንዘብ ማባዛት/መፍጠር መቻሉ የመጀመሪያው ጥቅሙ ነው። የብሔራዊ ባንክን ዘጠኝ እጥፍ ድረስ ገንዘብ ማተም ያስችላል። (Other things remain constant).
- ዕዳን ወደ ገንዘብነት ቀይሮ ሥራ ላይ ያውላል።
- ገንዘብ ቆጣቢዎች ገንዘባቸው ለተጠበቀበት የአገልገሎት አይከፍሉም፤ ይልቁንም ባንኩ ገንዘባቸውን ሥራ ላይ አውሎ ትርፍ ይከፍላቸዋል።
- በማንኛውም ወቅት ለሌላ ሰው እንዲከፍሉት፣ እንዲያስተላልፉትና፣ እንዲያወጡት ሊፈቅድላቸው ይችላል።

[42] Umar Ibrahim Vadillo, Fatawa on Banking, The Use of Interest Received on Bank Deposits PDF, 2006, Page 35.

- ባንኩ የአሳላጭነት ሥራ ስለሚሠራ ከአስቀማጮች ላይ ብዙ ጊዜና ወጭ ይቀንስላቸዋል።

የሪዘርቭ ባንኪንግ ሲስተም ጉዳቶች

- በችግር ወይም አለመተማመን ወይም የኢኮኖሚ ውድቀት ወቅት "ወደ ባንክ ሩጫ" ሊያመጣ ይችላል። ብዙ ሰው ብር ሊያወጣ ግር ብሎ ወደ ባንክ ቢሔድ ባንኩ የሚከፍለው ገንዘብ ላያገኝና ሀገሪቷ ችግር ውስጥ ልትወድቅ ትችላለች። ባንኮቻችን 95% በማበደራቸው ለሕዝብ የሚሰጡት ብር 5% ብቻ ነው።
- "መደበኛነት" የሚባል ስልቹ አኗኗርን ይፈጥራል።
- ገንዘቦች ከደሃ ወደ ሐብታም ይዘዋወራሉ።
- ፒራሚዳዊና ኢ-ፍትሐዊ የሐብት ክፍፍል ይፈጥራል።
- ግሽበት ያባብሳል።

اللَّهُمَّ صَلِّ عَلَىٰ سَيِّدِنَا مُحَمَّدٍ وَعَلَىٰ آلِهِ وَصَحْبِهِ وَسَلِّمْ

1.2.2.3. የፊያት መገበያያ መለያዎች

(FIAT Characteristics)

ፊያት ብዙ ጸባዮች አሉት። ከነዚህ ውስጥ አምስቱን እናነሳለን። እነዚህን ስናነሳ ከየት ወደ የት እንዳደገ አብረን ለማየት እንሞክራልን። ስለአራጣም በስፋት የምናየው በዚሁ ክፍል ነው። የምናነሳቸው ጸባዮች፡-

- ግልጽ አራጣ (ወለድ) መሆኑን
- የአራጣ ኢኮኖሚን ለማሳለጥ የተፈጠረ መሆኑን
- ሲለካም ሲቀመጥም ዋጋ አለመኖር
- አስገዳጅ መሆኑ
- ዘካ ላይ ያለው ሁኔታ እንደ አንድ ምሳሌ እናያለን።

እነዚህን በዝርዝር እናያለን። በጽሑፉ ውስጥ ክሬዲትም የፊያት አካል አድርጋች ተገንዘቡት። መሸጋገሪያ ክፍት ቦታዎች ላይ በነቢያችን ﷺ ላይ ሶለዋት ማውረዳችሁን አትዘንጉ።

اللَّهُمَّ صَلِّ عَلَىٰ سَيِّدِنَا مُحَمَّدٍ وَعَلَىٰ آلِهِ وَصَحْبِهِ وَسَلِّمْ

- ፊያት ግልጽ አራጣ (ወለድ) መሆኑ

ሀ. የአራጣ ትርጉም በሸሪዓ

1. የጊዜ መዘግየት አራጣ
2. የድንቁርና ዘመን አራጣ
3. የመጨመር አራጣ

ለ. የፊያት መገበያያ አራጣ የሆኑባቸው ሦስት ደረጃዎች

1. ፕሮሚሰሪ ኖት ሲፈጠር
2. የፕሮሚሰሪ ኖት ደጋፊ ወርቅ ሲካድ
3. ሁሉም ሀገራት የየራሳቸው ባዶ ኖት ሲያዘጋጁ
   - 3.1. ብሔራዊ ባንክ ባዶ ቁጥር ሲፈጥር
   - 3.2. ንግድ ባንኮች የሚፈጥሩት አራጣ
   - 3.3. ባዶ ፊያት ገበያ ገብቶ ንብረት ሲቀራመት

መንደርደሪያ፡- ፊያት ከመነሻው ያለምንም ንብረት “ከልብ-ወለድ” በመጀመሩ ብቻ አራጣነቱ (ወለድነቱ) እዚህ ጋር ይጀምራል። “ገንዘብ ሁን ይባላል፤ ይሆናልም”። ፊያት ማለት “ይሁን” ማለት እንደሆነ እላይ አይተናል። ልክ ገንዘቡ ሲፈጠር ወለድ አብሮት ይፈጠርና ወደ ሕዝቦች ይበተናል። ከዚያም አራጣው በተለያየ መንገድ ይሰበሰባል። ፊያት የአራጣ ሥርዓት መከወኛና ማሳለጫ ረቂቅ ሽቦ ነው። ለዚህም ባንኮች ተፈጥረዋል። መደበኛ ሥራቸው ይህንን ሥርዓት ማገልገል ሲሆን የብዙኃን ንብረቶች ተሰልፈውና መሥመር ሠርተው ወደ ጥቂት ግለሰቦች ይተማሉ። ከዚህ የአራጣ ሥርዓት ማፈንገጥ ቀርቶ ማሰብም ብዙ ዋጋ ያስከፍላል። የአሁኑ የዓለም

ሥርዓት ሙሉ ለሙሉ የቆመው በአራጣ ላይ ነው። ከአራጣ ውጭ መኖር የማይታሰብ ሆኗል። አራጣ በሰዎች መካከል የሀብት ክፍፍልን ያፋልሳል። አሁን የምናየው የሀብት ሥርጭት መፋለስ (disequilibrium) ትልቁን ድርሻ የሚወስደው አራጣና የአራጣ ሥርዓት ነው። አራጣ የባንክ ወለድ ብቻ የሚመስላቸው ብዙ የዋህ ሙሰሊሞች አሉ። እርሱ ምልክቱ እንጂ በሽታው አይደለም። በሽታው የካፒታሊዝም ሥርዓት ነው። አራጣን ያወቀ ካፒታሊዝምን ያውቃል። ካፒታሊዝምን ያወቀ አራጣን ያውቃል። ትልቅ ስህተት የተፈጠረው የሙስሊም አስተዳደር (ኸሊፋ) ወድቆ በሶሻሊዝምና በካፒታሊዝም ሲተካ የሙስሊም የተሀድሶ አራማጆች ካፒታሊዝምን እናሰልማለን ብለው አራጣን ቀባቡት። ቢራን ቅዱስ ጊዮርጊስ ቢባል ማስከሩን እንደማይቀይረው ሁሉ፤ አራጣን አማና ብንለው ነጃሳነቱን አይተወውም። እንደውም ይብሳል።

ብዙ ዓይነት አራጣዎች አሉ። “እንዴት ይፈጠራሉ?” የሚለው፤ በዚህ ንዑስ ርዕስ ሥር የምናያቸው ሁለት ክፍሎች ያስረዱናል። ወደዚያ ከመሻገራችን በፊት የአራጣ (ወለድ) ትርጉም እንመልከት። አራጣና ወለድ ሰፊ ልዩነት አላቸው። ሆኖም እዚህ ጋር አንድነታቸውን ወይም ልዩነታቸውን ማስረዳቱ ብዙም ፋይዳ አይኖረውም። **በዚህ መጽሐፍ አራጣና ወለድ እየተለዋወጡ (interchangeably) ጥቅም ላይ ውለዋል።**

የወለድ/አራጣ አጠቃላይ ትርጉም፡- ተመጣጣኝ ነገር ሳይሰጡ ጭማሪ መቀበል ወይም ተመጣጣኝ ነገር ሳይቀበሉ ጭማሪ መክፈል ወለድ ይሰኛል።

ከእንግሊዝኛ መዝገበ ቃላት፡-

“አራጣ ግብረገባዊ ወይም ሞራላዊ ያልሆነና አበዳሪዎች አግባብነት በሌለው መንገድ የሚከብሩበት ነው”። (ኦክስፎርድ የእንግሊዝኛ መዝገበ ቃላት 2015፣ የ“Usury” ትርጉም)

ወለድ በሸሪዓ የሚከተለው ትርጉም ተሰጥቶታል።

በቋንቋ ደረጃ፡-

“ያለምንም ተመጣጣኝ ጥቅም የሚደረግ ጭማሪ ወለድ ይባላል” (አልቃዲ አቡበክር ኢብኑል ዓረቢ፣ አህካሙል ቁርአን)

“ወለድ ማለት የሌሎችን ንብረት (ሀብት) ያለምንም አጸፋዊ ተመጣጣኝ ጥቅም መውሰድ ነው” (ኢማም ፈኽሩዲን አርራዚ፣ ተፍሲር ከቢር፣ የቁርአን ሱረቱል በቀራ፡ 275 ትንታኔ)

ሀ. አራጣ (ወለድ) በሸሪዓ መመሪያዎች

አራጣና ከአራጣ ጋር የተያያዙ ገንዘቦችን በቁርአን፣ በነቢያችን (ﷺ) ሀዲስ እና በሊቃውንት (ፉቀሐእ) ሥራዎች በአጭሩ እናያቸዋለን።

የአራጣና የገንዘብ አመዳደብ ወይም አተናተን የተለያዩ ሊቃውንት በተለያየ መንገድ ከፋፍለዋቸዋል።

- ✓ ቁርአናዊ አራጣ፣ ሀዲሳዊ አራጣና ፉቀሐዊ አራጣ በሚል በሦስት የከፈሉ
- ✓ ***ማዘግየት የፈጠረው አራጣ እና መጨመር የፈጠረው አራጣ በሚል በሁለት***
- ✓ ***የማዘግየት አራጣ፣ የመጨመርና የድንቁርና ዘመን አራጣ በሚል በሦስት***
- ✓ ጥቅል አራጣ እና ዝርዝር አራጣ በሚል በሁለት
- ✓ ግልጽ አራጣ እና ድብቅ አራጣ በሚል በሁለት
- ✓ የንግድ አራጣ እና የብድር አራጣ በሚል በሁለት
- ✓ የእጅ በእጅ አራጣ፣ የዱቤ አራጣ እና የብድር አራጣ በሚል በሦስት
- ✓ የጊዜ አራጣ (Time value) በሚል በአንድ ብቻ
- ✓ የዕቃ አራጣ እና የጊዜ አራጣ በሚል በሁለት ከፍለው ጽፈዋል።

ውጤቱ አንድ እስከሆነ ድረስ ሁሉንም ለያይተን ማየት ከማደናገር ውጭ ጥቅም የለውም። በጣም የተለመደው በሁለት የተከፈለው ማለትም **የማዘግየት አራጣ (ሪበ-ነሲአ)** እና **የመጨመር አራጣ (ሪበል-ፈድል)** ናቸው። አራጣ በመሠረቱ አንድ ሲሆን እርሱም የማዘግየት አራጣ ነው። ሪፈል-ፈድል ወይም ጭማሪ የሚፈጠረው መዘግየቱ ነው የሚል አቋም የያዙ አሉ። መዘግየት የገንዘብ ጭማሪ ባይፈጥር እንኳ የጊዜ ጭማሪ ያመጣል። ተበዳሪ ባይጎዳ አበዳሪ ይጎዳል። በሌላ በኩል ደግሞ የጊዜ ጭማሪ ሳይኖር እጅ በእጅ ቢሆን እንኳ፤ ማበላለጥ የተከለከለባቸው ስድስት ገንዘቦች አሉ። በእነርሱ ምክንያት የጊዜና የመጠን አራጣ በሚል ነው በሁለት የተከፈለው። የጊዜ አራጣ ውስጥ ልዩ ትኩረት የተሰጠው “ሪበል-ጃሂሊያ” ወይም የድንቁርና አራጣ የሚባል አለ። ይህ ደግሞ በዚህ ዘመን

ስለተስፋፋ እና የፈያት መገበያያ መሠረታዊ ባሕሪይ ስለሆነ ትኩረት ለመስጠት በሦስት ከፍለን እናያለን።

አራጣን (ሪባን) በሦስት ከፍለን እንይ

ነ) የጊዜ መዘግየት አራጣ (ሪበ-ነሲአ)፡-

አራጣን አራጣ ያሰኘው በጊዜ መዘግየት የሚመጣ አራጣ ሲሆን ሊቃውንት “ሪበ-ነሲአ” ይሉታል። የማዘግየት አራጣ ክልክልነቱ በሊቃውንት (ፉቀሐእ) ዘንድ የሐሳብ ልዩነት አይታይበትም። በአመዳደብ ደረጃ አንዳንድ ሊቃውንት ቁርአናዊ ሪባ (ቁርአናዊ አራጣ) ይሉታል። ሌሎቹ በጥቅል የተገለጸ አራጣ፣ የብድር አራጣ፣ የጊዜ አራጣ፣ ረቂቅ አራጣ ወዘተ እያሉ ይጠሩታል። በነቢያችን (ﷺ) ሀዲስም ሪባ የሚባለው ማዘግየት ብቻ ነው ብሎ ይህንን ያጠብቀዋል።

“ጥቅል ንግግር (ሙጅመል)” የሚለው ማንሳቱ ይጠቅማል። በቁርአንም ይሁን በነቢያችን (ﷺ) ሀዲስ፤ የመዘግየት አራጣ (ሪበ-ነስእ) በቁርጥ ክልክል ይደረግ እንጂ ከሁለተኛው የነቢያችን (ﷺ) ኸሊፋ (ምትክ) ዑመር ኢብኑል ኸጣብ (ረዲየሏሁ ዓንሁ) እና ታዋቂ የቁርአን ተንታኝና የነቢያችን (ﷺ) ባልደረባ ዓብዱላህ ኢብን አባስ (ረዲየሏሁ ዓንሁማ) እንዲሁም ከኡሳማ ኢብን ዘይድ (ረዲየሏሁ ዓንሁ) ጀምሮ “የቁርአኑ አራጣ” ጥቅል ከሚሰኙ የቁርአን አንቀጾች ውስጥ በመሆኑ ‹‹ይበልጥ በተብራራ›› የሚል ምልከታ አላቸው። አራጣ ክልክል መሆኑ አይደለም የሚያሻማው። ጥቅል (ሙጅመል) ስለሆነ ዝርዝር ትንታኔ ይፈልጋል ማለታቸው ነው። በኸሊፋው ዑመር ኢብኑል ኸጧብ (ረዲየሏሁ ዓነሁ)

ምልከታ፤ የአራጣ አንቀጾች መጨረሻ ከወረዱ አንቀጾች ሲሆን፤ ሦስት ነገሮች ማለትም አራጣ፣ ኽሊፋነት (የሥልጣን አተካክ) እና ወላጅም ተወላጅም ወራሽ ያጣ ንብረት (ከላላ)" ቢያብራሩልኝ ብዬ እመኝ ነበር ያሉበት ዘገባ (በሱነን ኢብን ማጃ ሀዲስ ውስጥ አለ)። በዚሁ ምክንያት ዑመር (ረዲየሏሁ ዓንሁ) ለጥንቃቄ ሲሉ፤ *ሪባ (አራጣ) ብቻ ሳይሆን "ረይባ (ጥርጣሬን)" ጭምር ራቁ* ብለዋል። የአራጣ ጉዳይ በቀላሉ ጀምረን የምንቋጨው አይደለም። ቁርአን የጠቀለለው ጉዳይ ሀዲስ ያብራራዋል። ሀዲስ ያላብራራው ሊቃውንት ማለትም የነቢያችን (ﷺ) ባልደረቦችም ጭምር ይበልጥ ይተነትኑታል። ምክንያቱም ቁርአንና ሀዲስ ጥቅል ቋንቋች ናቸው።

የማዘግየት አራጣ (ሪበ-ነሲኣ ወይም ነስእ) በብድር ወይም ዱቤ ሽያጭ ላይ የሚፈጠር የጊዜ ዋጋ (Time value) ነው። ጊዜ በመጨመሩ የሚጨመር ክፍያ ብቻ ሳይሆን ጭማሪ ክፍያ ባይኖርም እንኳ ጭማሪ ጊዜው (Time value of money) በራሱ አራጣ ነው ማለት ነው። ጭማሪ ጊዜው አበዳሪው ለአላህ ብሎ የሚተወው ከሆነ አራጣውን መልካም ብድር ወይም "ቀርዶን ሀሰን" ውስጥ ያስገባለታል። ገና ስናበድር ማሰብ አለብን። ዘካ ብቻ ሳይሆን ማንኛውም ምጽዋትና ብድር ከአላህ ምንዳ የሚገኝባቸው አምልኮዎች በመሆናቸው ከመነሻው ማሰብ ያስፈልጋል። ብድር ማበደር ከምጽዋት ያልተናነሰ ምንዳ አለው።

የነጻ ብድር የለም። ምክንያቱም ያለምንም ጥቅም መስጠትና ማነባበር የአላህ ብቸኛ ባሕሪይ ነው። ይህንን ባሕሪይ የምንላበሰው በአላህ በኩል ለአላህ ብለን ነው። አላህ በነጻ እንዲሁም በንብብር ስለሚሰጥ፣ ከፈለገም ስለሚወስድ እኛን ማነባበር ከልክሎናል። አላህ የሰጠውን ነው መልሶ የሚወስደው። እኛ ግን እርሱ በሰጠን ሀብት በንግድ ካልሆነ በስተቀር አነባብረን መውሰድ ከልክሎናል።

አላህ ምግብ ስለማይበላ ብሉ፣ ስለማያገባ አግቡ፣ ስለማይወልድ ውለዱ፣ ስለማይተኛ ተኙ፣ ስለማይሰግድ ስገዱ ብሎናል። አይጾምም፤ እንዲሁም አይራበም። ግን ጹሙ ብሎናል። መልሰን አቻኩለን እንድንገድፍ አዞናል። ምግብ ካልበላንማ ከፈጣሪ ጋር ተመሳሰልን ማለት ነው። ስለዚህ ከአንዱ ወደ አንዱ ያዟዙረናል። ወደንም ተገደንም እናደርጋቸዋለን። ምንም ሳይፈልግ የሚሰጥ አላህ ብቻ ነው። ሰዎች ሲሰጡ ምኞታቸው ይታያል። ሲጠቃለል ያለምንም ነገር ብድርም ይሁን ስጦታ ልንሰጥ ግን አንችልም። ባሕሪያችን አይደለም። ስንሰጥ የሆነ ነገር እንፈልጋለን። ለአላህ ብለን ካበደርን ግን ምንዳው ከአላህ ነው። እጅ በእጅ ሽያጭ ተፈቅዶ ማዘግየት የተከለከለው አራጣ ወይም ችግር ስለሚወልድ ነው። ዱቤ ክልክል ነው እያልኩኝ አይደለም። አራጣ ይፈጥራል። አሻሻጣችንን ማስተካከል ያስፈልጋል።

እዚህ ጋር አንድ ጭብጥ እንያዝ። እርሱም፡- ገንዘቦች በሙሉ የአላህ ናቸው። በቁርአን እጅግ በርካታ ቦታዎች እንዳሉ እሙን ነው። ዘካ እና ሌሎች ምጽዋቶች የምንሰጠው ከራሳችን ሳይሆን ከአላህ ወይም አላህ ከሰጠን ገንዘብ ነው። አንድ ሁለቱን ብቻ እንጥቀስ።

*ለእነዚያ በሩቁ ነገር ለሚያምኑ፣ ሶላትንም ደንቡን ጠብቀው የሚሰግዱ፣ **ከሰጠናቸው ሲሳይ** የሚቸሩ ለሆኑት (ቁርአን 2:3)*

እንኳን የምንለግሰው ቀርቶ የምንመገበውም ምግብ ሳይቀር የአላህ ስጦታ ነው።

አላህም ከሰጣችሁ ሲሳይ የተፈቀደ ጣፋጭ ሲሆን ብሉ። ያንንም እናንተ በእርሱ አማኞች የሆናችሁበትን አላህን ፍሩ። (ቁርአን 5:88)

በነጻ የምንሰጠው የለም። አንዱ ተገደን ሲሆን ሌላው ወደን ነው። በብድር ስም ተበዳሪው ሳያውቅ የሚወሰድበትን ብድር አላህ አያረባውም። አያሰባውም። የተቸገረን ሰው በችግሩ ውስጥ እንድንነግድበት አላህ አልፈቀደውም። ስጦታ ከግዴታ ዘካ ወይም ከውዴታ ምጽዋት፤ ካልሆነ ደግሞ የአላህ ውዴታና ምንዳ የተፈለገበት ብድር መሆን አለበት። ተበዳሪው በተባለው ወቅት መክፈል ካልቻለ ወደ ምሕረት ሊቀየርለት ይመቻል። ጊዜው ሲደርስ ጭማሪ ክፍያ ከጠየቅን ግን፤ ሁለቱንም ዓይነት አራጣ (ሪበል-ፈድል እና ሪበ-ነስእ) ይከሰታሉ። የዚህ ተቃራኒ ደግሞ ምሕረት ሲሆን ተበዳሪን ብንምረው ምጽዋት እና ከባርነት ነጻ ማውጣትን፤ ወይም ምርኮኛ መፍታትን ምንዳ እናገኝበታለን።

የድኽነት ባለቤት የኾነም (ባለዕዳ) ሰው ቢኖር፤ እማግኘት ድረስ ማቆየት ነው። (በመማር) መመጽወታችሁ ለእናንተ በላጭ ነው። የምታውቁ ብትኾኑ (ትሠሩታላችሁ)። (ቁርአን 2:280)

የያዝነው ማንኛውም ገንዘብ የአላህ መሆኑን ማመን፣ ከእርሱም ዘካ እና ምጽዋት መለገስ፣ ለተቸገረ ሰው ለአላህ ብሎ ማበደር፣ ተበዳሪ መቸገሩ እርግጠኛ ከሆንን እስኪያገኝ ጊዜ መስጠት፣ በዚህም ወቅት መክፈል እንደማይችል ከተገነዘብን ምሕረት አድርጎ ነጻ ማውጣት ነው። ወደ አራጣ ካዞርነው ከአላህ እና ከመልዕክተኛው ጋር ጦር እየተጋጠምን እንደሆነ ማወቅ ያስፈልጋል። የአራጣን ጣጣ ያመጣው ማበደር ነው። ስለዚህ ይህ እንዳይመጣ በዘካ (ምጽዋት) መበርታት ያሻል። የአራጣ ክልክልነት ደረጃዎች ላይ ይበልጥ ግልጽ ይሆናል።

አራጣ በቁርአን ልክ እንደ አስካሪ መጠጥ የክልከላ ቅደም ተከተል አለው። ከቀላል ተነስቶ በአራት ደረጃ ሕጉን እያጠበቀ ወደ እቀባ ሄዷል።[43]

(ነኛው) ነቢያችን (ﷺ) በመካ አስራ ሦስት ዓመት አስተምረው ወደ መዲና በተሰደዱ በሁለተኛው ዓመት (ሂጅራ) እንደተላለፈ (እንደወረደ) የሚታወቀው አንቀጽ ነው። ከሂጅራ በፊት ነው የሚሉ ተንታኞችም አሉ። አንቀጹ ቀዳሚ መሆኑ ያመለክታል።

« ከበረከትም (ሪባም) በሰዎች ገንዘቦች ውስጥ ይጨመር (ይራባ) ዘንድ የምትሰጡት አላህ ዘንድ አይጨምርም (አይራባም)። ከምጽዋትም (ዘካ) የአላህን ፊት የምትሹ ሆናችሁ የምትሰጡት እነዚያ (ሰጪዎቹ) አበርካቾቹ እነርሱ ናቸው። ቁርአን 30:39»

(የቅንፎቹ የእኔ ጭማሪ ማብራሪያ ሲሆኑ ዓረቢኛው ላይ ሪባ የሚል ቃል ስለተጠቀመ እንዳለ ለማስገባት የተሞከረበት ነው። (ሪባ፣ ሊየርቡው፣ ፈላየርቡ የሚሉ የዐረብኛ ቃላት ናቸው)።

የቁርአን ተንታኞች ይህኛው አንቀጽ ውስጥ ሪባ (አራጣ የተባለው) የሆነ የግል ጥቅም ተፈልጎ የሚሰጥ ስጦታ እንደ አራጣ ተቆጥሯል። የዚህ ተቃራኒ ደግሞ ዘካ (ምጽዋት) ነውና "ለአላህ ብላችሁ ስጡ፤ ለግል ውስጣዊ ጥቅም የሰጣችሁት አይራባም" ለማለት ነው።

[43] ከየትኛውም ዘመን ባልታየ ሁኔታ በአራጣ የተዘፈቅን ሕዝቦች ማለትም የእኛ ዘመን ነዋሪ፤ ይህንን መንገድ ነው የምንከተለው ወይስ የመጨረሻው የሚባለው አከራካሪ ነው።:

(2ኛው ደረጃ) አራጣ ለስብእና እና ለመልካም ጸባይ ተገቢ ያልሆነ መሆኑ ለመምከር ተከትሎ የመጣ ነው። ለዚህም የቀደምት ነቢያት ዘመን የአይሁዶች ምሳሌ ሙስሊሞች እንዳይደግሙ አስጠንቅቆበታል።

«ከእነርሱ (ከአይሁዶቹ) በቁርጥ የተከለከሉ ሲኾኑ አራጣንም በመያዛቸውና የሰዎችን ገንዘቦች ያለ አግባብ (በጉቦ) በመብላታቸው ምክንያት (የተፈቀደላቸውን እርም አደረግንባቸው)። ለእነርሱም ለከሀዲዎቹ አሳማሚ ቅጣት አዘጋጀን። (ቁርአን 4፡ 161)።

አራጣ የሚበላ ሰው በተለያዩ ችግሮች መልካምና የሚጣፍጥ ነገር እንዳይበላ ሊከለክለው ይችላል። በአሁን ወቅት ጣፋጭ ምግቦችን እንዳንመገብ በብዛት ስንከለከል ይስተዋላል። የዚህ ምንጭ የአራጣ ሲስተም ሊሆን ይችላል። ምክንያቱም ያልተነካካ ሰው ማግኘት እጅግ አዳጋች ነው። ሳንፈልገው ተገደን የምንገባበት ሲስተም ሆኗል። አንድ ሀብታም ከውሻው ያነሰና የጎመዘዘ ምግብ እንዲመገብ በሐኪም ሊገደድ ይችላል። ምዕራባዊያን በዘረጉት የአራጣ ሲስተም እየኖርን በመሆኑ ማምለጥ ቀርቶ ማሰብ እንኳ አልቻልንም።

(3ኛው ደረጃ) ይዞ ወደ ክልክል ሕግ የገባው የቁርአኑ አንቀጽ፤ ንብብር አራጣ (Compound interest) ን በመከልከል ነው። ምክንያቱም የተነባበረ በደል ሲሆን ባለዕዳን ወደ ባርነት ይከታል። ይህንን ድርጊት ቅጣት እንደሚያስከትል ማስጠንቀቂያ ተላልፎበታል።

«እናንተ ያመናችሁ ሆይ! አራጣን የተነባበሩ እጥፎች ሲሆኑ አትብሉ። ትድኑም ዘንድ አላህን ፍሩ»። ቁርአን 3፡130።

በዚሁ ምዕራፍ ቀጣይ አንቀጾች ሊያስከትል የሚችለውን የዚያኛው አለም ችግር ያትታል። እዚህኛው ደረጃ ላይ በንብበር አራጣ (ወለድ) የሚከብሩትን የተገሰጸበትና በዚህ የሚሰቃዩ ተበዳሪዎችን ነጻ ለማውጣት የተበየነበት ነው። የተወገዘው ንብበር አራጣ ብቻ እንጂ በስምምነት ውስጥ ያለው አይደለም የሚል አቋም ያላቸው ሊቃውንትም እናገኛለን። *"ዛሬ ከገዛህ ይህንን ያህል ከወር በኋላ ከከፈልክ ያንን ያህል"* ተባብለው ያለማንም አስገዳጅነት ተስማምተው፤ ተበዳሪ መክፈል አቅቶት ጭማሪ ቢታሰብበት ስምምነት ውስጥ የሌለ አራጣ (ንብበር አራጣን) ነው አራጣ የምንለው። ጊዜ በመጨመሩ የተፈጠረ የስምምነት ጭማሪ አራጣ አይባልም። ጊዜው ሲደርስ ግን ተበዳሪ መክፈል አቅቶት ጊዜ ቢጨመርና ለጭማሪ ጊዜው ገንዘብ ሲጨመር ነው አራጣ የምንለው። ይህም በነቢያችን (ﷺ) የመጨረሻ የሀጅ ዲስኩር (ኹጥባ) የተወገዘው የድንቁርና ዘመኑ አራጣ ነው የሚል መከራከሪያ በማቅረብ ነው። (ይህኛውን አራጣ ለብቻ በሌላ ክፍል ነጥለን እናየዋለን)። በቅደም ተከተል ስንሄድ ቀጣዩ ክፍል ሁሉንም አራጣ ይጠቀልላል።

(4ኛው ደረጃ) አራጣ (ወለድ) የተባለ ሁሉ የተወገዘበትና እምቢ ያለ ደግሞ ከአላህና ከመልዕክተኛው (ﷺ) ጋር የጦር ፍልሚያ ውስጥ እንደገባ የተገለጸበት ነው።

አንቀጾቹ በነቢያችን (ﷺ) የምድር ተልዕኮ የመጨረሻው ዓመት የወረዱ ናቸው።

በአንዳንድ የሀዲስ ዘገባ ከቁርአን መደምደሚያ አንቀጾች ውስጥ ነው የሚሉ አሉ። ወደ ሀዲስ ስንመጣ እናያቸዋለን። ከአዋጁ በፊት በአራጣ ያበደረ ሰው ዋና ገንዘቡን ብቻ ወስዶ አራጣውን እንዳይወስድ ማስጠንቀቂያ አለው።

«እነዚያ አራጣን የሚበሉ ያ ሰይጣን ከመንካቱ የተነሳ የሚጥለው ሰው (ከአውድቁ) እንደሚነሳ ብጤ እንጅ (ከመቃብራቸው) አይነሱም። ይህ እርሱ መሸጥ የአራጣ ብጤ

ብቻ ነው በማለታቸው ነው። ግን መሸጥን አላህ ፈቅዷል። አራጣንም እርም አድርጓል። ከጌታውም ግሳጼ የመጣለትና የተከለከለ ሰው ለርሱ (ከመከልከሉ በፊት) ያለፈው አለው። ነገሩም ወደ አላህ ነው፤ (አራጣን ወደ መብላት) የተመለሰም ሰው እነዚያ የእሳት ጓዶች ናቸው። እነርሱ በውስጧ ዘውታሪዎች ናቸው»። ቁርአን 2፡ 275።

ይህ መልዕክት እስከ 2፡281 ይደርሳል። (ቁርአን 2፡281 የቁርአን ዋህይ (መለኮታዊ ራዕይ) መዝጊያ ነው የሚሉ ሊቃውንት አሉ)። ምዕራፉ በዚህ አያበቃም። እስከ 2፡ 286 ይደርሳል። ከዚህ በመነሳት አራጣ የኢስላማዊ መልዕክት የመጨረሻው ነው የሚለው ሚዛን ይደፋል። እስከዚያ ድረስስ እንዴት ተገበያዩ የሚለው በዚሁ መጽሐፍ በሌላ ምዕራፍ ልታገኙት ትችላላችሁ። ማንኛውም ከፍያ ሲዘገይ አራጣ እንደሚፈጥር አይተናል።

2) **የድንቁርና ዘመን አራጣ (ሪበል ጃሂሊያ)፡-**

ሁለተኛው ዓይነት አራጣ የመጀመሪያው የማዘግየት (ነስእ) አራጣ ዓይነት ወይም ቅጥያ ቢሆንም አራጣውና ዋናው ብድር ሌላ አራጣ እየወለዱና እየተነባበሩ የሚፈጥሩት ዓይነት ነው። አራጣን በሁለት ሲከፈል እላይ (ቁጥር 1) ላይ ያሳለፍነው የማዘግየት አራጣ (ሪበ-ነሲአ) ውስጥ ይጠቃለላል። ይህ ሊቃውንት "ሪበል ጃሂሊያ፣ ሪበል የሁዲያ" ይሉታል። በሌላ አነጋገር የድንቁርና ዘመን ወይም የአይሁድ ዘመን አራጣ ማለት ነው። በዘመናችን ያለው የንብብሮሽ አራጣ (Compound interest) ጥሩ ምሳሌ ነው። ከሁሉም ምሌዎች ደግሞ በደንብ የሚገልጸው የፊያት መገበያያ ሲስተም ነው።

እላይ (ቁጥር ነ) ውስጥ የአራጣ ክልክል ቅደም ተከተሎች ወይም ደረጃዎች ላይ በሥስተኛ የአወራረድ ደረጃ (Chronology) የመጣው ነው። ከነቢዩ ሙሐመድ (ﷺ) በኋላ የመጡ የቀደምት የኢስላም ሊቃውንት የእኛን የካፒታሊዝም ዘመን ቢኖሩት ኖሮ ብዙ ጥናት ያዘጋጁልን ነበር። ምናልባትም ቁጥር አንድ አድርገው ያስተምሩ ነበር። መነጠል የፈለግሁት የካፒታሊዝም ሥርዓት ወፍሮ የንብብር ወለድ ውስጥ ከእግር እስከ ራስ ተዘፍቀንበታል። በዚህ መጽሐፍ ትኩረት የተደረገበት የፊያት መገበያያ አመጣጥ ታሪክ ውስጥ ዓይነተኛ ሚና ተጫውቷል። አሁን ላይ ወለዱ አውቶማቲክ ነው። ሲያድር ይጨምራል ወይም ይነባበራል። የተጠቃሚውን ፈቃድ የሚየጠየቅበት የብድር አራጣ ሲኖር፤ ፈቃድ የማይጠየቅበት ደግሞ የግሽበት እና የታክስ አራጣ አለ። ትንሹ ቀርቶ ይህንን ግልጽ የወጣ ንብብር አራጣ እንኳ መከላከል ወይም ከሥርዓቱ መውጣት አቅቶናል። (ይህንን ጉዳይ የፊያት መገበያያ የንብብሮሽ አራጣዎች የምናይበት ከፍል ላይ ከነአመጣጡ በደንብ ይብራራል)።

3) **የመጨመር አራጣ (ሪበል-ፈድል)፡-**

አንዳንድ ጸሐፊያን እና ተመራማሪዎች ሀዲሳዊ ሪባ (ሀዲሳዊ አራጣ) ይሉታል። አንዳንዶች የሸያጭ አራጣ፣ የእጅ በእጅ ግብይት አራጣ፣ ዝርዝር አራጣ፣ የዕቃ አራጣ፣ የልውውጥ አራጣ ወዘተ ይሉታል። በሊቃውንት (ፉቀሐእ) ዘንድ "ሪበል-ፈድል" ሲተረጎም "የማበላለጥ አራጣ ወይም የመጨመር አራጣ" የሚባለው ነው። እላይ የተጠቀሱት ሁለቱም ዓይነት ሪባዎች (አራጣዎች) በሀዲስ እንዳሉ ሆነው በተጨማሪ በታወቁ ስድስት ንብረቶች (ገንዘቦች) ላይ እጅ በእጅ ልውውጥ ወቅት ይሁን በማዘግየት የሚፈጠር ጭማሪ ከፍያ ካለ፤ አራጣ ይሆናል ብሎ የቁርአኑን አራጣ ይበልጥ ስላብራራና ቴክኒካዊ ትርጉም ስለሰጠ "ሀዲሳዊ ሪባ (ሀዲሳዊ

አራጣ)" በማለት ይጠራል። ቁርአን በጥቅል ያስቀመጣቸውን ነገሮች በሀዲስ ይዘረዘራሉ። የሶላት አሰጋገድ፣ የዘካ አሰጣጥ፣ ጋብቻ፣ ወዘተ ዝርዝር ነገሮች በሀዲስ እንደሚብራሩት አራጣም ላይ በሀዲስ የተብራሩ አሉ ለማለት ነው። የሀዲስ ማብራሪያዎች ጋር በሦስት ከፍለን እናያቸዋለን። ሁለቱ ከቁርአኑ የአራጣ ዓይነቶች ጋር ተመሳሳይ ሲሆኑ አንዱ ግን ለየት ብሎ ወደ ዝርዝር እና ቴክኒካዊ ትንተና ውስጥ ይገባል።

በሀዲስ የአራጣ አገላለጽ ሦስት ዓይነት ነው

(ነኛው) የማዘግየት አራጣ (ሪበ-ነሲአ)፡- *ኡሳማ ኢብን ዘይድ (ረ.ዐ.) እንዳሰተላለፈው ነቢያችን ﷺ ሲሉ ሰማሁ። ወለድ (አራጣ) የለም በማዘግየት እንጂ (የቡኻሪ ዘገባ ቁጥር 386፣ ሙስሊም እና አህመድ ዘግበውታል)።*

የቁርአኑ አራጣ የማዘግየት አራጣ ነው የተባለው ይህንን ሀዲስ ተንተርሰው ነው። አራጣን የሚፈጥረው **ጊዜ** ነው። ማበላለጥን የሚያመጣው የጊዜ መዘግየት ነው። ጭማሪ ክፍያው ውጤት እንጂ ሰበብ አይደለም በሚል፤ አራጣ አንድ ሲሆን ሌሎቹ ውጤቶቹ ናቸው የሚለው ይህኛውን በመንተራስ ነው። ክፍያ የዘገየበት ያለጭማሪ ቢቀበል ጉዳት (አራጣ) ሲሸከም፣ ማካካሻ ቢወስድ ደግሞ የመጨመር አራጣ ውስጥ ይወድቃል። በመሆኑም የአራጣ ጉዳይ ጥቅል ነው ብለው ሐሳብ ያቀረቡ የነቢያችን (ﷺ) ባልደረቦችም ጭምር ምክንያታቸው ጥልቅ ነው። ሀዲሱ በበርካታ ዘጋቢዎች የተዘገበ ስለሆነ ለታማኝነቱ ጥርጣሬ የለውም። ማዘግየት እንዴት ወለድ እንደሚፈጥር ሌላ ሀዲስ እንጨምር።

አነስ ኢብን ማሊክ (ረ.ዐ.) እንዳሰተላለፈው ነቢያችን (ﷺ) ሲሉ እንደሳማሁት አንዳችሁ ለሌላው ብድር አበድሮ ተበዳሪው ምግብ ካቀረበ አይቀበል፣ የሚጋለብ መጓጓዣ ቢጋብዘው አይቀበል። ሲበዳደሩ እንዲህ ያለ ውለታ ለመለዋወጥ ከተሰማሙ እንጂ። (የቢይሀቂይ ዘገባ፤ ኪታቡል ቡዩዕ ባቡ ኩሉ ቀርዲን ጀራ መንፋዓተን ፈሑወ ሪባ)።

ይህ የሚያመለክተው ተበዳሪ በሆነ ግብጣ ብድሩን ከስምምነት ጊዜ በላይ ለማቆየት በር እንዳይከፍት ወይም ያልተገባ ጭማሪ እንዳይከፍልና አራጣ ውስጥ እንዳይወድቅ ለመጠንቀቅ ነው። ገንዘብ ያበደርነው ተበዳሪ መንገድ ላይ አግኝቶ በመኪናው ቢሸኘን ወይም መኪና ቢያውሰን አራጣ ተፈጠረ ማለት ነው።

(2ኛ) የድንቁርና ዘመን አራጣ፡- ይህ የነቢያችን (ﷺ) አጎት የአባስ ኢብን ዓብዱልሙጦሊብ አራጣ ይባላል። የአይሁዶች አራጣ ጋር ይመሳሰላል። ንብብር ወለድም ይኖረዋል። የተከለከለውም በሃያ ሦስተኛው የነቢይነት ዘመን፤ ማለትም በመጨረሻው የሀጅ ኹጥባ (ዲስኩር) ላይ ነው። *ከጃቢር ኢብን ዓብዱላህ (ረ.ዐ.) እንደተላለፈው የነቢያችን (ﷺ) የሰንብት ሀጅ ቀን አሉ፡- ከዛሬ ጀምሮ የድንቁርና ዘመን አራጣ ተሰርዟል። ቀድሜ የምሰርዘው የእኛ (ቤት) አራጣ ሲሆን እርሱም የአጎቴ የአባስ ኢብን ዓብዱል ሙጦሊብ አራጣ ነው። ሙሉ ለሙሉ ተሰርዞላችኋል። (ሀዲሰ ኢማም ሙስሊም፣ ኪታቡል ሀጅ)*። ይህ የማዘግየት አራጣ በጣም ግልጹና የሚያሻማው ዓይነት ሲሆን፤ ጊዜ ሲጨምር ጭማሪ ክፍያን ማነባበር ነው።

(3ኛ) ይህኛው የሀዲሱ አራጣ የሚል ልዩ ስም ያሰጠ የአራጣ ዓይነት ሲሆን፤ የአራጣን ጉዳይ ከጥቅል (ሙጅመል) ወደ ዝርዝርና ቴክኒካዊ ትንታኔ ያስገባ ነው።

በድንቁርናው ዘመን እንደ አራጣ አይቆጠርም ነበር። በሚከተለው ሀዲስ ተብራርቷል። ሀዲሱ በተለያዩ አሰተላላፊዎች የተነገረና የተረጋገጠ ነው። ለአራጣ ተንታኝ እንደ መነሻ ወይም ማመሳከሪያ (Bench mark) ሆኖ ያገለግላል። የአራጣ ትምህርት ለጠበቀበት ሰው ያፍታታለታል። በተጨማሪም በሸሪዓ ገንዘብን (Currency) እንድንለይ ያደርገናል።

ኡባዳ ኢብን ሷሚት (ረ.ዐ.) እንዳስተላለፈው ነቢያችን ﷺ ሲሉ እንደሰማሁት ወርቅ በወርቅ ይከፈላል፣ ብርም በብር ይከፈላል፣ ሰንዴም በስንዴ ይከፈላል፣ ገብስም በገብስ ይከፈላል፣ ተምርም በተምር ይከፈላል፣ ጨውም በጨው ይከፈላል፤ ተመሳሳይ ለተመሳሳይ፣ እኩል ለእኩል፤ ክፍያዎች ደግሞ እጅ በእጅ ናቸው። ዓይነታቸው (የዕቃዎቹ) የተለያየ ጊዜ እንዳመቻችሁ ሸጡዋቸው። ክፍያው እጅ በእጅ እስከሆነ ድረስ። (ሒማም ሙስሊም ሀዲስ ቁጥር 3854)

ለግብይት የሚውሉ፣ ስፍርና ሚዛን እንዲሁም ተቀማጭነት ያላቸው ስድስት ዓይነት ታዋቂ ንብረቶች እንደ ግብይት መሣሪያነት እና “ሲት አምዋለ-ሪበዊያህ” ሲተረጎም “ስድስቱ አራጣ አምጪ ገንዘቦች” ተብለዋል። በተለይ ሁለቱ ወርቅና ብር በቁርአን እና በነቢያችን (ﷺ) ሀዲሶች በርካታ ቦታዎች ላይ በተለያዩ ርዕሶች (ንግድ፣ አራጣ፣ ውርስ፣ ጋብቻ፣ ዘካ፣ ጀነት፣ ጂሀድ፣ ሀጅ) ላይ ተጠቅሰዋል። ሊቃውንቱ (ፉቀሐዎች) እነዚህን ዕቃዎች እንደ መሠረታዊ መገበያያ ወስደው ሌሎች ማለትም ከስድስቱ ውጭ ያሉ ማዕድናትና የምግብ እህሎች በንጽጽር ሄደውባቸዋል። በማዕድን ብንሄድ መዳብ፣ ብረት፣ አልማዝ፣ ወዘተ እንዲሁም በእህል ብንሄድ ማሽላ፣ ጤፍ ወዘተ አራጣ አለባቸው ወይስ የለባቸውም የሚለው ጋር የሐሳብ ልዩነት

ቢኖርም ማንም ተራ ሰው ሊረዳቸው በሚችል መንገድ ስታንዳርድ አስቀምጠውላቸዋል።

የኢስላም የሕግ ትምህርት ዋና ሊቃውንት የሚሰጡት አራት ናቸው። በአራቱ ስር ብዙ ሊቃውንት ተነስተዋል። በግልጽ ንግድና አራጣ የሚመለከታቸው ስድስቱ ውጭ ላሉት ነገሮች የሊቃውንቱ ምደባ እንደሚከተለው ቀርቧል።[44] [45]

1. በኢማም አቡሀኒፋ ትምህርት ቤት አመለካከት ሁለት ምድብ ከፍለዋቸዋል። እነርሱም (ሀ) ክብደት እና (ለ) መጠን/ስፍር ጋር ከተመሳሰሉ የአራጣ ምድብ ውስጥ ይገባሉ። ለምሳሌ (ሀ) መዳብ ወይም ብረት እንደ ወርቅ በግራም ቢመዘኑ ቀጥታ አራጣ የሚመለከታቸው ንብረት ሆኑ ማለት ነው። ዘካ ጋር ስንመጣ መዳብ፣ ብረት አሉሚኒየም በግራም ተለክተው ዘካ አይወጣባቸውም። ከዘካ ውጭ ናቸው። ዘካ የሚመለከታቸው የንግድ ሽቀጥ ሲሆኑ ነው። ወርቅ 20 ሚስቃል (በሌላ አነጋገር 20 ዲናር) ሲሆን በዘመናዊ አለካክ 85 ግራም ሲያልፍ ዓመታዊ ዘካ ውስጥ ይገባል። ሌሎች ማዕድናት ግን እንዲህ ያለ የዘካም ይሁን የአራጣ ልኬት የላቸውም። (ለ) ወደ እህል ስናልፍ ስንዴና ገብስ ተለይተው ተጠቅሰዋል። በእፍኝ፣ በቁና፣ በዳውላ፣ በዘመናችን በኩንታል፣ በኪሎ ግራም፣ በፓውንድ ይሰፈራሉ። ጤፍ ወይም ማሽላ ተመሳሳይ ልኬት ውስጥ ከወደቁ የአራጣ እና ዘካ ንብረት ሆኑ ማለት ነው። እንስሳት፣ አልባሳት፣ ሌሎች ዕቃዎች የማበላለጥ አራጣ

[44] SALEH, Supra note 3, at 21; IBN RUSHD, supra note 20, at 500.
[45] MUHAMMAD B. MUHAMMAD AL-KHATIB AL-SHIRBINI, MUGHNI AL-MUHTAJ ILA MA'RIFAT MA'ANI ALFAZ AL-MINHAJ 363 ('Ali Muhammad Mu'awwad & 'Adil Ahmad 'Abd al-Mawjud, eds., Dar al-Kutub al-'ilmiyya 1994.

አይመለከታቸውም። ሁለት አነስተኛ ግመል በአንድ ተለቅ ያለ ግመል ቢቀየር አራጣ አይደለም።

2. በኢማም ሻፍዒይ ትምህርት ቤት አካሄድ በተመሳሳይ ሁለት መመዘኛ አስቀምጠዋል። (ሀ) ለምግብነት የሚውል እህል ወይም (ለ) የሚያገበያይ ማዕድን ከሆነ አራጣ ይመለከተዋል።[46] ሆኖም ግን የሚያገበያይ ቢሆንም ከወርቅና ብር ውጭ ያሉ ማዕድናት አራጣ እንደማይመለከታቸው አስቀምጠዋል። ስለዚህ አራጣ ከስድስቱ ውጭ ያሉ እህሎች ላይ አተኩረዋል። ምክንያቱም ሰው ደህም ይሁን ሀብታም ዱንያዊ (ዓለማዊ) ግቡ ለምግብ ነው። ምግቦች በአራጣ ወደ ተወሰኑ ግለሰቦች ከተጠቃለሉ ረሀብ ይከሰታል። ሰዎች ሰዎችን ማምለክ ይጀምራሉ።

ሲጠቃለል ካላገበያየ እና ለምግብነት ካልዋለ አራጣ አይመለከተውም። ለማገበያየት ከስድስቱ ውስጥ መሆን አለበት። ቆጮ ሳይቀር የአራጣ ገንዘብ ሊሆን የሚችልበት አካባቢ ይኖራል ማለት ነው። ምክንያቱም ይህንን ብቻ የሚመገቡ የማኅበረሰብ ክፍሎች ኢትዮጵያ ውስጥ አሉ። ቆጮ ማለት ምን ማለት እንደሆነ ለማያውቅ ሰው የሙዝ ተክል ጋር ተቀራራቢነት ያለው እንሰት ከሚባል ተክል ተፍቆ ወጥቶ የሚመረት የምግብ ዓይነት ሲሆን በአሁን ወቅት ከጉራጌ እና ከደቡብ ኢትዮጵያ ማኅበረሰቦች አልፎ በተለያዩ የሀገሪቱ

[46] IBN RUSHD, Supra note 20, at 500. Gold and silver are unique in serving this pricing function according to the Malikis and the Shafi'is and for that reason, the prohibitions applying to trading in gold and silver do not extend to anything else. Id. at 499. Thus, the Shafi'is do not apply the rules of riba to the exchange of copper coins. AL-SHIRBINI, supra note 29, at 369

ክፍሎች እየተለመደ መጥቷል። ልኬቱና ጥራቱ ይታወቃል። በሻፍዒይ ቀመር ቆጮ ላበደረ ተመሳሳይ ቆጮ መመለስ እንጂ ጨምሮ መክፈል አራጣ ውስጥ ይወድቃል ማለት ነው። እንስቱ ግን በቃይ ስለሆነ ላይመለከተው ነው። ከወርቅ፣ ብርና ጨው ውጭ ያሉ ማዕድናትም ማለትም መዳብ፣ ዚንክ፣ ነሀስ ወዘተ ለግብይት መሣሪያነት ከተጠቀምናቸው የአራጣ ቀመር ውስጥ ይወድቃሉ የሚል አቋም ያንጸባረቁ ቢኖሩም አብዛኖቹ ሻፍዒዮች ከወርቅና ከብር ውጭ ያለ ማዕድን አራጣ አይመለከተውም ይላሉ። አራጣ የተከለከለው ከጎጂነትና በዝባዥነት ጋር በተያያዘ ነው። ምግብ ላይ አጥብቀውት ማዕድናት ላይ ያላሉት በተለይ ገበሬዎች አውድማ ላይ ለአራጣ ከፍለው በረሀብ ወደ ክህደት እንዳይዘነበሉ ለመከላከል ነው።

3. በኢማም ማሊክ ትምህርት ቤት አመለካከትም በተመሳሳይ ሁለት መለኪያ አስቀምጠዋል። (ሀ) ለምግብ የሚውል እና (ለ) ለረጅም ጊዜ የሚቀመጥ (ንብረት የሚያከማች) በሚል ሄደዋል። በአንድ አካባቢ ለመደበኛ ምግብነት የሚውል እህል እንደ ገንዘብ ያገለግላል። ማለትም አራጣ ይመለከተዋል። ኢማም ሻፍዒይ ጋር ተመሳሳይ ነው። ለረጅም ጊዜ የሚቆይ የሚለው ጋር ማዕድናትን ይመለከታል። ማዕድኑ ለንብረት ማቆያነት ወይም ሀብት ማከማቻ መሣሪያነት ከዋለ አራጣ ይመለከተዋል።

4. የኢማም አህመድ ኢብን ሀምበል ትምህርት ቤት አመለካከት፤ ተማሪዎቻቸው በሦስት አካሄድ ሄደዋል። አንደኞቹ የአቡሀኒፋን (እላይ ቁጥር አንድን)፣ ሌሎቹ የሻፍዒይን ሲከተሉ፣ ሦስተኞቹ ግን ሦስት ነገሮችን ካጣመረ ማለትም ለምግብነት የሚውል፣ የሚመዘን እና የሚሰፈር የሚል አስቀምጠዋል።

ከስድስቱ መገበያያዎች ውስጥ ሁለቱ ማዕድናት ለአጠቃላይ ግብይት ይውላሉ። ወርቅና ብር ቀሪ አራቱንም (ስንዴ፣ ገብስ፣ ተምርና ጨው)ን ጨምሮ ጠቅላይ መገበያያ ናቸው። ምሳሌ ስንዴን በስንዴ አበላልጦ መገበያየት ሪባ (አራጣ) ይፈጥራል። ማለትም ስንዴ የግብይት ዕቃ (Cash, currency) ስለሆነ ጥራቱ ከፍ ያለ ስንዴ ለምሳሌ መቶ ኪሎ ስንዴ ጥራቱ ዝቅ ባለ መቶ ሃያ ኪሎ ስንዴ መቀየር ወይም ዕዳ መክፈል ሪባ (አራጣ) ነው። ስንዴ የተባለ ሁሉ ጥራቱም ይሁን ቀለሙ ቢለያይም በክብደት ማበላለጥ አይቻልም። በሌላ አነጋገር መቶ ኪሎ የንፍሮ ስንዴ በመቶ ኪሎ የቆሎ ስንዴ ሳያበላልጡ፤ መቶ ኪሎ ለመቶ ኪሎ መሆን አለበት። ስለዚህ ይህንን ያልተመቸው ሰው ስንዴዎቹ ወደ ወርቅ ወይም ብር ገብስ ይቀይራል ማለትም ይሸጥና ከዚያ በወርቁ ወይም ብሩ የተፈለገውን ዓይነት ስንዴ መግዛት ይቻላል።

በምናውቀው ምሳሌ ልጨምርና፡- ሰርገኛ ጤፍ አምጥቶ ማኛ የፈለገ ሰው እኩል በእኩል ሚዛን ይቀያየራል። ይህንን ያልፈለገ ማኛውን በሌላ ካሽ ቀይሮ ሰርገኛ ይገዛል። ስድስቱ መገበያያ (Currency) ስለሆኑ ካሽን በካሽ አበላልጦ መለዋወጥ የሪባ በር ስለሚከፍት ነው። የዘመኑ የገንዘብ ምንዛሪዎች ችግር የዚህ ውጤት ነው። አንድ ግራም የአሜሪካ ዶላር አንድ ግራም በሚመዛን የኢትዮጵያ ብር እኩል መለዋወጥ ነበረብን። ምንዛሪው ከወረቀቶቹ ጀርባ ባሉ እሴቶች ነው ብለን ውስብስብ የኢኮኖሚ እሳቦት ሲገባ ተራው ሕዛብስ?

اللَّهُمَّ صَلِّ عَلَىٰ سَيِّدِنَا مُحَمَّدٍ وَعَلَىٰ آلِهِ وَصَحْبِهِ وَسَلِّمْ

ማጠቃለያ (ማጠቃለያው ሙሉ ለሙሉ የተወሰደው ከሸይኽ ሰዒድ ዩሱፍ መጽሐፍ ነው)፡-[47]

በጊዜ ማዘግየትም ይሁን በማበላለጥ የሚፈጠሩ አራጣዎች የሚመጣባቸው ሦስት መንገዶች አሉ።

1. ዓይነታቸው አንድ ሆኖ ለምሳሌ፡- ወርቅን በወርቅ ወይም ስንዴን በስንዴ አበላልጦ መለዋወጥ (የመጨመር አራጣ ወይም ሪበል ፈድል ተገኘ)
2. ዓይነታቸው የተለየየ ሆኖ ለምሳሌ፡- ብርና ወርቅ ወይም ስንዴና ተምር ይመስል አንደኛው እጅ በእጅ አንደኛው የዱቤ ሆኖ መገበያየት የወለድ አካል ነው። (አንዱ መዘግየቱ የጊዜ አራጣ ፈጠረ ማለት ነው)
3. አንድ ነገር በጎሣው (በዓይነቱ) እኩል በእኩል ቢሸጥም አንደኛው እጅ በእጅ አንደኛው የዱቤ ከሆነ ወለድ ነው። ለምሣሌ ወርቁን በወርቅ ወይም ስንዴውን በስንዴ እኩል በእኩል ቢለዋወጡና አንደኛው የዱቤ አንደኛው እጅ በእጅ ተከፋይ ከሆነ ክልክል ነው።

የሸሪዓውን የአራጣ ምንነት ካየን በኋላ ወደ ዘመኑ ፊያት መገበያያ ስንመለስ፤ ፊያት እራሱ ወለድ (አራጣ) ነው ስንል በወለድ ላይ ወለድ ተነባብሮ (አዱዐፈል ሙደዐፉ) የሚመጣባቸው **ሦስት መሠረታዊ** ደረጃዎች አሉት። የፊያትን ወለድነትና ዕድገቱንም ያመላክተናል። እጃችን ላይ ያለውን **"ገንዘብን ለመገንዘብ"** እንዲሁም ታሪካዊ ሒደቶቹን ይበልጥ ለማወቅ የሚከተሉት ደረጃዎችን በእርጋታ ማየት ያስፈልጋል። ምክንያቱም ፊያት አራጣ (ወለድ) ሆኖ ያደገባቸው ወሳኝ ሒደቶች ናቸውና።

[47] ሐጂ ሰዒድ ዩሱፍ መንሱር፣ እስልምናና ተግባራቱ፣ የእስልምና ኃይማኖት መሠረታዊ መርሆዎችና የፊቅሕ ጽንሰ-ሐሳቦች፣ መርዋ ሶ. አታሚዎች፣ 2003 ኢት.አ. ገጽ 138

ለ. የፈያት መገበያያ ወለድ (አራጣ) ሦስት ደረጃዎች

1. በወርቅ ወይም ብር ማዕድናት የተደገፈ የመተማመኛ የቃል ኪዳን ወረቀት (Promissoey Note) የተጀመረበት ጊዜ
2. የኪዳን ወረቀቱን ሲደግፍ የነበረውን የወርቅና ብር ማዕድናት በአንድ ወገን ብቻ ኪዳኑን የፈረሰበት ወይም የተካደበት ወቅት
3. ምንም ድጋፍ የሌለው ፈያት ወረቀት በሀገራት ሕግ ገንዘብ ተደርጎ የቀጠለበት ሁኔታ

ደረጃ አንድ

የመተማመኛ ቃል ኪዳን ወረቀት (Promisory Note) ጊዜ፡-

ብዙ ዓይነት “Promisory note” አሉ። ቦንድ ሲባል ሰምተን እናውቃለን። የቦንድ ወረቀት ሕጋዊ የቃል ኪዳን ወረቀት ነው። ቦንድ ደግሞ እንደገና በተራው በርካታ ዓይነቶች አሉት። ለምሳሌ የመንግሥትን “ትሬዠሪ ቦንድ” ማለትም “የግምጃ ቤት ሰነድ” ከወሰድን መንግሥት ለተለያዩ ጉዳዮች በብሔራዊ ባንክ በኩል ሕጋዊ ወረቀት ያትምና ለአጭርም ይሁን ለረጅም ጊዜ ብድር ለሕዝብ ይሸጣል። ያ ወረቀት (ቦንድ) በስምና ያለስም ሊታተም ይችላል። ቦንድ የገዛ ሰው በመሀል ገንዘብ በሚፈልግበት ወቅት የተለያየ የቦንድ መሸጫ ገበያ ወስዶ እንደ ገበያው ሁኔታ ቀንሶም ይሁን አትርፎ ይሸጠዋል። ልክ እንደዚሁ የተለያዩ ዓይነት “Promisory note” አሉ። በአሁን ወቅት በፋይናንስና ኢኮኖሚክስ ትምህርት የምናውቀው “Promisory note & Bond” የተመለከተ የተጠላለፈ ርዕስ እዚህ ጋር ለማስረዳት ሳይሆን የገንዘብ ዕድገታዊ ደረጃዎችን በማብራራት ሒደት ላይ ጣልቃ መጥቶ ነው።

ለዚህ አጭር መጽሐፍ መንደርደሪያና መግባቢያ ይሆነን ዘንድ ጸሐፊው መረጃዎቹን እንደሚከተለው አጠናቅሮአቸዋል።

- ዕቃን በዕቃ (bartering) የነበሩ ግብይቶች እየተስፋፉ ሲመጡ የዓይነት ገንዘቦች በወርቅና ብር ወይም በሌሎች ማዕድናትና ጌጣጌጦች ተተኩ።
- ይህም ከቦታ ቦታ ማዟዟር በተለይም ከደህንነት አኳያ ሲከብድ ጊዜ፤ የአውራጃዎች ወይም ክፍለ ግዛት ግምጃ ቤቶች ወርቆችን እየተቀበሉ በአምጪው ስም የተጻፈ የመተማመኛ ወረቀት (Promisory note) መስጠት ጀመሩ።
- መተማመኛ ወረቀቶቹ (የቃል ኪዳን ወረቀቶቹ) በስም ይጻፉ ነበር። ባለስሙ (ስሙ የተጻፈበት ሰው) መምጣት የማይችልባቸው አጋጣሚዎች (መታመም፣ መሞት) ሲከሰት Promisory note ያለስም መውጣት ደረጃ አደጉ። ማንም ቢያመጣው የተቀመጠውን ጌጣጌጥ መውሰድ በሚያስችል መልክ ተበጁ። "ባለ ገንዘብ ማለት ይዞ የተገኘ ነው" እንደሚባለው፤ ማለትም በኪሳችን ውስጥ ያለን ገንዘብ የራሳችን ነው እንደምንለው ማለት ነው። ስለዚህ "ኖት" ይዞ የመጣ (ግለሰብም ሀገርም ሊሆን ይችላል) ወርቅ ይዞ መሄድ ወደሚያስችል ደረጃ አደገ። ይህ ማለት ወረቀቶቹ ተመሳስለው የማይታተሙበት ሁኔታዎች ነበሩ ማለት ነው። እንደሚታወቀው አታሚዎቹና ተቆጣጣሪዎቹ ታላላቅ የሀገር መሪዎችና ድርጅቶች ናቸው።
- ከጊዜ ብዛት ማዕድናትን በማስቀመጥ ወረቀት እየያዙ መጠቀም ቀልጣፋ መስሎ ታየና ወረቀቶቹን ለሦስተኛ፣ አራተኛ፣... ወዘተረፈ ወገን ማሸጋገር ቀጠለ። "Promisory note" ማለት ለተቀመጠ ወርቅ "በራሪ ካሽ / በራሪ ወርቅ" ሆኖ ያገለግል ያዘ።

- በዚህ ጊዜ ወረቀቶቹን ለማሳለጥ፣ ለመቆጣጠርና ለማስተዳደር ያመች ዘንድ ባንኮች ተፈጠሩ።
- እኒሁ ባንኮች በስሮቻቸው ሌሎች ባንኮችን እየወለዱ ሀገራትም የየራሳቸውን ሉዓላዊ ባንክ እየከፈቱና ቅርንጫፎቻቸውን እያስፋፉ ሄዱ። ቀስ በቀስም ብዙ ዓይነት ባንኮች መጡ።
- ብሎም የቅኝ ገዥ ባንክ ሁሉ መፈጠር ጀመረ። *በ19ኛው ክፍለ ዘመን በተለይም በእንግሊዝ እና በ20ኛው ክፍለ ዘመን በአሜሪካ፤ ወርቅን እያስቀመጡ ወረቀት የመውሰድ አሠራር በተደራጁ ባንኮች ተዋቀረ። (Michener, Ron Money in American Colonies (2003)።*
- ኢትዮጵያም ውስጥ የመጀመሪያውን ባንክ የከፈቱት ግብጾች ነበሩ። በኋላ ላይ ቀስ በቀስ ሉአላዊና ኢትዮጵያዊ ባንክ ተመሠረተ።

በሌላ ጎን ወርቅ የሚሰበስቡ ነበሩ

- ወደኋላ መለስ ስንል ባንኮች ከመምጣታቸው በፊት የወርቅና የብር ማዕድናት "በገንዘብ ግምጃ ቤት" በአደራ እያስቀመጡ የኪዳን ወረቀት (Promissory Note) የሚሰጡት ደግሞ በወርቅ አንጥረኝነት የሚታወቁ ቡድኖች ነበሩ (ስማቸውን መጥቀስ አስፈላጊ አይደለም)። ባንክ የሚለው ቃል የመጣው እነርሱ ከሚቀመጡባት ወንበርና ጠረጴዛ (ባንኮኒ) ነው። በፈረንሳይኛ "banque"፣ በጣሊያንኛ "banca"፣ በጀርመንኛ "banc, bank, bench" ተብሎ ይጠራ ነበር።[48] ዛሬ የኛን ፕላኔት እንደ ባንኮኒ አድርገው የተቀመጡባት የያኔዎቹ አራጣ አበዳሪዎች ናቸው።

[48]De Albuquerque, Martim (1855), Notes and Queries, London: George Bell, Page 431.

- ወርቅ ያለው ሰው ወርቁን ለባለ ባንኮኒው ወይም ለባለመጋዘኑ (ለገንዘብ ግምጃ ቤት) ሲያስረክብ ባለመጋዘኑ ለማዕድናቱ ባለዕዳ መሆኑ እርግጥ ነው። ወርቁን አስረክቦ የቃል ኪዳን ወረቀት Promisory Note ሲረከብ ወረቀቱ "የዕዳ ወረቀት" (Debt Note ማለትም Promisory Note) ይባላል። ሁለቱም ትርጉማቸው ተቀራራቢ ነው። በተለምዶ "ባለ መቶ ብር ኖት፣ ባለ አምስት ብር ኖት፣ ባለ መቶ ዶላር ኖት/ቢል፣ ወዘተ" ሲባል እንሰማለን። መነሻው ይኸው Promisory Note ነው።

በትርጉም (definition) ደረጃ (Promisory Note ወይም Promisory Payable ወይም Promisory Debt) የሚባለው የዕዳ ወረቀት ሲሆን አንዱ ወገን ማለትም ቃል ገቢው ለንብረት አስቀማጩ ፈርሞ የሚሰጠው ሆኖ ጊዜው ሲደርስና ወረቀቱን (ኖቱ)ን ይዞ ሲመጣ የተቀመጠውን ንብረት (ገንዘብ) የሚከፈልበት በሕግ ፊትም አስገዳጅ ወረቀት ነበር። በወረቀቱ ፊት ገጽ ላይ "ላምጪው እንዲከፈል ሕግ ያስገድዳል" የሚል ጽሑፍ አለው። ይህ የእኛ ሀገር የፊያት ኖት ላይ የምናገኘው ነው። ወረቀቱ ሲመጣ ንብረት የሚመለስበት (የሚከፈልበት) ወረቀት በመሆኑ ዓይነቱም "Redeemable paper" ይሰኛል። "Redeemable paper" ማለት "ወረቀቱን ይዞ ለመጣ ከብሔራዊ ባንክ ወይም ከወርቅ ግምጃ ቤት ወርቅ መውሰድ ይችላል" ማለት ነው። "ላምጪው እንዲከፈል ሕግ ያስገድዳል" የሚለው ጽሑፍ አሁን በምንጠቀምባቸው የገንዘብ ኖቶች ላይ ቢኖርም ትርጉሙ ግን ከያኔው በተቃራኒው ነው። በፊት ኖቱን የያዘ ሰው ኖቱን ያተመው ወይም ያሳተመው አካል (ብሔራዊ ግምጃ ቤት) ዘንድ ሄዶ ንብረት ማለትም ወርቅ መውሰድ ይችል ነበር። አሁን ግን "በሕግ አስገዳጅነት" ንብረቶች ከባንክ ሳይሆን ከሰዎች የሚወሰድባቸው ሆኑ። ለባንክ ወይም ላምጪው "Irredeemable paper" ሆኑ። ማለትም ***ብሔራዊ ባንኩ ወረቀት***

ያትማል እንጂ ወርቅ የመክፈል ግዴታ የለበትም እንደማለት ነው። ይህ ማለት ፊያት በአጭሩ ሲገለጽ ነው።

ገንዘብ ማለት ጉልበት ሆነ። በተቃራኒው ንብረት የመሰብሰቢያነት ቀስቱ ወደ ሕዝቡ ዞረ። ከሕዝቡ በግዳጅ ንብረት መሰብሰቢያ፣ የመንግሥትን ዕዳ መክፈያ እና በሕግ ዘንድ አስገዳጅ ወረቀት "irredeemable paper" ተደረገ። የሀገሪቷን ወረቀት ይዞ ለመጣ ንብረት አልሰጥም (አልሸጥም) ማለት ወንጀል ሆነ ማለት ነው። ገንዘብ ወይም ልውውጥ አስገዳጅነት ካለው እንደ ሸሪዓዊ ግብይት እንደማይታይ አሳልፈነዋል። ምክንያቱም በደል ይኖረዋልና። ተበዳይ ከዚህ በደል ለመውጣት ሌላ ሕግ (ሸሪዓ) አይጫንበትም።

ኖት አታሚዎቹ **ሦስት** ዓይነት ጥቅም ነበራቸው። **አንደኛው** ከወርቅ አስቀማጩ ላይ የተቀመጠበትን ክፍያ ያስከፍላሉ። **ሁለተኛ** ወርቁን ለሌላ ወገን በአራጣ ያበድሩት ነበር። **ሦስተኛ** ኖታቸው ገበያ ላይ በአስተማማኝ መግባቱን ካረጋገጡ በኋላ ምንም ወርቅ ሳይቀመጥ በጎን እያተሙ ንብረት መሰብሰቢያነት አዋሉት።

"ፕሮሚሰሪ ኖት" ወለድ (አራጣ) ነው ያስባለው አንኳሩ ነገር ተገቢያዮች ንብረት ሳያዩ በወረቀት መገበያየታቸው ነው። እቃው በልውውጥ ወቅት ካልታየ እና እጅ በእጅ ካልሆነ ወለድ ይፈጠራል። ከኢስላማዊ የግብይት ማዕዘናት በግንባር ቀደምትነት የሚመጣው ዕቃው በልውውጥ ወቅት ከነሙሉ መረጃው መገኘት አለበት። እቃው ብቻ ሳይሆን ተመጣጣኝ ክፍያውም መገኘት ይጠበቅበታል። ካልሆነ ከግብይት ስነሥርዓት ይወጣና ወደ መበዳደር ምዕራፍ ይገባል ማለት ነው። ይህ ደግሞ ሕጉ ሌላ ነው። ወርቁ ፊት ለፊት በማይታይበት ሁኔታ ሌላ ሰው ጋር ተቀምጦአል ብሎ የውል ወረቀት ማዟዟር ወለድን ይፈጥራል። ክፍያ ዘገየ ማለት

ወለድ ተፈጠረ ማለት ነው። የአራጣ ትልቁ መንስዔ መዘግየት ነው። ዛሬ ፊያት የተቀበለ ሰው ሳያሳድረው፣ ቢያድር እንኳ ሳያቆየውና ሳያዘወትረው በአስቸኳይ ወደ ንብረት መቀየር አለበት። በቀጣይ የተቀበለውም ሰው ወዲያው መቀየር የግድ ይለዋል። አራጣ ስለሆነ ባደረ ቁጥር ከውስጥ እየተበላ ይሄዳል። መጨረሻ የተቀበለ ሰው ተጎጂ ይሆናል። የኃይማኖታዊም ይሁን የዓለማዊ ትምህርት የሌለው ሰው ምሳሌ መቶ ሺህ ብር ባንክ አስቀምጦ አንድ ወር ቢያቆየው ገንዘቡ እየተበላ ሲሄድ ያያል። ፊያት (ፕሮሚሰሪ ኖት) አራጣ ለመሆኑ አስረጂ ሰው አያስፈልግም። ኑሮአችን ያስረዳናል። ብዙዎች የሚሸወዱት አራጣ ማለት መጨመር ብቻ ይመስለዋል። እስልምና ላይ ቁጥር አንድ አራጣ ማዘግየት ነው። ጭማሪ የማዘግየት ውጤት ነውና። ይህኛው በሌሎች ምዕራፎች ስላነሳነው መድገሙ አስፈላጊ አይደለም።

ዕቃ ገበያ ሳይገባ መንገድ ላይ ማስቀረት መከልከሉ፦

የውል ወረቀት እራሱን በባዶ መሻሻጥ ይቅርና ገበያተኞች ዕቃዎቻቸውን ገበያ ይዘው በሚመጡበት ወቅት መንገድ ላይ ማፈን ወይም መደለል ወይም መግዛት ወይም መሸጥ ነቢያችን ﷺ በበርካታ ሀዲሶች ከልክለዋል። አንድ ሁለት እንጥቀስ

ዓብዱላህ ኢብን ዑመር (ረ.ዐ.) እንዳስተላለፉት የአላህ መልዕክተኛ ﷺ እንዳሉት ነጋዴዎች ንግዳቸውን ገበያ እስኪያደርሱ መንገድ ላይ አትናገጂቸው። (ሙስሊም ሀዲሰ ቁጥር 3623)

ዓብደላህ ኢብን አባስ (ረ.ዐ.) ባስተላለፉት ሀዲስ ነቢያችን ﷺ ሲሉ ሰማሁ፡ የከተማ ነዋሪ ገጠሬውን ወክሎ ሊይነግድ፤ ሰዎቹን ተዉዋቸው (ገበያ ይግቡ)፣ አላህ ሲሳያቸውን አንዱ ከአንዱ ይሰጣቸዋል። (ቡኻሪ 2158 እና ሙስሊም 3629)

ለዚህ ተቀራራቢ ምሳሌ የሚሆነው “የኢትዮጲያ ምርት ገበያ” ወይም “Ethiopian Commodity Exchange – ECX” መጥቀስ ይቻላል። ገዥና ሻጭ በቀጥታ ያለ ድለላ ማገናኘት ማለት ነው። ዕቃው (ለምሳሌ ቡናው) እገበያ ቦታ ሳይደርስ ከገበሬው (ለምሳሌ ጊቤ ወንዝ ላይ) ማፈን ክልክል ነው ማለት ነው። ሆኖም ግን ጊቤ ወንዝ ገበያ ካለ መሸጥ ሙብት ነው። ከሌለ ግን ገበሬው አያውቅም ብሎ ማታለል አልተፈቀደም። ፕሮሚሰሪ ኖት ደግሞ ከዚህም ይከፋል። ጀማ የተለቀመ ቡና ጊቤ ወንዝ ወይም እዛው ማሳው ላይ ተዋውሎ፤ አዲስ አበባ ያለው ገዢ ቡናውን ሳያይ ውሉን አዲስ አበባ አምጥቶ ከሰው ሰው ማንካለብ ማለት ነው። የወረቀት መገበያያ የተፈጠረበት መነሻ የሆነው Promisory Note ጋር ቀጥታ የሚገናኝ ክስተት በነቢያችን ሶለሏሁ ዓለይሂ ወሰለም ባልደረቦች (ሶሀቦች) ዘመን በመርዋን ኢብኑል ሀከም (684-685 እ.ኤ.አ. ባስተዳደረበት) ጊዜ ተከስቶ ነበር። መርዋን እና ሶሀቦች እንዴት እንደተከላከሉት የሚከተለውን ሀዲስ እንመልከት።

ኢማም ሙስሊም በሶሂህ (በተረጋገጠ) ዘገባቸው ኢስሀቅ ኢብን ኢብራሂም እንዳስተላለፈልን፣ ዓብዱላህ ኢብን ሀሪስ አልመኽዙቢይ እንደነገረን፣ ደሀክ ከኡስማን፣ ከአቡበክር ኢብን ዓብዱላህ ኢብን አሸጅ (ይዞ) እንዳስተላለፈልን፣ ከሱሊይማን ኢብን የሳር፣ ከአቡሁረይራ (ረዲየሏሁ ዓንሁ) እንዳስተላለፈልን፡- አቡሁረይራ (ረዲየሏሁ ዓንሁ) እራሱ ለመርዋን ብሎ አለው “መርዋን ሆይ በአራጣ ግብይት የተፈቀደ አደረግከን? መርዋንም በፍጹም አላደረግኩም አለ። ሰዎች የምግብ እህል ዕጅ ላይ ሳይደርስ በወረቀት ይገበያዩ ዘንድ ፈቀድከን? ሲለው፤ መርዋን

ሕዝቡን ሰብስቦ ሹጥባ (ዲስኩር) አሰማና ጠባቂዎችን አሰማርቶ (ወረቀቶቹን) ከሰዎች ዕጅ ሰበሰባቸውና ወደ ባለቤቶቻቸው መለሳቸው። (ሙስሊም ሀዲስ ቁጥር 3652)

በሌላ ዘገባ

"ያህያ ከማሊክ እንዳስተላለፈልኝ በመርዋን ኢብኑል ሀከም ጊዜ የውል ወረቀት (ሱኩክ) ለሰዎች "በአል-ጀር ገቢያ" ሲሸጥ ሰሙ። ዕቃው ሳይደርስ ሰዎች ወረቀቱን ይሻሻጡት ነበር። ዘይድ ኢብን ሳቢት (ረ.ዐ.) እና ሌላ የነቢዩ ﷺ ባልደረባ የነበረ ሰው ወደ መርዋን አልሀከም ዘንድ ሄደው "መርዋን ሆይ አራጣን ሀላል አደረግክን"? ሲሉት መርዋንም "በአላህ እጠበቃለሁ። ምንድን ነው እሱ?'' ሲላቸው፤ "ሰዎች የዕቃ የውል ወረቀቶችን እየተሻሻጡት ነው" አሉት። መርዋንም ጠባቂዎችን መድቦ ወረቀቶቹን ከሰዎች ዕጅ አስወስዶ ወደ መጀመሪያው ባለቤቶች አስመለሳቸው። (ኢማም ማሊክ፣ ሙዎጦእ፣ 31ኛ መጽሐፍ 19፡45)

ዕቃው እጅ ላይ ወይም ገቢያ ሳይደርስ "ወረቀት መሻሻጥ" አራጣ (ወለድ) በመሆኑ እነዘይድ ኢብን ሳቢት (ረ.ዐ.) በአካባቢያቸው ለነበረው አስተዳደር አመልክተው አስተዳደሩም እርምጃ ወሰደ።

እነዚህ ክስተቶች ከሸሪዓው የንግድ "አርካኖች (ማዕዘኖች)" በተለይም "የሰመን-ሙስመን" (የሚሸጠው ነገርና በልዋጩ የሚሰጠው ክፍያ በግብይት ወቅት መገኘት የሚለውን በመጣሳቸው ነው)። (ዝርዝሩ በሌላ ምዕራፍ ስር ይመጣል)። ይህንን ሁኔታ የአውሮፓና አሜሪካ አራጣ አበዳሪዎች ወርቆችና ብሮችን እያስቀመጡ ወረቀት በመስጠት የጀመሩት ነገር እዚህ ጋር ባነሳናቸው ሀዲሶች ውስጥ ከነበረው

ክስተት ጋር የባሰም ቢሆን ተመሳሳይነት አለው። የአውሮፓና አሜሪካ አራጣ አበዳሪዎቹ እሚይዛቸው ጠንካራ ኃይል ባለማግኘታቸው አሁን የደረስንበት አስከፊ ደረጃ ላይ ደርሰናል። በእርግጥ የተቃወማቸው የለም ማለት አይቻልም። ብዙ የተቃውሞ ሒደቶች አልፈዋል። ብዙ ዓለም አቀፍ ጦርነቶችም ተካሂደዋል። የመካከለኛው ምሥራቅ ጦርነቶች መነሻዎቻቸው ነዳጅን በባዶ ወረቀት "መዝረፍ አለመዝረፍ" ጋር የተያያዙ ናቸው። ወርቅ ተቀምጦ ወረቀት ይታተም የነበረበት ደረጃ፤ በጊዜ ሒደት የሚከተለውን ሁለተኛና የባሰ አደገኛ ደረጃ ወለደ።

ደረጃ ሁለት

የፊያት ደጋፊ ወርቆቹ የተነሱ ጊዜ

በደረጃ አንድ ላይ የሚወጡ የኪዳን ወረቀቶች ሲውል ሲያድር ከአንደኛ ሰው ተነስተው ሲዘዟሩ፣ ዓይነታቸውም እየረቀቀና እየተለያየ ሲመጣ ለተራው ሕዝብ የማይገባ እየሆነ ሄደ። በጊዜ ሒደት ጉዳዩ ዓለም አቀፋዊ ሲሆን ይብስ ተወሳሰበ። ተዳዳሪው ሕዝብ ስለወረቀት መገበያያ ምንነት ያለው ዕውቀት ተመናመነ። ከላይ ያሉ ካፒታሊስቶች ደግሞ ወረቀት እያተሙ ዘረፋቸውን አጧጧፉት። (ቃሉ ከባድ ሊመስል ይችላል። መረጃዎች ላይ ያለው ግን ከዚህም በላይ ያስብላል። ስሜት የሚነኩ የዱለታና ሴራ ታሪኮችን ሳናነብ አንቀርም)። ሁኔታው ያላማራቸው ሰዎች "ወርቃችን" ብለው ሲጠይቁ ሰሚ አላገኙም። እየተነጠሉ የተገደሉና የተዋረዱ የሀገር መሪዎች በእኛው ዕድሜ አይተናል።

ወርቅን ከግብይት ቋንቋነት ማስወገድ ከተቃወሙት ከመጀመሪያዎቹ ውስጥ የፈረንሳዩ ቻርለስ ደጎል ተጠቃሽ ነው። ለምሳሌ፦ በፌብሩዋሪ 4 ቀን 1965 የፈረንሳዩ ጀነራል ቻርለስ ደጎል ከኒክሰን ንዝረት ስድስት ዓመት አስቀድሞ፤ ለዶላር ልዩ ግምት

የሚሰጠውን የ1944ቱ ብሬተን ዉድስ ስምምነትንና ተከትለው እየመጡ ያሉ ክህደቶችን በማጤን መረር ያለ መልዕክት እንደሚከተለው አስተላልፎ ነበር።

“አሁን እየተገበያየንበት ያለው ገንዘብ የማንም ሀገር ማንነትም ይሁን ቁጥጥር በፍጹም መኖር የለበትም። ከወርቅ ውጭ ሌላ ታማኝ መለኪያ በፍጹም አናገኝም። አዎ! ወርቅ! በተፈጥሮው የሚቀየር አይደለም። ወርቅ በጌጣጌጥ መልክም፣ በጥፍጥፍም፣ በሳንቲምም ቢሆን ዜግነት የለውም። ዘለዓለማዊና ዓለምአቀፋዊ የማይዋዥቅ ገንዘብ ነው” (ታይም መጽሔት ፌብሯሪ 1965)

ደጎል በ1968 ከፈረንሳይ ፕሬዝዳንትነት በፈቃዱ እንዲለቅ ካደረጉት ነገሮች አንዱ፤ ዓለም በአሜሪካ ፊያት ቅኝ ገዥነት የመውደቅ ጉዳይ ነበር። ልክ እንደ ደጎልም የተቃወሙ ብዙ መሪዎች ነበሩ። አሜሪካ ደግሞ ፈርጥማ እየወጣችበት የነበረችበት ደረጃ ስለነበር የወረቀት መገበያያ በተለይም የአሜሪካ ዶላር ወርቅን ተክቶ የዓለም ገንዘብ ሊሆን በቃ።

በፊያት ታሪክ ንዑስ ርዕስ ሥር ያነሳናቸው ነገሮች ዳግም እዚህ ጋር ለመጥራት ያህል እስከ 1960ዎቹ መጨረሻ ድረስ ወረቀቱን ይዞ ወደ ማዕከላዊ ባንኮች ወይም ግምጃ ቤቶች የሔደ ሰው ወርቅ የማግኘት መብት ነበረው። በእርግጥ በአሜሪካና በእንግሊዝ ከ1930ዎቹ ጀምሮ በሀገር ውስጥ ዜጎቻቸው ላይ “ወረቀትን በወርቅ” እንደማይለወጥ አውጀው ተግባራዊ አድርገውት ነበር።

ከላይ እንዳየነው ዕሁድ ኦገስት 15/1971 ላይ ***“ወረቀት ይዞ ለመጣ ወርቅ መክፈል አያስገድድም። መስኩቱንም ዘግተነዋል። የግምጃ ቤት ኃላፊውንም ከሥራ አግደነዋል”*** የሚል አዋጅ ከአሜሪካ ተሰማ። ከፊያቶች በተለይ ዶላር ማለት ቃል የፈረሰበት፣ ውል የተካደበት ወረቀት (Promisory Note) ነው። ይህንን ገንዘብ

ማለትም (ከ1971 በኋላ ያለውን ማለት ነው) የአደገኛ ሌባ ውል ነው። የሚጠቀም ሰው "የሌባ" ተባባሪ እንደማለት ነው። ምክንያቱም ወርቅ የተቀመጠበት "ታማኝ ባለአደራ" ታማኝነቱን ከዶበታል።

እላይ ደረጃ አንድ ላይ ያነሳነውን ሀዲስ መለስ ብለን ብናየው ዕቃው መንገድ ላይ ወደ ገበያ እየገባ እያለ መንገድ ላይ የተካሄደ "የሸያጭ ግዥ ውል" እንኳ "አራጣ" ነው ተብሎ መከልከሉን አይተናል። በሁለተኛው ደረጃ ላይ ደግሞ "ከድጡ ወደ ማጡ" እንዲሉ በአንድ ወገን የተጣሰ የኪዳን ወረቀት (የክህደት ወረቀት) ነው። በጥቂት ግለሰቦች የተያዘው እና ዶላር አሳታሚው የአሜሪካ የፌደራል ሪዘርቭ "ዶላር ላመጣ በአንድ የትሮይ ወቄት (ounce) 35 ዶላር ይከፍል" ነበር[49]። ይህ ጉዳይ በብሬተን ውድስ ስምምነትም ይገኛል።

በቀደሙት ገጾች ያወሳነውን ዳግም ለማስታወስ ያህል፡- አንድ የትሮይ ወቄት (ounce ወይም oz ወይም t.oz) ማለት በትሮይ ፓውንድ አለካክ 31.104 ግራም ነው። ወቄቱን ወደ ፓውንድ ስንቀይረው አንድ የትሮይ ፓውንድ ማለት 12 የትሮይ ወቄት ማለት ነው።

እንግዲህ በአጭሩ 35 ዶላር ያመጣ ሰው 31.104 ግራም ወርቅ ከፌደራል ግምጃ ቤት መውሰድ ሲችል፤ በተቃራኒው 31.104 ግራም ወርቅ ያስቀመጠ 35 ዶላር ወረቀት ይወስድና ይገበያይ ነበር ማለት ነው። አንድ ኪሎግራም ወርቅ ያስቀመጠ 1,125.25 ዶላር ይሰጠዋል። (ለማቅለል ሌሎች ነገሮችን ማለትም የጥበቃ ክፍያ፣ ወለድ፣ ትርፍ፣ ወዘተ ሳይገቡ ማለት ነው)። ከሰው እጅ ዶላር ስንወስድ ወርቅ

[49]Lowenstein, Rojer (August 4, 2011). "The Nixon Shock", Bloomberg BusinessWeek Megazine.

አስቀምጧል ብለን እናምናለን። ሌላውም ሰው ያምነናል። ይህንን ነው 1971 ላይ የተጣሰውና ክሕደት የተፈጸመው።

ወደ ኢስላማዊ ሕግጋት እንመለስና ወለድን ከሥሩ የሚያስተምሩ እጅግ ሰፋፊ ኢስላማዊ ሥራዎች አሉ። እስቲ ከቁርአን ስለብሪተን ውድስና ኒክሰን ሾክ የወረደ የሚመስለው አንቀጽ እንድገመው።

«ከመጽሐፉ ሰዎችም በብዙ ገንዘብ ብታምነው ወዳንተ የሚመልስ ሰው አለለ። ከእነሱም በአንድ ዲናር እንኳ ብታምነው፤ ሁል ጊዜ በርሱ የምትጠባበቅ ካልሾንክ በስተቀር የማይመልስ ሰው አለለ። «ይህ በመሃይማን (በምናደርገው) በእኛ ላይ ምንም መንገድ የለብንም» ስለሚሉ ነው። እነርሱ እያወቁም በአላህ ላይ ውሸትን ይናገራሉ። (ቁርአን 3:75)

በተጨማሪም የሚከተለውን ሀዲስ እና ማስጠንቀቂያውን እንመልከት።

ከኢማም ማሊክ ሙዎጦእ፡-

*“ያህያ ከማሊክ፣ ከዓብዱላህ ኢብን ዑመር እንዳስተላለፈልኝ ዑመር ኢብኑል ኸጣብ (ረ.ዐ.) እንዳለው (የነቢዩ ሀዲስ ነው)፡- ወርቅን በወርቅ አትሸጥ (በክብደት) መሳ ለመሳ ቢሆኑ አንጂ። አንዱን ክፍል በሌላው ክፍል ላይ አትጨምር (አታበላልጥ)። ብርን በብር አትሸጥ (በክብደት) መሳ ለመሳ ቢሆኑ አንጂ። አንዱን ክፍል በሌላው ክፍል ላይ አትጨምር (አታበላልጥ)። እላዩ ላይ ያለውን እላዩ ላይ በሌለውም አትሸጥ። አንድ ሰው እቤት ገብቼ ገንዘብ (ወርቅና ብር) ይዤ ልምጣ ካለህ አትልቀቀው (አትመነው)። **“ረማ” እፈራላችኋለሁ። “ረማ” ደግሞ አራጣ ነው።** (ኢማም ማሊክ፣ ሙዎጦእ፣ 31ኛ መጽሐፍ 16:34)*

በብርና ወርቅ ግብይት ወቅት እንኳ ሰውየው ከቤቱ ሄዶ እስኪያመጣ ድረስ ያለው ጊዜ አራጣ ተብሎአል[50]። ከ1971 በፊት ሆነን ብናስበው እዚህ ደረጃ ላይ አመኑም ካዱም በታተመው ወረቀት ልክ ወርቅ ይቀመጣል ተብሎ ይታሰባል። ይህኛው ደረጃ ሁለት ደግሞ "የክህደት ደረጃ ነው"። ቀጥለን በምናየው ሦስተኛ ደረጃ ላይ ግን ወርቅ እንደሌለ በቁርጥ አውቀናል። ስለዚህ የለየለት ፊያት ሆነ ማለት ነው። እኛ ተጠቃሚዎቹ ደግሞ "በሚታወቅ የዓለም አቀፍ ሌባ ወረቀት" እየተጠቀምን ነው ማለት ይቻላል። እኛ ሳንወድ በግድ ለመኖር ስንል ተባባሪዎች ነን ያስብላል። ሌብነት ደግሞ እጅ ያስቆርጣል።

ኢስላማዊ ሸሪዓ ይህንን "የክህደት ወረቀት"ን እንደ መሠረት አድርጎ እላዩ ላይ ቆሞ ሌላ ሸሪዓዊ ሕግ ማውጣት ለሸሪዓችን ስድብ ነው የሚሆነው። ለዚህም ነው **"በባንክ ኖት ላይ ወለድ አለ ወይስ የለም?"** ከማለታችን በፊት ወረቀቱ እራሱ ምንድን ነው ብለን ማጥናት አለብን የተባለው። በተለይ ገጠር ላይ ኢስላማዊ ትምህርት የተማሩ ሰዎች የኢስላማዊውን ሕግ ፊያት ላይ አምጥተው ሲተገብሩት ግራ ሲጋቡ ይስተዋላሉ። ወረቀቱ ምን እንደሆነና ከየት እንደተነሳ የሚጠቁማቸው እና በዓረቢኛ የተጻፉ ኢስላማዊ መጻሕፍት ገጠር ላይ ባለማግኘታቸው ብይን ለመስጠት ሲቸገሩ ብዙ ጊዜ አስተውለናል። እምነት የተካደበት ወረቀት መሆኑን ዕውነታውን ቢረዱት ኖሮ የሚጠቅም ፈትዋ (ብይን ለመስጠት) አይቸገሩም ነበር። ከእንግዲህም ቢሆን በአንድ ጀንበር እንደማይቀየር ይህም ጸሐፊ በደንብ ያምናል። ሒደት ሆኖ ነው የመጣው። ሊቀየርም የሚችለው በሒደት ነው። ከዚህ ትውልድ የሚጠበቀው ደግሞ ወደ ተፈጥሮአዊ ገንዘብ እንመለስ ዘንድ በእርጋታ መንገዱን መጥረግ ነው።

[50]እንደምታውቁት ሰዎች ዕቃ አሳይተው ዘወር ብለው የሞተ ዶሮ ሁሉ የሰጡበት አጋጣሚ አይተናል። ይህ ጸሐፊ በዓይኑ አይቶአል።

ደረጃ ሦስት

ሙሉ ለሙሉ ፊያት ሆኖ ወርቁ ከተረሳ በኋላ

እዚህኛው ደረጃ ላይ ያለው የለየለት ፊያት ነው። ፊያቱን ተቀብለን እየተጠቀምን ነው። የዶላሩ ፊያት፤ በስሩ በየሀገራቱ ስም ብዙ ፊያቶችን (ባዶ ወረቀቶችን ሲያልፍም የኮምፒዩተር ቁጥሮችን) አደራጅቶ እየተገለገልንበት ነው። ማንም ከዚህ ሥርዓት ውጭ ማሰብም ትንፍሽ ማለትም አይችልም። ዛሬውኑ ተግባራዊ ላድርግ ቢል ከዚህኛው ፕላኔት መውጣት አለበት። ይህኛው ደረጃ ብቻውን **ሦስት** ዓይነት ወለዶች አሉት።

ወለድ ቁጥር አንድ፡- ከተቀማጭ ገንዘብ እና/ወይም "ከምንም" የሚነሳ አዲስ ቁጥር ብሔራዊ ባንክ ወይም ፌደራል ሪዘርቭ ወይም ናሽናል ሪዘርቭ ለመንግሥት ያበድራል። ብድሩ ሁለት ቦታ ይሰነጠቃል። አንደኛው ወደዜጎቹ በታክስና ግብር መልክ ይሰራጫል። መንግሥትም ከዜጎቹ ሰብስቦ ዕዳውን ለብሔራዊ ባንክ ይከፍላል። ሁለተኛው ደግሞ ከዓለም አቀፍ አበዳሪና ግብይት ጋር ስለሚያያዝ ብሔራዊ ዕዳ ይሆናል። አቅርቦትና ፍላጎት ወይም ተጨማሪ ምርትና አዲስ ሰው ውልደት/ሞት ወይም ገቢና ወጪ ሳይጣጣም ሲቀር ዓለም አቀፍ ግሽበት ይፈጥራል። የምዕራባዊያን አጋባሽነት ሲደመር የገንዘባቸው "ጠንካራ ገንዘብ" ተብሎ መመደብ ችግሩ የደሀዎችን "soft currencies" ላይ ያርፋል። ነዋሪው ማለትም የመጨረሻ ተጠቃሚ (End users) የሚባሉት በታክስና ግብር ሲደመር በዓለም አቀፍ የገንዘብ ዲቫሉዌሽን (ማቃለል፣ ማሳነስ፣ ማጋሸብ) መልክ ይከፍላሉ። ሀገራችን የሚገጥማት ግሽበት የሀገር ውስጥ ግሽበት የፈጠረው ብቻ ሳይሆን ዶላርም በራሱ የሚፈጥረው ግሽበት አለ። አሜሪካ በጀቷ ላይ አዲስ ባዶ ቁጥር ስትጨምር ከፊሉ ለዜጋዋ በታክስ

መልክ ትበትነዋለች። ከፊሉ ወደ ዓለማት ሕዝቦች ይበተናል። ልክ እንደ አሜሪካው ማዕከላዊ ሪዘርቭ የኛም ብሔራዊ ባንክ የሚፈጥረው አዲስ ቁጥር አለ።

የዓለም ሦስት አራተኛ ገደማ የድንበር ተሻጋሪ ንግዶች በዶላር ስለሚካሄዱ ግሽበቱ ለየሀገራቱ ይሰራጫል። የሀገር ውስጡም አዲስ ቁጥር ማለትም ብሔራዊ ባንክ ለመንግሥት ሲያበድር የሚፈጠረው ቁጥር ወደ ዜጎች በታክስ መልክ ይሰራጫል። ለዚህ ዓይነተኛ ምሳሌ የተጨማሪ እሴት ታክስ (Value Added Tax – VAT) ነው። ምክንያቱም ቀጥታ ከመጨረሻው ተጠቃሚ ንጹሕ ገንዘብ ላይ የሚወሰድ ነው። በአጭር ቋንቋ ቫት ማለት የግሽበት ዲፕሎማሲያዊ ስሙ ነው። ከእነ ፐርሰንቱም ጭምር በሀገራት ላይ የሚጭነው ደግሞ አይኤምኤፍ ሲሆን የአንድ ሀገር መንግሥት ዝም ብሎ ማንሳትም ይሁን መቀነስ አይችልም። የኢትዮጵያ መንግሥት ምንም ማድረግ፤ ዜጋውም አልከፍልም ማለት አይችሉም። ዕቃ ወይም አገልግሎት ሲገዛ አውቶማቲክ ሆኖ ይቆረጣል። ስሙ ቫት ስለሆነ ወለድ አይመስለንም። የባንክ ወለድ ደግሞ ስሙ ወለድ ስለሚል ታክስ አይመስለንም። ከባንክ በቆጠብነው ገንዘብ የታክስ ወይም ግሽበት ማካካሻ ሲመለስልን «ወለድ ነው» ብለን እንተወዋለን። ወለዱን ታክስ ነው ብለን እንከፍለዋለን። (ይህንን ኮንሴፕት ለመረዳት ብዙ ማንበብ ይጠበቃል)።

እንግዲህ የተሰራጨው ወረቀት (ፊያት) ከምርታማነት ጋር ይመዘንና ወደ ዓለም አቀፍ ሲሄድ «ብሔራዊ ዕዳ» ይሆናል። እዚህ ስር ያለው በአጭር ቋንቋ የየሀገራቱ ብሔራዊ ባንኮች የሚፈጥሩት ብሔራዊ ዕዳ ወይም ብሔራዊ ግሽበት ነው።

ወለድ ቁጥር ሁለት

ይህኛው የወለድ ዓይነት ንግድ ባንኮች የሚፈጥሩት ነው። ፊያት ከብሔራዊ ባንክ ታትሞ ወይም ተበጅቶ ይወጣል። የብሔራዊ ባንክ ሥልጣን ማተም እንጂ መነገድ ባለመሆኑ የንግድ ሥራውን ለንግድ ባንኮች ይተወዋል። ንግድ ባንኮች ደግሞ የማተም ሥልጣን የላቸውም። ስለዚህ ገንዘብ የሚፈጥሩት ቆጣቢ ወይም አስቀማጭ ከብሔራዊ ባንክ ያመጣውን ፊያት መልሶ በማበደር ነው። ንግድ ባንኮቹ ሲያበድሩ ወለድ ጨምረው ያበድራሉ። የአሳላጭነት ዋጋ ሊባል ይችላል። ንግድ ባንኮች ዋና ሥራቸው ማሳለጥ (Intermediary) መሆን ነው።

ይህ ወለድ የምርት ወይም የንግድ ዋጋ (Costs) ጋር ተጨምሮ ለመጨረሻ ተጠቃሚ ይሰራጫል። ነጋዴውን አይነካም ማለት ይቻላል። አምራቾች ወይም ነጋዴዎች በዕቃ በኩል ያዞሩታል። እንዲሁም ከታክስ ጋር ያቀናንሱታል። ይህኛው ወለድ እንዳይነካው የፈለገ ሰው ከንግድ ባንኮች ይበደር። ከተበደረ የዕቃ ዋጋ ጋር ደምሮ ይሸጠዋል። የንግድ ባንኮች የብድር ወለድ ልክ እንደ ቢሮ ወይም መጋዘን ኪራይ ወይም የሠራተኛ ደመወዝ እንደ ወጪ ይያዛል። አመዘጋገቡ እንደየሥራ ጸባዩ ይለያያል። እየተዟዟረ እንዴት ወለድ እንደሚፈጥር እላይ የንግድ ባንክ ገንዘቦች በሚለው ሥር አሳልፈነዋል።

ወለድ ቁጥር ሦስት፡- ይህኛው ደግሞ አዳዲስ ገንዘቦች (ፊያቶች፣ ምንሞች) ምርት ሳይጨምር ገበያ ላይ በመረጨታቸው የተነሳ የሚደረግ የዕቃ (ምርት) ቅርምት መፈጠር ነው። ይህ ማለት ባዶ ግሽበት (ቅለት) ይሰኛል። በዜሮ ላይ ዜሮ እንደመጨመር ነው። በመንግሥት ዝም ብሎ መታተም፣ እንዲሁም በሕገወጥ መንገድ ወረቀት እያተሙ ማሰራጨት ነው። ሰዎች ከባዶ ተነስተው ገንዘብ ይፈጥሩና ዕቃ ይቀራመታሉ። መንግሥት ከምርትና አገልግሎት ጋር የተጣጣመ ፊያት ሲያትም

ያለፉት ሁለቱ ወለዶች ይፈጠራሉ። ዝም ብሎ ሲያትምና አልባሌ ቦታ ሲለቀቅ ገበያ ውስጥ ገብቶ ነዋሪውን ያሰቃያል። ግሽበት የሚኒስቴር መሥሪያ ቤት የሌለው ኢ-መደበኛ (Unlegislative) ታክስና ወለድ ነው።

ማጠቃለያ፡- የእሴት ገንዘብ ግሽበት አይነካውም። ከግሽበትም ከሕትመትም ነጻ ነው። የእስልምናው የገንዘብ ሕግጋት መሠረታቸው የእሴት ገንዘብ ነው። ፊያቶችን ያወግዛቸዋል። ምክንያቱም በሰዎች መካከል ሚዛንን ያዛባሉ። መነሻቸው ደግሞ ወለድ ነው። ወለድ ደግሞ ክልክል ነው። የእሴት ገንዘቦች ከግሽበት ይልቅ የምርት መዋዠቅ ነው የሚያጋጥማቸው። መጋሸብና መዋዠቅ ልዩነታቸው ከስር ይመጣል።

ለመውጫ ያህል አንድ ቀልድ መሳይ ዕውነታ ላክል።

የሆነ ዘመን ላይ አጎቴ አብራር ክፍለ ሀገር ሲሄድ መሸቶበት ወልቂጤ ከተማ ማደሪያ ፍለጋ አንድ ሆቴል ገባ። የማደሪያ ሒሳብ መቶ ብር እንደሆነ ነገሩትና 100 ብሩን ባንኮኒው ላይ አስቀምጦ ክፍል ሊያማርጥ ወደ ፎቅ ወጣ። በዚሁ ቅጽበት የሆቴሉ ባለቤት የሥጋ ዱቤ ነበረበትና አሟልቶ ለባለልኳንዳው ቤት ከፈለው። ሥጋ አቅራቢው የከብት መኖ ዱቤ ነበረበትና ከፍሎ ተገላገለ። የከብት መኖ ሻጩ በተራው የጭነት መኪና ዱቤውን አወራረደበት። ባለጭነት መኪናው አጎቴ አብራር የገባበት ሆቴል ደንበኛ ነበርና 100 ብሩን ከፍሎ ሳያንገራግር ቁልፍ ተረከቦ መኝታ ክፍሉ ሄደ። አጎቴ ደግሞ ክፍሎቹ ብዙም ስላልተመቹት ከፎቅ ወርዶ 100 ብሩን ይዞ ማረፊያ ፍለጋ ሌላ ሆቴል ሄደ። የእርሱ 100 ብር ግን የልኳንዳ፣ የከብት መኖ እና የማጓጓዣ ዱቤ አወራርዶ ተመልሶ ባንኮኒው ላይ መጣና ይዞ ወጣ። የዓለም የፋይናንስ ሲስተም እንደዚያ ነው። (ቀልዱ የእኔ ፈጠራ ሳይሆን የሕዝብ ቀልድ ነው።

1.2.3. ሲለካም ሲቀመጥም ዋጋ አለመኖር

የፊያት መገበያያ በኢስላማዊ ሕግም ይሁን በዘመናዊ ኢኮኖሚክስ እንደ ገንዘብ የሚያስቆጥር ነገር የለውም። ምክንያቱም ገንዘብ መገበያያ ነው ለማለት እራሱ ዋጋ ያለውና ሲቀመጥ ደግሞ የማይጨምርም የማይቀንስም መሆን አለበት። ፊያት (የወረቀት ወይም የቁጥር ገንዘብ) በዋለ ባደረ ቁጥር በቀድሞ ዋጋው አናገኘውም። ከተጀመረ ጀምሮ የመጨመር ባሕሪይ አይታይበትም። ሌሎች ገንዘቦችን ይቅርና ወርቅን ተክቶ እያገበያየ ያለው ዶላር እንኳ በወርቅ ብንመዝነው በ50 ዓመታት ታሪክ ከ35 ዶላር ወደ 1,200 ዶላር በወቄት ደርሶአል። ዶላር በ50 ዓመታት ውስጥ 3,400% (34 ጊዜ) በላይ ጋሽቦአል ማለት ነው። (ይህ አሀዝ እ.ኤ.አ. የ2018 ነው)።

የዛሬ ሀምሳ ዓመታት የነበረው አንድ ወቄት ወርቅ ያው አንድ ወቄት ወርቅ ነው። እላይ እንዳነሳሁት እዚህ ብደግመው «ወርቅ ስንት ዶላር ገባ እንላለን እንጂ ዶላር ስንት ወርቅ ገባ» አንልም። ወረቀቱ ግን ቀድሞውንም ቢሆን ዋጋ ነበረው ማለት አይደለም። ከምንም ተነስቶ ነው ዋጋ የተሰጠው። ውሎ ሲያድር መቀነሱ ደግሞ በዜሮ ላይ ዜሮ እንደመጨመር ነው። 35 ዶላር ከ34 ጊዜ በላይ አድጎ እና በዜሮ ላይ ዜሮዎች ተጨምረውለት እ.ኤ.አ 2018 መጀመሪያ ድረስ 1,200 ዶላር ሆኖአል። የዛሬ ሀምሳ ዓመት 35 ዶላር ሲገዛው የነበረው ነገር፤ ዕቃው እራሱ ሆኖ ዛሬ እንግዛው ብንል 1,200 ዶላር ያስፈልገናል ማለት ነው።

በዜሮ ላይ ዜሮ ማለት አምና ወይም የዛሬ አምስት ዓመት ከኋላው አንድ ዜሮ ያለበት ወረቀት ማለትም የእኛ አስር ብር ሲገዛው የነበረውን፤ ያንኑ ነገር ለመግዛት ዘንድሮ ሁለት ዜሮ ወይም መቶ ብር ያስፈልጋል ማለት ነው። በኢትዮጵያ 0.01 ሳንቲም ግብይት ላይ ይውል እንደነበር እናስታውሳለን። ነገር ግን ይህ ሳንቲም ላለፉት ሠላሳ ዓመታት አላገለገለም (ይህ ጸሐፊ ዛሬ አርባ ዓመቱ ላይ ሆኖ፤

ማስታወስ ከጀመረበት ዓመቱ ጀምሮ ለሠላሳ ምናምን ዓመታት እምብዛም ወይም ጭራሽ ግብይት ላይ አልዋለም)። በአጼ ኃ/ሥላሴ ዘመን በሁለት ብር የሚገዛ በግ ከ45 ዓመታት በኋላ ያንኑ በግ ለመግዛት ሁለት ቁጥር ላይ ሦስት ዜሮ በመጨመር ሁለት ሺህ ብር ያስፈልጋል ማለት ነው። ግሽበት (ቅለት ወይም ድከመት ልንለው እንችላለን) የፊያት መገበያያ መታወቂያ ሲሆን አንዱ ከአንዱ መነጠል አይቻልም። ይህ ጸሐፊ ባደረገው መጠነኛ የገበያ ዳሰሳ በ 1400 ዓመት ታሪክ ውስጥ የወርቅና የፍየል ዋጋ ተመሳሳይ ነው። በአንድ ዲናር (4.25 ግራም) ወርቅ እንደየ መጠኑ አንድ ወይም ሁለት ፍየል ይገዛ ነበር። በዚህ ዋጋ አሁንም አነስ ያለ ሁለት ወይም ሰባ ያለ አንድ ፍየል ይገዛል። በአንድ ወቄት ወርቅ (30 ግራም ወርቅ ገደማ) ነቢያችን ﷺ ከጃቢር (ረ.ዐ.) ፈረስ ገዝተው ሙሽራ ስለነበር አንድ ወቄት ጨምረውለታል። አሁን ላይ የፈረስ ወይም የግመል ዋጋ ብንጠይቅ ተመሳሳይ ነው። እንዲሁም አንድ ዳውላ ስንዴ በወርቅ/ብር ሲለወጥ የነበረውን፤ ያኔ እና አሁን ብናስተያይ ግሽበት አናስተውልም።

ፊያት ካለ ግሽበት አለ፤ ግሽበት ካለ ፊያት አለ። “ምንም ወደ ብዙ ምንም” ወይም “ዜሮ ወደ ብዙ ዜሮ” ይቀየራል። “ያ ምንም” እንግሊዝና አሜሪካኖች በ1971 ለአስቀማጮቻቸው ክህደት የፈጸሙበት (ቃል ያጠፉበት) ወረቀት ነው። መነሻው ዕዳ ነው። ዕዳውም ወደ ነጻው የዓለም ሕዝብ በስልት አዙረው ረጩት። መርጨታቸው ሳያንስ ውሎ ሲያድር የተነባበረ ወለድ አደረጉት። የዓለም መንግሥታትና ዜጎች “የቃላባዮቹን” ዕዳ ከነወለዱ መክፈል አቅቶአቸው በሁለቱ ሀገራት ሥር ቅኝ ተይዘዋል። ቃላባይነት፣ ምንምነት፣ ወለድና ሌብነት አንድ ላይ የተጋቡበት ገንዘብ ነው። የሰውን ንብረት ከአየርም በቀጠነ “ምንም” ነገር መውሰድ የበደሎች ሁሉ በደል፣ የአራጣዎች ሁሉ አራጣ ነው። ዓለም ከበረከት ወደ መርገምት

ምድርነት ተቀይራ በዋለ ባደረ ቁጥር የሰቀቀን ወሬዎች መስማት የዘወትር ትዕይንት ነው። ብዙ ገንዘብ አለ፤ ነገር ግን በረከት የለም። ምክንያቱም ዓለም በንብርብር አራጣ ውስጥ ተለውሶአል። ለዚያም ነው በረከቱ የጠፋው።

“አላህ አራጣን (በረከቱን) ያጠፋል ...” ቁርአን 2፡276

ይህንን አንቀጽ ለመረዳት የቁርአን ትንታኔ መጽሐፍ መፈለግ አይኖርብንም። ፊያት እጃችን ላይ ወይም ባንክ ሲያድር እንዴት በረካው እንደሚነሳ በራሳችን እያየነው፣ እየሰማነውና አጥንታችን ድረስ እየተሰማን ነው። አደረ ማለት ጎደለ ማለት ነው። አራጣ በረካውን ነስቶታል። እቃ ወይም አገልግሎት የሰጠ ሰው ፊያት ሲቀበል አራጣ ተቀብሏል። ሌላ ቦታ ሄዶ ሌላ ዕቃ/አገልግሎት የሚቀበልበትን ኩፖን እንጂ የሚረባ ዕቃ አልተቀበለም። እጁ ላይ ሰከንድ በቆየ ቁጥር እየተበላ ይሄዳል። ይህንን የአራጣ እሳት ለሌላ ሰው ያስጨብጠውና እርሱ ዕቃ ይወስዳል። ሄዶ ያረፈበት ሰው በድሕነት እየተበላ ይሄዳል። አቆይቼ ለትውልድ ላውርሰው ሊል ቀርቶ እላዩ ላይ እየነደደ ነው። መንግሥት በማንኛውም ሰዓት ሊለውጠው ይችላል።

ፊያት አራጣ፤ ከአራጣም የማዘግየት አራጣ (ሪበ-ነሲአ) ለመሆኑ ከዚህ በላይ አስረጅ የለም። አራጣነቱ ደግሞ የተነባበረ ነው። ስናስቀምጠው ይጎድላል። ከባንክ ስንበደረው ያስጨምሩናል። ያለጭማሪ ስናበድረው ደግሞ አንሶ ይመጣል። በወርቅ ወይም ስንዴ ብናበድር እና ባበደርነው ልክ ቢመለስልን ብዙ ጉዳት እንቀንስ ነበር። ባንኮቻችን እንኳንስ በወርቅ ተምነው ሊያስቀምጡልን ቀርቶ፤ የተለየ ሁኔታ ካልገጠማቸው በስተቀር፤ ከውጭ ሀገራት በዶላር ያመጣነውን ገንዘባችንን በብር ለውጠው ያስቀምጡታል። ሲከፍሉንም በሰጠናቸው ዶላር ሳይሆን በኢትዮጵያ ብር ለውጠው ነው። ዶላር በራሱ ፊያት በመሆኑ ከወርቅ ጋር ስናስተያየው እየጎደለም ቢሆንም ቅሉ፤ ባንኮች ግን በዚህ ሊያስቀምጡልን ፈቃደኞች አይደሉም።

እስቲ ስለፊያት አንድ መከራከሪያ እናቅርብ። አንዳንድ ሰዎች ኸሊፋው ዑመር ኢብኑል ኸጣብ (ረ.ዐ.) የግመል ቆዳን እንደ ግብይት መሣሪያ ተጠቅሟል የሚል መከራከሪያ ያቀርባሉ። ይህ መከራከሪያ **"ምንም"**ን ገንዘብ ለማድረግ የሚያስኬድ ነገር የለውም። የግመል ቆዳ ዋጋ አለው። ውስጡም ውጪውም ገንዘብ ነው። ቆዳው ብንቆራርጠው እንኳ ዋጋ ያወጣል። አንድ ግመል ለማሳደግ ብዙ ጊዜ ይወስዳል። በልፋት ነው የሚገኘው። የግመል ቆዳ እንደ ሌሎች እንስሳት ቆዳዎች ብዙ ጥቅም አለው። ንብረት ነው። እንደውም የቆዳ ዋጋ ብዙ ጊዜ አይዋዥቅም። ቆዳን እንደ ገንዘብ መጠቀም ከወረቀት መገበያያ ጋር በምንም ሊመሳሰሉ የሚችሉ አይደሉም። መጠቀሚያ ወረቀትና የወረቀት መገበያያም የተለያዩ ናቸው። ለፋብሪካ ግብዓት ወይም ለተለያዩ አገልግሎቶች የሚቀርብም ይሁን ያለቀለት የወረቀት ምርትና የወረቀት መገበያያ የተለያዩ ናቸው። የሚያሳዝነው ምን የሚያክል ጣቃ ወረቀት ስዕልና ቁጥር ባለበት ትንሽ የወረቀት መገበያያ ይገዛል። ሀምሳ ኪሎ ግራም (ሀምሳ ሺህ ግራም) መገልገያ ወረቀት በአምስት ግራም ቁራጭ ወረቀት (ዶላር) ይገዛል ማለት ይቻላል።

እንግዲህ ቆዳው የግመልም ይሁን የበሬ፤ እላዩ ላይ ዜሮዎችን በመጻፍ ፊያት ማድረግ ይቻል ይሆናል። "የአንድ የግመል ቆዳ ይዘን እላዩ ላይ ብዙ ዜሮ ጽፈን ለምሳሌ ስድሰት ዜሮ ጽፈን የስድስት ሚሊዮን ግመሎች ቆዳ ነው" ቢባል ማለት ነው። ምዕራባዊያን እንደዚያ ነው ያደረጉት። አውሮፓና አሜሪካዊያን አንድ ግራም ወረቀት መቶ ዶላር ብለው ጽፈውበት ነው ሀብት የሚዘርፉት።

1.2.4. የአራጣ ኢኮኖሚን ለማሳለጥ የተፈጠረ ስለመሆኑ

የፊያት መገበያያ ዋና ተዋናዮች እንግሊዝና አሜሪካ እንደሆኑ እጅግ በርካታ መረጃዎች አሉ። የአራጣ አስተናባሪዎቹ ሩቅ ሀገራት ያሉ ሀብቶችና ንብረቶች በፊያት አማካይነት በቦይ እንደተከላ ውኃ ቀጥ ብሎ ወደነርሱ ይደርሳል። በወለድ (አራጣ) ባይዘርፉት ኖሮ ሙስሊሙ እንዲሁም ሦስተኛው ዓለም ብለው መደብ የሰጡት ክፍል ከማንም ያልተናነሰ ሀብት ነበረው። አሁንም ቢሆን አለው። ድህነቱ የፊያት እንጂ የተፈጥሮ ሀብት አይደለም። ነጮቹ ጠላቶቻቸውን በአስተማማኝ መሣሪያ ይዘውታል ማለት ይቻላል። በወረቀት ቦይነት ዓለሙ እነርሱን እያገለገለ ነው። ያለ ምሥጋና እና ተመጣጣኝ ክፍያ እያገለገልን ያለነው የአራጣ ኢኮኖሚን ነው። ማገልገል ብቻ ሳይሆን ዓይን ያወጣ ዘረፋም ጭምር ነው። እኛ ብቻ ሳንሆን አጠቃላይ ዓለሙን በአራጣ ዕዳ አስረው የዕለት ተለት ሰቆቃ እየቆጠረ ነው። በሙስሊሙ ላይ ግን ችግሩ ከማንም በላይ ከፍቶአል። ፊያት ውሸት መሆኑን ባለመገንዘቡ ሀብቱ መዘረፉ ሳያንስ ሥራ እንዳይሠራ እንኳ ተሸብቦ ቁጭ ብሎአል። በማያውቀው ዕዳ ተዘፍቆአል። ገንዘቡ መጋሸቡን ወይም ባደረ ቁጥር መቀነሱን ቢገነዘብም ምንም እንዳልሰማ ሰው ወይም ምን እንደሚያደርግ ግራ ገብቶት ተቀምጦ የግሽበት ዕዳ ብቻ መላወሻ ነስቶታል።

እንግዲህ ብዙ ሕዝብ ለቤተሰቡ የሚሆን ዕለታዊ ጉርሱን ለማግኘት ይዋሻል። ኑሮ፣ ቤት፣ ትምሕርት፣ ወዘተ ማሟላት ከብዶታል። እስከ መቼ ብሎ መተንበይ ከባድ ሆኖአል። በታማኝነት የሚታወቀው ሙስሊም በማያውቀው በር ገብቶ ታማኝነቱን እየሸረሸረበት ነው። ከባንክ በወለድ አልበደርም ብሎ ከወንድሙ ይበደራል። ብሩ በፊያት በተቃጠለ ገበያ ሲከተው ይበታተንበታል። መክፈል ይከብደዋል። እርስ በእርስ እየተበዳደረ ይበላላል። ይወሻሻል። ታማኝ እና የማይዋሽ

የነበረው ሙስሊም ውሸትን ተለማምዶታል። አበዳሪም ተበዳሪም ተያይዘው እየወደቁ ነው። ይህ የዕለት ተዕለት ኑሮአችን ሆኖአል።

የዕዳ ጫና ዓለማዊም መንፈሳዊም ሕይወታችንን ያጨላልማብናል። ነቢያችን ﷺ *"አላሁመ ኢኒ አዑዙቢከ ሚነል ማእሰም ወል መግህረም, አላህ ሆይ ከወንጀልም በዕዳ ከመጭጫንም ባንተ እጠበቃለሁ"* የሚለውን ዱዓ አብዝተው ያደርጉበት ነበር። *"ለምንድን ነው ከዕዳ ጭነት ጠብቀኝ የሚሉት"* ተብለው ሲጠየቁ *"ዕዳ ያለበት ሲናገር ይዋሻል፣ ቃል ይገባና መልሶ ያፈርሳል"* ብለው መልሰዋል። (ሀዲስ ቡኻሪ 832፣ ሙስሊም 589)።

የሚገርም ነጥብ ለመጥቀስ "እገሌ በባንክ ተጨማልቆአል፣ እኔ ከባንክ ንጹሕ ነኝ" የሚሉ፤ ነገር ግን ከወንድሞቻቸው ተበዳድረው በነፍስ የሚፈላለጉ፣ የሚወሻሹ፣ የሚካካዱ፣ የሰቀቀን ኑሮ የሚኖሩ "ምእመናን"ን ይህ ጸሐፊ በብዛት ገጥሞታል። ውሸት እና ቃል ማፍረስ ደግሞ የመናፍቅ ምልክት ናቸው። በአሁኑ ወቅት ከመንግሥታት እስከ ተራው ዜጋ ድረስ ሁሉም ወይም አብዛኛው ዋሾ ሆኖአል ማለት ይቻላል። ሲስተሙ ተቀይሯል። ስለዚህ ሲስተሙን ከእነከፋቱ መጠቀማችንን አንርሳ። ምክንያቱም በተቃራኒው ከባንክ የተበደሩት በተሻለ የተረጋጋ ቢዝነስ እና ኑሮ ያላቸው፣ የተሻለ ሀብት እና ስብእና ያላቸው፣ በገንዘብ ከወንድሞቻቸው ጋር የማይናከሱ፣ ለብዙ ሰዎች የሥራ ዕድል የፈጠሩ፣ ወገናቸው ለሚፈልግባቸው ጉዳይ ገንዘብ የማያጡ ናቸው። ከባንክ ቢደወል እንኳ የተያዘው ንብረታቸው እንጂ እምነታቸው አይደለም። ቢከፋ ቢከፋ ንብረት ቢሸጥ እንጂ እምነት አይሸጥባቸውም። ከግለሰቦች የተበደረ ሰው እምነቱን አስይዞ ስለሆነ፤ ያጓደለ ወቅት እምነቱ ይጎድላል። **ሰዎች የሚያስይዙትን መምረጥ ይችላሉ። ንብረት ማስያዝ ወይስ እምነት እና ታማኝነትን ማስያዝ?**

ትምህርቶችም ይህንኑ አራጣ ለማሰለጥ የተቀረጹ ናቸው። በቢዝነስና ኢኮኖሚክስ ክፍል የሚሰጡ ትምህርቶች “ገንዘብ ምንድን ነው?” ሳይሆን እንዴት ይመጣል? እንዴት ይወጣል? ወለድ እንዴት ይሰላል? የሚሉና መሰል ነገሮች ናቸው። ልፋቱ ይህንን የአራጣ ሥርዓትን ለማገልገል ነው። የአራጣ ገንዘብ ቢቀየርና ወደ ዋናው ገንዘባችን ብንመለስ ኖሮ የአካውንቲንግና በተለይ ደግሞ የኢኮኖሚክስ ትምህርቶች አስፈላጊነታቸው እምብዛም ይሆን ነበር። ግብይቶች የሚታይ ዕቃ በሚታይ ዕቃ፣ የማይለካ ሲሆን ደግሞ በወርቅና ብር ስለሚቀየሩ ልውውጡ እዛው የግብይቱ ሜዳ ላይ ስለሚያልቅ የሚጓተት ዕዳ (ለአካውንታንት) እና የማይጨበጥ ስሌት (ለኢኮኖሚክስ) አይኖርም። ድለላና የይሆናል ግምቶች ስለሚቀንሱ ኢኮኖሚክስ ሊጠፋ ይችላል። (የሸኽ ኢብራሂም ቫዲሎ ሥራዎች በስፋት ያነሱታል። ለተጨማሪ ማብራሪያ ማንበብ ይቻላል። ከጀርባ ላይ ተገልጸአል)።

1.2.5. አስገዳጅ መሆኑ

በቁርአን በምዕራፍ 4፡29 ላይ “*እናንተ ያመናችሁ ሆይ! ገንዘቦቻችሁን በመካከላችሁ ያለ አግባብ አትብሉ። **ግን ከእናንተ በመዋደድ የሆነችውን ንግድ (ብሉ)**። ነፍሶቻችሁንም አትግደሉ። አላህ ለእናንተ አዛኝ ነውና*” ይላል።

ፊያት ሕዝቡን በማስገደድ ነው ገንዘብ የሚሆነው እንጂ ሁሉም ሰው ትተነዋል ቢል ሀብታምና ደሀ ይገለባበጡ ነበር። የግዴታ፣ የሌባ እና የበዳይ ወረቀት ላይ እንደ ንጹሕ ወርቅ በመውሰድ ወይም በመተካት፤ ምን ተብሎ ነው የኢስላም ሸሪዓ የሚቆመው? ብዙ ሰዎች «በቃ ተክቷል ብያለሁ ተክቷል» ብለው ይሟገታሉ። ይህንን ጉድ ባለመገንዘባቸው የተነሳ ነው።

ፊያትን ድንገት ትተነዋል ቢባል ግን ዘረፋው በጣም ይጧጧፍና የማናውቀው ዓለም ይፈጠራል። ሥርዓቱ በአንድ ሌሊት የሚቀየር አይደለም። ዘመናት የወሰደ ግዳጅ ነው። በአሁን ወቅት ሀገሮች በካፒታሊስት ተጽዕኖ ሥር ስላሉ የዓለም አቀፍ ጠንካራ ፊያቶች (hard currencies) በሥሮቻቸው ያሉ ሌሎች ደካማ ፊያቶችን (soft currencies) ያስገድዳሉ። “Hard Currency” እና “Soft Currency” ልዩነታቸውን ለማጥናት ብዙም መድከም አያስፈልግም። ጠንካራ ገንዘብ የሚባሉት “ጠንካራ” ያስባላቸው የመንግሥቶቻቸው የጦር መሣሪያ ጉልበት ነው። በመሣሪያ ኃይል “የደካማ ሀገር” ፊያቶች “በጠንካራ ሀገር” ፊያቶች ይለካሉ። መሣሪያው የተሰበሰበውም በዚሁ የማሞኘት ስልት ነው። በመሆኑም ዜጎች በተዋረድ ሳይወዱ በግድ soft currenciesን ይጠቀማሉ። በተዋረድ የየሀገራት መንግሥታት ለምዕራቡ ሥርዓትና መንግሥታት ተገዢ በመሆን ሕዝቦቻቸውን ያስገድዳሉ። ለዜጎቻቸው ብለው አልገዛም ቢሉ በሥልጣን ያችን አንዷን ሌሊት አያድሯትም። ወደ እምነቱ ሚዛን ስንመጣ እንኳን የማይጨበጥ ፊያት ይቅርና በወርቅና ብር ተገበያይ ብሎ ማስገደድ አይቻልም። ሰው በፈለገው መንገድ በመረጠው መገበያያ የመገበያየት ነጻነት አለው።

ሰው በገዛ ላቡ ያገኘውን ገንዘብ የግድ በባንክ ማስቀመጥና ማዘዋወር ካልሆነ በስተቀር፤ እቤቱ ማስቀመጥም ይሁን በእጁ ይዞ መዘዋወር ወንጀል ነው። ለሕጉ ተገዥ መሆን አለበት። በግለሰብ ደረጃ ቀርቶ በመንግሥታት ደረጃ እንኳ ይህንን ሥርዓት ማመጽ አይችሉም። ወደግለሰብ ሲወርድ ደግሞ ቁጥጥሩ ይከፋል። ተገዳጅ ነጻ ለመውጣት ብዙ ሀራሞች (ክልክሎች) ሊፈቀዱለት ይችላሉ። በእንዲህ ያለ አስገዳጅ ሁኔታ፤ የኢስላም ሊቃውንት በወርቅና በብር ቢሆን እንኳ አራጣን ከግዴታነት ያወጡታል። ምክንያቱም ጉዳዩ ከአራጣም በላይ በእምነትና በሕይወት የመጣ በመሆኑ ነው።

1.2.6. ዘካን እንደ ምሳሌ

ይህ ርዕስ ሲነሳ ወደ ዝርዝር የሸሪዓ ሕግጋት (ፈቅህ) ውስጥ መግባት ተፈልጎ ሳይሆን በሚከተሉት ምክንያቶች ነው። አንደኛው ስለወረቀት መገበያያ ሲነሳ "ዘካ በወረቀት መገበያያ የለም የሚሉ ሰዎች መጥተዋል" የሚል ጉርምርምታ ስላለ እሱን ለማጥራት ነው። ጉርምርምታ ብቻ ሳይሆን ከተለያዩ ሰዎች ጋር በርዕሱ ላይ ውይይት በተነሳ ቁጥር የመጽሐፉ አዘጋጅ ይህ ጥያቄ ቁጥር አንድ ሆኖ ሲነሳ ብዙ ጊዜ ገጥሞታል። ሁለተኛው ዘካ በቀጥታ ከገንዘብ ጋር የተያያዘ በመሆኑና ከኢስላም አምስቱ ማዕዘናት አንዱ በመሆኑ ከየትኛውም ገንዘብ ነክ ሕግጋት በቅድሚያ ስለሚመጣ በምሳሌነት መነሳቱ ሌሎችን ልናገናዝብበት ይረዳናል ከሚል ነው። ከዚህም ባለፈ ዘካና አራጣ የሚነሳባቸው መሠረቶች ብዙ ጊዜ ተመሳሳይ ናቸው። ቢሆንም ወደ ሕግጋቱ ዝርዝር ጉዳይ ውስጥ አልተገባም። ከመጽሐፉ ነጥቦች ጋር የሚገናኘውን የጥሬ ገንዘብ ጉዳይ ብቻ ነው የተዳሰሰው። ከመሆኑም ጋር ይህንን ንዑስ ርዕስ የጀመረ አንባቢ እንዲጨርሰው ይመከራል።

ሀ. ዘካ "በዓይን" (ተጨባጭ) እንጂ "በደይን" (ዕዳ) የለም

የኢስላም አራቱም ሊቃውንት ይሁኑ ሌሎች፤ ዘካ በ"ዓይን" ማለትም "ዋጋ ባለው በሚታይና የራስ በሆነ ተጨባጭ" ገንዘብ መሰላትና መከፈል እንጂ በ"ደይን" ማለትም "በዕዳና በማይጨበጥ" ነገር መሆን እንደሌለበት በመካከላቸው የሐሳብ ልዩነት የለም። የፈያት መገበያያ ደግሞ ከዕዳነትም ባሻገር ወለድ ሆኖ ጭራሽ ንብረት አስቀማጩ 1971 ላይ እምነት የካደበት ወረቀት ነው። ምናልባት ሌብነቱ በይፋ የሚታወቅ "የአደገኛ አታላይ" ወረቀት ነው። ታዲያ የከሀዲ ወረቀት እንዴት ተብሎ ነው የኢስላም መሠረት የሚቆምበት?

ለ. ፊያት 1971 ላይ የተቃጠለው የኪዳን ወረቀት ጭስ እንጂ ገንዘብ አይደለም

(ክስተቱን ዳግም እንጥራውና) ከ1944ቱ የብሪተን ዉድስ ስምምነት በኋላም ቢሆን በወርቅ የተደገፈ የኪዳን ወረቀት ነበር። ሲውል ሲያድር ግን ውስጡ “ቅዠት” ያለበት ወረቀት ብቻ ቀረ። ወረቀቱ “ምንም” ወይም “ቅዠት”(Illusion) ነው። ይህንን የቃልኪዳን ወረቀት (Promisory Note) በቀደሙት ገጾች እንዳየነው ለይቶለት ኦገስት 15 ቀን 1971 ላይ ነደደ ወይም ተካደ። አሁን ላይ ሁላችንም በነደደው የኪዳን ወረቀት ጭስ እየተጨናበስን ነው። ዓይናችንን እያሸን ከማየትና ውጪውን ከማድነቅ ውጪ የጠራ ብርሀን አይታየንም።

ስለዚህ ወርቃችንና ንብረታችን የት ነው ያለው? ካልን ወደ ምዕራባዊያን እየሄደና በምትኩ የጨሰ ወረቀት እየወሰድን ነው። ዕጃችን ላይ ባዶ ወረቀት እንጂ ጥሬ ገንዘብ የለም። ታዲያ ዘካ “በከህደት የአራጣ ወረቀት” ወይም “በጭስ” መክፈል አለብን ወይ? አዎ ከሆነ ግን ሸሪዓችንን እየሰደብን ነው። መክፈል ያለብን ግን ነቢያችን ﷺ በከፈሉበት በጥሬ ንብረት ነው። ታዲያ ዘካ መክፈል እናቁም? መተውማ አንችልም። ዘካን መክፍል ከተውንማ ከኢስላም ማዕዘናት አንዱ የሆነውን ዘካን መተው ሊሆን ነው። ይህ ደግሞ “ኩፍር” ነው። ከኢስላም ያስወጣናል። (ጽሑፉን ተከታተሉት)።

ሐ. የዘካ “ኒሳብ” (የመክፈያ ልክ)

በጥሬ ገንዘብ ላይ የዘካ ስሌትም ይሁን የስሌት መነሻ የተወሰነው በነቢያችን (ﷺ) ሲሆን እነሱም ወርቅና ብር ናቸው። የወርቅ ኒሳብ (ልክ) 20 ዲናር/ሚስቃል ሲሆን የብር ደግሞ 200 ዲርሀም ነው። (አንድ ዲናር/ሚስቃል 4.25 ግራም ወርቅ

ሲሆን ዲርሀም ደግሞ 2.975 ግራም ብር ነው)። 20 ሚስቃል 85 ግራም ወርቅ ሲሆን 200 ዲርሀም 595 ግራም ጠገራ ብር ይመጣል።

ዳግም ለማስታወስ ያህል አንድ ወቄት ወደ 7 ዲናር ነው። ሰባቱ ዲናር 500 ፍሬ የገብስ ወይም ስንዴ ዘር ነው። 20 ዲናር ማለት 1,428 የስንዴ ዘር ክብደት ነው። የአንድ ስንዴ ዘር አማካይ ክብደት 0.06 ግራም በመሆኑ የ20 ዲናር ክብደት 85 ግራም ወርቅ ይመጣል ማለት ነው። በትሮይ የፓውንድ አለካክ ሲስተም የአንድ ወቄት 480 የስንዴ ዘር ክብደት ሲሆን በኢስላማዊ አለካክ ደግሞ 500 የስንዴ ዘር ክብደት ነው። ተቀራራቢ ናቸው።

የወረቀት/ቁጥር (የፊያት) ገንዘብ የዘካ ኒሷብ (መነሻ ልኬት) የለውም። 85 ግራም ወረቀት ወይም 85 ግራም ቁጥር አይባል ነገር። የሆነ ዓመት ላይ 1,000፣ ሌላ ዓመት ላይ 8,000፣ ቆይቶ 85,000 እያሉ የኒሷብ ጨዋታ የለም። ጭራሽ ከሀገር ሀገር ይለያያል። ልኩ ከቦታ ቦታ፣ ከጊዜ ጊዜ አይታወቅም። ከአየርም የቀጠነ ሐሳብ ስለሆነ በሰከንድ ሽራፊዎች ሳይቀር ይለዋወጣል። ኒሷብ ደግሞ የዘካ አንዱ ማዕዘን (አርካን) ነው። ያለ ኒሷብ (ልኬት) ዘካ አይተመንም። ማን እንደሚከፍል ማን እንደሚቀበል ለመወሰን አዳጋች ነው። በራሱ ችሎ ለመቆም ስለማይችል ሌላ ምርኩዝ ይፈለግለታል። ወይም ንጽጽሮሽ ጋር ይኬዳል። አርካን (ማዕዘን) በቂያስ (ንጽጽሮሽ) አይቆምም።

ማስተዋል ያለብን በፊያት መገበያያ ዘካ ሲከፈል በወርቅና ብር ነው እንጂ በልኬቱ አይደለም። አሁን ባለው ሁኔታ ለችግርተኛው ጭስ መክፈልማ ለማጨናበስ ነው። በፊያት የምንከፍል ከሆነ ኒሳቡ ዘወትር ሊወዛገብ ነው። የሚቀያየር ኒሳብ ደግሞ ኒሳብ አይባልም። ይህማ የሶላትን ረካአ እንደማዋዠቅ ነው። የዛሬ 1400 ዓመት አንድ ዲናር (4.25 ግራም 22-24 ካራት ወርቅ) ሁለት ወይም ሦስት በግ

የሚገዛ ከሆነ ዘንድሮም ያው ነው። ይህ የአላህ ገንዘብ ስለሆነ ክብሩን እንደጠበቀ ይቆያል። ከመሆኑም ጋር አሁን ወርቅና ብር አናገኝም። ብናገኝም ደሀው አይበላውም። ሄዶም አይገዛበትም። ደሀው ወርቁን ጌጣጌጥ ቤት ወስጄ ልሸጠው ቢል ደግሞ አሁን በምናስተውለው ሁኔታ ከግማሽ በታች ነው የሚረከቡት። ቢሆንም ጨክነን በወርቅና ብር እንክፈል? ተከተሉኝ።

ዘካ “ሚባዳ ተውቂፊያ” ነው። “ሚባዳ ተውቂፊያ” የሚሰኙት “የማይነኩ አምልኮዎች” ስለሆኑ ከአላህ የወረደውን እንዳለ ተቀብለን የምንተገብራቸው ናቸው እንጂ የሰው ልጅ ማስተካከያና ማሻሻያ የሚፈልጉ አይደሉም። ዘካ ደግሞ የኢስላም መሠረት ነው። የሶላት “ረካአዎች” (የስግደት ብዛቶች) እንደማንነካው ሁሉ የዘካንም አንነካም። “በተውቂፊያ” (አላህ የደነገጋቸውና የፍጡር ጣልቃ ገብነት የማይሹ) የአምልኮ ጉዳዮች ላይ “ቂያስ” ወይም “ንጽጽር” ማድረግ በጣም ከባድ ነው። ሳንለውጥ እንዳሉ መቀበል ነው። በወርቅና በብር ማዕድናት ገንዘብ ሲከፈል የነበረው ዘካ፤ በወረቀት ማመሳሰል የሙስሊሞችን ሶላት ሙስሊም ያልሆኑ እምነቶች ከሚሰግዱት ሶላት ጋር እንደማመሳሰል ነው። ሀገሩ ሁሉ የአይሁድ አሰጋገድ “ተፊላህ” ይሰግዳል ብለን እኛም መስጂዳችን ውስጥ “ተፊላህ፣ ተፊላህ” አንልም። ያም ሶላት ይህም ሶላት፤ ያው ናቸው እንደማለት ነው።

ዘካን በፊያት መክፈል የፊያትን ሲስተም በአምልኮአችንም ጭምር ዕውቅና መስጠት ነው። ስለዚህ ምን እናድርግ?

ጊዜያዊ የዘካ አከፋፈል መፍትሔ

እላይ የጠቀስናቸው በሙሉ ዘካን በፊያት መክፈል እንደሌለብን የሚያስገነዝቡ ናቸው። የማዕድናት ዲናርና ዲርሀም በዝውውር እስካሉ ድረስ በእነርሱ መክፈል የግድ ነው። ከሌሉ ግን ወደ ተግባር የማምጣቱ ሥራ በውለማእ (ሊቃውንት) እና ኡመራእ (መሪዎች) ትከሻ ላይ የወደቀ ግዴታ ነው። እዚህ ድረስ ግልጽ ነው።

ታዲያ ዲናርና ዲርሀም ዝውውር ላይ የሉም። በእነርሱ ብቻ ነው የምንከፍለው። በፊያት ግን አንከፍልም ካልን ዘካ የሚከፍሉት ገበሬዎች ጎተራ ላይ ባለው ምርታቸው፣ አርብቶ አደሮች በበረታቸው፣ ነጋዴ በሸቀጡ እና የወርቅና የብር ማዕድናት (ጌጣጌጥ) ያለው ብቻ ነው የሚከፍለው ማለት ነው። በአሁኑ ወቅት አብዛኞቹ ሀብታሞች የሚሰጡት ደግሞ ገንዘባቸው በፊያት ነው የሚገኘው። ስለዚህ ዘካ ከፋይ የሚሆነው በይበልጥ ደሀው ሊሆን ነው ማለት ነው። ደሀው ዘካ ከፋይ ሆኖ ሀብታም ላይከፍል ነው? ደሀ ገበሬ ለሀብታም ነጋዴ ሊከፍል? ይህማ ጭራሽ ይገላበጣል። የደሀውም ቁጥር እየጨመረ ይመጣል። ምናልባት ይህ ቢደረግ ዘካ ከናካቴው ሊቆም እና የኢስላም አንዱ ምሰሶ ተነቅሎ ከኢስላም ውጭ ልንሆን ነው።

“ማላ ዩተሙል ዋጂቡ ኢላ ቢሂ፤ ፈሁዎ ዋጂብ (ግዴታን ለመሙላት ግዴታ የሆነ ነገር ሁሉ እራሱም ግዴታ ነው)” በሚለው የሸሪዓ መሠረታዊ መርህ መሠረት ***ፊያትን በወርቅና ብር እየለካን እንከፍላለን***። ስለዚህ ዘካ በፊያትም ቢሆን ግዴታችን ነው። ነገር ግን ይህንን የምናደርገው ወደ ዲናርና ዲርሀም እስክንመለስ ነው። አሁንም የምንችልና በተለይ ለተመጽዋቹ የሚመች ከሆነ ወርቅና ብር እየገዛን ብንሰጥ ለነቢያችን ﷺ ሱና ይበልጥ እየቀረብን ነው ማለት ነው። አሜሪካ አንድ ግዛት ውስጥና ማሌዢያ የሆነ ክፍለሀገር በወርቅ ሳንቲም ግብይት አለ የሚል ነገር

ሰምቻለሁ። (ሰምቻለሁ ለመጽሐፍ መረጃ አይሆንም እንጂ)። ምናባዊ ይሁንና በእነዚህ ግዛቶች ውስጥ የሚኖር ሙስሊም፤ ዘካውን በወርቅ ሳንቲም የመክፈል ግዴታ ውስጥ ወድቋል ማለት ነው።

እነዚህን ነገሮች በሐሳባችን ካሳደርን ዘወትር ስለሚቆረቁረን ወደ ኢስላማችን ለመመለስ ይረዳናል። እዚህም ጋር ለማንሳት የተፈለገው ይህንን ስሜት ለመፍጠር ነው። ነጥቡም ይኸው ነው። የወረቀት ገንዘባችን በጀርባው ንብረቶች አሉት። ወረቀቱ ይጋሸብም ይጠንከር፤ ለጊዜው በወርቅ እየተመንነው በሐሳብ ዘካ እንከፍላለን። ከመንገድ መራቃችንን ግን መዘንጋት የለብንም።

ስለዚህ ፊያት ዘካ ላይ ይህንን ከመሰለ ሌሎች ጉዳዮችም ላይ ተመሳሳይ ችግሮች እና የአለካከ ዘዴዎችን መጠቀም ያስፈልጋል። ለምሳሌ የጋብቻ መህር (ጥሎሽ) በፊያት ሦስት ሺህ ወዘተ ተብሎ ይጠራል። ሸሪዓው ለሙሽሪት ወዲያው በደስታ መክፈል እንዳለበት ቢያስቀምጥም ብዙ ጊዜ ይዘገያል። ምናልባትም ሲፋቱ ነው ጥያቄው የሚነሳው። የዛሬ 20 ዓመት በሦስት ሺህ ብር መህር የታሰረ ጋብቻ ዛሬም በሦስት ሺህ ብር መፈታት አይኖርበትም። የዛሬ ሀያ ዓመት ወርቅ በግራም ሁለት መቶ ብር ገደማ ነበር እንበል። ለምሳሌ በ2021 የአንድ ግራም ወርቅ ዋጋ በዓለም አቀፍ ገበያ በአማካይ ሁለት ሺህ አምስት መቶ የኢትዮጵያ ብር ገብቷል። ያኔ 15 ግራም ወርቅ መግዣ ነበር ማለት ነው። ዛሬ ሦስት ሺህ ብር ሊገዛ የሚችለው ሁለት ግራም እንኳ የማይሞላ ወርቅ ነው። እና ከአስራ ሦስት ግራም በላይ ወርቅ የት ገባ? ፍቺ ቀልድ ሊሆን ነው ማለት ነው። ያውና ሦስት ሺህ ብርሽን። እንካ ሦስት ሺህ ብርህን ሊባባሉ ነው ማለት ነው። ወለድ ማለትም መበዳደርም ጋር ስንመጣ ተመሳሳይ ነገር ነው ያለው።

1.3. የዓይነትና የፊያት መገበያያ ንጽጽር

ሁለቱን ገንዘቦች በተወሰኑ ነጥቦች ላይ ለማወዳደር እንሞክራለን።

ሀ. ባለቤትነት የሚገኝበት ነጥብ

የፊያት መገበያያ መነሻው ዕዳ ስለሆነ ዕዳዎችን ከላይ ከጀማሪዎች ተነስተው ከሰዎች ወደ ሰዎች እንዲሁም ከሀገር ሀገር እያንከባለሉ ማሻገር ነው። የመጨረሻ ተቀባይ ዕዳ ተሸካሚ ወይም ባዶ ወረቀት ታቃፊ ይሆናል። ገንዘቡ ያለው ባንክ ውስጥ ኮምፒዩተር ላይ በተጻፈ ቁጥር ከሆነ ደግሞ ለሙዚየም የሚሆን ወረቀት እንኳ አይኖረውም። ጠንቃቃ ሰው እጁ ላይ የፊያት ወረቀትም ይሁን ቁጥር አይዝም። ቢችል በንብረት ይቀይረዋል። ሰው ቶሎ አእምሮው ላይ የሚመጣው በዶላር ቀይሮ ማስቀመጥን ነው። ዶላርም እኮ ፊያት ነው። የማይበላሹ ንብረቶችና ኢንቨስትመንቶች ግን ጥሩ አማራጭ ናቸው።

በተቃራኒው በዓይነት የገንዘብ ግብይት ሒደት ወቅት ዕቃና ክፍያው ወይም “ዕዳና ምንዳው” በግብይት ቅጽበት ይጠናቀቃል። ዕዳ የሚባል ነገር የሚፈጠርበት ክፍተት አናሳ ነው። ይህ ሲሆን እንኳ በጥንቃቄ እንድንመዘግበው ቁርአን በአጽንኦት ያዛል። የቁርአን ረጅሙ አንቀጽ (በቀራ 2፡282) ስለዚህ ጉዳይ ነው የሚያትተው።

የዓይነት ገንዘብ ይዞ ገበያ የወጣ ሰው አየር ላይ “አለኝ” የማይባልና እዚያው የሚታይ ዕቃ ገዝቶ ይመለሳል። ጤፍ ፈልጎ ገብስ ይዞ የወጣ ሰው በጥራትና ልኬት እስከተስማሙ ድረስ ዕዳና ምንዳው ሲለዋወጡ ያበቃል። ግብይቱ በወርቅ ተመን ከሆነ ጤፉ ወይም ገብሱ ወይም አጋሰሱ በወርቅ ከተቀያየሩ ያበቃለታል። ልውውጡ እዚያው በዚያው ነው። “እቤት ስደርስ እከፍልሀለሁ” ማለት ወለድ እንደሆነ እላይ በጠቀስነው ሀዲስ ላይ አይተናል።

ለ. የመንግሥት ሚና

በዓይነት ገንዘብ ወቅት መንግሥታት ገንዘብን እንደፈለጉ ማጫወት አይችሉም። ገብስ ያለው ሰው ሲፈልግ በሌላ ዕቃ ይቀይረዋል፣ ሲፈልግ ቆልቶ ይበላዋል፣ ሲፈልግ ይዘራዋል። ቢያንስ ቢያንስ ገንዘቡ በዓይነት ማለትም በወርቅ የተደገፈ (gold backed) ገንዘብ ከሆነም መንግሥታት እንደፈለጉ መጨመርም ይሁን መቀነስ ሊከብዳቸው ይችላል። ከዚህ አልፎ በፊያት መልክ ካለ ግን፤ መንግሥታት እንደ ፖለቲካ አመለካከታቸው ከፍም ዝቅም ያደርጉታል። ወይም የዓለም አቀፍ አታሚዎቹና ተቆጣጣሪዎች ከፍና ዝቅ ያደርጉባቸዋል። የአሜሪካ መንግሥት “ማዕቀብ ጥያለሁ” እያለ መንግሥታትን የሚያስፈራራው ፊያትን በመጠቀም ነው። ዶላር የወርቅን ቦታ ስለተካ ብቸኛ ሰጪና ነሺ አሜሪካኖች ሆነዋል። ድርጊታቸው የአምላክን ቦታ ተክተው ለመሥራት ይመስላል። ***ገንዘብ ሁን ይሉታል። ይሆናልም። (ኩን ማለን ፈየኩን)።***

ሐ. ብዛቱን መወሰን

የዓይነት ገንዘብ ሲስተም ከሆነ መንግሥትና ሕዝብ ምን ያህል ወርቅ ለሳንቲምነት እንደሚቀልጥ፣ ምን ያህሉ ለጌጣጌጥና ለኢንደስትሪ እንደሚውል ፖሊሲ ነድፈው፣ ሕግ አርቅቀው ሊወስኑ ይችላሉ። ቴክኖሎጂው አሁን ካለው የባንክና የገንዘብ ተቋማት በላይ እንደሚዘምን ጥርጥር የለውም። ስለዚህ በዓይነት የገንዘብ ሥርዓት ሁሉም የሕብረተሰብ ክፍል በአንጻራዊ ዲሞክራሲያዊ መንገድ በገንዘብ ሕትመት (ማቅለጥ) ሊሳተፉ ይችላል። ምክንያቱ ይነስም ይብዛ ሁሉም ግለሰብ ዘንድ ውስጡም ውጪውም ገንዘብ የሆነ ሀብት ይኖረዋል። በፊያት ሥርዓት ግን የተወሰኑ ኤክስፐርቶች የተስማሙበትን የገንዘብ ሥርዓት ይነድፋሉ።

መንግሥትም ያንን ፖሊሲ ያስፈጽማል። ሲፈልግ ይጨምረዋል። ሲፈልግ ይቀንሰዋል።

መ. ተቆጣጣሪ መሥሪያ ቤቶች

ከወርቅ ገንዘብም በተጨማሪ የዕቃ በዕቃ ልውውጥ ስለሚኖር ግብይቶች በዘርፋቸው በሚተመኑ መሥሪያ ቤቶች አማካይነት ስለሚፈጸም ክፍያ ከፊያት በበለጠ ይፈጥናል። አሁን ብሔራዊ ባንክ የሚቆጣጠረው ገንዘብ፤ በዓይነት ገንዘብ ወቅት የማዕድን ሚኒስቴር ይቆጣጠረዋል ማለት ነው። የእህል ደግሞ ግብርና ሚኒስቴር። ወይም ግብይትን የሚመለከት ከንግድ ሚኒስቴርም የሚሰፋ "ግብይት ሚኒስቴር" የሚል ይኖረን ነበር ማለት ነው።

ሠ. የገንዘቡ አቅርቦት

ፊያት የፖለቲካ ገንዘብ በመሆኑ በመንግሥት ፍላጎት ይወሰናል። ለሕዝብ የሚቀርበውም በነጻ ነው። የዓይነት ሲሆን ግን የሚቀርበው በሕዝብ ሲሆን የሚወሰነውም በማምረት ብቃት ነው። "ሕጋዊ" በሚሰኝ ማዕቀፍ ከሚታተመውም ባሻገር ፊያት ሰው ሰራሽ በመሆኑ በጎን "ፎርጅድ ፊያት" እየታተመ ገበያ ውስጥ ተቀላቅሎ ምርት ሊሰበሰብበት ይችላል። ምክንያቱም በመንግሥት በኩል የሚመጣው በሰው ሰራሽ ማሽን የታተመ በመሆኑ ሌሎች ሰዎችም እራሱኑ ቁጭ ሊያደርጉት ይችላሉ። ቴክኖሎጂ ባልዳበረባቸውና ወረቀትን እንደ ገንዘብ በሚጠቀሙ ሀገራት በዝውውር ውስጥ የሚገኙ ወረቀቶች አንድ ሦስተኛው ያህል ከመንግሥት ዕውቅና ውጭ እንደሚታተሙ ጥናቶች ያመለክታሉ። ወርቅ ግን ሲፈልጉ ይጠፍጥፉት ሲፈልጉ ያድቦልቡሉት ያው ወርቅ ነው። የኢስላማዊ የገንዘብ ሥርዓት ውስጥ ወርቅ ሳንቲምም ይምሰል ማጭድ መለኪያው ሚዛን ነው። የአንጥረኝነት ዋጋ ስለሚያወዛግብ ግምት ውስጥ አይገባም። ለጌጥ የፈለገ ሰው

ማሠራት መብቱ ነው። ወደ ገንዘብነት ሲቀይረው ግን በክብደት ነው። ይህ መርህ ብዙ ራስ ምታቶችን ያሳርፋል። የቀድሞ የአሜሪካው ፕሬዝዳንት ጆርጅ ዋሽንግተን ምስል ከቀድሞ የዚምባቡዌው ፕሬዝዳንት ሮበርት ሙጋቤ ምስል ጋር ልዩነት አይኖረውም።

ረ. ዋጋ ትመና

የፊያት መገበያያ ሙሉ ተቆጣጣሪዎች መንግሥታት በመሆናቸው በሕዝቡ ኪስ ውስጥ ያለው ገንዘብ ማጋሸብና ሙሉ ለሙሉ ከጥቅም ውጭ ማድረግ ይችላሉ። ኃያላን መንግሥታት ደሀ መንግሥታትን በሳምንታት ውስጥ በማዕቀብ ከጥቅም ውጭ የሚያደርጉት እነዚያ ደሀ የተባሉ ሀገራት አነስተኛ ምርት ኖሮአቸው ሳይሆን የግብይት ሥርዓቱ በአርተፊሻል ገንዘብ በመቀየሩና ተቆጣጣሪዎቹ ኃያላን መንግሥታት በመሆናቸው ነው። የዓይነት ሲሆን ግን ገንዘቡ የሚተመነው በምርታማነት ወይም በአቅርቦት ነው። ዛሬ ፊያት መጠቀም እናቁም ቢባል አንድ ቢሊዮን ዶላር ካለው ቱጃር አንድ ኩንታል ጤፍ ያለው ሰው ይሻላል።

اللَّهُمَّ صَلِّ عَلَىٰ سَيِّدِنَا مُحَمَّدٍ وَعَلَىٰ آلِهِ وَصَحْبِهِ وَسَلِّمْ

1.4. ግሽበት (INFLATION) እና መዋዠቅ (FLUCTUATION)

አጠቃላይ፡- ግሽበት ውስጣዊ ሲሆን መዋዠቅ ደግሞ ውጪያዊ ነው። ፊያትና ግሽበት በሥጋና በነፍስ የተጋቡ ናቸው። ግሽበት (INFLATION) ፊያት ሲፈጠር ጀምሮ ውስጡ አለ። አንዱ ያለ አንዱ መፈጠርም፣ መኖርም አይችሉም። ግሽበት በዓይነት ገንዘብ ወቅት ይፈጠር ይሆናል። ግን ዋና ባሕሪያቸው አይደለም። ከግሽበት ይልቅ የተፈጥሮ (የዓይነት) ገንዘቦች ላይ ሊከሰት የሚችለው በውጭ ኃይል በ(Extra ordinary force) የሚፈጠር ውዥቀት ነው። ነገር ግን ግሽበቱም ውዥቀቱም ያን ያህል አይደለም። ቢዋዥቅ እንኳ የምርት መትረፍረፍ ስለሚሆን "ፖዘቲቭ ተጽእኖ" ነው ያለው። ፊያት ላይ ያለው ግሽበት ግን ዘወትር በኔጌቲቭ በኩል ነው። አንዳንዴ ፖዘቲቭ (ጥንካሬ) አለ። ጥንካሬው እራሱ ሰው ሰራሽ ነው። ፊያት ከተፈጠረ ጀምሮ የሁሉም ገንዘቦች ጸባይ መጋሸብ ነው። ስለዚህ ሁለቱንም በአጭሩ እናያቸዋለን።

ሀ. የዋጋ ግሽበት (Inflation) በወረቀት መገበያያ (ፊያት)

ትርጉም፡- ተከታታይነት ያለው አጠቃላይ የምርትና አገልግሎት የዋጋ ጭማሪ ነው።[51]

የሚለካበት ጊዜ፡- ብዙ ጊዜ ዓመታዊ ሆኖ ካለፈው ዓመት ተመሳሳይ ወቅት ጋር ወይም በጥቅል ካለፈው ዓመት ጋር ይወዳደርና ልዩነቱ ግሽበት ይባላል።

[51]Paul H. Walgenbach, Norman E. Dittrich and Ernest I. Hanson, (1973), Fiancial Accounting, New York: Harcourt Brace Javonovich Inc, Page 429.

መለኪያ፡- CPI (Consumer Price Index) [52] የምርትና አገልግሎት የመጨረሻ ተጠቃሚዎች የዋጋ ኢንዴክስ (ውድድርና ልዩነት) እና PPI (Producer Price Index) አምራቾች ለምርት ግብዓት የሚከፍሉት የዋጋ ውድድርና ልዩነት ናቸው። ለምሳሌ የአምና የአንድ እንጀራ ዋጋ ወይም የአንድ ኪሎ ጤፍ ዋጋ ከዘንድሮ ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነጻጸር የሚገኘው ልዩነት "የዋጋ ግሽበት" ይባላል። ይበልጥ ለማብራራት አምና በኪሎ 35 የነበረው ጤፍ ዘንድሮ 40 ብር ቢገባ ልዩነቱ 5 ብር ነው። በመቶኛ ሲሰላ ግሽበቱ 14% ይሆናል። 14% የመጣው ጭማሪዋ 5 ብር ለአምናው የጤፍ የኪሎ ዋጋ ማለትም ለ35 ብር ተካፍሎ ነው። ለግሽበት ጤፍ ብቻ ሳይሆን ሌሎችም ተመሳሳይ የሆኑ ምርትና አገልግሎቶች ማለትም አጠቃላይ የምግብ፣ የልብስ፣ የመድኃኒት፣ የነዳጅ፣ መጓጓዣ፣ ወዘተ ፍጆታዎች የአምናና የዘንድሮ ሲወዳደሩ ማለት ነው። በአጠቃላይ አነጋገር በ"CPI (Consumer Price Index)" ወቅት ተመርቶ ያለቀለት የምርትና አገልግሎት ዋጋ ነው የሚሰላው።

የአምራች የዋጋ ኢንዴክስ (Producers PriceIndex) ግብዓቶች፡- ጥሬ ዕቃ፣ የኢንዱስትሪ ሠራተኞች ደመወዝ እና ተያያዥ ግብዓት ሲሆኑ ከአምና ተመሳሳይ ወቅት ጋር ይለካና ልዩነቱ እንደ ግሽበት ይወሰዳል። ለምሳሌ መዳብ የፋብሪካ ግብዓት በመሆኑ የአምራች የዋጋ ኢንዴክስ ውስጥ ይገባል።

መንስኤ፡- የፊያት ዋነኛው ምክንያት ውስጣዊ ነው። ውስጣዊ ሲባል ከገንዘቡ ፍልስፍና ጋር የተቆራኘ ነው።

[52] Mankiw, N. Gregory (2002), "Macroeconomics" (5th edition), Pages 22-32.

የግሽበት ምክንያቶች፡- ይህ ነው የሚል የተቆረጠ ነገር ባይኖርም ኢኮኖሚስቶች የፍላጎት መሳብ እና የዋጋ መግፋት (Demand Pull and Cost Push) ቲዮሪ ይወሰናል ይላሉ[53]።

Demand Pull (የፍላጎት መሳብ)፡- ይህ በፍላጎትና አቅርቦት ልዩነት የሚፈጠር የዋጋ ለውጥ ነው።

Cost Push (የዋጋ መግፋት)፡- ኢንዱስትሪዎች የግብአት ዋጋ ሲጨምርባቸው ሕዝብ ላይ ዋጋ በመጨመር የሚፈጠር የዋጋ ለውጥ ነው።

ሌሎች የግሽበት አባባሾች እጅግ በርካታ ናቸው። እስካሁን የምንገልጸው የወረቀት መገበያያ አዲስ ሕትመት፣ የዓለም አቀፍ ምርቶች የዋጋ ለውጥ፣ የሕዝብ ቁጥር መጨመርና የተጨማሪ ምርት አለመጣጣም፣ በተለይ የሰው ልጆች የማያልቅ ፍላጎታቸውን በደሀው ላይ በሚጭኑ ምዕራባዊያን ምክንያት የሚፈጠር የደሀ ሀገር ገንዘቦች ግሽበት ሊጠቀሱ ይችላሉ።

ይህ የገንዘብ ሥርዓት በተለይ ሙስሊሙን የገንዘብና የወለድ ትርጉም በትክክል ባለመተንተኑ ለእምነቱ ባለው ቀናኢነት የተነሳ ለባርነት፣ ለድህነትና ለከፍተኛ ሰቆቃ የዳረገ በመሆኑ በጥልቀት ልናየው እና ሁኔታው እየታየ ሀይማኖታዊ ብይን ሊሰጥበት ግድ ይላል። የባንክ ሰዎች (ባንከርስ) "ወለድ የምናስከፍለው ግሽበትን ለመተካት ነው" ይሉ ይሆናል። ጉድጓድ ቆፍሮ መልሶ መሙላት ለምን አስፈለገ? የተንኮል ጉድጓድ ቀድሞ ቆፍረው ማለትም ግሽበቱ ገንዘቡ ሲፈጠር ጀምሮ ተፈጥሮ ሲያበቃ

[53] Robert J. Gordon (1988), Macroeconomics: Theory and Policy, 2nd edition, McGraw-Hill, Page 22.

መልሶ እሱን ጉድጓድ መሙላት ከፍተኛ የሆነ አሻጥር አለበት። እስካሁን ባየናቸው ጉዳዮች አሻጥሩ ወለል ብሎ ይታያል።

ለ. የዓይነት ገንዘቦች ከግሽበት ይልቅ ለመዋዠቅ ያላቸው ተጋላጭነት

የዓይነት ገንዘብ ከinflation (ግሽበት) ይልቅ ለመዋዠቅ (Fluctuations) ሊጋለጥ ይችላል።[54] የመዋዠቅ መንስኤዎች ውስጣዊ ሳይሆኑ ውጫዊ ናቸው። ምክንያቶቹም

1. **የአዲስ ምርት (ማዕድናት) ክምችት መገኘት፡-** ይህ እንግዲህ ለሰው ልጅ ጠቃሚ እንጂ ጎጂ አይደለም። አንድ የተለመደ ወይም አዲስ ማዕድን ሲገኝ ተጨማሪ የርዝቅ (ሲሳይ) በር ይከፍታል። ብዙ ሰው ይጠቀማል። ነዳጅ ሲገኝ ብዙ የርዝቅ በሮች መከፈታቸውን እናውቃለን።

2. **የምርት መትረፍረፍ፡-** ልፋታችን ምርት እንዲትረፈረፍ ነው። ይህ ደግሞ ፖዘቲቭ (አዎንታዊ) ጥቅም ነው ያለው።

3. **ድርቅ፡-** ኔጋቲቭ (አሉታዊ) የሆነ ተጽእኖ የሚያመጣው ለዓይነት ገንዘብ ብቻ ሳይሆን ለፊያትም ጭምር ነው። ድርቅ በፊያት መገበያያ ላይ ይልቅ ይብሳል።

4. **የጦርነት ምርኮ፡-** ጦርነት ተፈልጎ የሚካሄድ አይደለም። ዘወትርም አይካሄድም። ስለዚህ ምርኮ ሁልጊዜ አይገኝም። በዘመናት ለተወሰነ ጊዜ የሚገኝ ምርኮ የገንዘብ መዋዠቅ ላይ የሚያደርሰው ተጽእኖ ያን ያህል አይደለም። የጦርነት ምርኮ ገቢ ብቻ ሳይሆን ጦርነቱ በሚካሄድ ወቅት ከፍተኛ የሆነ ወጪም አለው።

[54] www.investopedia.com - Commodity Money (ገንዘብና ኢኮኖሚ ነክ መረጃዎች በአጭሩ የምናገኝበት ድረ-ገጽ)

የተጠቀሱት ቢኖሩ እንኳ የሰው ልጅ ዞሮ ዞሮ ንብረት ነው የሚፈልገውና ንብረቶቹ ቢገኙ ጥቅም እንጂ የጎላ ጉዳት የላቸውም። የያዛቸውም ሰው ለችግር አይጋለጥም። አቆይቶ ለኑሮው ሊጠቀምባቸው ይችላል።

ሐ. ግሽበት (Inflation) እና አራጣ (Interest) ሲነጻጸሩ

- ✓ ሁለቱም የሚፈጠሩት በጊዜ መዘግየት ነው።
- ✓ የግሽበትም የአራጣም **ጥቅል ትርጉም ለሁሉም ሰው ግልጽ** ናቸው።
- ✓ **በዝርዝር ጉዳያቸው ላይ ግን እጅግ አወዛጋቢ ናቸው።**
- ✓ ግሽበት ከባለፈው ላይ ዋጋ ጨምሮ መክፈል/መቀበል ሲሆን አራጣም ከባለፈው ላይ ጭማሪ አድርጎ መክፈል/መቀበል ነው።
- ✓ ግሽበት በምን እንደሚለካ የኢኮኖሚክስ ቲዎሪዎች እንዳሉ ሁሉ አራጣም በእነማን እቃዎች ላይ እንዳሉ በደፈናው ቢቀመጥም ዝርዝሮቹ ላይ ግን ስምምነት የለም።
- ✓ የፊያት ግሽበት ከሸሪዓው አራጣ ጋር ማመሳከር እጅግ የተሳከረ ውጤት ያመጣል። ትምህርቱ፣ ጥናቱና ውድድሩ በሦስቱ መካከል ማለትም፤ (1) የፊያት ግሽበት (2) ከዓይነት ገንዘብ ግሽበት እና (3) ከአራጣ ጋር ከሆነ የተሻለ ስዕል ይሰጣል። በሌላ አነጋገር፤ ዶላር ከወርቅ ከዚያም ሌሎች ዕቃ/አገልግሎት ጋር መወዳደር አለበት።
- ✓ በተጨማሪም የፊያት ግሽበት እና የባንክ ወለድ አወዳድረን፤ ከዚያ ከሸሪዓው አራጣ (ሪባ) ጋር ወደማመሳከር መሸጋገር ይቻላል።

- ✓ ግሽበት መታወቂያው የሆነ ፈያት ላይ የተመሰረተ የባንክ ወለድ ብዙም ግሽበት ከማያጋጥመው የሸሪዓ ገንዘብ አራጣ ጋር ማወዳደር የስንፍና እንጂ የዕውቀት ሊሆን አይችልም። ምክንያቱም “ወለድ” የሚለውን ቃል በሰማን ቁጥር የሸሪዓው ሪባ ነው ብሎ እንዳለ መውሰድ፤ በሙስሊሙ ዓለም ትልቅ ተፋልሶ አምጥቷል።

የግሽበት ዝርዝር ምንነት በደንብ ሳይበየን፤ የአራጣም ዝርዝር ሁኔታ ከፈያት ጋር ሳይጣጣም “ኢስላማዊ ባንክ” መክፈት ከቲዎሪው ጋር የተጣረሱ ባንኮችን ፈጥሯል። መፍትሔው ከችግሩ ብሷል። ለመፍትሔ ተብሎ የተፈጠረው ““ኢስላማዊ ባንክ”፣ የወለድ ነጻ መስኮት” ከድጡ ወደ ማጡ የሆነ በዝባዥ ሥርዓት ገንብቷል። (ዝርዝሩ በሌላ ምዕራፍ ይመጣል)።

اللَّهُمَّ صَلِّ عَلَىٰ سَيِّدِنَا مُحَمَّدٍ وَعَلَىٰ آلِهِ وَصَحْبِهِ وَسَلِّمْ

ምዕራፍ ሁለት

የሀገራችን ተግባራዊ ዕውነታዎች

ተግባራዊ ዕውነታዎቹን የምናየው ዘወትር የሚገጥሙንና የዚህ መጽሐፍ አዘጋጅ የታዘባቸው ዕውነታዎችም ጭምር ናቸው። የዚህ ምዕራፍ ወሰኖች ሕገ-መንግሥቱና ተያያዥ ፖሊሲዎች ናቸው። ሙስሊሙም ሌላውም በጋራ ግንባር ፈጥረው የሚታገሉዋቸው ለቁጥር የሚታክቱ ችግሮች አሉ። መንግሥት ለሁሉም ዜጎች ይመቻሉ ያላቸውን ፖሊሲዎች አሰናድቶታል። በእኩልነት ላይ መሠረት አድርገው የተቀረጹ ናቸው። ሀይማኖታዊ አድልዎ አናይባቸውም። የኛ ሚና የፖሊሲዎቹን አመቺነት በመጠቀም በሀገር ዕድገት ላይ የድርሻችንን መወጣት ነው።

መንግሥት "ወለድ በኢስላም ይህንን ወይም ያንን ይመስላል" ብሎ መስጂድ ገብቶ ለምእምናን ፈትዋ (ሀይማኖታዊ ብይን) መስጠት ሕገ መንግሥቱ አይፈቅድለትም። የምእምናን ሥራ ነው። እኛም በየወቅቱ የሚወጡ ሕጎችና ፖሊሲዎችን ተንትነን ከእምነታችን ሕግጋት ጋር ማጣጣም ከቻልን በሀገር እድገት የበኩላችንን ድርሻ መወጣት እንችላለን። የመጽሐፉ አንዱ ዓላማም ያንን ማፍታታት ነው።

ቀጥለን አመለካከታችንና እንቅስቃሴያችን በሀገር ዕድገት ላይ ምን ጉዳት እንዳመጣ፤ የጋራ ወይም ብሔራዊ ገንዘቦች ሆነው እያለ ሥራ ላይ ሳናውላቸው መክነው መቅረታቸውን እናያለን። በተጨማሪም ከሀይማኖታችን ሕግጋት ጋር በጥልቀት ባለመፈተሻችን በራሳችን በግል ሕይወታችንም ላይ "እራስ-ሰራሽ" ችግሮችን ስንፈጥር እንታያለን ቢባል ተራ ወቀሳ አይደለም። አንዳንድ ሕጎች በኛ ላይ

የወጡ እስኪመስለን ድረስ በጥርጣሬ የምናይበት ሁኔታ ይስተዋላል። ስለዚህ ችግሮቻችን “ፖሊሲ-ሰራሽ” ሳይሆኑ የኛ በጥልቀት አለማየት እንደሆነ ይጠቁማሉ። ከሥር ለምሳሌ ያህል እንደ ርዕስ የቀረቡት ነጥቦች በዓይን የሚታዩ ዕውነታዎችና እያንዳንዳቸው እራሳቸውን የቻሉ ታላላቅ ርዕሶች ናቸው።

2.1. የማሕበር ሱቆች

ሱቆች በማኅበር ሲገነቡ አንድ ሙስሊም አብሮ ይጀምርና ሙስሊም ያልሆኑት ከባንክ እበደራለሁ ሲሉ ሙስሊሙ "ወለድ ጋር ላለመነካካት" ብሎ ድርሻውን ከነተለጣፊ ጊዜያዊ ሱቁ ጋር ሽጦ ይወጣል። በትንሹ በሙስሊም-ክርስቲያን ነጋዴ መካከል ከንፈር መነካከስ ተፈጠረ ማለት ነው። ከሚያሳዝነው ሁሉ የሚያሳዝነው ደግሞ አንዳንዱ ሙስሊም ካደገበትና ደንበኞቹ ካሉበት ሰፈር ላለመልቀቅ፤ በግንባታ ሒደት እያለ በባንክ ብድር ንክኪ ምክንያት ሽጦት በነበረው ሱቅ ተገንብቶ ሲያልቅ መልሶ ይከራየዋል፤ ወይም በዚያው አካባቢ ሌላ ተረኛ ፈራሽ ሱቅ ላይ ተከራይቶ ይሠራል። ከባለርስትነት ወደ ጭሰኝነት ይዞራል። ወይም ሕንጻው ተገንብቶ አልቆ ተለጣፊው ሱቆች ሲፈርሱ፤ ያኔ ድርሻውን የገዙት “የባንክ ተበዳሪ ጓደኞቹ” ድርሻቸውን ተረክበው ሲዘንጡ እሱ ለኪራይም ላያገኝ ይችላል። ሰዎቹ ከባንክ ተበድረው ሕንጻውን እየገነቡ በዋና ገንዘባቸው ደግሞ በተለጣፊ ጊዜያዊ ሱቃቸው ምናልባትም በነጻ ያለ ኪራይ ይነግዳሉ። ተበዳሪዎቹ የሚበደሩት ደግሞ የማይበደረው ሰውዬ “ከወለድ ነጻ” በሚል ያስቀመጠውንም ብር ጭምር ነው። ንግዱን አፋፍመው ይያያዙታል። ሩጫው በመኪናና በእግር መሽቀዳደም እንደ ማለት ነው። [አብዛኛውን ጊዜ በመኪና የሚግገጨው እግረኛ መሆኑን አንዘንጋ]።

የሚገርመው የዚህ የማይበደረው ሰውዬ አንደኛው ሎጂክ (እሳቤ) "በወለድ ከምነካካ ገንብተው ሲጨርሱ እገዛለሁ" ነው። እንግዲህ ሰውየው እስከዚያ ከጨዋታ

ውጭ ሆኖ ካላለቀ ነው። አሁን ሱቅ የሚገዛበት ገንዘብ ከአሥር ዓመት በኋላ የኪራይ ዋጋ ይሆናል። ሰዎቹ ከነወለዱ ለምሳሌ 400ሺህ ብር የፈጀባቸውን ሱቅ እሱ በ900ሺህ ብር መልሶ ይገዛቸው ይሆናል። ምክንያቱም ካላተረፉ ስለማይሸጡት። እነሱም ሊሸጡለት ፈቃደኛ ከሆኑ ነው። ብድሩ ሳያልቅ ወይም እኔ እጨርስላቸዋለሁ ካላለ ስም አይዞርም። ስለዚህ እሱ ከነወለድ እና ትርፍ ለሰዎቹ እየከፈለ እነሱ ሌላ ማኅበር ይመሠርታሉ። ምክንያቱም ያኛውን ወለድ የሚከፍልላቸው የዋህ ሙስሊም አግኝተዋልና። አንዳንድ ሙስሊም ድርሻውን ሱቅ በሸጠበት ገንዘብ ምናልባት ከከተማው ዳርቻ "የጨረቃ ቤት" ይገዛና አዲስ ትግል ይጀምራል። ሰፈሩ ሞቅ እንዳለ ባንኮቹ ተከትለው ይመጡና ያፈናቅሉታል። ያፈናቀሉት ባንኮቹ ሳይሆን ለእስልምና ያለው እጅግ ደካማ ዕውቀት ነው። ከገጠር መጥቶ መርካቶ ገብቶ የነበረ የጉራጌ ብሔረሰብ ሙስሊም፤ ቤተል ወደሚባል ሰፈር ተሰደደ። ከቤተል ዓለም ባንክ፣ ከዓለም ባንክ ካራቆሬ፣ ከካራቆሬ ወለቴ፣ ከወለቴ ወደ ቀድሞ ትውልድ መንደሩ ወልቂጤ፣ ጉንችሬና አውድ ደርሷል። ምእመኑ ማንም ሒድ ሳይለው ወዶና ፈቅዶ ተፈናቅሏል። ወለድ ሲስተማዊ ሀብት መቀሚያ ዘዴ ነው። ከቤተሰቦቼ የትውልድ መንደር አውድ ገበሬ ማኅበር እና ከጉንችሬ የገጠር ከተማ እስከ አሜሪካ ዋይት ሀውስና ፌደራል ሪዘርቭ የተሰናሰለ የብዝበዛ ገመድ መሆኑ ይመስለኛል። ይህ በጉራጌ ማኅበረሰብ ምሳሌነት የሰጠሁት በአራቱም አቅጣጫ ተመሳሳይ ነው።

2.2. የኮንዶሚኒየም ወይም የመኖሪያ ቤቶች ዕድሎች

ኮንደሚኒየም ሲሠራ ብዙ ሙስሊም ወለድ አለው ብሎ አልተመዘገበም። የቻሉ ሙስሊሞች ሲያልቅ ጠቅልለው ገዝተዋል [ተጠቅልሎ ተከፈለም አልተከፈለም ሙስሊሙ "ወለድ" በሚለው መርህ ከሆነ ወለድ አለው]። ያልቻሉት ደግሞ

ለመከራየት ከኮንዶሚኒየም ኮንዶሚኒየም ይንከራተታሉ። መሀል ከተማ ሰፋ ያለ ባለሁለት መኝታ (2012 ኢ.አ. ላይ) ወርሀዊ ኪራዩ 7ሺህ ብር ከሆነ ለመንግሥት የሚከፈለው ወርሀዊ ክፍያ በእርግጠኝነት ከዚያ በታች ነው። ምናልባት 1,700 ብር ቢሆን ነው። እንግዲህ አስቡት "ወለድ በላ የሚባለው ሰው" ብር 1,700 በየወሩ ሲከፍል፤ የኮንዶሚኒየም ይዞታ የሌለው ሙስሊም ግን በየወሩ 7ሺህ (አድዐፈል ሙዷዐፉህ ~ የእጥፍ እጥፍ) በኪራይ ስም በሚከፍል ጊዜ ሀላል ይመስለዋል። ያ ባለ ይዞታ ግን በልጁ ስም ሌላ ኮንዶሚኒየም ይመዘገባል። በየእርከኑ እያየን ያለነው፤ ተያይዞ ማሽቆልቆል ነው። ሀራም ወይም (ሪባ) ሆኖ ቢሆን ኖሮ ሰው አቧራ ጠርጎ ቢተኛ ምንም አልነበር። ሆኖም ግን መብት ወይም መጠቀም ግዴታችን ሆኖ ሳለ በቃላት ተሸውዶ ወይም በርግጎ መተዉ አስፈላጊ አይደለም።

ይህ ነገር በውጭ ሀገራት የሚኖሩ ዜጎቻችንም ላይ ይስተዋላል። የዕውቀት ጊዜ እየተጣሉ የማይምነት ጊዜ መስማማት፤ ወይም በሚጠቅመን ነገር ተለያይተን በሚጎዳን ነገር ላይ ከጥግ እስከ ጥግ መስማማት የጤና አይደለም። በብዙ የአውሮፓና የአሜሪካ ግዛት የሚኖሩ ዜጎቻችን ጋር ባደረግሁት ውይይት፤ የቤት ይዞታ እንደ ሀገራችን ተመሳሳይ ግንዛቤ ነው ያለው። ከመንግሥት ወይም ሪልኢስቴቶች በረጅም ክፍያ የሚገዛው ቤት ከግለሰብ በኪራይ ሲሆን ይጨምራል። ምሳሌ በ 1,000 ዶላር ወርሀዊ ክፍያ በ10 ዓመት የራሳችን የሚሆን ይዞታ እያለ፤ ከግለሰብ ጭራሽ ጨምሮ በወር 1,200 ዶላር መከራየት ማለት ነው። ዋጋውም ቀንሶ ለራሱ የሚሆነው ቤት እምቢ ብሎ፤ በማንኛው ሰዓት ውጣ የሚባልበትን ቤት ዋጋ ጨምሮ ይከራያል። ያከራየው ግለሰብ ከየትም አያመጣውም። ከመንግሥት ወይም ከሪልኢስቴት ገዝቶት ነው። ሙስሊሙ ከነወለዱ ይከፍልለታል። እንዲህ ያለ ድንቁርና ነቢያት ለሚከተል ብርሃናማ አማኝ የሚመጥን አይደለም። የአላህ ነቢይ

ፍትሕን እንጂ በደልን አያስተምርም። ከሰዎች ላይ ችግርና ባርነትን ይቀርፋል እንጂ ወደ ባርነት አይሰድም።

መቶ በመቶ ብንከፍልም በፊያት መገበያያ ስለሆነ የምንከፍለው፤ ፊያት የፈጠረው ወለድ አለው። በየጊዜው የግሽበት ማስተካከያ (Inflation Adjustment) ካልተደረገ 100% ዛሬ ከፈልንም በ50 ዓመታት ከፍለንም ወለዱ ተቀራራቢ ነው። ወሬውን ላለማወሳሰብ "የግሽበት ማስተካከያ (inflation adjustments)" ትተናቸው ነው።

ይበልጥ ለመረዳት ዛሬ አንድ መቶ ሺህ ብር የተገመተ ቤት ዓመታዊ ወለዱ 12% ቢሆን ከሃያ ዓመታት በኋላ አጠቃላይ ዋጋው ሁለት መቶ ስድሳ አራት ሺህ ብር ይሆናል። ዓመታዊ ወለድና ግሽበት እኩል 12% ቢሆን ማለት ነው። ዛሬ ላይ 100,000 ብር ማለት ከሃያ ዓመታት በኋላ 264,000 ብር ጋር እኩል ነው እንደማለት ነው። በእኛ ሀገር የግሽበት አማካይ ፐርሰንት ማለትም 20% ብንሠራው የዛሬ መቶ ሺህ ብር ከሃያ ዓመት በኋላ 407,700 ብር እኩል ናቸው። (ስሌቱ ከፋይናንስ ውጭ ላለ ሰው እንዳያደናግር በጣም አቅልዬው ነው)። መቶ ሺህ ብር በሃያ ዓመታት ውስጥ 307,700 ብር ያህል ይወድቃል። አዲስ አበባ ውስጥ በ1997 የኢ.አ. 40 ሺህ ብር የነበረ ኮንዶሚኒየም፤ ዛሬ ላይ አንድ ነጥብ አምስት ሚሊዮን ብር ይሸጣል። ቤቱ በቁመት አላደገ፣ አልሰፋ፣ ልጅ አልወለደ። እንደውም እያረጀ ሄዶ ግን በማይታመን እጥፍ ይሸጣል። ይህ ማለት የፊያት መፈጥፈጥ ነው። በተደጋጋሚ እንደተነሳው በ1400 ዓመታት ውስጥ በወርቅና በሌላ ግብይት መካከል ግሽበት አይስተዋልም። እንዳንዴ ትንሽ ይነቃነቅና መልሶ ቦታው ይገባል። የግሽበት እና መዋዠቅ ርዕስ ላይ አንስተነዋል።

አሁን ላይ ባለውና ኢስላማዊ በሚሰኘው ባንክ ቢገዛ ያው የማዘግየት ወለድ አለው። እንደውም ይብሳል። የዚህኛው ችግር አንድ ሰው አንዴ ከተዋዋለ በኋላ በመሀል ብር አግኝቶ ልዝጋ ቢል ሙሉ ወለዱን (ትርፉን) ይከፍላል። ምክንያቱም ሽያጭ ተብሎ ስለሚመዘገብ፤ አንዴ ከተሸጠ ቅናሽ የለውም። ይህኛው ችግር የ"ኢስላማዊ ባንክ" ተግባራዊ ተፋልሶ ክፍል ላይ ቀርቧል።

2.3. ኢንቨስትመንት

የንግድ ባንኮች የብድር አቅርቦት ለምሳሌ በ30:70 (ratio) ስናይ፤ ኢንቨስተሩ 30% ካመጣ ባንኮች 70% ብድር ያቀርባሉ እንበል። ከባንክ የማይበደሩ መቶ ሰዎች የሚሠሩትን ሥራ፤ ተበዳሪዎች ለ30 ሆነው ይሠሩታል ማለት ነው። ወይም ቁጥሩን በትይዩ (parallel) ብንቀንሰው 10 የማይበደሩ ሰዎች አንድ ቦታ የሚሠበሰቡበትን ሥራ፤ 3 ተበዳሪዎች ባንክን 4ኛቸው አድርገው (ባንክ 7 ዕጅ አቅርቦ) ይሠራሉ። በአንጻራዊነት ሲታይ ደግሞ በሒሳብ አያያዝና ጥናት በኩል ባንኩ ስለሚያስገድዳቸው የሚበደሩት ከማይበደሩት በተሻለ ጽድት አድርገው ይሠራሉ። ምክንያቱም የባንክ ቅድመ ሁኔታ እና ቁጥጥር ከፍተኛ በመሆኑ የሪፖርት ጥራትና ወቅታዊነት ላይ ይጠነቀቃሉ። የሚከተለውን ሰንጠረዥ ብናይ 10 ተበዳሪና 10 የማይበደሩ ሰዎች የተወዳደሩበት ነው። በሰንጠረዥ ውስጥ ለአንድ ተመሳሳይ ድርጅት ተበዳሪዎቹ 3ቱ ብቻ ስለሚበቁ ሦስቱ ሰዎች አስር ከማይበደሩት ጋር ነው የሚወዳደሩት። የማይበደሩት ሙሉ በሙሉ ሲካተቱ ከተበዳሪዎች ውስጥ ግን ሰባቱ ሌላ ቦታ ከሌላ ባንክ ጋር ሌላ ሥራ ይሠራሉ። እያንዳንዳቸው ተበዳሪውም በአስር ሚሊዮን ብር (ሰባት ሚሊዮኑ ከባንክ ብድር)፤ የማይበደረውም በአስር ሚሊዮን ብር (ስለማይበደሩ ሁሉንም ገንዘብ ከኪስ) ያቋቋሚቸው ድርጅቶች በዓመት እያንዳንዳቸው ሀያ አምስት ሚሊዮን ብር ሽያጭ አከናወኑ እንበል። የግብአት ግዢ

ሀያ አንድ ሚሊዮን እናድርገው። ዓመታዊ ወለድ 16% እንበልና ለማሳጠር የሚከተለውን ሠንጠረዥ እንመልከት።

ዝርዝር	የማይበደር ድርጅት	የሚበደር ድርጅት	የተሻለ ነጥብ
ዓመታዊ ሽያጭ	25,000,000	25,000,000	እኩል
ዓመታዊ የግብዐት ግዢ	21,000,000	21,000,000	እኩል
ያልተጣራ ትርፍ (ከሽያጭ ሲቀነስ ዕቃ ግዢ)	4,000,000	4,000,000	እኩል
ሌሎች ወጪዎች	1,000,000	1,000,000	እኩል
ትርፍ ከወለድና ታክስ በፊት (ያልተጣራ ትርፍ ሲቀነስ ሌሎች ወጪዎች)	3,000,000	3,000,000	እኩል
ወለድ (7,000,000 X 16%)	-0-	1,120,000	የማይበደሩት ይሻላሉ
ትርፍ ከወለድ በኋላ	3,000,000	1,880,000	የማይበደሩት ይሻላሉ
ታክስ (30%)	900,000	564,000	ተበዳሪዎች ያነሰ ታክስ ይከፍላሉ
የተጣራ ትርፍ	2,100,000	1,316,000	የማይበደሩት ትርፋቸው ብዙ ነው
የባለ አክሲዮኖች ብዛት	10	3	የተበዳሪ ተካፋዮች በቁጥር ያንሳሉ
የአንድ ሰው የትርፍ ድርሻ	210,000	438,667	ተበዳሪዎች ከእጥፍ በላይ ያገኛሉ
የዲቪደንድ ታክስ (10% ተቀናሽ)	21,000	43,867	የማይበደሩት ያነሰ ዲቪደንድ ታክስ ይከፍላሉ
የመጨረሻ የአንድ ሰው የተጣራ ድርሻ	189,000	394,800	ተበዳሪዎች ከእጥፍ በላይ ያገኛሉ
10ለ10 ሰዎች ብናወዳድር የተጣራ ድርሻ	1,890,000	3,948,000	የሚበደሩት ከእጥፍ በላይ ያገኛሉ

በድጋሚ ለማስታወስ ሰንጠረዙ ውስጥ ያወዳደርነው 3 ተበዳሪዎች 10 ከማይበደሩ ሰዎች ጋር ነው። የቀሩ የ7 ተበዳሪዎች ሥራ ባንክ ሸፍኖላቸዋል። ስለዚህ ቀሪ ሰባቶቹ ሌላ ቦታ ለሦስት ለሦስት እየሆኑ ከሌላ ባንክ ጋር ስለሚሠሩ በተመሳሳይ ስሌት ይዘው ይመጣሉ። ወደ ሰንጠረዙ ተመለሱና "የመጨረሻ የተጣራ ድርሻ" የሚለውን ተመልከቱት። 10 የማይበደሩ ሰዎች እያንዳንዳቸው ብር 189,000 በድምሩ 1,890,000 ያገኛሉ። እዚህ ያወዳደርነው አስር የማይበደሩ ሦስት ከሚበደሩት ጋር ነው። ሆኖም ግን አስር የማይበደሩት አስር ከሚበደሩት ጋር ማወዳደር ስላለብን ተበዳሪዎቹ እያንዳንዳቸው 394,800 ብር ከደረሳቸው የአስሩ ተበዳሪዎች ድምር 3,948,000 ይሆናል ማለት ነው። ተበዳሪዎች ከእጥፍ በላይ ሀብት ያከማቻሉ ማለት ነው። ስለዚህ ከአጠቃላይ ትርፍና ሀገራዊ ምርታማነት ጋር ሲታይ የሚበደሩት ከሦስት እጥፍ በላይ ሥራ ይፈጥራሉ ተብሎ ይታሰባል።

"ሞጅሊያኒ እና ሚለር" የተሰኙ የፋይናንስ ተመራማሪዎች በተለያዩ በመጽሐፎቻቸው ላይ"[55],[56] "በአንድ ሀገር ውስጥ ታክስ ካለ እና የሚያበድራችሁ ካገኛችሁ መቶ ፐርሰንት ተበደሩ ይላሉ። በእነርሱ አባባል የላይኛውን ምሳሌ ብንጠቀምና ሁሉንም ማለትም አስር ሚሊዮኑ ብር ባንክ አዋጥቶ 16% ወለድ ቢሰበስብ የሚያስፈልገው ተበዳሪ አንድ ሰው ነው። ተበዳሪው ባዶ ኪሱ ሆኖ ወይም የሆነ ነገር አስይዞ ከተበደረው አስር ሚሊዮን ብር ለባንክ 1,600,000 ብር ሲከፍል መጨረሻ ላይ 980,000 ብር የተጣራ ትርፍ ያገኛል። አንድ ሰው አክሲዮን ማቋቋም ስለማይችል ዲቪደንድ ታክስ የለበትም። የማይበደሩት 189,000 ብር ላይ እንደቆሙ

[55]Modigliani, F. Miller (1958), "The Cost of Capital, Corporation Finance and the Theory of Investment", American Economic Review.48(3).
[56] Modigliani, F. Miller (1963), "Corporate Income Taxes and the Cost of Capital: a correction", American Economics Review, 53(3).

ይቀራሉ ማለት ነው። 10 የማይበደሩ ሰዎች 1,980,000 ብር ሀብት ሲኖራቸው በዚህ መላምት መሠረት 10 ተበዳሪዎች 9,800,000 ብር ሀብት ይኖራቸዋል ነው። ሲስተሙ እንዴት ወለላ ማር እንደሆነ ልብ ማለት ነው። ይህማ እንዴት ይሆናል ልትሉ ትችላላችሁ። ባንክ ከኛ ይበደርና ኢንቨስት አድርጎ ለኛ 5% ወለድ ይከፍለናል። 10,000,000 ብር ስናበድረው ሌሎች ውስብስቦችን እንተውና 500,000 ብር ወጪ ነው ያለበት። ነገር ግን ባንክ ከኛ ከተራ የቁጠባ አስቀማጮች ላይ አስር ሚሊዮን ብር አስቀምጠንና ባንኩ ለሌላ ሰው አበድሮት ምንም አላተረፈበትም ቢባል 1,600,000 ብር ያተርፍበታል። ከወለድ ነጻ ብሎ ሙስሊሙን ሲያሞኝ ግን ምንም ወጭ የለበትም።


ሞጂሊያኒና ሚለር ማሳሰቢያ አላቸው። (ከመ-ገንዘብ መጽሐፍ የተቀነጨበ)

ሞዴላቸው ላይ አራት ዓይነት አካሄድ አለው። ታክስ ሲኖርና ሳይኖር ብለው ይከፍሉታል። ታክስ የሌለበት የኢኮኖሚ ሥርዓት እየኖርን አይደለም። እኛ ባለንበት አውድ ታክስ ግዴታ በመሆኑ እርሱኛውን ሞዴል ነው የወሰድነው። ይህም ከመሆኑ ጋር ማሳሰቢያቸው ይሠራል። አንድ ሰው ለመበደር ከባለቤትና ከባለአክሲዮን ኪስ መጠቀም ያለበትን ሁሉንም አማራጮችን ተጠቅሞ "የተማከለ ቦታ" ላይ መሆን አለበት። ማለትም ሁሉም ነገር ልክ አለው። ብድር አገኘን ብለን የምንገባበት አጣን ብለንም የምንተወው አይደለም። ሁለቱም ዋጋዎች አሉዋቸው። **<u>ብድር ላይ ከዋጋዎች ሁሉ ትልቁ ዋጋ የተበዳሪው ጤንነት ነው።</u>** ይህንን አስምሩበት። ብድር አለብኝ ብሎ ማሰብ፤ ጤና ላይ ከፍተኛ ጫና ያመጣል። ከመበደር የሚገኘው ዋጋ እና የሚጣው ጤንነት ብሎ ማሰብ አስፈላጊ ነው። በተቃራኒው ገንዘብ በማጣት የሚመጣ ጭንቀትም አለ። ገንዘብ ማጣት አየር ከማጣት ጋር ይመሳሰሉብኛል። ኪሴ ውስጥ ገንዘብ ሲመናመን ጸጉሬን ተከርክሜው ወጥቼም የተንጨባረረ፣ አዲሱ ጫማዬ

የተንሻፈፈ፣ አዲሱ ሽሚዜ ኮሌታው ወይ የተቀደደ ወይ የተገለበጠ ወይ የመከየተ (ማኪያቶ የመሰለ) ይመስለኛል። ችግር ከሚያሯሩጠኝ አበዳሪ ቢያሯሩጠኝ እመርጣለሁ። ለነገሩ ብድር ሲኖርብኝ ከብርሃን ይልቅ ጭለማ ውብ ሆኖ ይታየኛል። ሲመሸና ሲጨላልም ደግሞ ደስ ይለኛል። ሲነጋ ምንም ያላጠፋ ፀሐይ ጋር ቅይም እጀምራለሁ። የብድር ሸክሜን አንስቼ እሸከማለሁ። ሰው ሳይፈልግ እንዳይበዳደር እመኛለሁ። እመክራለሁ። በሁለቱም አቅጣጫ ዘወትር እየለካንና እያጠናን የተማከለው ላይ ጤናማ ሥራ እና ጤናማ ሕይወት መምራት አለብን።

ግራፉ ላይ እንደምናየው፡-

- ከ “0” ወደ ላይ ያለው ቀስት የድርጅት ዕድገት ሲያመለክት፤ ወደ ጎን ደግሞ ብድርን ያመለክታል።
- 1 ቁጥር ላይ አግድም መስመር ከባንክ ሳንበደር የምናካሂደው እንቅስቃሴ ነው።
- 2 ቁጥር ባለን ካፒታ ላይ የባንክ ብድር ብንጨምር የድርጅታችን ዕድገት ሳንበደር ከነበረው ጋር ያለውን ከፍታ ያመለክታል።
- 3 ቁጥር ደግሞ ወለድን ከታክስ ጋር ማጣፋት የምናገኘውን የመበደር ጥቅም ምክንያት ብድራችን ሲለጠጥ



- 4 ቁጥር ምንም ባለመበደር እና ብዙ በመበደር መሀል የምናተርፈው ገንዘባዊ ትርፍ ነው።
- 5 ቁጥር በወጉ መበደር ያለብን እና ብዙ በመበደር ባመጣነው መካከል የሚገኝ የጤና መታወክ ወይም የአዕምሮ ጭንቀት ዋጋ ነው። የዚህ ግራፍ ወሳኙ ነጥብ 5 ቁጥርን ነው። ሞጂሊያኒና ሚለር ይህንን "The cost of financial distress" ወይም የፋይናንስ ጭንቀት እንደማለት ነው። ጭንቀቱ ተዘዋዋሪ ሲሆን በቀጥታው ሲተረጎም በብድር የተጨናነቀ ድርጅት ላይ ደንበኛም ይሁን ዕቃ

አቅራቢ ወይም ብድር ሰጪዎች እምነት ሰለሚያጡ እንቅስቃሴን ያቀዛቅዝና የድርጅቱ መደበኛ ሥራው ለባንኮች ወለድና ብድር መክፈል ይሆናል። ወደ መክሰር ይሄዳል።

በመሆኑም ብድር ከነጠብጣቡ ወይም ከተቀለመው ክፍል ሳይወጣ መንቀሳቀስ ያስፈልጋል። ነጠብጣቡ ማለት የጤናማና ጤናማ ያልሆነ የካፒታል መዋቅር አካፋይ ነው። ብድራችንን ከ “0” እስከ ነጠብጣቡ ድረስ መሆን አለበት። ከዚያ ካለፈ የጭንቀት መጠናችን እየጨመረ ይመጣል። ወደ “0” ም እየተጠጋን በሄድን ቁጥር ያለ ሥራ መቀመጥና ድርጅት ወደ መዝጋት ያደርሰናል። ይህ እንግዲህ የኢኮኖሚ ቲዎሪ ቅምሻ ያህል ነው። አጥኚዎቹ በ1985 (ሞጂሊያኒ) እና በ1990 (ሚለር) የኖቤል ሽልማት ያገኙ ኢኮኖሚስት ናቸው። አለመበደርና በኪስ ገንዘብ ብቻ ጤናማ ኑሮ መኖር የሚያስችሉ ሞዴሎች አሏቸው። ሆኖም ግን አሁን ያለው የካፒታሊስት የኢኮኖሚ መዋቅር አይፈቅድም። እዚህ ጋር ብናመጣቸው አንባቢን ማደናገር ስለሚሆን በቀጣይ ሥራዎች ይዳሰሳሉ ወይም ሌላ ጸሐፊ ለእኛ ሀገር አጣጥሞ ያካትታቸው ይሆናል።

اللَّهُمَّ صَلِّ عَلَىٰ سَيِّدِنَا مُحَمَّدٍ وَعَلَىٰ آلِهِ وَصَحْبِهِ وَسَلِّمْ

2.4. የገንዘብ ኖት ሕትመትና የዜጎች የጋራ በጀት መሆኑ

ሀ. በዘፈቀደ አይታተምም

የገንዘብ ኖቶች ደረሰኝ እንደሚታተመው በጨረታ ይታተማሉ። የማተሚያ ማሽን ያላቸው ማተሚያ ቤቶች መጽሐፍ፣ ቴምብር፣ ጋዜጣ፣ ወዘተ እንደሚያትሙ ያትሙታል። የገንዘብ ኖት ከሌሎች የሕትመት ውጤቶች ለየት የሚያደርገው ሕትመቱ በማንኛውም የቢሮ ማሽን ወይም ማተሚያ ቤት አለመታተሙ ብቻ ነው። ልክ ነጋዴዎች ደረሰኝ ሳያስፈቅዱ እንደማያሳትሙት፤ የገንዘብ ማተሚያ ማሽንና መሰል ግብዓቶችም ከፈቃድ ውጭ መትከልም ይሁን ማንቀሳቀስ አይቻልም። በአጭሩ የገንዘብ ኖቶች ለማተም ሳያስፈቅዱ ማሽን አይተከልም። ካልተፈቀደለት የማተሚያ ማሽን አምራች መግዛት አይቻልም። ተደርጎ ቢገኝ ቅጣቱ ከባድ ነው። የዓለምን የፋይናንስ ሥርዓት የተቆጣጠሩ ወገኖች (ሲኾሮች) ለንግድ ዓላማ የሚሰራጩ ፕሪንተሮችና የፎቶ ኮፒ ማሽኖች የገንዘብ ኖቶችን እንዳያትሙ ዕቃ ወይም ዓይነት (Features) እንዲጎሉዋቸው ይደረጉ ነበር።

ያን ያህል ከባድ አይደለም። የየሀገራቱ መንግሥታት ንግድና ኢንደስትሪ ሚኒስቴሮች ይቆጣጠሩታል። ለአሜሪካ ወይም ምዕራባውያን ብለው ሳይሆን ለራሳቸው ብለው ይቆጣጠራሉ። የሚታተመው ገንዘብ ብቻ ሳይሆን ፓስፖርት፣ ቴምብር፣ ቼክ፣ ሰርተፊኬት፣ ዲፕሎማ፣ ሎተሪና መንግሥት ብቻ ሊይዛቸው የሚችሉ የሕትመት ውጤቶች እንዳይታተሙ ቁጥጥር ያደርጋሉ። አስመስሎ መሥራት የመንግሥትን አሠራርና ቁጥጥር ስለሚያደናቅፍ መንግሥት ማተሚያ ድርጅቶችን ይቆጣጠራል። የማተሚያ ማሽን የሚፈበርኩ ሀገራት ለንግድ የሚሰራጩ ፕሪንተሮችና መሰል ማሽኖች ይለዩዋቸዋል። የጦር መሣሪያ እንደመቆጣጠር ነው። ከሕትመት ዓይነቶች ወይም ዲዛይኖች ውስጥ የሆነ ነገር፤ ለምሳሌ ቀለበት መሳይ፣

ሸንተረር፣ አንጸባራቂና ተሰዋሪ ዲዛይን ለገንዘብ ኖቶች ብቻ ይተው ነበር። (አሁንማ ማን ይተዋል? ከተባለ ማንም)። የገንዘብ መቁጠሪያ ማሽንም የሚሠራው በዚያ ስታንዳርድ ነው። አንዱ መለያ “የፍሎረሰንስ ደረጃ” ይባላል። የማንጸባረቅ ወይም ማብረቅረቅ ደረጃ ነው። ጨረር በመልቀቅ ይለያል። ይህም ሰው ሠራሽ በመሆኑ በሌሎች ባልተፈቀደላቸው ሰዎች የመሠራት ዕድሉ እጅግ ከፍተኛ ነው። (ከሙያዬ ራቅ ስለሚል እዚሁ ልግታው)።

የፎቶ ኤዲት ማድረጊያ ሶፍትዌሮች ፕሮግራም ሲደረጉ የገንዘብ ኖቶችን ዲዛይን እንዳይሠሩ ይደረጋሉ። ኤዴት ማድረግ እንዲችሉ አይሠሩም ማለት ሳይሆን ከተገኘ ቅጣቱ ከፍ ለሚል ነው። አሠራሩ ሥርዓተ ትምህርት ውስጥ አይካተትም። የገንዘብ ኖቶች ልዩ ምትሓት ያላቸው መስሎን እናድጋለን። ውስጡ የተጋደመው ወርቅማ መስመርን፤ ወርቅ የሚመስለው ሰው ይኖራል። ወረቀቱም ከልዩ እንስሳ ቆዳ ለፍቶ የተሠራ ይመስላል። ከጥጥና ናይለን የሚሠራ ወረቀት መሆኑን የሚያውቁት እዚያው ሕትመት አካባቢ ያሉ ሰዎች ቢሆኑ ነው። ከምን እና እንዴት እንደሚታተም ሳናውቅ አድገን እናረጃለን። ይህ የፈጠረው የትምሕርት ካሪኩለሙ ውስጥ በጥልቀት ባለመኖሩ ነው። በእርግጥ የኮምፒውተር ኢንጂነሮች መሥራት ይችላሉ። ለምሳሌ የAdobe Photoshop ፕሮግራም የገንዘብ ኖትና መሰል ነገሮች ዲዛይን ማድረጊያ ነበረው። ሆኖም ግን ብዙ ሳይቆይ መሥሪያው እንዲወጣ ተደርጓል። የገንዘብ ኖትን ዲዛይን ስንጠይቀው እንደማይቻል ማስጠንቀቂያ ያመጣል። ስለዚህ ሁለቱን ማለትም ፕሪንተር እና ዲዛይን ማድረጊያ ሶፍትዌር ያበጀ ሰው የገንዘብ ኖቶችን ማምረት ይችላል። በመጨረሻም ብዙ ሰው የገንዘብ ኖት ማተም ይጀምርና ፊያት መገበያያ ሙሉ ለሙሉ ይወገዳል ማለት ነው። የፊያትን ሲስተም ከሚያፈርሱ ነገሮች ሁለቱ ሊጠቀሱ ይችላሉ። ምን ማለት ነው? ጠንቋይ ለራሱ አያውቅም ይባላል።

ጠንቋይ ለራሱ ቢያውቅ ኖሮ ሁሉም ሰው ጠንቋይ ይሆንና ጠንቋይ ይጠፋ ነበር እንደማለት። ሲብራራ ጠንቋይ ለራሱ ቢያውቅ ኖሮ ለሌላ መጠንቆል ሁላ ሳያስፈልገው ያሻውን ነገር በምትሃት እያመጣ መኖር ስለሚችል ሰው ሁሉ በጥንቁልና ይወዳደር ነበር። ሰው ለራሱ ካወቀ ለምን ይለፋል? የምንለፋው ስለሚሆነው ነገር ስለማናውቅም አይደል?

የገንዘብ ኖቶችም ሁሉም ቢያትም ኖሮ ይጠፉ ነበር። አውሮፓውያን የሙስሊም ዑስማኒያ (አቶማን) ኢምፓየርን የጣሉት፤ በቅኝ ከያዙዋቸው አፍሪካና የላቲን አሜሪካ ባመጡት ወርቅና ብር የኡስማኒያ ግዛት ላይ ግሽበት (ማዋዠቅ) በመፍጠር ነበር። ይህኛው "ተገዢ" ግን ወረቀት እንኳ ሠርቶ ማጋሸብ አቃተው። ምክንያቱም የገንዘብ ኖቶች በኮሎኒያሊዝም ድንበር የተገደቡ ሆኑ። ድንበሮቹ ሉዓላዊ ግዛት ወይም ሀገር ፈጠሩ። ሀገራቱ በውስጣቸው ማዕከላዊ/ብሔራዊ ባንኮችን አቋቋሙ። ብሔራዊ ባንኮቹ ገንዘብና መገበያያን እየተቆጣጠሩ ለበላይ አካላት ማለትም ለዓለም አቀፉ የገንዘብ ተቋማት ሪፖርት ያደርጋሉ። ስለዚህ ንግድ ባንኮች ማለት የገንዘብ ሥርዓት መቆጣጠሪያ የወረዳ ጽሕፈት ቤት የመሰሉ ነገሮች ናቸው። በዶላር ኢምፓየር አወቃቀር የኢትዮጵያ ጠቅላይ ሚኒስትር ማለት ከቀበሌ ሊቀመንበር ብዙም ላይለይ ይችላል። ትንሽ ውልፍት ካለ ይገለብጡታል። ሌላው ችግር ደግሞ የሀብታሙ ሁላ ሀብት የተቀመጠው በዶላር ስለሆነ ለራሳቸው ሲሉ ይጠብቃሉ። ደሃ እንደሆን ቢጮኽም አያሰማ። የፈያት ሲስተም ሳይመታ የዲጂታል ሲስተም መጣ። ይህኛው የባሰ አሳሪ ነው። መቀናቀን የሚቻለው በቴክኖሎጂ በመብለጥ ነው። በየትኛውም ሲስተም አዋጪው እሴት (ንብረት) እና ብረት (ጦር) መያዝ ነው።

ለ. የኢትዮጵያ ብር ሕትመት አጭር ታሪክ

እስከ 1914 ዕቃን በዕቃ እንዲሁም ወርቅ፣ ብር፣ የማሪያ ቴሬዛ ጠገራ ብር፣ አሞሌ ጨው የኦቶማን ሊራ፣ ወዘተ ጥቅም ላይ ሲውል ነበር። በተለይ በ1914 የምኒሊክ ሳንቲም ሲታተም የኦስትሪያው ማሪያ ቴሬዛ ከጥቅም ውጭ እየሆነ ወይም አገልግሎቱ እየቀነሰ መጣ። ሁለተኛ ሕትመት በ1931 ተከናወነ። (ከ1944ቱ ከብሬቶን ስምምነት ማግሥት) የቀዳማዊ አጼ ኃይለ ሥላሴ ምስል ያለበት የወረቀት ኖት በ1945 በአሜሪካ ፊላዴልፊያ ሲታተም ለዋስትና 75 በመቶው (999 ንጹሕ ወርቅ) እና 25 በመቶው ከኢትዮጵያ ግምጃ ቤት ይሸፈን ነበር።የኢትዮጵያ ሕዝብ የወረቀቱን ገንዘብ (ቢል) ሲላመደው መንግሥት ለዋስትና የሚያስቀምጠው ወርቅ ወደ 30 በመቶ ወረደ። ሕዝቡ ሙሉ ለሙሉ ሲቀበለው ወርቅን ለሕትመት ሳይሆን ለዓለም አቀፍ ኢንሹራንስ ይከፈል ጀመር። በማሪያ ቴሬዛ እና ሌሎች መገበያያዎች የሚካሄዱ ግብይቶች ተቋረጡ[57]። (በእኛ እድሜ ወይም አንድ ወደላይ የማሪያ ቴሬዛ ጠገራ ብር ይዞ መገኘት ያስቀጣ እንደነበር ሳንሰማ አይቀርም)። በውጭ ሀገራት እንደማንኛውም ሸቀጥ በጨረታ ይታተም የነበረውን እዚሁ ለማተም ብሔራዊ ባንክ በዲሴምበር 2/2014 በኢትዮጵያን ሔራልድ ባስነገረው ዓለም አቀፍ ጨረታ መሠረት ወረቀቶቹ እዚሁ እንዲታተሙ ተወዳደሩ ተብሎ ነበር። የእኛ ብር በውጭ ሀገራት ሲታተም ቆይቷል።

አዳዲስ ኖት እንደሚታተመው አሮጌው ተሰብስቦ ይቃጠላል። ዝውውር ላይ ከሚፈለገው በላይ ሲኖርም ተሰብስቦ መጋዘን ሊገባ ባስ ሲልም ሊቃጠል ይችላል። እጃችን ላይ ያለው ገንዘብ እላዩ ላይ የተጻፈው ቁጥር ለምሳሌ አንድ ብር እንዳለ ሆኖ

[57]Arlando Mauri (2010), “The Short Life of th Bank of Ethiopia”, University of Milano, Pages 104-114

በአንድ ሌሊት 90 ሳንቲም ሆኖ ሊያድር ይችላል። የአዳዲስ ገንዘብ ሕትመት ነባር ገንዘቦችን ዋጋቸውን ይቀንሳቸዋል። ወይም ሙሉ ለሙሉ ያጠፋቸዋል። አልያም ይቀይራቸውና የቀደምቶቹ ከአገልግሎት ውጭ ሆነው ብሔራዊ ባንክ ሰብስቦ ያቃጥላቸዋል። ትናንትና በ50 ሳንቲም ስንገዛው የነበረው እቃ ዛሬ 65 ሳንቲም ሆነ እንደማለት ነው። ስለዚህ ኪሳችን ውስጥ ያለው የፊያት ገንዘብ የአምናውን ዋጋ ይዞ የመቆየት ዋስትና የለውም። ያረጁት ገንዘቦች ምንም ውስጣዊ ዋጋ (intrinsic value / inherent value) ስለሌላቸው ብሔራዊ ባንክ እየሰበሰበ በማቃጠል ያስወግዳቸዋል። ሰው ሰራሽ ገንዘብ መሆኑን እያወቅን፣ ማተሚያ በጀቱም የጋራ በጀት ሆኖ፤ እየዋለ እያደረ የሚጋሽብ ገንዘብ ላይ "ወለድ አለው" ብለን ከሥራ ውጭ መቀመጥ አግባብ እንዳልሆነ ደራሲው ያስገነዝባል።

የገንዘብ ኖቶች ቀለማቸው እየተቀያየረ ይታተማል። እንደ ኢት.አ. ከመስከረም 6 እስከ ታሕሳስ 6/2013 ማለትም በሦስት ወራት ውስጥ የተቀየረው የኢትዮጵያ የብር ኖት፤ ለአንድ ቅጠል 1 ብር ከ28 ሳንቲም ወጭ ተደርጓል ማለት ነው። 100 ብር ለማተም 1 ብር ከ28 ሳንቲም ሲወጣ መንግሥት 98 ብር ከ72 ሳንቲም ያተርፋል ይመስላል፤ ወይም በ100 ብር የገነባኸውን በ1 ብር ከ28 ሳንቲም ይገዛሃል ማለት ነው።

ቀድሞ አረንጓዴ የነበረው 100 ብር ወደ ውኃ ሰማያዊ ቀለም ተለውጦ የመቶ ብሩን ቀለም ለአስር ብር ተሰጥቶታል። የዚህ መጽሐፍ ጸሐፊ ገንዘቡ የተቀየረ ሰሞን አዲስ አበባ ለገሃር የትራፊክ መብራት ጋር 2 ባለ 10 ብር አዲሱን ኖት ለችግረኛ ሲሰጥ ችግረኛው ገንዘቡን ይዞ በደስታ ተፈተለከ። ምናልባት 200 ብር መስሎት ይሆናል። የ200 ብር ምግብ በልቶ 20 ብር ሲከፍል ችግር ሊፈጠር ይችል ይሆናል። በዚያው ዓመት ገንዘብ የተለወጠ ሰሞን አገር ቤት ለበዓል የገቡ ሰዎች የ17,000 ብር

በሬ በ1,700 ብር ገዝተው ተመልሰዋል። በሬ ሻጩ ወይ ገንዘብ መቀየሩን አልሰማም፤ ወይ ኖቶቹ ምን እንደሚመስሉ አላወቀም። ምክንያቱም 100 ብር ተቀይሮ 10 ብር መስሎ ይመጣል ብሎ አይጠረጥርም።

2013 ኢ.ኦ. የታተሙ ኖቶች

- ✓ ብዛት 2 ነጥብ 9 ቢሊዮን ቅጠል ኖት
- ✓ የያዙት ዋጋ መጠን 262 ቢሊዮን ብር
- ✓ ለሕትመት የፈጀው ገንዘብ 3 ነጥብ 7 ቢሊዮን ብር ነበር።

የአሜሪካ ዶላርም ልክ እንደኛው በማሽን ነው የሚታተመው። ወደኋላ ሄደን እ.ኤ.አ. 2016 ላይ መረጃ ብንጠቅስ 209 ቢሊዮን ዶላር ለማተም 761 ሚሊዮን ዶላር ከሕዝብ ካዝና ወጪ ተደርጓል። መቶ ዶላር ለማተም የዶላር 15.2 ሳንቲም (0.155) አስፈለገ ማለት ነው። በሌላ አነጋገር በወቅቱ በእኛ በ27 ብር ብንመነዝረው ብር 2,700 ለማግኘት ወጪው ብር 4.19 ማለት ነው። ምንም ሳይሠሩ የተጣራ ብር 2,695.81 ያገኛሉ። ይህንን ስንል በኢኮኖሚክስ ቋንቋ "ሴትሪስ ፓሪበስ" ማለትም "Other things remained constant, ሌሎች ነገሮች ባሉበት ትተን" ነው። የየሀገራቱ ማዕከላዊ ባንኮች የሚያትሟቸው ገንዘቦች የሀገሪቱ ብሔራዊ ገንዘቦች በመሆናቸው "ገንዘብነታቸው" የጋራ ነው። የሁሉም ዜጎች ታክሶች አሉባቸው።

አንዴ ታትሞ የሚያበቃ አይደለም። 262 ቢሊዮን ብሩ ከሁለት የግል ባንኮች ሀብት አይዘልም። የሚታተመው ለባንኮች መስኮቶች አገልግሎትና ለATM ክፍያ ቢውል ነው። ገንዘቦች በብሔራዊ ባንኮችና በንግድ ባንኮች መሀል ይጫወታሉ። በዚህ መጽሐፍም ሁለቱ ትኩረት ተሰጥቶባቸዋል።

ሐ. የአሜሪካን ዶላር ሕትመት ዋጋ (ለማነጻጸሪያ)

የአሜሪካ ዶላር የዓለም መገበያያ ከሆነ 70 ዓመታት አልፎታል። እያተሙ ለዓለም ያከፈፍላሉ። ልዩ ምትሃት ያው የሚመስለው ዶላር ከሌላው ሀገር ኖት የተለየ ንጥረ ነገር የለውም። እንደማንኛውም ሰነድ በማሽን ይታተማሉ። የሕትመት ዋጋቸውን ለማየት የ2017 የዶላር ሕትመት መረጃ እንመልከት።

ጠቅላላ የታተመው በዋጋ፡- 209 ቢሊዮን ዶላር

የቅጠሎች ብዛት፡- 7.1 ቢሊዮን ቅጠሎች

የኖቶቹ ዓይነት (ባለ)	የቅጠሎች ብዛት	የሚይዙት የዶላር ዋጋ	አንዱን ቅጠል ማተሚያ	ጠቅላላ የሕትመት ዋጋ
1	2,425,600,000	2,425,600,000	5.4 ሳንቲም	130,982,400
2	0	0	5.4 ሳንቲም	
5	915,200,000	4,576,000,000	11.5 ሳንቲም	105,248,000
10	262,400,000	2,624,000,000	10.9 ሳንቲም	28,601,600
20	1,715,200,000	34,304,000,000	12.2 ሳንቲም	209,254,400
50	268,800,000	13,440,000,000	19.4 ሳንቲም	52,147,200
100	1,516,800,000	151,680,000,000	15.5 ሳንቲም	235,104,000
ድምር በዶላር	**7,104,000,000**	**209,049,000,000**		**761,337,600**

ምንጭ፡- የአሜሪካ የፌደራል ሪዘርቭ ሲስተም የገዥዎች ቦርድ የ2017 የገንዘብ ሕትመት በጀት፣ ጁን 2016 ላይ እንዲጸድቅ የቀረበ

2.5. ከገንዘብ ተቋማት ውጭ መበዳደር አለመቻሉ

ማንኛውም ድርጅት ገንዘብ መበደር የሚችለው ከገንዘብ ተቋማት ብቻ ነው። ገቢዎችና ጉምሩክ የድርጅቶችን ገቢዎችና ወጪዎች ሕጋዊነት ኦዲት በሚያደርግ ወቅት "ከሽያጭ ውጭ የገባ ገቢ" በቂ ማስረጃ ካልቀረበለት "ያልተገለጸ ሽያጭ" ይሆናል በሚል ታክስና ግብር ይጠይቅበታል። አንድ የድርጅት አባል ወይም ባለቤት ከኪሱ ወደ ድርጅቱ ገንዘብ ፈሰስ ቢያደርግ የገቢው ምንጭ በጥርጣሬ ይታያል። ይህ ግለሰብ ያፈሰሰው አዲስ ገንዘብ (Cash injection)፤ የሆነ የግል ንብረት ሽጦ ሊሆን ይችላል። ገቢዎችና ጉምሩክ ግን ሕጋዊ ሰነድ ካልቀረበ የሚያውቅበት መስመር አይኖረውም። ምክንያቱም ባለሥልጣኑ ኦዲት የሚያደርገው ሰነድን ተከትሎ ስለሆነ ነው። ስለዚህ ግለሰቡ በፈቃድና ያለፈቃድ አዳቅሎ የሚያንቀሳቅሳቸው ሥራዎች ይኖራሉ ወይም ደግሞ ደረሰኝ በትክክል እየቆረጠ አይደለም ተብሎ ስለሚታሰብ በተጨማሪው ገንዘብ ላይ ግብር ከነወለድና ቅጣት የመክፈል ግዴታ ይኖርበታል። ዘመድ ወይም ጓደኛ አበድሮት ሊሆን ይችላል። አሁንም ባለሥልጣኑ የሚያረጋግጥበት ክፍተት አይኖርም። እነዚያ አበዳሪዎች ዘመዱም ይሁኑ ጓደኞች፤ ያበደሩት ብድር በአራጣ ሊሆን ይችላል የሚል ጥያቄ ያስነሳል። ብድሮች ግልጽ የሚሆኑት መንግሥት ከፈቀደላቸው የገንዘብ ተቋማት መሆን ይጠበቅባቸዋል። ሙስሊሙ ከገንዘብ ተቋማት ስለማይበደር በእንዲህ ያሉ ገቢዎች ብዙ ዋጋ ከፍሏል።

እራሳችን ለገዛ ድርጅታችን እንኳ ማበደር የማንችል ከሆነ ዕጣ ፈንታችን ምንድን ነው? የተገደደ ሰው ምን ማድረግ ይጠበቅበታል? እስከመቼስ ተገዶ ይኖራል?

2.6. ከገንዘብ ተቋማት ውጭ መንቀሳቀስና ማከማቸት አለመቻሉ

ዜጎች በፊያት ብቻ መገበያየት፣ ክፍያና ብድር በባንክ ብቻ እንደሆነ በሕግ ተገደዋል። ብሔራዊ ባንክ ዜጎቹን ሳያማክር ያትማል። በማንኛውም ወቅት ኖቱን ሊቀይርና በጊዜ ገደብ ያልቀየረ ሰው የያዘው ፊያት ሊመክንበት ይችላል። ፊያት እጁ ላይ በመያዙ ወይም ባንክ በማጠራቀሙ ብቻ ይከስራል። በተቃራኒው ንብረት መያዝ ደግሞ "በአከማችነት" ያስከስሳል። ሁሉም ገቢ ወደ ባንክ፣ ሁሉም ወጪ ደግሞ ከባንክ ስለሚሆን በዕጅ ገንዘብ ይዞ መዟዟር፣ ከሽብርተኝነት ጋር ይያያዛል ተብሎ ስለሚታሰብ እቤት ማስቀመጥ እንኳ ላይቻል ነው። የተሻሉ የሚባሉ የሌላ ሀገራት ጠንካራ ፊያቶችን ማለትም የአሜሪካ ዶላር ወይም የእንግሊዝ ፓውንድ ተጠቅሞ ማከማቸትም ወንጀል ነው። በመሆኑም የሲስተሙ ታዛዥ በመሆኑ ብቻ ኪሳራ ይሸከማል። ይህን ኪሳራ ማከም የሚቻለው ያለውን ሲስተም በመጠቀም እንደሆነ የዚህ መጽሐፍ አዘጋጅ ያምናል።

"መገደድ" ብቻውን የባንክ አራጣን ብይን ይቀይረዋል። አንድ ሰው በመንግሥት ወይም በሆነ አካል ከተገደደ ሌሎች ግዴታዎች ይቀንሱለታል። አስገዳጅነት በወርቅና ብር ማዕድናት ላይ እንኳ ቢመጣ የአራጣ ሕግ ይቀየራል። ተገዳጅ "መጅቡር" ከግዴታው ነጻ ለመውጣት ብዙ መፍትሔዎችን ሊጠቀም ይፈቀድለታል። የምዕራባዊያን መንግሥታት ሲስተሞችና ባንኮች ያስገደዱት ሰው መውጫ መንገድ ይበጅለታል እንጂ ባርነቱን እንዲቀጥል ሌላ ኃይማኖታዊ ወይም መንፈሳዊ ግዴታ ሊጨመርበት አይገባም። (መፍትሔው መውጫ መንገዶች የሚለው ምዕራፍ ላይ ታገኙታላችሁ)።

اللَّهُمَّ صَلِّ عَلَىٰ سَيِّدِنَا مُحَمَّدٍ وَعَلَىٰ آلِهِ وَصَحْبِهِ وَسَلِّمْ

ምዕራፍ ሦስት

መውጫ መንገዶች

ከሥር የተጠቀሱ ነጥቦች ችግር አውርቶ ከመለያየት ይሻላሉ በሚል የተነሱ ናቸው። በርግጥ የጸሐፊው ዓላማ ስለወረቀት መግበያያ ለግንዛቤ መጨመሪያ የምትሆን ነጥብ አስተላልፎ ለአንባቢው መተው ነበር። ዓላማው እንዳለ ቢሆንም አንባቢዎች "እሺ ምን ይሁን? ለምን መፍትሔ አልተጠቆመም?" ወዘተ. የሚል ጥያቄዎችን ማንሳታቸው ስለማይቀር፣ ከመጻሐፉ ሕትመትም በፊት ያነሱም ስለነበሩ፤ ለውይይት ርዕስ የሚሆኑ ነገሮችን ጠቁሞ ለማለፍ በመጽሐፉ አዘጋጅ የቀረቡ ጥቂት የመፍትሔ ርዕሶች ናቸው እንጂ ውሳኔዎች አይደሉም። እያንዳንዳቸው ሰፋፊ ጥናትና የዑለማእ (ሊቃውንት) ይሁንታ የሚሹ ሲሆኑ መቅረባቸው ለጥናት እና ምርምር በር ሊከፍቱ ይችላሉ።

3.1. ችግሩን እና ደረጃውን ማወቅ

የመጽሐፉ ምልከታም ችግሩ መኖሩና ጥልቀቱን መጠቆም ነው። አብዛኛው የዓለም ማኅበረሰብ በተለይ ይኽኛው ትውልድ ሲወለድ ከወላጆቹ ቤት እና ከአካባቢው አግኝቶ የተጋፈጠው የገንዘብ ችግር ሁሉ የተፈጥሮ ችግር እንደሆነ አምኖ ተቀብሎ ይኖራል። ብዙ ነገሩ ሰው ሰራሽ ችግር መሆኑን አይረዳም። ምክንያቱም ከዚያ በፊት ምን እንደነበር የሚያውቀው ነገር የለም። የምንማረውም ትምህርት ካፒታሊስቶቹን የምናገለግልበትን የባርነት ቀንበር ማሳመሪያ እና ምሁሩ እራሱን በራሱ "ምርጥ ተገዢ ባሪያ" የሚሆንበትን እንጂ የችግሩን ምንጭ የሚጠቁም

አይደለም። ምሥጢሩ የፋይናንስና ኢኮኖሚክስ ትምህርት ቤቶችም ላይ ሳይቀር ተድበስብሶ ያልፋል።

ለአብዛኞቻችን አዲስ የሆነው ይህ ርዕስ፣ በምዕራቦች ዘንድ ግን ከአናኒራቸው ጋር በማያያዝ ብዙ ጽፈውበታል። ወደኛ ስንመጣ ለችግሩ ምንጭ ቅርብ የሆኑ የፋይናንስና ኢኮኖሚክስ ትምህርት ቤቶች ካላተኮሩበት ከዚያ የራቁ የትምህርት ክፍሎች ሊገነዘቡት አይችሉም። ያልተማረው ክፍልማ ምንም አማራጭ የለውም። ይልቅስ ሸሽትን መርጧል። "ከተማረው ባሪያ" ሕገ-ልቦናውን ተጠቅሞ ዝም ያለው ያልተማረው ክፍል የበለጠ ለዕውነት ቅርብ ነው። የሚገርመው ከዘመነኛ ትምህርት ርቀው በገጠር ውስጥ የኢስላም ትምህርት የተማሩት የተሻለ ዕውቀት አላቸው። ችግሩ ግን ነገሩ ስለተምታታ እነርሱም ዝም ብለው ቁጭ ብለዋል። ወይም ሕዝባቸውን ከባንክ እንዲርቅ ከማስፈራራት ውጭ መውጫውን መንገድ ለማመላከት የምዕራቡን የዘመነኛ ዕውቀት ማወቅ የግድ ሆኖባቸዋል። ያ መንገድ ግን ርቆ ተሰቅሎአል፣ ወይም ጠልቆ ተቆፍሮአል።

የተሻለ ቅርብ የሆነው "ተምሬያለሁ" የሚለው ወገን ነው። ስለዚህ ይኸኛው ክፍል ለችግሩ መነሻ ሥፍራ ቅርበት ስላለው ለሊቃውንቱ የማቅረብ ኃላፊነት አለበት። ዛሬም ገንዘብ ምንድን ነው? ከየት ነው የሚነሳው? የሚታተመውስ የት ነው? ለምን? እንዴት? ወዘተ ጥያቄዎችን እያነሳ ቢሞግት እና ቢቆፍር ምንጩ ጋር መድረስ ይችላል። "ችግሩን ማወቅ የመፍትሔው ግማሽ ነው" እንደሚባለው ችግሩን፣ ምንጩን፣ ጥልቀቱንና ስፋቱን ከተረዳነው ለመውጣት ቅርብ ነን። ይህ ከመሆኑ ጋር የዘርፉ ጉዳይ ለዘርፉ ሰዎች እና ፉቀሐዎች (የኃይማኖቱ ሊቃውንት) መተዉ የግድ ይላል። ከኃይማኖት ጋር ስለሚገናኝ ብዙዎች ያለሙያቸው ገብተው ሲያማስሉት ይስተዋላል። ሙያን ለባለሙያው መተው ያስፈልጋል። ዐዋቂዎችን

ገፍቶ ለታዋቂዎች መጫወቻነት መልቀቅ ችግሩን ያብሰዋል። ወለድን ሀራም ነው ማለት ዕውቀት የሚጠይቅ አይደለም። ልክ ዝሙት፣ ስርቆት፣ አስካሪ ነገር ሀራም ነው እንደማለት ወይም አፍንጫ ለማሸተት፣ ዓይን ለማየት ይጠቅማል እንደማለት ግልጽ ነው። አያከራክርም። ወለድ ሀራም ነው ብሎ ማስፈራራትም አይለውጠውም።

የገንዘቡ ምንነት ከተረዳን ግን ብዙ ጥያቄዎች መልስ ያገኛሉ። ከልጁ (ወለዱ) በፊት ወላጁን (ገንዘቡን) መረዳት የግድ ነው። ለዚህ ይረዳ ዘንድ የግዙፍ አስተሳሰቦችና ኢኮኖሚ አይዲኦሎጂያቸውን እንመልከት። ከእነዚህ ውስጥ **ሦስቱን ማለትም የካፒታሊዝም፣ የሶሺያሊዝምና የኢስላም የኢኮኖሚ መሠረቶችን ስናይ የገንዘቦች መሠረት ጋር እንደርሳለን።** ግዙፍ አድርገን ስንሸሸው የነበረው የወለድ ጉዳይ ቀረብ ብለን ወደ መፈተሽና ወደ መለወጥ እናድጋለን። ይህ ርዕስ ከመጽሐፉ አጠቃላይ ይዘት አንድ እርምጃ ወደ ኋላ የሚሄድ እና ለብቻው አንድ መጽሐፍ ወይም መጽሐፎች እንዲጻፍበት የሚሻ ርዕስ ነው። እዚህ ጋር ማንሳታችን ለአራጣ (ወለድ) ምንነት ተጨማሪ ነጥቦች ይሰጠናል። በአጭሩ እንቃኘዋለን።

3.1.1. የካፒታሊዝም የኢኮኖሚ ሲስተም

ካፒታሊዝም ከስሙ እንደምንረዳው መሠረቱ የገንዘብ ካፒታል ላይ ነው። ገንዘብና ምንጩ ከተያዘ ጥሬ ዕቃ፣ የማምረቻ መሣሪያ፣ መሬትና የተሻለ ብቃት ያለው ሠራተኛ በመቅጠር ጥራት ያለው ምርትና አገልግሎት ማቅረብ ይቻላል። ዋጋዎች በገበያ ይወሰናሉ። የግል የምርትና የትርፍ ውድድር ዓለምን ያዘምናል።

ይህ ሥርዓት አሁን እየኖርንበት ያለው ሥርዓት ነው። ካፒታሊዝም ምዕራቡን የዓለም ንፍቀ-ክበብ ይዞ የተነሳና የፊያት ገንዘብን ተቆጣጥሮ ዓለምን በአንድ ገንዘብ ሥርዓት ስር አስገብቶ ኢኮኖሚውን ብቻ ሳይሆን ሀብትና ሀብታምነትን/ድህነትን

በፒራሚድ መልክ ደርድሮታል። ከላይ ያሉት ሀብታሞች የሁለት እጅ አስር ጣቶች ያህል እንኳ ቁጥር ሳይኖራቸው፤ ከግማሽ በላይ የሚሆነውን የዓለም ሀብት በቁጥጥር ስር አውለዋል። ቀሪውን ለቢሊዮኖች የሚከፋፈል ነው። እነዚህ ጥቂት ግለሰቦች የየሀገራቱ ገንዘቦችን ይወስናሉ። ሀብቶች ቦይ ተበጅቶላቸው ወደ እነርሱ ይፈሳል። ማዕድናት የትም ሀገር ቢመረቱ፣ አዝርዕት የትም ሀገር ቢበቅሉ፣ ዳመና የትም ሀገር ቢያጠል፣ ምሁር የትም ሀገር ቢማር በዚህ ቦይ አማካይነት ልክ ከጣና ከፍ ብሎ ተነስቶ ሜዲትራኒያን ባሕር እንደሚገባው ዐባይ ይፈሳሉ። ፒራሚዱ በምዕራፍ አንድ ላይ የቃኘነው በመሆኑ እዚህ ግን ከጀርባ ያለውን የካፒታሊዝም ሲስተምን ለማየት እንሞክራለን። በተለያዩ መጻሕፍት የተለያዩ መሠረቶች ቢቀመጥለትም አማካዩን ይዘን እንቃኝ።

የካፒታሊዝም መሠረቶቹ፡- ሀብት ስብሰባ፣ የግል ሀብት እና ባለቤትነት፣ የገበያ ተወዳዳሪነት፣ የዋጋ ሲስተም፣ ነጻ ገበያ እንዲሁም ቅጥርና ደመወዝ መጥቀስ ይቻላል።

ሀ. ሀብት መሰብሰብና ግለኝነት

ሲስተሙ የተመሰረተው በግል ሀብት ላይ ነው። አንድ ግለሰብ ትክክል የሚሆነው ይዞ መገኘቱ ብቻ ነው። ገንዘብ ካለህ አለህ፣ ትክክል ነህ፤ ከሌለህ የለህም፣ ስሁት ነህ ወደሚያስብል በሀብት ቅርምት የሚያወዳድር ሥርዓት ነው። መስመሩ ካልገባህ ሲስተሙ ከመሀል እየተፋ ወደ ዳር ይወስድሀል። አንድ ሰው በተቻለው ብልጠትም ይሁን ዕውቀት፤ የዘመድም ይሁን የባዕድ፣ የመንግሥትም ይሁን ባጠቃላይ የሕዝብ ሀብት ከቅርቡም ይሁን ከሩቅ ሀገር ከሰበሰበ ዘንዳ፤ ዳኛው፣ ፖሊሱ፣ ዘመዱ፣ ባዕዱ፣ ወዘተ. ብቻ ሳይሆን ግዑዙም ጭምር ለእርሱ ያግዛሉ። ቴሌፎኑና ሚዲያው ያወሩለታል፣ ብረታ ብረቱ ይመሰክሩለታል፣ ቢያወራ ይሰማል፣

ለመቀለድ ቢሞክር ይሳቅለታል፣ ለቅሶ ቢደርስበት ሀገር ሁሉ ተሰብስቦ ይቀብርለታል። በምንም መንገድ ገንዘብ ይዞ መገኘት ነው። Snatching the capital ይሉታል። የመንጠቅ ብቃት ያለው ሰው የተሻለ የሚኖርበት ሥርዓት ነው። ኑሮ የሚወሰነው በብልጠት ልክ ነው። መልካም ጸባይም የሚገዛው በገንዘብ ነው ተብሎ ይታመናል።

ይህ ግለኝነት የኃይማኖት ሰዎችን ሳይቀር እጅግ ፈትኖ ከአንድ ኃይማኖተኛ ይልቅ ትንሽ "ሰው"ነት ያለው ዱርዬ ይልቅ ይታመናል። ከሌባ ይልቅ ፖሊስ ይፈራል። ከሸይኽ ይልቅ ዘፋኝ ይከበራል። አንድ ሰው ሀጅ ስለማድረግ ስነሥርዓት ለማወቅ ቢፈልግ ከደሀ የኃይማኖት ሸይኽ ይልቅ ሀብታም ነጋዴ የተሻለ ዕውቀት ይኖረዋል ብሎ ይገምታል። ምክንያቱም ሀጅ የተግባር ሥራ በመሆኑ ሀብታሙ ደጋግሞ ሀጅ ስላደረገ ይበልጥ ያውቃል ከሚል በመነሳት እና ደሀው ሸይኽ ጭራሽ ሀጅ አስደርገኝ ብሎ እንዳይጠይቀው በመስጋት ሊሆን ይችላል።

ለ. የዋጋ ቁጥጥርና ተመን

የዚህ መሠረቶች ሁለት ሲሆኑ እነርሱም ታክስ እና ወለድ (Tax & Interest) ናቸው። ካፒታሊዝም የቆመው በአራጣ (ወለድ) ላይ ነው። አራጣ ከሌለ ካፒታሊዝም አንድ ሌሊት ማደር አይችልም። የአራጣ መሠረቱ ደግሞ ቁጠባ ነው። ለቆጣቢ ወለድ ይታሰባል። ብዙ መቆጠብ ብዙ ወለድና ሽልማት ከባንኮች ያስገኛል። ሀብቶች ከመንደር በቁጠባ መልኩ በፊያት ተተርጉመው ወደ ባንኮች ይጠራቀማሉ። በገንዘቡ ባንኮችና ሀብታሞች ለሁለት ይሠሩበታል። ለቆጣቢ ወለድ ይታሰብለታል። የኢስላማዊ ባንክ ክፋት ይህንንም ጥቅም ለድሆች ይነፍጋል። በካፒታሊዝም የገቢ ግብር እና ጡረታ የተከፈለበት "የተጣራ ገቢ" ለሁለት ይካፈላል። ቁጠባና የግል ወጪ (Saving and Expenditure) ናቸው። የመንግሥትም ይሁን የግል

ኢኮኖሚስቶች ሁለቱን ያጫውታሉ። የሁለቱ ማጫወቻ ደግሞ ወለድና ታክስ ናቸው። አፉ ብሔራዊ ባንክ ሲሆን ፈገራው (መቀመጫው) ገቢዎችና ጉምሩክ ነው። ፊያት (ቁጥር) ከብሔራዊ ባንክ ታትሞ በነጻ ይወጣል። ያንኑ ፊያት (ቁጥር) በገቢዎችና ጉምሩክ በኩል "ያው በለቅሶ" ማለት ይቻላል፤ ይሰበሰባል። ሆኖም ግን ታክስም ፊያትም ቁጥር ስለሆኑ እንደፈለገው ለማጫወት ይመቻሉ። ፊያትን ስናጫውት ቀጥታ እሴትን ያጫወትን መስሎን መሰቃየት የለብንም።

ፊያት ገንዘብ ገበያ ውስጥ ሲበዛና ግሽበት ሲያባብስ ብዙ መሰብሰቢያ መንገዶች አሉት። ዋነኛዎቹ ወለድና ታክስ ናቸው። በታክስ ተሰብስቦ ይታሰራል። ወረቀቱ ከበዛ ይቃጠላል። የቁጠባ ወለድ ፐርሰንት ሲጨምር ሰዎች የተሻለ ጥቅም ፈልገው ወደ ባንክ ይመጣሉ። ምርቶች ሲበዙ እና ፋብሪካዎች ገዢ ሲቀንስባቸው አሁንም ማጫወቻዎቹ ወለድና ታክስ ናቸው። ወለድና ታክስ የምርት ግብዓት፣ የሠራተኛ ቅጥር፣ ቁጠባ፣ ኢንቨስትመንት፣ ብድር? ወይስ አክሲዮን?፣ የጋራ ዲቪደንድ? ወይስ የግል ንግድ? ወዘተ ይወስናሉ። ይህ እያንዳንዱ አንዳንድ መጽሐፍ ስለሆነ እዚሁ ልግታው።

ባይሆን አንድ ወሳኝ ጉዳይ እዚሁ ላክል። ስለታክስ ዕውቀት የሌለው ምሁርም ይሁን የእስልምና ሸይኽ ስለአራጣ ብይን ባይሰጥ ይመከራል። ምክንያቱም በእስልምና ውስጥ ዘካ (ምጽዋት) እንጂ ታክስ የለም። በክርስትናም አስራት እንጂ ታክስ አይኖርም። በአሁኑ የካፒታሊዝም ሲስተም ታክስ ከሶላትና ሌሎች አምልኮዎች በላይ ምእመኑም ጭምር ተገዳጅ ነው። ሶላት አልሰገድክም ሰንበት አልተገኘህም ወይም ዘካ አልከፈልክም አስራት አላስገባህም ብሎ የሚጠይቅ አንድ ግለሰብ ሳይኖር ታክስ ግን ከየትኛውም አምልኮ በላይ ይተገበራል። ምእመኑ ከጀሀነም ይልቅ ገቢዎችና ጉምሩክ ሊፈራ ይችላል። ስለዚህ ይህንን ጉዳይ በጥልቀት

ያላወቀ፣ አውቆም ለመፍትሔ ያልተዘጋጀና እንደማንኛውም ሰው የሚኖር ሸይኽ ወይም “ምሁር” ወይም ቄስ፤ ድንገት የአራጣ ብይን ቢሰጥ ብዙ ነገሮችን ያበለሻሻል። ምክንያቱም ወለድና ታክስ ቦታ ተቀያይረው ያገለግላሉ። ታክስ የምንለው ነገር ወለድ፣ ወለድ ተብሎ የሚጠራው ነገር ደግሞ ታክስ ሆነው የሚመጡባቸው ቦታዎች አሉ። ከዚህ በተጨማሪም ሁለቱ በአንድ ቦታ ሲመጡ አንዱ አንዱን ሙሉ ለሙሉ ወይም በከፊል ያጠፋል። አንድ ከባንክ ተበዳሪ ለባንኩ ወለድ ስለከፈለ፤ ዓመታዊ ግብር ሲከፍል በከፈለው ወለድ ልክ ቢያንስ 30 ፐርሰንት ከግብር (ታክስ) ላይ ተመላሽ ይደረግለታል። በሒሳብ ቋንቋ ወለዱ እንደ “ታክስ ማቀናነሻ” ወጭ ይያዝለታል።

ሐ. ገበያ ፈጠራና ተወዳዳሪነት

በካፒታሊዝም ብዙ ካፒታል የሰበሰበ የተሻለ ብቃት ያለው ሥራተኛ መቅጠርና የተሻለ ጥሬ ዕቃ ማግኘት ይችላል። ይህም የተሻለ ምርትና አገልግሎት ለማቅረብ ያስችሉታል። የካፒታሊዝም ፒራሚድ ጫፍ በዶላር አማካይነት ከዓለም ሁሉ ጥሬ ዕቃና የተማረ ሰው ወደ አሜሪካና አውሮጳ ያጓጉዛል። በመሆኑም አሜሪካ የተሻለ ኢኮኖሚ ያስባላት የፊያት ሲስተም ነው። የምሥራቅ ንፍቀ-ክበብ ሶሺያሊስቶች ይህንን ሲስተም ለመቃወም ሞክረው ፈራርሰው ለካፒታሊዝም እጅ ሰጥተዋል። ቻይና፣ ራሺያና ሌሎች ምሥራቆች የተሻለ ሊቆዩ የቻሉት የፊያትን ሲስተም ተቀብለው ጥሬ ዕቃ ለመሰብሰብና ለመቀራመት በመቻላቸው ነው።

መ. ደመወዝና ቅጥር

የካፒታሊዝም ሌላው መታወቂያው ደመወዝና ቅጥር ላይ የተመሠረተ ነው። የተማረውም የሚማረውም፣ የሚሸየኸውም (ሸይኽ የሚሆነውም)፣ የተሸየኸውም

የዚህ ሲስተም አገልጋይ ቅጥረኛ ስለመሆንና የግል ሀብቱን ስለማካበት እንጂ ሲስተሙን ስለማጥናት አይደለም። እንደዚህ ዘመን ሀብት የፈላበትና ደሀ የበዛበት ዘመን የለም ማለት ይቻላል። የዚህ መጽሐፍ አንዱ ዓላማ በቅርንጫፍ ጉዳይ ማለትም ስለገንዘብና አራጣ ከመብሰልሰል ይልቅ መሠረቱን ማሳወቁ ነው። ከዚያ እያንዳንዱ ሰው በተለይ ሙስሊሙ ሲስተሙ ከገባው የተንሻፈፈው ትርጓሜውን አስተካክሎ ከሲስተሙ ጋር ተግባብቶ እራሱን ማቆየት እንዲችልና ከቅጥረኛነት እንዲላቀቅ ነው። ምክንያቱም በዚህ ሲስተም ጥሩ ተምሮ ጥሩ የካፒታሊዝም ባሪያ መሆን እንጂ ከባርነት ለመውጣት ማሰብ አታካች ነው። ከአኗኗሪነት ወደ ነዋሪነትና ነጻነት መውጣት አያልምም። መደምደም አይቻልም። ማለሙ አይቀርም። ግን ጭልምልም ያለ መንገድ ሆኗል። ዘወትር ለሀብት ቅርምት እንደማሰነ ሞት ይይዘዋል። በቁንጽል ስለሚያስብ በጥቃቅን ነገሮች ባተሌና ተከራካሪ ይሆናል። የዓለም መድኅን የነበረው ኃይማኖት የዓለም በሽታና ችግር እንዲመስል አድርጎታል። (ወቀሳው የዚህ መጽሐፍ ጸሐፊም እራሱን አካቶ እንጂ ሌላውን ለመውቀስ አይደለም። ለቃላቱ ጥንካሬ አንባቢን ይቅርታ ይጠይቃል። ችግሩ ከዚህም በላይ ያስብል ስለነበር ነው)።

3.1.2. የሶሺያሊዝም የኢኮኖሚ ሲስተም

ሶሺያሊዝም እንደ ስሙ ማኅበራዊ እሴት ላይ ያተኩራል። ከገንዘብ ሀብት ይልቅ የሰው ሀብት ያስቀድማል። በሕዝብ፣ በሥራና በሠራተኛው ላይ ቀልድ የለም። ሶሺያሊስት ኢኮኖሚ ሲስተም በጣም የሚታወቀው ሕዝቡ በአጠቃላይ እስኪባል ድረስ መሠረታዊ ነገሮችን አያጣም። የሶሺያሊዝም እምነቱ የማኅበረሰብ የኑሮ መስተካከል ያስቀድማል። የካፒታሊዝም ቀጥተኛ ተቃራኒ ነው። ግለኝነትን ለመፍታት ሀብቶች የወል ወይም የጋራ ለማድረግ የተሞከረበት ነው። ዓይነቱ ብዙ

ቢሆንም ዋና መሠረቱ የጋራ ሀብት ላይ ነው። ሀብቶች በመንግሥት ቁጥጥር ስር ሆነው ለዜጎች በእኩልነት ማከፋፈል ነው። የግል ነጣቂን ማጥፋትና ለጋራ ሀገር ብቻ መልፋት ነው። የእኔ ሳይሆን የእኛ ብሎ ማሰብና መሥራት ላይ የተመሠረተ ነው። ትርፍ ሀብት የያዘ ለመንግሥት ያስገባል። አሊያም ይወረሳል።

ከጥቅሞቹ ውስጥ፡-

- ከግል ትርፍ ይልቅ የጋራ ብልጽግና ላይ ያተኩራል።
- ለድሕነት ቅነሳ ዓይነተኛ መሣሪያ ነው።
- የትምሕርት ጥራትና የጤና ተቋማት ላይ በትኩረት ይሠራል።
- አላግባብ የሆነ የገበያ ውድድርን ፈር ያስይዛል።
- ሰው ተኮር በመሆኑና በትክክል ከተተገበረ የአምራች ብቃት ላይ ጥሩ ነው።
- የጋራ ሀገራዊ ግብ ይፈጥራል።
- እኩልነት በመኖሩ ወንጀል ይቀንሳል።
- ከትርፍ ሩጫ ይልቅ ለማኅበረሰብ ደሕንነት ስለሚያስቀድም ለአካባቢ ብክለት ጥበቃ የተሻለ ነው።
- ሁሉም ሰው ተቀራራቢ እድል ስለሚኖረው የእድል ሽሚያና ግድያ ይቀንሳል።
- የግለሰቦች የዋጋ ሞኖፖሊና ብዝበዛን ያስወግዳል።
- የምርት ጥራት በቁጥጥር ላይ የተመሠረተ በመሆኑ ቁጥጥር ከተሳካ ጥሩ ምርትና አገልግሎት ማቅረብ ይቻላል።
- ቁጠባ ስለማይበረታታ ገንዘቦች ወደ ተወሰኑ ብልጦችና የፖለቲካ ሽፋን ወደሚያገኙ ሰዎች ሄዶ አይሰበሰብም።

- ብዙ ድርጅቶች የመንግሥት ስለሆኑ ወለድና ታክስ አነሳ ነው።
- ከትርፍ ይልቅ እሴት ያስቀድማል።

ከጉዳቶቹ፡-

- የግል ውድድር ስለማይኖር የፈጠራ ተነሳሽት ይቀንሳል።
- መሠረታዊ ፍላጎት ስለማይጠፋ የመሥራት ሞራል ላይ አሉታዊ ተጽእኖ አለው።
- የመንግሥት ቁጥጥር ላይሳካ ይችላል። በመሆኑም ሥርዓቱ ቶሎ ይወድቃል።
- የመንግሥት ከፍተኛ ቁጥጥር ሠራተኛን ያሰላቻል።
- ከፍተኛ ቢሮክራሲ ይፈጠራል።
- መንግሥት ችርቻሮና አስቤዛ ውስጥ ይገባል።

በመሆኑም በሶሺያሊዝም የተሳካላቸውም የተምታታባቸውም ሀገራት አሉ። ሶሺያሊዝምም ካፒታሊዝምም እንደ መሠረተ ሐሳቡ አልሄደም። ካፒታሊዝም በነጻ ውድድር ጥሩ ምርትና አገልግሎት ይመጣል ቢልም የፋይናንስ ሲስተሙን በሞኖፖል ለጥቂት ሰዎች አስገባው። ገንዘብ ሳይኖር ነጻ ውድድር ቢባል በፈጣን መኪናና በባዶ እግር እንደመወዳደር ነው። ሶሺያሊዝም ብዙ ሀገር እንዳልተሳካለት ካፒታሊዝምም ሀብቶችን ወደ ጥቂት ሰዎች ማጋዝ ነው የተረፈው። መንግሥት ደሃን ረስቶ ወይም መጠቀሚያ አድርጎ ጥቂት ሀብታሞችን ለመንከባከብ የተቋቋመ ይመስላል። እንደ ቻይና ያሉ የሁለቱንም ጥምር የሞከሩ ሀገራት አሉ። ኢኮኖሚውን የካፒታሊስት የውድድር መስመር አስይዘውት ለሠራተኛ መደብና ለአጠቃላይ ሕዝብ የኑሮ ዋስትና

ቅድሚያ ሰጥተው እየሠሩ ናቸው። ለእኛ ሀገር ዝም ብለን መኮረጅ ሳይሆን የሕዝባችንን ኢኗኗርና እሴት መሠረት ያደረገ የኢኮኖሚ ርዕዮተ ዓለም ያስፈልጋል።

3.1.3. የኢስላማዊ የኢኮኖሚ ሲስተም

የሁለቱም ማለትም የካፒታሊዝም እና የሶሺያሊዝም የኢኮኖሚ ሲስተሞች ድምርም ብዜትም ሳይሆን የራሱ መርሕ አለው። በእነርሱ ላይ አይመሠረትም። መመሥረቻው የእምነቱ መጻሕፍት ናቸው። በሰው ልጆች መካከልና በአንድ ፀሐይ ስር ስለሚካሄድ ከሌሎቹ ሲስተሞች ላይ የሚጋራው ነገር ይኖራል። ከሰው ልጅ ባሕሪይ ጋር የተያያዙ ማለትም ሰው "ግለኝነት" ስለሚያጠቃው የግል ሀብት መያዝ ስለሚፈልግና፤ እንዲሁም ማኅበራዊ ኑሮ ስለሚኖር ለጋራ ጥቅም መኖርንና የግድ በጋራ መያዝ ያለባቸው ነገሮች ስለሚኖሩ የኢስላም የኢኮኖሚ ሲስተም ለሁሉም ቦታ ቦታቸውን ይሰጣል። ጸሐፊው ሙስሊም ስለሆነ ማዳላት የሚመስለው ሙስሊም ያልሆነ አንባቢ ሊኖር ይችል ይሆናል። ሆኖም ግን ይህንን ሲስተም ከአጠቃላይ የሰው ልጆች አኳያ የተቀረጹና ዘመን-አይሽሬ ስለሆኑ አድሎአዊነት አይኖራቸውም። ሌሎች እምነቶችም የየራሳቸው የኢኮኖሚ መርሕ ይኖራቸዋል። እዚህ ጋር የምናየው የእስልምናውን ብቻ ነው። እንደ ኃይማኖት የሚወራረሱ ብዙ ነገሮች ይኖሩታል። ግን ርዕሱ አይደለም። የተወሰኑ መርሆዎችን እንይ!

ሀ. ሀላል እና ሀራምን መለየትና አላህን መፍራት

ሌሎቹም ሲስተሞች ክልክልና ፍቁድ (ሀላልና ሀራም) አላቸው። የኢስላማዊ ኢኮኖሚ "ሰው ባያየኝ አላህ ያየኛል" የሚል መርህ አለው። ፍቁድ እና ውጉዝ ነገሮችን መለየት ያስፈልጋል። በእርግጥ ፍቁድና ውጉዝ የኢስላም ብቻ አይደሉም። ሰዎች በተፈጥሮአቸው የሚያውቁት ነው። ምክንያቱም ሀላል እና ሀራም

ግልጽ ናቸው። በእያንዳንዱ የሰው ልጅ ልብ ላይ በተፈጥሮ ታትመዋል። በየትኛውም እምነትም ይሁን ባሕል አስጠያፊ ነገሮች ውጉዝ ናቸው። ግድያ፣ ዝሙት፣ አራጣ፣ ስድብ፣ ስካር፣ አደንዛዥ ዕጽ ወዘተ. የማያወግዝ ኃይማኖት አይኖርም። ወደ ካፒታሊስታዊና ሶሺያሊስታዊ ርዕዮተ-ዓለም ስናመጣው ግን እንደ ኃይማኖቶቹ አይሆንም። ካፒታሊዝም ላይ ገንዘብ የሚያመጣ ሁሉ እንደ ትክክል ሊቆጠር ይችላል። ካፒታሊዝምን ስንተች መቆሚያው መበላሸቱ የብዙ ነገሮች ብልሽት ምክንያት መሆኑ እንጂ በጎ ጎን የለውም እያልን አይደለም። የኢስላሙ ሕግ ከይሆናል/አይሆንም ባሻገር በሚቀጥለው ዓለም የጽድቅና ኩነኔ እሳቤዎች ይካተቱበታል። አላህ እንዲቀበለው ንጹሕ መሆን አለበት። የሚከተለውን የቁርአን አንቀጽ እንመልከት።

እናንተ ያመናችሁ ሆይ! ገንዘቦቻችሁን በመካከላችሁ ያለ አግባብ አትብሉ። ግን ከእናንተ በመዋደድ የሾነቸውን ንግድ (ብሉ)። ነፍሶቻችሁንም አትግደሉ። አላህ ለእናንተ አዛኝ ነውና። ወሰን በማለፍና በመበደልም ይህንን የሠራ ሰው እሳትን እናገባዋለን። ይሽም በአላህ ላይ ገር ነው። (ቁርአን 4:29-30)

ንግድ በተናጋጅ መካከል ያለአስገዳጅ በውዴታ ብቻ መፈጸም እንዳለበት፣ አግባብ ባልሆኑ በየትኛውም መንገዶች መግባት (መሥራት) እንደሌለብን ከመከረን በኋላ ይህንን የተላለፈ ጀሀነም እንደሚጠብቀው ያስጠነቅቃል። ከዓለማዊው ሕግ የሚለየው ከምድራዊ ቅጣት ባሻገር ሌላ ቅጣት ሊያስከትል ስለሚችል ተጨማሪ ጥንቃቄ አለው።

በሁሉም ማኅበራዊ አኗኗሮች ላይ ከጀሀነም ጋር የተያያዙ ተመሳሳይ ማስጠንቀቂያዎች አሉ። ሰው አየኝ/አላየኝ የሚባሉ ብቻ ሳይሆኑ ከሕዋሳት የራቁ መላዕክት እንደሚመዘግቡዋቸውና የልብ ጭምር አዋቂ የሆነው አላህ

እንደሚያውቃቸው በመገንዘብ የሚጠነቀቁዋቸው ናቸው። ፖሊስ በአካባቢው መኖር አለመኖሩ የሚወስናቸው አይደሉም። ፖሊሶች የሚያስፈልጉት ሰዎች የሸይጧን መጫወቻ እንዳይሆኑ ተጨማሪ ሥርዓት አስከባሪ ናቸው። በሁሉም የስነሥርዓት እና ግብረገብ ጉድለት ቀዳዳዎችና ክፍተቶችን የሚሸፍኑ በርካታ የቁርአንም የሀዲስም ማስጠንቀቂያዎች አሉ። የሀላል ሀራም ዓይነቶችና ድንበሮቻቸውም ጭምር እንደ ኮድ ተለቃቅመው በሊቃውንት ለብቻቸው ተበጅተዋል።

ለ. ሀብት ማከማቸትን በተመለከተ

በፍቁድ ሥራ የተገኙ ገቢዎች በዝተው መከማቸት የለባቸውም። ማከማቸት በራስ ላይ ፈተናና ተጠያቂነት ማብዛት ነው። የጀነት ቢሆን እንኳ ጥያቄው ብዙ ነው። ገንዘብ አመጣጡ ጥያቄ አለው፣ አቀማመጡም ጥያቄ አለው፣ አወጣጡም ጥያቄ አለው። ሀብት በግል መያዝና ሀብታም መሆን አልተከለከለም። ጀነትን በብዛት የሚወርሱት ሀብታሞች ናቸው። ምክንያቱም በገንዘባቸው ለሰው ልጅ የሚጠቅም የተሻለ ነገር ስለሚያደርጉበት ነው። ቁጭ ብሎ ወይም በሱስ ብዛት ለማኝ የሆነውና ሠርቶ ለፍቶ ለሌላ የተረፈው እኩል አይዳኙም። እኩል አይመሰገኑም። ከአምስቱ የእስልምና መቆሚያ ሦስተኛ የተደረገው ዘካ የሀብት ውጤት ነው። አምስተኛ ላይ የሚመጣው ሀጅም ለሀብታም ነው። ሌሎች ዘላቂ መገልገያ የነበቡ ሰዎች ቢሞቱም እንኳ የሠሩት ነገር የመልካምነት መዝገባቸውን ክፍት አድርጎ ይቆያል። ዝርዝሩ ብዙ ነው። በኢስላም ሀብታም መሆን አይኮነንም። የሚኮነነው ሐቁ ሳይወጣ ማከማቸቱ ነው።

እነዚያም አላህ ከችሮታው በሰጣቸው ገንዘብ የሚነፍጉ እርሱ ለእነሱ ደግ አይምሰላቸው። ይልቁንም እርሱ ለነሱ መጥፎ ነው። ያንን በርሱ የነፈጉበትን

በትንሳኤ ቀን (እባብ ኾኖ) ይጠለቃሉ። የሰማያትና የምድርም ውርስ ለአላህ ብቻ ነው። አላህም በሚሠሩት ሁሉ ውስጠ ዐዋቂ ነው። (ቁርአን 3:180)

በተለይ የኃይማኖት ሰው ገንዘብ ሲሰበስብ አይወደድም። የቀደምት ነቢያት ዘመን የኃይማኖት ሰዎች በኃይማኖት ስም ገንዘብ ሲበሉ እንደነበርና ምን እንደሚገጥማቸው አውስቶ፣ ሙስሊሞችም ተመሳሳይ ችግር ውስጥ እንዳይገቡ አስጠንቅቋል።

እናንተ ያመናችሁ ሆይ! ከሊቃውንትና ከመነኮሳት ብዙዎቹ የሰዎችን ገንዘቦች በውሸት በእርግጥ ይበላሉ። ከአላህም መንገድ ያግዳሉ። እነዚያንም ወርቅና ብርን የሚያደልቡት በአላህም መንገድ የማያወጧትን በአሳማሚ ቅጣት አብስራቸው። (ቁርአን 9:34)

የቅጣት ዓይነቱ ሳይቀር በስዕላዊ አገላለጽ አስቀምጦታል።

በእርሷ ላይ በገሀነም እሳት ውስጥ በሚጋልባትና ግንባሮቻቸውም፣ ጎኖቻቸውም፣ ጀርባዎቻቸውም በርሷ በሚተኮሱ ቀን (አሳማሚ በኾነ ቅጣት አብስራቸው)። ይኽ ለነፍሶቻቸው ያደለባችሁት ነው። ታደልቡት የነበራችሁትንም ቅመሱ (ይባላሉ)። (ቁርአን 9:35)

ግንባር የቀደመው ችግርተኛ ላይ ቀድሞ ስለሚቋጠር ነው። በግንባር ቋጠሮ ያልሄደ ችግርተኛ ላይ ጎን ስለሚሰጥ እና ጭራሽ ጀርባ አዙሮ ስለሚኬድ በቅደም ተከተል አምጥቶታል። እንግዲህ እነዚህ ዛቻዎች ለካፒታሊስት አይገቡትም። እዚህ ጋር ሲያነባቸው እንኳ ግር ሊለው ወይም ምንም ስሜት ላይሰጠው ይችላል። ለኃይማኖተኛ ልብና ጭንቅላት ግን ጥሩ ፈውሶች ናቸው። ያከማቸውን ገንዘብ ለሌላ ክምችት ዳግም ኢንቨስት የሚያደርግ ሰው ከማድረጉ በፊት ያስባል። የእስልምና

ሥልጣኔ ከወደቀባቸው ምክንያቶች አንዱ ሀብትን ለማጠራቀም በመሯሯጥ ነው። ሀብቶች በሕዝቦች መካከል መንሸራሸር ሲገባቸው በጥቂት ሱልጣኖችና አሚሮች ስር ገብቶ ሕዝቡ አማጺ ሆነባቸው። በጦርነት ወቅት ሊያግዛቸው ፈቃደኛ አልሆነም።

ሰው መልፋትና መሥራቱ ተወዶለታል። ተበረታቷል። ንግድ ተፈቅዶለታል። ልመና ተወግዟል። የሥራ ዕጅ አላህና መልዕክተኛው የሚወዱት እጅ እንደሆነ ተመስከሮለታል። ከተሠራ ገንዘብ ተወደደም ተጠላም መከማቸቱ አይቀርም። የዚህ የግል ሀብት መቀነሻ መንገዶች አሉት። እንዴት ይቀነስ የሚለው ቀጥለን እናየዋለን። ከካፒታሊስት የሚለየው ሲከማች "አላህ ይጠይቀኛል፣ ሐቁን ሳልወጣ ሞት ይቀድመኛል" ብሎ ይሰጋል።

ሐ. ዘካ እና ጂዝያ (ምጽዋት እና ግብር)

በኢስላም ኢኮኖሚ ሲስተም ውስጥ ካፒታሊዝም የቆመባቸው ታክስም ይሁን ወለድ የሉም። ወለድ ሙሉ ለሙሉ ተወግዟል። ዘካ ደግሞ የአራጣ (የወለድ) ተቃራኒ ነው። ዘካ የእምነት/ክህደት መለያ ተደርጎ ተደንግጓል። ማንኛውም ሙስሊም በእስልምና ውስጥ ለመኖር ዘካ ግዴታ መሆኑን አምኖ መግባት አለበት። በሙስሊም አስተዳደር ውስጥ የሚኖር ሙስሊም ያልሆነ ሰው ደግሞ ግብር (ጂዝያ) እየከፈለ መኖር ይችላል። ሙስሊሙ ዘካ እየከፈለ ሌላው ሳይከፍል መኖር ፍትሐዊ አይደለም። በተቃራኒው ሙስሊም ያልሆነ ሰው ጂዝያ ካልከፈለ በሀገር ግንባታም ላይ እኩል ባለቤትነትና እኩል ስሜት አይሰማውም። በሌላ በኩል አንድ ሰው ከዘካ ቢያመልጥ ግብር ያገኘዋል። ከግብር ቢያመልጥ ዘካ ያገኘዋል። ስለዚህ ሀብታም ከገንዘቡ ለድሆች ማከፋፈል አለበት። ያን ያህል ከባድ ሆኖ ሳይሆን ለማኅበረሰቡ ሰላማዊ አኗኗር መፍትሔ ስለሆነ ነው። ዛሬ ሀብታም የነበረ ሰው ነገ ደሀ ቢሆን ወይም ችግር ቢገጥመው ዘካ ኢንሹራንሱ ነው።

ዘካ ሁለት ዓይነት ሲሆን (አንደኛው) የረመዷን ጾም ማገባደጃ ሁሉም ሙስሊም ሊከፍለው የሚገባ የነፍስ-ወከፍ የምግብ ዘካ ነው። የሀብት ደረጃ የለውም። ስሌቱ ለሁሉም ሰው ተመሳሳይ ነው። በረመዷን ጾም ውስጥ የመጨረሻው ቀን ጸሐይ ከመጥለቋ በፊት ከተወለደ ሕጻን ጀምሮ ጸሐይቷ ከጠለቀች በኋላ እስከ በሚድ ሶላት ባለው መካከል በሞተ ሰው ሳይቀር አንድ ቁና (2.5 ኪሎግራም) የምግብ እህል ክፍያ የሚታሰብ ነው። ይህን መክፈል የሚያስችል ትርፍ ምግብ ያለው ሰው ለሌለው ይከፍላል። (ሁለተኛው) የገንዘብ ዘካ የሚባለው ሲሆን በሀብታም ወይም የሀብት መጠኑ የዘካ መክፈያ መነሻ የደረሰ ሁሉ የሚከፍለው የገንዘብ ማጽጃ ነው። ዘካ ያልተከፈለበት ሀብት የድሆች ሐቅ ስላለበት እንደ ቆሸሸ ይቆጠራል። በዘካ መጽዳት አለበት። ዘካ የሚለው ቃሉ “ማጽዳት” ከሚል ስርወ-ቃል የመጣ ነው።

ከገንዘቦቻቸው ስትኾን በእርሷ የምታጠራቸውና የምታፋፋቸው የኾነችን ምጽዋት ያዝ። ለነሱም ጸልይላቸው። ጸሎትህ ለእነሱ እርጋታ ነውና። አላህም ሰሚ ዐዋቂ ነው። (ቁርአን 9፡103)

ገንዘቦች የአላህ ናቸው። ከዚያ ገንዘብ ለድሆች መክፈል እንደ ግዴታ አምልኮ ይቆጠራል። በዘካ የሚጎድል ገንዘብ እንደማይኖር አላህ ቃል ገብቷል። የነቢያችን ﷺ ዱዓ (ጸሎት) አለበት። ይህ ገንዘብ ለእነማን ይከፋፈላል ለሚለው አላህ እራሱ ነው ለስምንት ዓይነት ተከፋዮች የመደበው።

ግዴታ ምጽዋቶች (የሚከፈሉት) ለድኾች፣ ለምስኪኖች፣ በርሷም ላይ ለሚሠሩ ሠራተኞች፣ ልቦቻቸውም (ለእስልምና) ለሚለማመዱት፣ ጫንቃቸውንም (በባርነት ተገዢዎችን) ነጻ በማውጣት፣ በባለ ዕዳዎችም፣ በአላህ መንገድ በሚሠሩ፣

በመንገደኞችም ብቻ ነው። ከአላህ የተደነገገች ግዴታ ናት። አላህም ዐዋቂ ጥበበኛ ነው። (ቁርአን 9፡60)

1. ለድኾች፡ ሙሉ ጤነኛ ሆኖ ግን የሚያገኘው ገቢ ከመሠረታዊ ወጪው ጋር ያልተመጣጠኑለት ደሀ
2. ምስኪኖች፡ ከድህነት ጋር ዕድሜ ለሥራ አለመድረስ ወይም የአካል ጉዳት ያለበት ወይም ወላጅ አጥ
3. በርሷም ላይ ለሚሠሩ ሠራተኞች ሲባል ዘካ ሰብሳቢና አሠራጭ የሆኑ ሠራተኞች በአግባቡና መሪው በሚያስቀምጠው ተመን
4. ልቦቻቸው ለሚለማመዱት፡ አዲስ የሰለመ፣ ለመስለም የተዘጋጀ ወይም እስልምና ጥሩ መሆኑን ለማሳያ
5. ጫንቃቸውንም ነጻ በማውጣት፡- ለየትኛውም ዓይነት ባርነት ነጻ ለማውጣት
6. በባለዕዳዎች፡- ዕዳ ያለበት ሰው መንግሥት ከዘካ ገንዘብ ሊከፍልለት ይችላል። ከወለድ ነጻ ተበድሮ እንኳ መክፈል ያልቻለ የብድር እስረኛ ወይም ምርኮኛ ከዘካ ማካካስ አለ። ከካፒታሊዝም አኳያ ስናየው በወለድ ላይ ሌላ ወለድ ይጨመርበታል። በኢስላማዊ የኢኮኖሚ ደግሞ ብድሩ በነጻ ሆኖ እንኳ መክፈል ያልቻለ ሰው ዘካ መቀበል ይችላል። መሥራት የራሱ ምንዳ አለው። ምክንያቱም ጀነት የሚገኘው ገንዘብን በመለገስ ነውና። መለመን ደግሞ እጅግ ከተኮነኑ ነገሮች ነው።
7. በአላህ መንገድ በሚሠሩ፡- ይህ ከስምንቱ ውስጥ ትርጉመ-ሰፊው ነው። ምክንያቱም ሁሉም የእስልምና ሥራ በአላህ መንገድ ነውና። ለሙስሊም ጦር ሰራዊት ወይም ለመከላከያ ማዋል ይቻላል የሚለው የተሻለ ይቀርበዋል።

8. በመንገደኞች፡- መንገድ ለሚቆርጥ ሰው መጓጓጥ መስጠት፣ ማመቻቸት፣ ለመንገደኛ የሚሆን ማረፊያ ለመገንባት ሊውል ይችላል።

ዘካ የሚወጣባቸው ገንዘቦች በግልጽ አራጣ አለባቸው የተባሉት ስድስቱን ቅድሚያ ይመለከታቸዋል። ከዚህም ባሻገር አራጣ ቀጥታ ባይመለከታቸውም ለምግብ የሚውሉ እንስሳት፣ እንዲሁም እንደ ገንዘብ (ካሽ) ከተቆጠሩ ስንዴና ገብስ ውጭ ያሉ ሌሎች የግብርና ምርቶች ዘካ ይመለከታቸዋል። ማርና ስኳርም በተመረተባቸው ወራት ዘካ ውስጥ ሊገቡ ይችላሉ። ከወርቅና ብር ውጭ ያሉ ማዕድናት የንግድ ዕቃ ወይም የመጋዘን ዕቃ (Merchandise stock) ሲሆኑ ዘካ ውስጥ ይገባሉ። ወርቅና ብር በግራም ተለክተው ዘካ ውስጥ እንደሚገቡት መዳብና አሉሚኒየም ወዘተ. ግን አይገቡም። እንደሌሎች የንግድ የመጋዘን ዕቃ ጋር ተደምረው የዘካ አካል ይሆናሉ። የጠቀስኳቸው እንደው ቅንጭብ ነው እንጂ እራሱን የቻለ መጽሐፍ ነው። እንደየፉቀሐው (ሊቃውንቱ) ልዩነት አለበት።

የዘካ አሰላል ምጣኔው ለየዘርፉ ቀጥታ (straight line method) ነው። ለምሳሌ፡ - የወርቅ ገንዘብ 85 ግራም ሲደርስ በቀጥታ 2.5% ሲባዛ፣ በዝናብ ለበቀሉ የግብርና ምርቶች ከመቶ አስር እጅ ወይም 10% ይሆንና በመስኖ ሲሆን 2.5%፣ ለእንስሳት ደግሞ በዕድሜና በዓይነት የየራሳቸው ዝርዝር አላቸው። ምሳሌ ፍየልና በግ 40 ሲደርሱ አንድ ፍየል/በግ፣ 120 ሲደርሱ ሁለት ፍየልና በግ ዘካ ይከፈላል። እያለ ዝርዝር አለው። ልክ እንደዚሁ የግመል ደግሞ 5 ግመል ሲደርስ አንድ ፍየል/በግ ሲከፈል፣ አስር ግመል ሲደርስ ሁለት ፍየል/በግ ይከፈላል። ይህም የዕድሜና የጾታ ጉዳዮች ከግምት የሚገቡበት ዝርዝሮት አሉት። የቀንድ ከብትም ሠላሳ ሲደርስ አንድ ባለአንድ ዓመት የሆነው ጥጃ ይከፈላል። የዚህም ዝርዝሮች አሉት።

ፊያት ጋር ስንመጣ ግን እንዲህ ያለ ዝርዝር እና የዘካ መክፈያ ታሪካዊ ሰነድ የለውም። እራሱን ችሎ አይቆምም። በስንዴ ቦታ ስንዴ እንጂ በስንዴ ቦታ ገብስ፣ በዲናር ቦታ ዲርሀም፣ በግመል ቦታ ተምር ሆኖ አይቆምም። ማለትም ሁሉም እራሱን ችሎ ሲቆም ፊያት ግን እራሱን አይችልም። ከአየር የቀጠነም በመሆኑ መቆሚያ የለውም። በየዓመቱ ብቻ ሳይሆን ከኮሎኒያሊዝም ድንበር ለድንበር ሲሸጋገር ይለያያል። ኢትዮጵያ ውስጥ የተከፈለበት ፊያት ኬንያ ሌላ ነው። ላቲን ብንሄድ ሌላ፣ አውሮፓ ሌላ ሆኖ ይዋዥቃል። ፊያት ጽድት ጥርት ያለ መረጃ ላይ ለሚቆመው ኢስላም መርሕ ሊሆን አይችልም። ሆኖም ግን በተለምዶ በወርቅና በጠገራ ብር ሲቀየስ ይስተዋላል። እንደነ ስንዴ፣ ገብስ ወይም ቴምር ባሉ በሌሎች ዕቃዎች ለምን አልተቀየሰም? እራሱን የቻለና ጥናት የሚፈልግ ጥያቄ ነው።

በ2013 ኢ.ኦ. የረመዷን ወር ላይ የገንዘብ ዘካ የ85 ግራም የወርቅ ሒሳብ ወደ ፊያት መገበያያ ሲቀየር 198,000 ብር ገደማ ነበር። በዋጋ ደረጃ ሦስት ዓይነት ዋጋዎች ነበሩ።

- ✓ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የወርቅ ዋጋ፣
- ✓ የዓለም አቀፍ የወርቅ ዋጋና
- ✓ የአዲስ አበባ ከተማ ሱቆች የወርቅ መሸጫዎች ዋጋ ናቸው።

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የወርቅ መግዣ ዋጋን ከግምት ማስገባት የተሸለ ይሆናል። ምክንያቱም ብቸኛና አስተማማኝ መረጃ ልናገኝ የምንችለው ከመሰል ተቋማት በመሆኑ ነው። ወርቅ ከግብይት ዕቃነት በመውጣቱ ብሔራዊ ባንክ አሊያም በሱቆች በጌጣጌጥነት ደረጃ ነው ልናገኘው የምንችለው። ለወደፊቱ ለሚመጣ ትውልድ መረጃ ሊሰጥ የሚችለው የብሔራዊ ባንኩን ስንወስድ ነው። ዘካ እንደ ሶላትና ጾም አምልኮ በመሆኑ መረጃዎችን በጥንቃቄ መሰደር እና ቢቻል ለሁሉም

ምእመን በቀላሉ ሊገኙ የሚችሉ መሆን ይገባቸዋል። ለዚህ ደግሞ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ዋጋ የተሻለ አስተማማኝ ነው። የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ በተራው ዋጋ የሚወስደው ከዓለም አቀፍ የወርቅ ገበያ ነው። ምክንያቱም ወርቅ ወደ ውጭ የሚላክ ዕቃ ስለሆነ ይህንን መሠረት ያደርጋል። የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ይህንን መነሻ ያደርግና እንደ ውጭ ምንዛሪ ፍላጎት ከወርቅ አምራቾች መግዣውን ከፍና ዝቅ ሊያደርገው፣ በድርድር ሊስማማ ይችላል። ለሁሉም አስማሚ የሆነው ግን ቁርጥ ያለ መረጃ የሚገኝለትን ነው።

በሊቃውንት ደረጃ የተሻለው መካከለኛ የወርቅ ጥራት ቢሆንም ቅሉ አሁንም ወርቅ ከግብይት መሣሪያነት በመውጣቱ የተሟላ መረጃ ያለው ንጹሕ የሚባለው 24 ካራት ወይም 999.99 ወርቅ ነው። የዚህ ዋጋ በ2013 ኢ.አ. ወይም በ1442 ሒጅሪያ ረመዷን መግቢያ መሠረት፡-

1. በዓለም አቀፍ እና በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ መነሻ መሠረት $56 የአሜሪካን ዶላር ገደማ ሲሆን በእለቱ የምንዛሪ ዋጋ በ41.70 ብናበዛው 2,335 ብር ይሆናል። በ85 ግራም ቢባዛ 198,425 ብር ይመጣል።
2. የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የሚገዛበት አማካይ የድርድር ዋጋ ከዓለም አቀፍ መነሻው ላይ 15% ብንጨምርበት 2,685 ብር ይሆናል። ግልጽ ለማድረግ እርስዎ ወርቅ ለመሸጥ ብሔራዊ ባንክ ቢሄዱ የዕለቱን የዓለም ዋጋ ያዩና እርሱ ላይ የሆነ ፐርሰንት ጨምሮ ይከፍሎታል ማለት ነው። በዚህኛው ምሳሌ የአንድ ግራም ወርቅ ዋጋ 2,685 ብር ሲሆን በ85 ግራም ብናበዛው 228,225 ብር ይደርሳል።
3. የአዲስ አበባ ከተማ የወርቅ ቤቶች አማካይ የጌጣጌጥ መሸጫ ዋጋ 3,500 ሆኖ ወደ ላይና ወደታች ይዋዥቅ ነበር። በተለይ የአዲስ ብር ኖት ለውጥ

ጋር ተያይዞ ለግምት ሁሉ አስቸግሮ ቆይቷል። በዚህ ግምታዊ ስሌት ብንሄድ የ85 ግራም ዋጋ 297,500 መሆኑ ነው።

በፉቀሐዎች አካሄድ መካከለኛ የተባለው ይመረጣል። መካከለኛ ስንል የጥራት ደረጃውን ነው። ግን ተገቢ መረጃ አይገኝም። ስለዚህ ነኛ ደረጃውን ወሰድን። በዋጋ ደግሞ ትልቁን ብንወስድ ዘካ መክፈል የነበረባቸው ሰዎች ከዘካ ውጭ እንዳይሆኑ ትንሹን ማለትም ቁጥር ነ ላይ ያለውን ነ98,425 ተወሰደ። ይህ መረጃ በየትኛውም ዘመን ቢፈለግ ከብሔራዊ ባንክም ይሁን ከዓለም አቀፍ የወርቅ ገበያ ማግኘት ይቻላል።

ወደ ዘካ ጥበቦቹ ስንመጣ፡-

ነጋዴ፡- አንድ ነጋዴ 85 ግራም ወርቅ ቢኖረው ነ98,425 ብር መንዝረነው የዚህ የዘካ ፐርሰንት ማለትም 2.5% ብንሠራው 4,960 ብር ይከፍላል። ቁጥር ስለሆነ እንዳያደናግሮት ልድገመው። በ2013 ረመዷን ከዕዳ ቀሪ ነ98,425 ብር ካለዎት 4,960 ብር ለሚገባቸው ምስኪኖች መስጠት ይኖርብዎታል።

አርብቶ አደር፡- ከአርባ ፍየል/በግ አንድ ለዘካ መክፈል አለበት። በተስተካከለ ኢኮኖሚ አርባዎቹ ፍየሎች ወደ ወርቅ ብንቀይራቸው በቀጥታ 85 ግራም ይመጣል። በፍየል ዘካ ከ40 አንድ ፍየል፣ በገንዘብ ዘካ እላይ ባሰላነው መሠረት ከነ98,425 ብር 4,960 ብር ይመጣል። አሁን (2013 ኢ.አ.) ገበያ ወጥተን ብናየው የፍየል ዋጋ ጋር ተቀራራቢ ነው። ከ40 ፍየል አንድ ፍየል ለዘካ የሚሰጠው ጋር ተመሳሳይ ወደ መሆን ይጠጋል። የተወሰነ ልዩነት ቢኖረው እንኳ ከፊያት መገበያያ ግሽበት አኳያ በነ400 ዓመት ቀርቶ በነ4 ቀናት ውስጥ እንኳ ብዙ ልዩነት ያመጣል። የወርቅና የፍየል ዋጋ ልዩነት ቢኖረው እንኳ የገበያ መዋዠቅ እንጂ መጋሸብ አይባልም። ምክንያቱም

ሁለቱም ንብረቶች ናቸው። የዋጋቀው ላይ ትኩረት በመስጠትና ምርት በመጨመር ይስተካከላል። አርተፊሻል ቁጥር በመጨመር የምናጫውተው አይደለም።

ከግሽበት አኳያ ብናየው ወርቅና ፍየል በ1,400 ዓመት ውስጥ ግሽበት አላሰዩም ማለት ይቻላል። ይህ የአላህ ተዓምር ነው። ስንዴም ጋር ተመሳሳይ ነገር እናገኛለን። የገበሬውና የነጋዴው ዘካ የሚሰላበት መነሻ ካፒታል ተመጣጣኝ ሲሆን፤ እንዲከፍሉ የተቀመጠውም ተመጣጣኝ ነው። ለ85 ግራም ወርቅ እና ለ40 ፍየል የሚከፈለው ዘካ አንድ ፍየል መምጣቱን አይተናል። ይህ የሥርዓቱ ጥልቅ ጥበበኛነት ያመላክታል። ፊያት ላይ ስንሄድ ግን መሬት ላይ ለመተርጎም የሚያዳግት የቁጥር ጨዋታ እናገኛለን።

በተስተካከለ የኢኮኖሚ ሥርዓት የአርባ ፍየል፣ የሠላሳ ከብት፣ የአምስት ግመል፣ የ85 ግራም ወርቅ እና የ595 ግራም ጠገራ ብር ዋጋ ተመሳሳይ ወለል አካባቢ መገኘት ወይም በትየዩ ተናባቢ መሆን ይጠበቅበታል። ከተዛባ በዚያ ሴክተር ትኩረት የሚሻ የኢኮኖሚ መዛባት አለ ማለት ነው።

የምግብ እህሎች ላይ ግን የዘካ መነሻው ዝቅ ይላል። የእህል የዘካ መነሻ ስድስት ኩንታል ገደማ ነው። ነቢያችን ﷺ የእህል ዘካ ያስቀመጡት አምስት “ወስቅ” ሲደርስ ነው። ወደ ዘመናዊ የሜትሪክ ልኬት ሲቀየር 610 ኪሎግራም ይመጣል። የዚህን ያህል የእህል ምርት ያለው ሰው ዘካ መስጠት ይጠበቅበታል። በዝናብ የተመረተ ከሆነ ከአስር አንድ እጅ (10%) ሲሆን በመስኖ ወይም በተጨማሪ ጉልበት የተመረቱ ከሆኑ 5% የመክፈል ግዴታ አለባቸው። እህል ላይ ዘካም ይሁን አራጣ በጣም ትኩረት ተሰጥቶአቸዋል። ምክንያቱም የዘካም ይሁን የአራጣ ትልቁ ዓላማው ሰዎች ምግብ አጥተው እንዳይቸገሩ ነው።

ዘካ የእስልምና አንዱ መቆሚያ ምሰሶ መሆኑ የራሱ ጥልቅ ነገር እንደሚኖረው እሙን ነው። የዘካ ሳይንስና ጥበብ አልተነካም ወይም ተዘንግቷል። ምክንያቱም ወደኋላ ወደ 9ኛው እና 13ኛው ክፍለዘመን መካከል ወደነበሩ ሙስሊም ግዛት መዛግብት ስንሔድ ብዙ ውስብስብ የሒሳብ ቀመሮችን እናገኛለን። የዘካ፣ ውርስና ሌሎች ኃይማኖታዊ ሳይንሶች ጋር የተያያዙ ናቸው። በተጠቀሰው ክፍለዘመናት ሙስሊሞች በሒሳብ ከፍታ የደረሱበት ወቅት እንደነበር ታሪኮች ያስረዳሉ። የዘካ መተሳሰቦሽ አንዱ መነሻ ሆኖአቸዋል። የማዕድናት ገንዘብ፣ እህል፣ ጥራጥሬና ለምግብነት የሚውሉ እንስሳት ጋር በመካከላቸው ያሉትን የዘካ “proportion” ስናሰላ የኢኮኖሚ ሚዛን (Economy Optimality) እናገኛለን። የዘጠነኛው ክፍለዘመን ሸይኾች በ Mathimatics coefficient ፎርሙላ ይሠሩት ነበር።

መንግሥት እነዚህ ፎርሙላዎችን በመጠቀም ለጌጣጌጥና ለግብይት የሚውለውን ወርቅ ይተምናል። በእርግጥ ነቢያችን ﷺ ወርቅን በክብደት ብቻ ስላስቀመጡትና ለወንድ በመከልከሉ ጌጣጌጥ አይበዛም። ግልጽ ለማድረግ ጌጣጌጥ ተጨማሪ የዕደጥበብ ዋጋ (values) ስላለው ዋጋው ይጨምራል። ወደ ገንዘብ ልቀይረው ያለ ሰው በክብደቱ እንጂ በዲዛይኑ አይሸጠውም። የዲዛይን ዋጋ አሻሚ ስለሆነ እስልምና ከአሻሚነት እርግጠኛነት ስለሚያዝ በክብደት ብቻ አድርጎታል። ጌጣጌጥ አደርጋለሁ ያለ ሰው ሲለውጠው በክብደቱ እንደሚለውጠው አስቦ ነው። ልክ ልብስ ገዝቶ እስኪያልቅ እንደሚጠቀም ሰው ነው።

በስብከት ስንጠቀልለው፡- ዘካ የኢኮኖሚ ሚዛን መቆጣጠሪያ መሳሪያ ነው። በዚህ እትም ወደ ሒሳባዊ ቁጥሮችና ቀመሮች መግባት አልተፈለገም። በመንፈሳዊ ሰበካው በኩል ይህንን የንዑስ ንዑስ ርዕስ ስንጠቀልለው፤ ሶላት (ስግደት) የመልካም ጸባይ ወሰን እንደሆነው ሁሉ ዘካ የኢኮኖሚ ፍትሐዊነት ወሰን ነው። ጸባያችን

ሶላታችን እንደሚመስለው ሁሉ ኢኮኖሚያችንም ዘካችንን ይመስላል። የሶላት ማማር የጸባይ ማማር እንደሆነ በቁርአን እና በሀዲስ እናገኛለን፤ ማለትም ጸባያችን ከተበላሸ የሰገድነው ሶላታችን መበላሸት ምልክት ይሰጠናል። በተለይ ዝሙት ከሶላት ጋር ይያያዘል። ሶላት ዝሙትን ይከላከላል። የገንዘብ አራጣ ንብረትን አመድ እንደሚያደርገው፤ ዝሙት ፊትን ጨለማ ያለብሳል። ምጽዋት ወይም ዘካ ንብረትን እንደሚያፋፋው፤ ሶላት ፊትን ብርሀን ያለብሳል። ዝሙት ቆሻሻ ሥራ በመሆኑ ዝሙት ላይ የሚሆን ሰው ለሶላት አይነሳሳም። ምክንያቱም ሶላትና ቆሻሻ አብረው አይኖሩም። በተመሳሳዩ በግልም ይሁን በማኅበረሰብ ደረጃ የኢኮኖሚ ብልሽትና የሚዛን መዛባት (imbalances) ከተፈጠረ የዘካችን ስነሥርዓት ብልሹ መሆኑ መጠራጠር የለብንም።

ፈያት ነክ የሌሎች ንብረቶች ዘካ፡- ከኢስላም የኢኮኖሚ ውጭ ያለ ሙስሊም ነዋሪ ማለትም የአሁን ዘመን ሙስሊሞች ጋር ያሉ ጡረታ፣ አክሲዮን፣ ደመወዝ፣ ወዘተ. ጉዳዮች የዘካ አካል የሚሆኑበት አግባብ ይኖራል። ሆኖም ግን ለዘካ የተቀመጡ ቅደም ተከተሎች ማሟላት አለበት። ምሳሌ፡- ገንዘቡ የዘካ መክፈያ ወለል (ኒሷብ)፣ እንዲሁም የእፎይታ ጊዜ (አንድ ዓመት - ሀውል) ያለፈው መሆኑ ይታያል። ከዚህ በተጨማሪ ሙሉ ለሙሉ በራስ ቁጥጥር ስር የነባ ወይም እንደሚነባ እርግጠኛ የተኾነበት መሆን ይኖርበታል።

ጡረታ እና ፕሮቪደንት ፈንድ ላይ ዘካ ለማስላት አዋጆቹ ይወስኑታል። ደመወዝም የአሠሪና ሠራተኛ አዋጆችና የድርጅት መመሪያዎች መታየት ሊኖርባቸው ነው። አክሲዮንም ጋር ስንመጣ ከንግድና የታክስ ሕጎች በተጨማሪ የድርጅቱ የመመስረቻና መተዳደሪያ ደንቦች ከግምት ይገባሉ። በብድርና በዱቤ ሽያጭ የወጣ ተሰብሳቢ ገንዘብ (Receivables) የተሰብሳቢነት ታሪክ (Collection history)

ይታያል። ዘካ ሲሰላ የግልም ይሁን የንግድ ዕዳዎች (Payables) ይቀነሳሉ። እዚህ ጋር የመንግሥት ግብር ዕዳ በመሆኑ ከዕዳዎች ጋር ይገባል እንጂ እንደ ዘካ አይቆጠርም። ታክስ ስለምከፍል ዘካ አይመለከተኝም ማለት አይሆንም። ዘካ የሚከፈለው ለአላህ ነው። የእስልምና የኢኮኖሚ ሲስተም ውስጥ ታክስ የለምና። ታክስን እንደ ዕዳ ሲያዝ የሀገሪቷ የታክስ አዋጆችና መመሪያዎች ከግምት መግባት አለባቸው። ምክንያቱም "ቁርጥ ግብር" ያለባቸው ዘርፎች እንዳሉ ሁሉ፤ እስከ አምስት ዓመት የይርጋ ጊዜ ድረስ መንግሥት ሊጠይቅባቸው የሚችሉ የንግድ ዓይነቶች አሉ።

የዘካ አስተዳዳሪ፡- ዘካ ለመሰብሰብ የተሻሉ የሚባሉት የነቢያችን ﷺ ቤተሰቦች ናቸው። ምክንያቱም የዘካ ገንዘብ በእነርሱ ላይ እርም ነች። በትክክል እየሰበሰቡ ማከፋፈል ይችላሉ። ምክንያቱም በሶሺያሊዝም ከሄድን ታክስና ወለድ አነስተኛ ነው ቢባልም፣ እንዲሁም የመንግሥት ናቸው ቢባልም ቅሉ፣ የመንግሥት ሳይሆኑ የመንግሥት ባለሥልጣናት ናቸው። የሶሻሊስት ሀገራት መሪዎች ከካፒታሊስት ያልተናነሱ ዘራፊና አምባገነን ናቸው። ዘካም ሱልጣኖችና አሚሮች እንዳይፈነጩበት የነቢዩ ﷺ ቤተሰቦች (አህሉል በይቶች) ቢይዙት ለፍትሕ የተሻለ ነው።

اللَّهُمَّ صَلِّ عَلَىٰ سَيِّدِنَا مُحَمَّدٍ وَعَلَىٰ آلِهِ وَصَحْبِهِ وَسَلِّمْ

የዘካ ዓላማ ከካፒታሊዝሙ ወለድና ታክስ ጋር በማነጻጸር፡-

የካፒታሊዝም መቆሚያ ታክስ እና ወለድ መሆናቸውን ከላይ አይተናል። በኢስላማዊ ኢኮኖሚ ሲስተም ደግሞ ሁለቱም የሉም። ወይም ታክስ በዘካ እና ጂዝያ ሲተካ ወለድ ውጉዝ ነው። ሁለቱ ሲስተሞች ተቃራኒ ናቸው የማለት ያህል ያደርሳል።

1. የካፒታሊዝም ታክስ ከንግድ ገቢ (Income) ላይ ሲይያዝ፤ የኢስላም ዘካ ግን ከሀብት (wealth) ላይ ነው።
2. ታክስ ሥራን ሲያጠቃ፤ ዘካ ግን የተቀመጠ ገንዘብን ወደ ሥራ ያስገባል።
3. ታክስ ገንዘቦችን ወደ አንድ የመንግሥት ቋት አስገብቶ ሲያስር፤ ዘካ ግን ያለሥራ የተቀመጡትን እየቆረሰ 85 ግራም ወርቅ በታች እስኪወርዱ ድረስ ወደ ሥራ ያሰራጫቸዋል። ምክንያቱም ወደ ሥራና ሰው መዟዟር አለባቸው።
4. ታክስ ደሀ ላይ ይበልጥ ሲጫን፤ ዘካ ግን ከሀብታም ላይ ብቻ ነው።
5. ታክስ በአብዛኛው አሠባሰቡ ወርሀዊ ዕለታዊ ሲሆን፤ ዘካ ዓመታዊ ነው።
6. ታክስ ሀብቶችን ወደ አንድ አቅጣጫ ወደ ላይ ሲያተምም (ሲያስጉዝ)፤ ዘካ የሀብታም የተከማቸ ንብረቱን (Wealth) ወደ ደሀ ያወርዳል።
7. ታክስ እና ወለድ ተደጋጋፊ ሲሆኑ፤ ዘካና ወለድ ተጻራሪ ናቸው።
8. ካፒታሊስት በተከማቸው ሀብት አስይዞ ከባንክ መበደር ያልቻሉ የድሆችን ቁጠባ ሲበደር፤ በኢስላም በሀብቱ ለደሀ ይሰጣል፣ ምንዳውን ከአላህ ፈልጎ በነጻ ያበድራል።
9. ካፒታሊስት ከባንክ የቆጣቢዎችን ገንዘብ ይዞ ዞሮ ሀብቶቻቸውን ሲገዛ፤ በኢስላም በነጻ አበድሮ ሀብት እንዲያፈሩ ይረዳል።

10. በካፒታሊስት ለባንክ የከፈለው ወለድ ለታክስ ማቀናነሻ ሲውል፤ በኢስላም ተበዳሪ የሚከፍለው ወለድ ስለሌለ ከንጹሕ ሀብቱ ላይ ዘካ ይከፍላል።
11. በካፒታሊዝም የደሀ ድርሻ እየሠሩ እና ታክስ እየከፈሉ መቆጠብና ሀብታሞች ሲያካብቱ ማየትና ማገልገል ሲሆን፤ በኢስላም የደሀ ድርሻ ለፍተው እየሰሩ ለዘካ ከፋይነት መሸቀዳደም ነው።
12. በካፒታሊዝም ሀብታምና ደሀ በተለያዩ ማዕቀፎች ሲውሉ፤ በኢስላም ሀብታምና ደሀ በአንድ መስጂድ እግር ለእግርና ትከሻ ለትከሻ ገጥመው ይሰግዳሉ።
13. በካፒታሊዝም ሀብታምና ባንክ በደሀ ብር ሲሰሩ፤ በኢስላም ሀብታም ለደሀ የመስጠት ገዴታ አለበት።
14. በካፒታሊዝም በጣም የሚሰቀጥጠው ድሆች የገቢ ታክስ (Direct tax) ከፍለው ያጠራቀሙት ገንዘብ የወጪ ታክስ (የተጨማሪ እሴት ታክስ - Indirect tax) ይመለከተዋል። በኢስላም የገቢና የወጪ ታክስ የሚባል የለም።
15. በካፒታሊዝም ተበዳሪ መክፈል ካልቻለ ተነባባሪ ወለድ ሲጣልበት፤ በኢስላም በነጻ የተበደረ ሰው መክፈል ቢያቅተው ከዘካ ገንዘብ ይከፈልለታል። (ከላይ ከተብራራው ከስምንቱ 6ኛው ተከፋይ)
16. በካፒታሊዝም ተበዳሪ ተነባባሪ ወለድ ተጥሎበት መክፈል ካልቻለ ወደ ባርነት ወይም አኗኗሪነት ሲገባ፤ በኢስላም የዘካ ገንዘብ ለባሪያ ነጻ ማውጫነት ወይም ወደ ጨዋ ነዋሪነት መቀላቀያ ይከፈላል። (ከስምንቱ ውስጥ 5ኛው ምድብ)
17. ዘካ ለዘመድ መስጠት ተወዳጅ ሲሆን ታክስ ለማይታወቅ ገሸር ይሰጣል።

18. ታክስ መንግሥት ከሌለ የማይሰበሰብ ሲሆን፤ ዘካ መንግሥት ኖረም አልኖረም ይከፈላል።
19. ታክስ መንግሥት ብቻ ሰብስቦ ሲያከፋፍለው፤ ዘካ በመንግሥትም በግለሰብም ደረጃ መከፈልና መሠራጨት ይችላሉ።
20. ወለድ፣ ታክስና ሥልጣን ተያያዥ ሲሆኑ፤ ዘካ ግን ይህንን በደል ወይም ጥምረት አይቀበልም። በኢስላማዊ መንግሥት ደረጃ የዘካ ኃላፊዎች ዘካ እርም የተደረገባቸው ናቸው። እነርሱ በሌሉበት ጊዜ አላህን ፈሪ ሊቃውንት ይሰበስቡታል። እነዚህም ባይኖሩ ሰው በግሉ ይከፍለዋል።

የታክስ ጉዳት በኢኮኖሚ ላይ

ይህ ነጥብ ሲነሳ ብዙ ሰው ሊደነግጥ ይችላል። ምክንያቱም "ታክስ ገቢ ነው" የሚል እምነት አጽንተናል። ሆኖም ግን ታክስ ገቢ ሳይሆን ገቢን ከሚንከባከበው ሠራተኛ ኪስ ወደ "ሚደፋፋው" መንግሥት ካዝና ነው የሚሄደው። የቁማር ገንዘብ ከተበይ ኪስ ወደ በይ ኪስ እንደሚሄድ ዓይነት ሽግግር ነው ያለው። አብዛኛው የቁማር ዓይነት በአንዱ ኪሳራ ሌላው የሚያገኝበት (win-lose) ነው። ብዙ ታክስ መሰብሰብ ከጥቅሙ ጉዳቱ ያመዝናል። የሙስና ዋነኛ ፈረሱ የታክስ መብዛት ነው። በተለይ ሥልጣንና ንግድ በተቆራኙበት የካፒታሊዝም ሥርዓት ውስጥ "ታክስ የሙስና ችግኝ" ነው። ሀብታም መሆኛ ዋነኛው መንገድ ታክስን ማጭበርበር እንደሆነ ከታመነ ውሎ አድሯል። ታክስና ቀረጥ የምርትና የጥሬ ዕቃ ግብዓት ጭምር ላይ ስላለ፤ ግብአት ሲገዛ ታክስ ያጭበረበረ ሰው የተረጋገጠ ትርፍ አግኝቷል። ስለዚህ ከባለሥልጣን ጋር ይቆራኛል። ሥልጣን ደግሞ በጥቂት ሰዎች እጅ ነው። ብዙ ደሀና ጥቂት ሀብታም ከሚፈጥሩ ነገሮች ከአራጣ ጎን ለጎን ታክስ ዋነኛው ነው።

ያደጉ የሚባሉ ሀገሮች ለዕድገታቸው ትልቁን አስተዋጽዖ ያበረከተው ታክስን መቀነስና ሰዎች እንዲሠሩ መልቀቅ ነው። ዜጋቸው ሲያድግ ያገኙታል። ድሕነት እንዲጠፋም ተፈልጎ፣ ሠራተኛውን በታክስና ግብር አሸማቆና አስሮ፣ በታክስ ስም ገንዘቦች ከዝውውር ወደ ገንዘብ ሚኒስቴር ካዝና ታስረው፣ ብዙ ገቢም ተፈልጎ እንዴት ሊጣጣም ይችላል? በፍጹም! ሌላው ችግር ዓለማችን ተማርኩኝ ባሉ ማይማን ስለተሞላች እና የተግባር ተሞክሮና የችግራቸው መፍትሔ ቢኖራቸውም "አልተማርኩም" ብለው የተሸበቡ የማኅበረሰብ ዓይን አብራዎች ከፊት አለመምጣታቸዉ ነው ይላሉ የሶሺዮሎጂ ምሁሩ ዶክተር ዓሊ ሸሪዓቲ። ሲያክሉም በአንድ ሀገር ውስጥ እንኳ መፍትሔና ውጤቱ ከከተማ ከተማ ይለያል። ብዙ ሀገራት የሚሳሳቱት የሌላ ሀገር ጥናት ቀጥታ አምጥቶ ለመተገበር ሲሞክሩ መፈትሔው ከችግሩ የባሰ ችግር ይሆናል። የተማረው ከመሥራት ይልቅ ተቀጣሪ የታክስ ተጧሪ ነው። አገልጋይ ይባላል እንጂ ተገልጋይ ነው።

በኢትዮጵያችን ነባራዊ ሁኔታ ከድሕነታችን ምንጮች አንዱ የታክስ ሲስተማችን ነው። ይህ ከፊውዳሉ ሥርዓት ጀምሮ የመጣ ነው። የመሬት ከበርቴው ወይም ፊውዳሉ ለጭሰኛው መሬት ይሰጠውና ሚሶ እንዲያስገባ ያዘዋል። ለገባሩ ፈተና የሆነው ማምረት ሳይሆን ተሸክሞ ፊውዳሉ ድረስ መውሰድ ነበር። "የተሸከምኩት ብዙ ሰላመረትኩም አይደል?" ብሎ ምርት መቀነስ ጀመረ። ምርት ሲቀንስ ሸክምና ቁጥጥር የቀነሰለት ጊዜ ጭራሽ ማምረቱንም ተወ። ገባሩም ደሀ፣ መንግሥትም ደሀ ሆኑ። ይህንን ጉዳይ ፕሮፌሰር መስፍን ወልደማርያም በተለያዩ መጻሕፍታቸው ደጋግመው ይወቅሱታል።

ከምዕተ ዓመት በኋላ አሁንም ያው ነው። አንድ ሠራተኛ ብዙ በተንቀሳቀሰ ቁጥር፤ ቁጥጥሩ ይከፋል። አዲቱ ይሰፋል። በሕጋዊ ፈቃድ ከመንቀሳቀስ ይልቅ

ያለፈቃድ አየር ላይ መሥራት ተመራጭ ነው። ትልቁ ጥያቄ “ሕጎቹ ሕጋዊ ናቸውን” የሚል ነው። ምክንያቱም ሰዎች በተፈጥሮ ሕገ-ልቦና ስላላቸው የተፈጥሮን ሕግ አይጥሱም። ባይሆን የሰው ሰራሽ ሕጎች የሰዎችን አኗኗር ይጥሳሉ። በአጼዎች ወይም በፊውዳሎች ዘመን የሚያሳስር ሕግ በደርጎች ኮሚዩኒስቶች ዘመን ግን ያሾም ነበር። በደርጎች የሚያሳስረው በኢሕአዴጎች ሲያሾም እንዳየነው አሁን በብልጽግናዎች መልሶ ተገላበጠ። ምናልባት ተዋናዮቹ እኒያው ጥቂት ሰዎች ናቸው።

አንድ ሰው አየር በአየር መንቀሳቀሱ ችግር አይደለም። ችግር የሚሆነው ለሰው ጤና የሚጎዳ፣ ጊዜው ያለፈበት፣ ባሕል የሚያበላሽ፣ አየር የሚበክል፣ ንብረት ከሀገር የሚያሸሽ የሆነ ድርጊት ውስጥ የገባ ጊዜ ነው። የመንግሥት ተቀጣሪዎች ከዚህ ይልቅ ትኩረት የሚሰጡት ለገቢ ነው። ገና በጥናት ተፈትሾ ያልታየና አእምሮን የሚነድል ጥያቄ ባነሳላችሁ “ብሔራዊ ባንክ የቁጥር ገንዘብ ወይም ባዶ ፊያት በነጻ እያሰራጨ፣ ገቢዎችና ጉምሩክ ያንኑ ቁጥር እያስለቀሰና እያሸበረ መሰብሰቡ ጥቅሙ ምንድን ነው”? ከስር በመጠኑ ሌላ ክፍል ላይ ተነካክቷል። ግን ለብቻው ጥናት ይፈልጋል።

አንድ ነዋሪ ከማንም ጠላት በላይ የገቢዎችና ጉምሩክ ሠራተኛን ይፈራል። እነርሱ ደግሞ ቅጣቱን በመንተራስ እንደ ግል ገቢያቸው አይተውታል። ሰው ከመሥራት ይልቅ አለመሥራትን ይመርጣል። በጥናት ባይመረኮዝም ከምናውቀው ኑሮአችን በሀገራችን “ሥራ አለው” የሚባለው ሰው ከ24 ሰዓት ውስጥ ስድስት ሰዓት እንኳ ላይሠራ ይችላል። ስምንት ሰዓት ቢተኛ ትርፍ የሆነ አሥር ሰዓት አለው። ገቢው አናሳ በመሆኑና ሰፊ የባከነ ሰዓት ስላለው ለወንጀል ይነሳሳል። ወይም የአመጽ ቅጥረኛ ይሆናል። ይህንን ለመቆጣጠር ተጨማሪ የጸጥታ ኃይል ያስፈልጋል። ለጸጥታ ኃይሉ ደመወዝ፤ ተጨማሪ ገቢ ሊያስፈልግ ነው። ከዚያ ሌላ ሥራ ላይ ካለ ሰው ሊወሰድ ነው። እርሱም በጊዜ ሒደት ወደ ድሕነት ሊወርድና ልጆቹን ማሳደግ

ያቅተውና ተጨማሪ ቦዘኔ ያፈራል። እንዲህ ያለ የአዙሪት ክበብ (Vicious circle) ከመውደቅ፤ ዜጎች ፖሊስ እንዳያስፈልጋቸው ማድረግ ይቀላል። አንድ ሰው በሥራ ተወጥሮ ፖሊስ ካልፈለገ ብዙ ታክስ ከፍሏል። ፖሊስ ያልኩት በቀላሉ ነው። አንድ ቦዘኔ የሚፈጥረው ብክነት ለገንዘብ ግምት አይመችም። ካፒታሊዝም እስካለ ድረስ ታክስና ወለድ አይቀሩም። ሲበዙ ከድህነትና ሙስና ውጭ ጸጋ አያመጡም። በቀነስናቸው ቁጥር ሀገር ታድጋለች። ምክንያቱም ቁጥር እንጂ ምርት ስላልሆኑ። የምንሰበስበውም ከኬንያ ወይም ካናዳ ወይም ቡርኪናፋሶ ወይም ቻይና ሳይሆን እዚሁ ጠንክሮ ከሚሠራ ዜጋችን ነው። የምናስገብረው ሌላ ሀገርን በቅኝ ይዘን ወይም በጦር ድል አድርገን ሳይሆን እዚሁ ያሉ ታታሪዎችን ነው። ታክስ የሚያስፈልገው በግል የማይሠሩ እንደ መከላከያ፣ ፖሊስ፣ ዳኝነት፣ መንገድ፣ ጤና፣ ትምህርት የመሳሰሉ ልማቶች በመንግሥት እንዲሠሩ ነው። የታክስ ዓላማ ለዜጋ ጥቅም እስከሆነ ድረስ መቀነሱ የተሻለ እስከሆነ ድረስ መታየት አለበት። ታክስ ስንጨምር ገቢ የጨመርን ቢመስለንም፣ ምርትና የገቢ መንገዶችን እየቀነስን ነው። ዘካን ተመራጭ የኢኮኖሚ ሲስተም የሚያደርገው ለዚህ ነው። የዘካ ገቢ ትንሽ ቢመስልም ሰዎች በሥራ ያካክሱታል። የታክስ ገቢ ብዙ ቢሆንም ሰዎች በቦዘኔነት ተያይዘው በሚመጡ ችግሮች ይፈጁታል።

አንድ ዜጋ “ታክስ አጭበረበረ” የሚባለው ግብር አለመክፈሉ ሳይሆን አለመሥራቱና አለመንቀሳቀሱ ነው። በቀላል ምሳሌ፦ በአዲስ አበባ ከተማ ሁለት ሚሊዮን እማወራዎች ቢኖሩ የቁጥራቸው ያህል የእንጀራና የዳቦ መጋገሪያ መሣሪያዎች ማለትም ምጣዶች ይኖራሉ። የመንግሥት ታክስና ፈቃድ በመፍራት ሥራ ፈተው ይውላሉ። እነዚህ እናቶች ብዙ ታክስ “እያጭበረበሩ” ናቸው። ጊዜ ያባክናሉ፣ ያልተገባ ወሬ ሊያሠራጩ ይችላሉ። ከሰዎች ምርጦች የሚባሉት እናቶች በሲስተሙ ምክንያት ይህንን ያህል ብክነት ካስከተሉ፣ ወትሮም እሳት የሆነው ወጣት

ምን ያህል ውድመት ሊያስከትል ይችላል ብሎ መገመት አይከብድም። ሰው በተፈጥሮው ጥሩ ነው። ሕግ ያከብራል። በካፒታሊስት የሚወጡ ሕጎች ግን ይጥሱታል፣ ይረግጡታል፣ ያፍኑታል። አፈናና ጭቆና ሲበዛ ያምጻል። መንግሥትን ይገለብጣል። ሆኖም ግን ሲስተሙ ያው ካፒታሊዝም በመሆኑ ተረኛ ጨቋኝ ይሆናል። ዓለም የዕውከት መድረክ ያደረጋትና የሀብታም/ደሀ መራራቅ የፈጠሩት የካፒታሊዝም ወለድና ታክስ ናቸው።

ታክስ ፍጹም አያስፈልግም ወይ ከተባለ አስፈላጊ ነው። በግለሰብ ደረጃ የማይሠሩ ሥራዎች ገቢያቸው ታክስና ግብር ናቸው። ታክስና ግብር የልማት መዋጮ ወይም የልማት አገልግሎት ኪራይ ናቸው። ምጣኔያቸው ከመንግሥት ርዕየተ ዓለምና ከፍ ሲልም ከመንግሥት ፍልስፍና ጋር የተያያዙ ናቸው። [58]

መ. ውርስ

ውርስ ሌላው የኢስላማዊ ኢኮኖሚ ማስተካከያ ነው። ከዘካ የተረፈ ሀብት ካለ፣ ዝም ብሎ አይከማችም። ወይም የጥቂት ግለሰቦች መጫወቻ አይሆንም። በሟች ኑዛዜም ብቻ አይሄድም። የሟች ኑዛዜ ከሸሪዓው ሕግ ጋር ከገጠመ ኑዛዜው ይቀደማል። ዕዳና ውለታ እንዲሁም ስእለት ካለ ይታያል። በተቃራኒው በግል ጸብ ምክንያት አይወርሱም ያላቸው ወራሽ ዘመዶች ቢኖሩ በሕጉ መሠረት ይወርሳሉ። ይህ ሕግ የእስልምና ዕውቀት ከሩብ በላይ የያዘ ነው። ግማሹን ነው ያሉም አሉ። ከእስልምና ዕውቀቶች ቀድመው የሚጠፉ ዕውቀቶች የተባለለት ነው። ብዙ የኢስላም ዘመን የሒሳብ ፎርሙላዎች ውርስን መሠረት አድርገው የተፈጠሩ ናቸው።

[58] ዝርዝራቸው ከዚህ ተከትሎ በወጣው መ-ገንዘብ መጽሐፍ ላይ ተብራርተዋል።

የዘመድ ጥልፍልፎሽ በውርስ ሕግ ይታያል። ሟች ቀጥታ ወደ ላይ አባትና አያት ሲኬድ የራሱ ጣጣ አለው። አባቱም እናቱም ወላጆች አሉዋቸው። አያቱ ሁለት ሚስት አግብተው ቢሆንስ? እናቱ ሌላ ቦታ አግብታ ተፋታ ወይም ባሏ ሞቶ ልጅ/ልጆች ይዛ መጥታ ቢሆንስ? እያለ ወደ ላይ ሲኬድ መአት ቅርንጫፎች አሉ። ወደ ታች ሲወረድ ልጅና የልጅ ልጆች አሉ። የቀድሞ ባዕድ አሁን ግን ዘመድ ደግሞ ሚስት አለች። ወደ ጎን ወንድም እና እህት አሉ። በአባትና በእናት የሚገናኙ ወይም በአንዱ ብቻ የሚገናኙ ይኖራሉ። እንዲሁም አሁንም ወደ ጎን ሲኬድ እነ አጎትና አክስት ስንወስድ፤ አጎትና አክስት በእናትና በአባት በኩል ይመጣሉ። የአጎት ልጅና የአክስት ልጆች ሲመጡ መጋባት አለ። ከሟች አባት ተጀምሮ ወደ ላይ ሲኬድ ብቻ ማትሪክሱ 124 የአያት ጥልፍልፎሽ ይሠራል። ስሌቱን በመቶዎች የሚያደርሱትም አሉ። የላይኞቹ በሞት ስለሚቀነሱ ወደ ታች ይብሳል። የጸታ ጉዳይ ሌላው ነው። አዲስ ልጅ ወይም እርግዝና ላይ እያለ ወላጁ የሞተ ይደመርበታል። ድርብ ጸታ የያዙም የፎርሙላው አካል ናቸው። የመጀመሪያ ወራሽ ባይኖር ቀጣይ ማን ይቀድማል በሚለው ይኬዳል። ድርሻውም እንደ ቅርበት ርቀት ነው። **በሁሉም አቅጣጫ ወራሽ ሲጠፋ "ከላላ"[59] ይባላል። መንግሥት ይወርሰዋል። የሕዝብ ሀብት ይሆናል።** እንደ ኢስላም የውርስን ሕግ ያብራራ ሳይንስም ይሁን የሕግ መጽሐፍ አይገኝም። ባይሆን ዕውቀቱ ቢመናመንም ሊቃውንቱ የአልጀብራ የሒሳብ ቀመሮችን ፈልስፈውበታል። በዚህ ምክንያት የተማረ የገጠር "ደረሳ (የኃይማኖት ተማሪ)" ከታላላቅ የሒሳብ ሊቅ የበለጠ የሒሳብ ቀመር ይችላል።

[59] ወራሽ የሌለው ማለት ሲሆን ኸሊፋው ዑመር (ረዲየሏሁ ዐንሁ) ሦስት ነገሮች አራጣ፣ ከላላ እና ኸሊፋ ቢብራሩልኝ እወድ ነበር ያሉዋቸው ውስጥ ከላላ አንዱ ነው።

ሠ. የጦር ምርኮ

እንደማንኛውም ማኅበረሰብ ኢስላማዊ ማኅበረሰብም የራሱ የመከላከያ ኃይል አለው። በጦርነት ሒደት የሚገኙ ሀብቶች ከውድመቶች ጋር ተሰልተው ለማኅበረሰቡ ይከፋፈላሉ። ይህም የአምስቲዮሽ ከዚያ አንድ አምስተኛው በዘካ ስሌት የስምንቲዮሽ ስሌት አለው። የተፈጥሮን ገንዘብ ከሚያጋሽቡ (ከሚያዋዥቁ) ነገሮች አንዱ የጦር ምርኮ ነው። የሀገሩ ምርት ያላስገኘው ንብረት ከውጭ ሀገራት በምርኮ ይገባል። አዳዲስ ገንዘቦች ወደ ገበያው ሲገቡ የምግብ እህል ግሽበት ሊፈጥር ይችላል። እንደ ፊያት ያለ ውድመት ግን አያመጣም። ምክንያቱም ባዶ ወረቀት ሳይሆን ንብረት በመሆኑ ነው።

ረ. ምጽዋት

ይህ እጅግ መሠረታዊ የኢኮኖሚ ማስተካከያ ዘርፍ ነው። ይህ ዘርፍ የግዴታ ዘካንም ጠቅልሎ የሚይዝበት አተረጓጎም ቢኖርም የውዴታና የውዴታ ግዴታ ምጽዋት ልንለው እንችላለን። ምጽዋት በቁርአን የአራጣ ተቃራኒ ሆኖ ይመጣል። ከካፒታሊስታዊም ሶሺያሊስታዊ ስጦታና ዕርዳታ በጣም ይለያል። ምክንያቱም የኢስላማዊ ስጦታ ከንብረቶች ውስጥ እጅግ ውዱ ወይም ሰጪው የሚጠቀመው እንጂ የናቀውና የሚጥለው መሆን የለበትም።

የምትወዱትን እስክትለግሱ ድረስ በጎን ሥራ (ዋጋውን) አታገኙም። ከምንም ነገር ብትለግሱ አላህ ያውቀዋል። (ቁርአን 3:92)

የሚሰጠውም የተለየ ጥቅም ወይም አጸፋ ፈልጎ መሆን የለበትም። ከተመጽዋች ልዩ ጥቅም ፍለጋ ልቦና ላይ ከወደቀ ወደ አራጣ ይገባል። ይህኛው ክፍል አራጣ በሚለው የመጽሐፉ ክፍል ላይ ተብራርቷል። ምንም ውለታ ሳይፈለግበት ተለግሶ

በኋላ ላይ የተመጽዋቹን ሞራል የሚነካ ነገር ከተሠራም ምጽዋቱ ይበላሻል። ለዚህም በርካታ የቁርአን አንቀጾች አሉ።

ልገሳው ዝም ብሎ የሚረጭ ሳይሆን ልክ እንደ ግዴታ ዘካ ቅደም ተከተል እና ሚዛን አለው። የሚሰጠውም ከፍላጎት ትርፉን ነው።

... ምንን እንደሚመጸውቱም (መጠኑን) ይጠይቁሀል። "ትርፍን (መጽውቱ)" በላቸው። ... (ቁርአን 2:219)

ምንን (ለማን) እንደሚለግሱ ይጠይቁሀል። ከመልካም ነገር የምትለግሱት፤ ለወላጆችና ለቅርብ ዘመዶች፣ ለየቲሞችም፣ ለድኾችም፣ ለመንገደኞችም ናቸው። ከበጎ ነገርም ማንኛውንም ብትሠሩ አላህ እርሱን ዐዋቂ ነው በላቸው። (ቁርአን 2:215)

ምጽዋት ትርፉ ነው ከተባለ ሰውየው የራሱን አሳልፎ እንዲለግስ አይገደድም። ከዚያ ከቅርብ ቤተሰብ ማለትም ከወላጅ ይጀምራል። በካፒታሊዝም ልግስናዎች ማስታወቂያዎች ናቸው። ሌላ ጥቅም ተፈልጎባቸው ይሰጣሉ። በኢስላማዊ ኢኮኖሚ ልግስና ከቤት ይጀምራል። የቤተሰብ ትክክለኛ ፍላጎት እና ችግር የሚያውቀው የቅርብ ሰው ነውና። እቤት ደሀ እያለ ውጭ መሄድ ልገሳ ሳይሆን ጉራ ነው። ይህንን አንቀጽ ይበልጥ የሚያብራራ ሌላ አንቀጽ አለ።

አላህንም ተገዙ። በእርሱም ምንንም አታጋሩ። በወላጆችና በቅርብ የዘመድና ባለቤትም፣ በየቲሞችም፣ በምስኪኖችም፣ በቅርብ ጎረቤትም፣ በሩቅ ጎረቤትም፣ በጎን ባልደረባም፣ በመንገደኞችም፣ እጆቻችሁም ንብረት ባደረጉዋቸው (ባሮች)፣ መልካም (ሥሩ)፤ አላህ ኩራተኛ ጉረኛ የኾነን ሰው አይወድም። (ቁርአን 4:36)

“በጎን ባልደረባም” ማለት በቁጥጥር ስር የሆነ ወይም የለመደ እንስሳት ናቸው ተብሏል። ጓደኛም ማለት ነው ያሉ ተንታኞችም አሉ። ድመት ወይም ውሻ አስሮ እያስራበ የሩቅ ሰው ቢጋብዝ ወይም ቢያበላ ቢያስቀጣው እንጂ አያስመነዳውም። ካልሆነም እንስሶቹ እድላቸውን እንዲሞክሩና ለቃቅመው እንዲበሉ መልቀቅ አለበትና ነው። ስለምጽዋት የትኛውም ኃይማኖት ጋር ቢኬድ እጅግ ሰፊ ነው። እዚሁ ልግታው።

ሰ. በልክ ማውጣት

ልገሳ በጣም ቢበረታታም ቅሉ አንድ ሰው ያለውን ሁሉ በትኖ ይቀመጥ አልተባለም። ወይም ቆጥቋጣና ጨባጣ እንዲሆንም አልተፈለገም። በዚህ መካከል የሆነ አሰጣጥ መስጠት አለበት።

(የአላህ ባሮች) እነዚያም በለገሱ ጊዜ የማያባክኑ የማይቆጥቡትም ናቸው። በዚህም መካከል (ልግሰናቸው) ትክክለኛ የኾነ ነው። (ቁርአን 25:67)

እጅህንም ወደ አንገትህ የታሰረች አታድርግ። መዘርጋትንም ሁሉ አትዘርጋት፤ የተወቀሰክ የተቆጨ ሽ ትኾናለህ። (ቁርአን 17:29)

የስግብግብ (ጨባጣ) ሰው አምሳያ በውሻ አንገት ዙሪያ በታሰረ ጠባብ ሰንሰለት አሾልኮ እንደሚሰጥ ነው። የአብዛኛው የውሻ ዝርያ የአንገትና ጭንቅላት ውፍረት ተቀራራቢ ስለሆነ ማሰሪያ ዘለበቱ የማነቅ ያህል በጣም ጠባብ ነው። በሌላ ምሳሌ እጁ የካንጋሮ እጅ እንደሆነ ኪሱ ጋር የማይደርስለት እንደማለት ይሆናል። ካንጋሮ የምትባለው እንስሳ ግልገሏን የምታዝልበት ኪስ ያለው ከሆዷ ላይ ነው። የምትራመደው በኋላ ሁለት እግሮቿና በጅራቷ በመታገዝ ሲሆን እጅ የሚመስለው የፊት እግሯ ሆዷ ጋር የሚገኘው ኪሷ ጋር አይደርስላትም። በተቃራኒው አገኘሁ

ብሎ የሚበትን ሰው አላህ የሚጠላው ጉረኛና ኩራተኛ ሰው ይሆናል። ስለዚህ ሲለግስ ሳይበትን፣ እንዲሁም ሳይሰስት፣ ከራሱና ከቤተሰቡ ጀምሮ በሒደት እየቀረፈ ይሄዳል። የኢስላም የኢኮኖሚ ሲስተም ለብቻው የራሱ መጽሐፍ ይፈልጋል።[60]

3.2. በሒደት እንጂ በአብዮት እንደማይፈታ

ልክ ችግሩን በውል ስንገነዘብ በመጀመሪያ ደረጃ አዕምሮአችን ላይ የሚመጣው "አብዮት" ነው። ሄነሪ ፎርድ እንደሚለው *"የዓለም ሕዝብ ሰለኛ የባንክ ሲስተም በውል ሊያውቅም እንጂ፣ ቢያውቅ ኖሮ ግን ከጠዋት በፊት አብዮት ይነሳ ነበር"*[61] ይላል። በመሆኑም አጉል የአሜሪካን ጥላቻ የትም ሊያደርሰንም። ማንም ሥልጣኔ ለሀገሩና ለወገኑ በጎ ነገር እንደሚያደርገውና ጠላቱን ደግሞ በሁሉም ሜዳ ለማሸነፍ እንደሚተጋው እነርሱም የተለየ ነገር አላደረጉም። የሀገራችንም መንግሥት የወሰድን እንደሆን የምንወቅስበት ብዙም ክፍተቶች አይታዩኝም። ምክንያቱም የኛም መንግሥት የተጠቀሰው የፊያት መገበያያ እና የመንግሥት (State) እና የሉአላዊነት ፍልስፍና ሒደት አካል ነው። ሀብታም ሀገራትም አልቻሉትም። ችግሩ ያለው እኛው ዘንድ፤ በተለይ ዑለሞቻችን (ሊቃውንት) ላይ ነው። ማሳበብ መፍትሔ አይደለም። በዚያ ላይ የብዙ ሥራዎቻችን ችግር ከጎል ነው የምንጀምረው፤ ማለትም "ጎል አግብተን ጨዋታ መጀመር ነው የምንፈልገው"።

ተፈጥሮአዊው አካሄድ ግን እንዲህ አይደለም። ሥራን ተለማምደን፣ በውጣ ውረድ ውስጥ አልፈን፣ ችግሩ ገብቶን፣ ያለውን ሲስተም አጢነን፣ በጉዳዩ ላይ የሰፋ ንቃተ ሕሊና ዳብሮ፣ ምን ይሻለናል ብሎ ተጨንቆ፣ የሁሉም ሰው መነጋገርያ ሆኖ፣

[60] የዚህ ክፍል ዝርዝሮች ከፊሎቹ ከአቡል አዕላ መውዱዲ "INTEREST" ከሚለው መጽሐፍ የተወሰዱ ናቸው።። የሕትመት ዝርዝሩ ከዚህ መጽሐፍ መጨረሻ ላይ አለ።።

[61] ዑለማኡል ሙነወራ ገጽ 4 (ከዋና ዋቢ መጻሕፍት ነው)

ተመካክሮ፣ ቀስ በቀስ ወይም በሒደት በአስርታት ወይም በመቶ ዓመታት ጊዜ ውስጥ የሚቀየር ይሆናል። የኛ ሥራ ቢያንስ ጥያቄውን ማንሳትና ጥርጊያ መንገዱን መጀመር ነው። በጣም በእርጋታ እንድናየው አደራም ጭምር ነው።

3.3. ያለውን ሲስተም መጠቀም

“እሱማ እየተጠቀምን አይደለም ወይ” የሚል ጥያቄ ይነሳል። ወደ መቀየር ስንነሳ “ኒያችንን (እሳቤያችንን)” እንቀይራለን። ነቢያችን ﷺ ወደ መዲና ሲሰደዱ ብዙ ሰዎች አብረው ተሰደዋል። ከእነዚህ ውስጥ ለአላህ፣ ለመልዕክተኛውና ለእምነቱ ብሎ ሀብት ንብረቱን ጥሎ የተሰደደ ነበር። በሌላ በኩል ፍቅረኛው የተሰደደችበት ሰው አብሮ ያንን አድካሚ ጉዞ ተከትሎአል።

በኢማም ቡኻሪና ሙስሊም ዘገባ መሠረት ነቢያችን ﷺ *“ሥራ ማለት በእሳቤ ነው። ሂያንዳንዱ ግለሰብ ያሰበው አለው። ሰደቱ ወደ አላህና መልዕክተኛው የሆነ፣ ሰደቱ ወደ አላህና መልዕክተኛው ነው፤ ሰደቱ ለዱንያ (ዓለማዊ ፍላጎት) ወይም ለሚያገባት ሴት ከሆነ ሰደቱ ለተሰደደለት ነገር ነው”* አሉ። ተመሳሳይ ድካም፣ ነገር ግን የተለያየ ግብ እንደ ማለት ነው።

አሁን ፊያትን እየተጠቀምን ያለነው ያለዕውቀት፣ መገደዳችን ሳናውቅ፣ ግባችንም ሳንተልም ይሆን ይሆናል። እሺ ችግሩን አወቅን እንበል። ግባችንም ተልመናል። ግን ዛሬውኑ ተነስተን የወረቀት መገበያያ (ፊያት) አራጣ በመሆኑ ሀራም (ክልክል) ነው ብለን ብንነሳና መጠቀም ብንተው ከሰዓታት በላይ መዝለቅ እንችላለን? አንችልም። ዓለም ሁሉ በዚሁ እየተገበያየ፤ አይደለም አንድ ግለሰብ

ይቅርና አንድ ሚሊዮን ሰው መጠቀም ቢያቆም “ምንም” ሊሆን አይችላል። ለማለት የተፈለገው ሲስተሙን መጠቀማችን እስካልቀረ ድረስ ጉዳት መቀነሱ የተሻለ ነው።

መካን ባለበት ትቶ ስደት ወደ መዲና፡- ነቢያችን ﷺ መካ ተወልደው፣ እዚያው አድገው፣ የማኅበረሰቡን የጣዖት አምልኮ ተጠይፈው ዋሻ ገብተው አላህን ይማጸኑ ነበር። መልዕክቱ መጥቶ ማስተማር ሲጀምሩ የመካ ጣዖቶችን በመስበር አልጀመሩም። ስለ አላህ አንድነት እና ኢጋር እንደሌለው ማሳወቃቸውን ተያያዙት። ለ13 ዓመታት የሚያስተምሩትና በኋላ ሶላት የታዘዙም ጊዜ የሰገዱት እዛው የሚቃወሙዋቸው ጣዖታት ያሉበት ካእባ ጋር ነበር። ከመካ ወደ መዲና ከተሰደዱ በኋላም ካዕባን ቂብላ (የሶላት አቅጣጫ) ሲደረግ ጣዖታቱ እዚያው ውስጥ ነበሩ። ሕዝባቸውን አስተምረው፣ ጣዖታቱ እንደማይጠቅሙና እንደማይጎዱ በደንብ ካሳመኑ በኋላ ሕዝቡ እራሱ ለመሰባበር ተረባረበ።

ገና ከመጀመሪያው ከትልቁ ጣዖት ቢጀምሩ ኖሮ፣ ጸቡ ከድንጋዩ ጋር ሆነ ማለት ነው። ድንጋዩ ምን አጠፋ? ጸቡ ከእርሱ ጋር ሳይሆን ከአምላኪዎቹና ከአምልኮኣቸው ጋር ነበር። ድንጋይ ቢሰበር ልቦች እስካልተስተካከሉ ድረስ በድንጋይ ይተካል። በሰዎች ልብ ትክክለኛውን መንገድ ካሰረጽነው ግን ልብና አእምሮ ሳይፈጽሙት እረፍት አያገኙም። ድንጋይን መስበር የተሻለ ውጤት የሚያስገኝ ከሆነ ከዚያ መጀመር ይቻል ይሆናል። ነቢዩ ኢብራሂም (ዐ.ሰ.) በልጅነታቸው ከድንጋይ ሰበራ እንደ ጀመሩ ይታወቃል። ሆኖም ግን ትልቁን ጣዖት ትተውት የሰበሩበትን ፋስ እላዩ ላይ አስቀምጠውት ነበር። ሰዎቹ ግን በጀ አላሉም። ነቢዩ ኢብራሂምን (ዐ.ሰ.) እሳት ውስጥ ጥለዋቸዋል። ከእሳቱ መዳናቸውን እያዩ እንኳ ሰዎቹ አላመኑም። ከሀገር አባረዋቸዋል። ነቢዩ ሙሀመድ ﷺ ጣዖት ከመስበር ባይጀምሩም ከሀገር

ተሰደዋል። በሁለቱም መንገድ ቢሆን ልፋት ይኖራል። ስለዚህ ለኛ የሚበጀውን መምረጥ ላይ ማተኮር አለብን። በጸሐፊው ዕይታ ግን ሲስተሙን እየተጠቀሙ ለመቀየር መታገል ነው።

አሮጌውን ባለበት ትተን አዲስ አማራጭ ማቅረብ፡- አንድ ከተማ ለመመሥረት ብዙ ዓመታት ይፈጃል። እንኳንስ ለሰው ልጆች የሚጠቅም ከተማ ማውደም ይቅርና ጣዖት እንኳ ለትምህርት ካልሆነ በስተቀር አይፈርስም። መቆየቱ የበለጠ ያስተምራል። ለታሪክ ይኖራል። እኛም ያለውን ሲስተም እንዳለ እንተወዋለን። ምክንያቱም ባንከሮቹ ኒኩሊየር ከመጠቀም፣ ስም ከማጥፋት፣ ከማይገናኙ ነገሮች ጋር ስማችንን ማገናኘታቸው አይቀርም። የዓለምን ጉሮሮ ይዘውታል። ሁሉም ነገር በእጃቸው ነው። እኛ ላይ ችግር ቢመጣ አላህ ለነብዩ ኢብራሂም (ዐ.ሰ.) "እንቺ እሳት ሆይ ለኢብራሂም ብርድና ሰላም ሁኝለት" እንዳለው እንባላለን ወይ? ወይስ እንደ ነቢዩ ሙሀመድ (ﷺ) ዋሻ ውስጥ ሸረሪት ድር ታደራልናለች? አላህ በምን እንደሚጠብቀን እና ምን እንደሚከፍለን አናውቅም። አላህን ከመመካት ጋር ስልቶቻችንን አሟጠን በመጠቀም ለመቀየር እንነሳለን።

በራሳችንም እንደምናውቀው ሰው ሳይበላ ከአንድ ቀን በላይ መቆየት አይችልም። እኛ ጀነት የመሰለ ቲዮሪ ብናቀርብ አብዛኛው ሰው አይቀበለንም። ምክንያቱም የሲስተሙ ትውልድ ነው። ይህኛው ትውልድ የድሮውን (ዕውነተኛውን) የገንዘብ ሥርዓት አልኖረበትም። አያውቀውም። በተጨማሪም ከሌላ ወገን የሚመጣው ጦርነት ቀላል አይደለም። በመሆኑም ሲስተሙን እንደ መሣሪያ መጠቀሙ የተሻለ ነው። **ዓላማችን ግን ሲስተሙን ማስለምም አይደለም። ግዑዝ ጣዖት አይሰልምም።** ነገር ግን በተረጋጋ ትምህርት እና ለውጥ በሚያሳይ ሥራ የሰዎችን ልብ መማረክ ያስፈልጋል። ሰዎች ከተፈጥሮአዊ ገንዘብ በመራቃቸው ተስፋ

አስቆራጭ ችጋር ውስጥ እንደወደቁ ማሳየት ነው። እኛ ወደ ባንክ የምንሄደው ባንኮችን በመቀየር "ኒያ (እሳቤ)" ነው። ሌሎች የሚሄዱት ግን በባንኮች ኑሮአቸውን ለመቀየር ነው። ኒያችን (ዓላማችን) እጅግ የተለያየ ነው። ባንኮች ባሉበት ይቀጥላሉ። ንብረታቸው የሕዝቡ ንብረት ነው። የሰለጠኑ ሠራተኞቻቸውም እንዲሁ። አፍርሰን አንገነባም። በሒደት ልዋጭ አስቀምጠን ነው ምረጡ የምንለው። ያለ መልካም ልዋጭ ሀራምን (ክልክልን) ቀድሞ ማስወገድ በቦታው የበለጠ ሀራም እንዲመጣ ሰዉን ማነሳሳት ነው። ሀላል ከጎን አስቀምጠን ሰዎችን መጥራት ግን ተፈጥሮአዊ አካሄድ ነው።

የኢስላማዊ ባንኮች ስህተት፡- እጅግ መጠንቀቅ ያለብን አማራጫችን መሠረቱን ኢስላማዊ ሳናደርገው በእነርሱ ባንክ ላይ ካደረግነው የአሸዋ ላይ ግንብ ነው። **"የወለድ ነጻ" ባንኮች ቁጥር አንድ ስህተትም ይኸው ነው።** ካፒታሊዝምን ለማስለም (Islamization of Capitalism) ሲሞክሩ ከቅርንጫፉ ሞከሩ። ሙከራቸውን አናወግዝም። ስህተታቸውን ማረም ግን የእኛ ኃላፊነት ነው። እነርሱ ሞክረው አልፈዋል። ተረኛ ባለታሪኮቹ እኛ ነን። ስህተቱን እንዳለ ከተቀበልነው ደራርበን እናሻግረዋለን። የታሪክ ተወቃሾች እንሆናለን። መሠረቱ በተበላሸ የገንዘብ ሲስተም ላይ ኢስላማዊ ብለው ለማስለም ሲሞክሩ ሁለት ጥፋት ፈጸሙ። (አንደኛው) አራጣን ሀላል አደረጉ። ምክንያቱም ባንኮቹ የተቋቋሙት በአራጣ ሲስተም በመሆኑ የሚያገለግሉት የካፒታሊዝም የኢኮኖሚ ሥርዓትን ነው። ወትሮም በዳይ ሥርዓት ነው። እዚህ ላይ በመመሥረት መሰል አራጣ አመጡ። እንደውም በተግባር የታየው የባሰ አራጣ ነው። በኢስላማዊ ባንኮች ስር በስፋት እናየዋለን። (ሁለተኛው) እስልምናን ሕግ የሥርዓቱ አገልጋይ አደረጉት። ሙስሊሞችን ጠቅልለውና በአንድ ቅርጫት ከተው በሁለት ሕግ እንዲዳኙ አደረጉዋቸው።

በፊያት ላይ መስርተውት ግራ ተጋብተው ምእመኑን ግራ አጋቡት። የኛዎቹን ብቻ እያልኩኝ ሳይሆን በዓለም አቀፍ ደረጃ የሚሠሩ “ኢስላማዊ ባንኮችን” ለማለት ነው። የኛዎቹ ገና ጅምር ላይ ናቸው። ገንዘብ መሰብሰብ ካልሆነ ወደ ሥራ ገና አልገቡም። ከመሆኑም ጋር በወለድ ደረጃ ካየነው አሁን ካለው “የኢስላማዊ መስኮት” የኮንቬንሽናሉ (የመደበኛው) ባንክ የሚመረጥባቸው ብዙ ነገሮች አሉ። የባንክ ሠራተኞች “ምኑ ነው ኢስላማዊ የሚባለው” ሲሏችሁ ሰምታችሁ ይሆናል። “ኢስላማዊ ባንክ” የተዋጣለት የሚሆነው በኢስላማዊ (ተፈጥሮአዊ) የገበያ ሥርዓት ሲሆን ነው። “ኢስላማዊ ባንክ” በቲዎሪ ደረጃ እንዴት እንደሚያምርና በፊያት ላይ በተግባር ሲተረጎም ግን እንዴት እንደሚያስጠይፍ በቀጣዮቹ ገጾች ለማየት እንሞክራለን። ምክንያቱም በፊያት ላይ ተግባራዊ ማድረግ አዳጋች ነውና።

ማጠቃለያ፡- ወደ ርዕሳችን ስንመለስ ለዘካ ፊያት እንደምንጠቀመው ሁሉ ኢኮኖሚያችን ተወስዶ አልቆ ቆላልፈው መውጫ ጊዜውን እንዳያራዝሙብን ሲስተሙን ቀጥታ አንነካውም። ከራሱ ከገባንበት ባንኮቹን የሚያፈርሱት እራሳቸው ባንከሮቹ ናቸው። ለምሳሌ ወረቀት ቀርቶአል ቢባል ሰዉ ወደየት የሚሄድ ይመስላችኋል? ወደ ባንክ? ምን ሊሠራለት? ወደ ተናቁ ገበሬዎችና አርብቶ አደሮች እንጂ! ትክክለኛ ሀብታሞች እነርሱ ናቸው።

“ሀብታሞችማ” የሆነ ፎቅ ውስጥ የተቀመጠና ባንክ የተሰኘ ተቋም ጋር ኮምፒዩተር ውስጥ የተጻፈ ቁጥር ነው ያላቸው። ከአየር የቀጠነ ቁጥርስ የማን ሆድ ውስጥ ይገባል? የባንክ ሠራተኞች ሳይቀሩ የካዝና ቁልፋቸውንና ከረባታቸውን ወርውረው ወደ ማሳ ነበር የሚሮጡት። አየር ላይ የቆመ ሲስተም ነው። እዛው እንዳለ ከጎኑ ተፈጥሮአዊ የግብይት ሥርዓት ቢዘረጋ ለመለወጥ 50 ዓመታት ላይፈጅ ይችላል።

3.4. የባንክ ወለድን (interest) ለባንኮች አለመተው

በባንክ ወለድ ጉዳይ ላይ በዓለም አቀፍ ስምምነት እስኪመስል ድረስ ሦስት ዓይነት የግለሰብ መፍትሔ ይታያል።

1. ግዴታ ሆኖብን ለመጠቀም ብሎ ዕድሜውን በግዴታ የሚገፋ
2. ወለዱን አውጥቶ ለምስኪን ወይም ደስ ላለው ሰው የሚሰጥ
3. ከምወዛገብ ብሎ ወለዱን ለባንክ የሚተው ወይም ከወለድ ነጻ በተባለ መስኮትና ባንክ የሚጠቀም

የመጀመሪያውን ካየን እስከመቼ የሚል ጥያቄ ያስነሳል። ግዴታ (ዶሩራ) የሚሆነው ለአንድ ወቅታዊ ችግር፤ አነስ ያለው ችግር አማራጭ ወይም ብቸኛ መፍትሔ ሲሆን ማለት ነው። በባንክ እየሆነ ያለው ግን ተስፋ ቆርጦ ዝም ብሎ ተፋጦ መቀመጥ ሆነ። ሁለተኛውን ስንወስድ ወለዱን ለምንሰጠው ምስኪን ጊዜያዊ ችግር ይፈታ እንደሆን እንጂ የባንክን አሠራርና የካፒታሊዝም ሲስተም ላይ የሚፈጥረው ለውጥ አይኖርም። የተቀናጀና የተደራጀ አይደለም። ሊሆንም አይመችም። ሦስተኛውን ስናይ ካለፉት ከሁለቱ የባሰ አደገኛ መፍትሔ ነው። ጭራሽ ባንኮችን ወይም ባንክ የከፈቱ ጥቂት ባለሐብቶችን ማፈርጠም ነው። ሲስተሙ በተለይ ካፒታሊዝም ዓለምን መምራት ከጀመረ ወዲህ የሚወግነው ለሀብታሞች ነው። ሀብታሞች ሀብታቸው ሲጨምር፤ ድሆች ድህነታቸው እየጨመረና ይብስ አገልጋይ እየሆኑ ይሄዳሉ። የዓለም ሀብት በጥቂት ግለሰቦች እጅ እንዲገባ አስችሏል። መፍትሔው ግን ይህንን ሲስተም አብሮ መቀላቀል ነው። "ጅቡ ከሚበላህ በልተኸው ተቀደስ" እንዲሉ የካፒታሊዝም ሲስተም እንዳይበላን አብረን እየበላን ለመለወጥ ማሰብ ነው። ክልክላትን እንብላ ሳይሆን እየመጣ ያለው ነገር ከዚያ በላይ ስለሆነ ነው። ኃይማኖትን በገፍ ከማስቀየር ጀምሮ ነፍስን እስከመንጠቅ ይዟል።

ግሽበትና ፊያት መቸም የማይለያዩ አንድ አካል እንደሆኑ በተደጋጋሚ አይተናል። የኛ የኢትዮጵያ የወረቀት ብር ብናይ እንኳ በሃያ ዓመታት ብቻ ከ3 እስከ 4 እጥፍ በላይ ጋሽቦኣል። በአጼ ኃ/ሥላሴ ዘመን በ1945 በአሜሪካ ፊላዴልፊያ የታተመው እና 75% በወርቅ የተደገፈው የኢትዮጵያ ኖት ያኔ በ2.45 የአሜሪካ ኖት ይመነዘር ነበር። በ2021 ኣጋማሽ 42.45 ብር ደርሶኣል። ይህ ማለት ብር 1,600% ጊዜ ወይም 16 እጥፍ በላይ ጋሽቧል ማለት ነው። ወርቅ ለወረቀቱ ብር ደግሞ ሌላ ግሽበት አለው።

በተቃራኒው በነቢያችን ﷺ ዘመን በወርቅ የሚገዙት ዕቃዎች ዛሬም ብናያቸው ዋጋቸው ተቀራራቢ ነው። ያኔ በአራት ግራም ከምናምን (አንድ ዲናር) ወርቅ የሚገዛ ዕቃ አሁንም ያው ነው። አንድ ዲናር ወርቅ በግራም ሒሳብ አንድ ሺህ ብር ብንለው ወደ 4,250 ብር ማለት ነው። ስለዚህ የማይዋዥቅ ገንዘብ ላይ ጨምሮ መውሰድ ወይም መስጠት በእርግጥም ወለድ ነው።

ፊያት መግበያያ ወለድ አለው/የለውም ብለን ለመከራከር ገንዘብ ሆኖ ችሎ መቆም አለበት። ሀላል "ሸሪዓ" እንዲቆምበት መጀመሪያ እራሱ ሀላል መሆን አለበት። ባንኮች "ወለድ" የሚል ስም የሰጡት ጭማሪ ገንዘብ ቀድመው በግሽበት የወሰዱብንን እንኳ አይተካልንም። ሌሎች እዚህ ጋር ለማንሳት ያልተመቹኝ ነገሮችን ትቼ ከ10 እስከ 20 ፐርሰንት በግሽበት ተወስዶብን ሲያበቃ 5 ፐርሰንት ሲመልሱልን ወለድ ነው ብለን መተው ማለት ሎጂካል አይደለም። ገና ከ5 እስከ 15 ፐርሰንት አንጡራ ገንዘብ ባንክ ጋር አለን። የርዕሳችን መስመር ያስተናል ተብሎ ባይፈራ ኖሮ የንግድ ባንኮቻችን ዳታዎች እዚህ ሥር በተተነተኑ ነበር። ወለድ ነው አይደለም ብለን ጥርጣሬ ውስጥ ለመግባት፤ ቢያንስ ግሽበት ከወለድ በታች መሆን አለበት።

3.5. ኮንቬንሽናል (መደበኛ) የፋይናንስ ኢንደስትሪዎችን መጠቀምና ባለቤት መሆን

“ጅቡ ከሚበላህ በልተኸው ተቀደስ” ነው ነገሩ። በይ እና የተበይ ተመልካች መሆን የካፒታሊስት ባንኮች ደሃውን በልተው ጨርሰውታል። ጅብነት አይገልጻቸውም። ኮንቬንሽናል ባንኮች በዳይ ናቸው እያልን እነሱኑ መክፈት ከበዳይ ተራ እንደመሰለፍ ማለት ስለሚመስል ማንኛችሁም ብትደነግጡ አልፈርድም። ዓለም ላይ ድህነት ያመጡት ባንኮች ናቸው የሚሉ በርካታ መጻሕፍትና ጥናቶችን ማግኘት እንችላለን። ባንክ ማለት የሀብታም እቁብ ነው። የደሀው ድርሻ እየለፉ የማይወጣ እቁብ መጣል ሲሆን፤ ለሀብታም ግን ድሆች ለፍተው ያመጡትን ወስዶ መጠቀም ነው። በቅርብ ዓመታት ከባንክና ከዱቤ (ክሬዲት) ሲስተም በፍጹም መውጣት አንችልም። በምዕራቡ ዓለም የአንድ ሰው ስብእና የሚለካው በዱቤ ታሪክ (Credit History) ነው። የብድር አወሳሰድና አመላለስ ታሪክ በዚያ ሀገር የምንኖርበትን ደረጃ ይወስናል። ሥራ ለመቀጠር፣ ድርጅት ለመክፈት፣ ኢንቨስትመንት ለማስፋፋት፣ በምርጫ ለመወዳደር፣ ዜግነት ለማግኘት፣ ወዘተ. የክሬዲት ታሪክ (Credit History & Credit Rating) ይታያል። ነዋሪዎች ከካሽ ይልቅ ክሬዲት ይጠቀማሉ። ይህ ሲስተም ወደኛም ሀገር እየመጣና እኛም ወደዚያ ሲስተም እየገባን ነው። የብድር አወሳሰዳችን እና አከፋፈላችን ለወደፊቱ ለሚኖረን የኢንቨስትመንት ሒደት ወሳኝ እየሆነ ነው።

በእኛ ሀገር አሠራርም ይሁን በሌሎች ሀገሮች ከባንክ ብድር ለማግኘት፦

በቲዎሪ፦ 5C ማሟላት ያስፈልጋል።

- ✓ Character የተበዳሪው የግል ጸባይ እና ታሪክ (ከወንጀል ነጻ መሆን፣ የቤተሰብ ሁኔታ፣ ያለፉ ተሞክሮዎች፣ ብድር ከፋይነት
- ✓ Capacity የተበዳሪው የመክፈል አቅም ወይም ትርፋማነት (በድርጅት ቢከስር የግል ይዞታ ጭምር ይታያል)
- ✓ Capital የድርጅቱ የካፒታል አቅም
- ✓ Condition የተሰማራበት የሥራ መስክ የወደፊት ዕጣ ፈንታ
- ✓ Collateral ይህ ሁሉ ከታየ በኋላ ለጠየቀው ብድር የሚያዝ በሰነድ የተረጋገጠ ቋሚ ንብረት ይታያል። ለእነዚህ ዝርዝር ፎርማሊቲዎች አሉት።

ይህንን አምስቱን ወደ ሁለት ምሰሶ ብንጠቀልላቸው ከባንክ መበደር የሚችለው አትራፊ ሥራ ላይ የተሰማራና የዋስትና ንብረት ያለው ሰው ብቻ ነው። ከሁለት አንዱ ምሰሶዎች የጎደለበት ሰው ከባንክ መበደር ስለማይችል፤ የእርሱ ቋሚ ድርሻ ይህንን ለቻሉ ሰዎች ለፍቶ መቆጠብ ነው። ሀብታም በደሀ ገንዘብ ሀብቱን እየጨመረ ሲሄድ፤ ደሀው ድህነቱን እየጨመረና አኗኗሪ ባሪያ እየሆነ ይሄዳል። መደበኛ ባንኮቹ መበደር ለማይችል ደሀ ያልተቋረጠ ዓመታዊ ትርፍ ያስባሉ። ለምሳሌ ቢያንስ 7% ትርፍ (ወለድ) ያስባሉ። "ከወለድ ነጻ" የሚባሉት ግን ይህንንም ርኅራሄ የላቸውም። ከወለድ ነጻ ብለው ይከለክላሉ። ጸሐፊው ለዚህም ነው መደበኞቹ ባንኮች መቅደም አለባቸው የሚለው። ምክንያቱም ለደሀው ትንሽም ቢሆን ርኅራሄ አላቸው። ለደሀ ዘካን እንደ እምነት/ክህደት ምሰሶ (አርካን) ያስቀመጠ ኢስላም፤ ለምን ሲባል ነው ኢስላማዊ ባንኮች ከካፒታሊዝም የባሰ ዘራፊ የሚሆኑት?

ለብድር የሚያስፈልጉ ቅድመ ሁኔታዎች፡-

1. ከገቢዎች ሚኒስቴር እና መሰል ተቋማት ግብር መክፈሉን ማረጋገጫ (ክሊራንስ)
2. የብድር ዓይነት ማመልከቻ
3. ያለፉ ዓመታት የሒሳብ ሪፖርቶች
4. የታደሰ ንግድ ፈቃድ
5. የዋና ምዝገባ
6. የሥራ አስኪያጅ የግብር ከፋይነት (ቲን) ሰርተፊኬት
7. የተበዳሪ ባል ወይም ሚስት የግብር ከፋይነት (ቲን) ሰርተፊኬት
8. የጋብቻ ወይም ያላገባ ሰርተፊኬት
9. የውክልና ማስረጃ (በውክልና ከሆነ)
10. የመመሥረቻ ጽሑፍ (ከአንድ በላይ አባላት ላሉት ድርጅት)
11. የመተዳደሪያ ደንብ (ከአንድ በላይ አባላት ላሉት ድርጅት)
12. የቃለ ጉባዔ (ከአንድ በላይ አባላት ላሉት ድርጅት)
13. የዋስትና ንብረት የባለቤትነት ማስረጃ (ካርታና ፕላን)
14. አስያዥ ሌላ ሰው ከሆነ የራሱና የባለቤቱ የጋብቻና የቲን ሰርተፊኬት
15. ደረሰኞች እና የካሽ ረጂስተር ዜድ ሪፖርት (እንደ አስፈላጊነቱ)
16. የአቅራቢዎች እና ደንበኞች ዝርዝር
17. የሌሎች ባንኮች እንቅስቃሴ
18. ጉርድ ፎቶ ግራፍ
19. የሥራ ፕላን ፎርም መሙላት

እንግዲህ እነዚህ ጥቅል ሲሆኑ እንደየ ድርጅቱ እንደየባንኩ፤ እያንዳንዱ የየራሱ ንዑስ ዝርዝሮች አሉት። በግንባታ ላይ ያለ፣ የተገነባ፣ ባዶ ቦታ ወዘተ ሲሆን ዝርዝሩ ይለያያል። ይህንን ያሟላ ነው ከባንክ መበደር የሚችለው። የደሀ ድርሻ እየለፉ መቆጠብ ነው። ከወለድ ነጻ የሚሰኘው ግን በእስልምና ስም መዋሸት ነው ቢባል ማጋነን አይሆንም። ወይም ሥራው ከእስልምና ጋር መያያዝ የለበትም ለማለት ነው።

ጉዳዩን ለማብራራት በጥቂት ገጾች የሚታለፍ ሳይሆን ስፋትና ጥልቀት ያላቸው ጥናቶች መሠራት እንዳለባቸው ይህ ደራሲ አበክሮ ያምናል። ጸሐፊው ይህንን እንደ አንድ አማራጭ ሲያስቀምጥ የዓላማው ጥግ ነው ብሎ የሚያስብ ሰው ይኖራል ብሎ አይጠብቅም። ለመረማመጃ ወይም "ለመናጆነት" ነው። መናጆ ማለት ለምሳሌ አንድ በሬ ነጂ በሬውን እየነዳ ገበያ ይሁን ሌላ በረት መውሰድ በሚቸገር ወቅት ሌላ የሚያናዳው በሬ ወይም ላም ከበረት ጨምሮ ይዞ ይሄዳል። ሱቅም ውስጥ የማይሸጡ ነገር ግን ለማሻሻጫ የሚሰቀሉ የመናጆ ዕቃዎች አሉ።

3.6. የግብርና ልማት ባንክ እና ኢንቨስትመንት ባንክ

ስለፊያት ያወቀ ሀብትና ንብረቱን እሳት ላይ ጥዶ አመድ እስኪሆን አይጠብቅም። በግለሰብ ደረጃም ይሁን በወል ተደራጅቶ ወዲያውኑ ወደ እርምጃ ይገባል። በግለሰብ ደረጃ ከሄድን በአሁን ወቅት ባለው ግሽበት ስናየው ባንክ ውስጥ ካደረ ፊያት ይልቅ ፍሪጅ ውስጥ ያደረ ቲማቲም ወይም ዐሳ የተሻለ ነው ወደ ሚያስብልበት ደረጃ ተደርሷል። ፊያት ባንክም አደረ ቦርሳችን ውስጥ፤ ውጤቱ ተመሳሳይ ነው። ባደረ ቁጥር መቀነስ ተፈጥሯዊ ባሕሪው ነው። ግሽበት የሚሰኝ ነቀዝ ውስጡ ይዟል።

3.6.1. በግለሰብ ደረጃ

ከዕለታዊ ወይም የአጭር ጊዜ ፍላጎት ውጭ ጥሬ ካሽ (ፊያት) ባንክም ይሁን ቦርሳችን ውስጥ አለማቆየት ነው። ወዲያው ወደ ዕቃ መቀየር ያስፈልጋል። አንድ ደመወዝተኛ “አስቤዛ” ቢሸምት የተሻለ ነው። የማይበላሹ እና ለአያያዝ ምቹ የሆኑ እንዲሁም ፊያት ባስፈለገ ወቅት ቶሎ ተቀያሪ የሆኑ ዕቃዎች ላይ ማዋል ይቻላል። ሌላው እንግዲህ የተሻለ የባንክ ትርፍ (ኢንተረስት) የሚያስገኙ ቁጠባዎች ላይ ማስቀመጥ ቢያንስ የግሽበት ማካካሻውን ከፍ ያደርግልናል። ከወለድ-ነጻ በሚባለው ከቆጠበ ሰው ይልቅ በመደበኛው የቆጠበ ሰው ቢያንስ 7% ከግሽበት ይህንን ያህል ያድናል። 2014 ላይ ባለው ሪፖርት የባንኮች ተቀማጮች ውስጥ 70% የሚሆነው ቁጠባ መሆኑን ማስታወስ ያስፈልጋል። በመሆኑም የመጀመሪያ ደረጃ እርምጃ ገንዘቦች በግሽበት ከሚያወድመው “ከወለድ-ነጻ” ከተባለው መስኮት ማዳን ነው። ይህ አስቸኳይ የነፍስ አድን እና የሀብት አድን እንቅስቃሴ ነው። ይህ ማለት ምንም መላ የሌለው የደሀ እርምጃ ነው። ከ7% ደግሞ 8% ላይ ያኖረው ይሻላል። ገንዘቡ ዘለግ ላለ ጊዜ የሚቆይ ከሆነ ከባንኮች ጋር በድርድር ከፍ ባለ ትርፍ ማስቀመጥ ይችላል። አሁን ባለው ቴክኖሎጂ ደግሞ፤ ከባንክ ሠራተኛና ኃላፊም ጋር መነጋገር ሳያስፈልግ በእጅ የሞባይል ስልካችን ላይ በተጫኑ የባንክ ወይም የቴሌ ብር መተግበሪያዎች እራሳችን መርጠን ባሻን የባንክ የቁጠባ አማራጭ መዶል እንችላለን።

ሌላው አካሄድ የማይንቀሳቀስ ንብረት ለምሳሌ እንደ መኖሪያ ቤት መያዝ አንዱና ተቀዳሚ አማራጭ ነው። እስካሁን ባለው ተጨባጭ ከዚህ የተሻለ ሀብት መጠበቂያ አማራጭ አላስተዋልንም። ጥሮ ተጣጥሮ ቤት የያዘ ሰው እራሱን ከካፒታሊስት ጎራ ደብልቋል። ወርሃዊ ኪራይ፣ የግሽበት ማካካሻ፣ ለባንክ ብድር

ቢፈልግ ዋስትና ይሆናል። መኪና መግዛት ተመሳሳይ አማራጭ ሊሆን ይችላል። ለጥቆማ ያህል ነው። የሚበጀውን እያንዳንዱ ሰው ይወስናል።

ቤት መግዛት ላልቻለ በሥራ ላይ የቆዩ አክሲዮኖችን መግዛት ቀጣይ አማራጭ ሊሆን ይችላል። እዚህ ጋር አደራ የምለው ነገር ቢኖር ለሕዝብ ይፋ የሆኑ አክሲዮኖች የሀብታም እንጂ የደሃ ኢንቨስትመንት ባለመሆናቸው ጥንቃቄ ይሻል። አንድ ደሃ በተለይ አዳዲስ የሕዝብ አክሲዮኖች ላይ በፍጹም ኢንቨስት ማድረግ የለበትም። የአክሲዮን ድርጅቱ የሀገራችንን ቢሮክራሲ ተቋቁሞ፣ ከዚያም ሥራ ጀምሮ ትርፍ ለማምጣት ዓመታት ይፈጅበታል። ትርፍ አምጥቶ ክፍፍል (ዲቪደንድ) የምንከፋፈለው በከፈልነው አክሲዮን መሠረት እና በአብዛኛው ጊዜ በዓመት በመሆኑ፤ ለዕለት ጉርስ ለሚሯሯጥ ሰው አይሆኑም። አክሲዮኖች ላይ ኢንቨስት ስናደርግ እያንዳንዱን ነገር አበጥረን አይተን እና ከዕለታዊ ትርፍ (Profit) ይልቅ ዘላቂ ሀብት (Wealth) ላይ ስናተኩር እንዲሁም ገንዘባችንን (በኢንቨስትመንት ቋንቋ እንቁላላችንን) በአንድ ቅርጫት ውስጥ ላለማስቀመጥ ነው። በቀጣይ የሚመጡ መንገዶች በሕጋዊ መንገድ በውጭ ምንዛሪ ማስቀመጥ ሊሆን ይችላል። ይህ በራሱ ዞሮ ዞሮ ፊያት በመሆኑ አስተማኝ አይደለም። የራሱ ብዙ ስጋቶች አሉት። ቢሆንም አንዱ አማራጭ ሆኖ ሊወሰድ ይችላል።

ወደ ገበሬዎች ስንሄድ በመኸር ወቅት ያገኙትን ምርት ሸጠው ባንክ ከሚዶሉት እህሉን በጎተራ ቢያስቀምጡ የተሻለ ነው። ምክንያቱም ክረምት ላይ ለዘር መልሼ ልግዛው ቢሉ በሸጡበት ዋጋ አያገኙትም። ገበሬዎች ፊያት ከሚቆጥቡ እሴት ማለትም እህል ቢቆጥቡ የተሻለ ይሆናል። ይህ ሲባል የባንክ ቁጠባን ላለማበረታታትና ባንኮችን ለመቃረን ሳይሆን ለቆጣቢው የተሻለውን ለመምረጥ ነው። ምክንያቱም ረሃቡ ዞሮ ሁላችንም ቤት ያንኳኳል። ገበሬው በደኸየ ቁጥር ረሃቡ

የጋራ ነው። ገበሬውን ከግሽበት ሰደድ ካልታደግነው ለምዕተ ዓመታት የማንወጣው ድህነት ውስጥ እንዘፈቃለን። ለምዕተ ዓመታትም ኖረንበታል። አብረውን የነበሩ ወይም ከእኛ የሚያንሱ ሀገራት በጥቂት ዓመታት ጥለውን ከሄዱበት ምክንያት አንዱ፤ እሴት ተኮር አካሄድ ነው። የዚህ ንዑስ ርዕስ ዓላማው በፊያት ቁጥባና በማስያዣ ብድር ላይ የተመሠረቱ ባንኮች ወደ እሴት ተኮር ሥራ እንዲሸጋገሩ ከማሰብ ነው። የግብርናና የኢንደስትሪ ባንኮች በጣም ያስፈልጉናል። ሕንጻ ተከራይቶ ኪራይ መሰብሰብ መውጣት የግድ የሆነበት ወቅት ላይ ነን። ቀጣዩን የግብርና ልማት ባንክ "ቅንጭብ" እንመልከት።

3.6.2. በመንግሥት ደረጃ

እስከ 2014 ኢ.አ. መጨረሻ ድረስ 30 የንግድ ባንኮችና አንድ ልማት ባንክ ብቻ ነው ያለው። የንግድ ባንኮቹ የትርፍ ውድድር ላይ ሰጥመው ገብተዋል። ግዙፉ ኢትዮ-ቴሌኮም የንግድ ባንኩን ዘርፍ ተቀላቅሏል። ጥሩ ነው። ከእነዚሁ በተጨማሪ የውጭ ሀገራት ንግድ ባንኮችና የቴሌኮም ድርጅቶች እንዲገቡ ተብሎ ፖሊሲ ጸድቆላቸዋል። አሁንም ግን የፋይናንስና ኢኮኖሚ ዘርፋችን ንግድ እና "ኪራይ ሰብሳቢነት" ላይ አተኩሯል። ይህን ያስባለው የተወሰኑ ቡድኖች ተሰባስበው ባንክ ይከፍቱና ቢሮ ተከራይተው ብቻ የሕዝቡን ሀብት ሰብስበው ለቡድናቸውና ለዘመዶቻቸው ትርፍ ይሯሯጣሉ። 84% ሕዝባችን ኑሮውን ግብርና ላይ

አድረጓል[62]። 65% ሠራተኛ (Employmen)[63] ከግብርና ዘርፍ ነው። የሀገሪቱ ሲሶ ዓመታዊ ምርት (Gross Domestic Product – GDP) ከግብርና ነው[64]። በዚህ ሁኔታ በሀገራችን የግብርና ባንክ አለመኖሩ እጅግ ያሳፍራል። በጣም በሚያሳዝን ሁኔታ በ2022 ከ16 የግል ባንኮች ለገበሬው የቀረበው ብድር 1% ብቻ ነው። ለመነሻ ያህል ሰንጠረዡን ከዚህ መጽሐፍ መጨረሻ ላይ ተቀንጭቦ ተያይዟል።)

አደጉ የምንላቸው ሀገሮች ካሳደጋቸው ግብዓት ውስጥ የግብርና ልማት ባንክና ኢንቨስትመንት ባንክ ይጠቀሳሉ። የኔዘርላንድ ራቦባንክ ከሀገሩ አልፎ በ40 ሀገራት ላይ ቅርንጫፎች አሉት። የኢንዶኔዢያው ራካያት ባንክ ገጠሩን ክፍል በማልማት ስመጥር ባንክ ነው። የኢንዶኔዢያ የወጭ ንግድ የዚህ ባንክ ውጤት ነው። ቻይና የግብርናና የኢንቨስትመንት ባንክ ላይ ትኩረት ሰጥታ በመሥራት ነው የተለወጠችው። ስኬታማ ከሆኑ ባንኮችዋ በ1951 የተቋቋመውና ከአንደኛ እስከ ሦስተኛ ደረጃ የሚገኘው የቻይናው Agricultural Bank of China Limited የ2022 የሀብት መጠኑ 23 ትሪሊዮን ዩዋን ($3.3 ትሪሊዮን ዶላር ደርሷል[65]። ከገጠር ተነስቶ በዓለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ ባንክ ነው። የአሜሪካው ኮ-ባንክ፣ የአርጀንቲናው ባንኮ ዲ ላ ናሲዮ፣ የቱርኩ ዚራአት ባንክ ለአብነት መውሰድ

[62] Solomon Tsehay, Zewdie Adane and Adem Feto (2022), Agriculture-Industry Linkages for Employment and Economic Transformation in Ethiopia, Ethiopian Journal of Economics, Volume 31 Number.

[63] Sisay Debebe, Endale Gebre, and Tadesse Kuma, Yield Gaps and Technical Inefficiency Factors for Major Cereal Crops in Ethiopia: Panel Stochastic Frontier Approach, Ethiopian Journal of Economics, Volume 31 Number.

[64] National Bank of Ethiopia Annual bulletin 30 June 2022

[65] የ Agricultural Bank of China Limited ከባንኩ የ2020 ዓመታዊ ሪፖርት የተወሰደ

እንችላለን። አብዛኞቹ የአፍሪካ ሀገራት የግብርና ልማት ባንክ አላቸው። ግብጽ፣ አልጄሪያና ደቡብ አፍሪካ ጠንካራ የግብርና ባንክ ካሉዋቸው ሀገራት ናቸው። እንዲሁም የጋና እና የናሚቢያ የግብርና ልማት ባንኮች፣ የዚምባቡዌ ብሔራዊ የግብርና ልማት ባንክ ማንሳት ይቻላል። (ዝርዝሩን: The Viability of Agricultural Development Bank in Ethiopia የሚለው የዚሁ መጽሐፍ ጸሐፊ ጥናት ላይ ሠፍሯል።) ስለዚህ የገበሬ ልማት ባንክ ሲቋቋም የኢኮኖሚ ርዕዮተ ዓለማችንን ሊቀየር እንችላለን። ከፊያት ወደ እሴት አብዮት መዞርና ሀገራችንን ከፊያት ግሽበት መታቸግ እንችላለን።

3.7. በወርቅ ሒሳብ ማስላት፣ መመዘንና መበዳደር

ይህ የአጭር ጊዜ እና ዛሬውኑ ልንጀምረው የምንችለው መፍትሔ ነው። ብዙዎች ይህንን ጽሑፍ አንብበው በደንብ ቢረዱት እንኳ ቶሎ ሐሳባቸውን ይቀይራሉ ወይም ከከርከር ወጥተው ወደ ተግባር ይገባሉ ተብሎ አይጠበቅም። ለሚቀጥሉት ጥቂት የማይባሉ ዓመታት ክርክሩ ሞቅ ብሎ ይቀጥል ይሆናል። ስለዚህ ክርክሩ አብቅቶ ነገሮች እስኪስተካከሉ ድረስ ስትበዳደሩ በዕለቱ የወርቅ ቢሆን መልካም ነው። ልክ ዘካ ስንከፍል በወቅቱ የስንዴና የወርቅ ሒሳብ አስልተን እንደምንከፍለው የእርስ በእርስ ብድሮቻችንም በወርቅ እየተመንን እንበዳደር። ብድራችንን ስንመልስም በምንመልስበት ቀን የወርቅ ዋጋ አይተን በፊያት ተርጉመን መክፈል ነው። በዚህ ውስጥ አበዳሪም ተበዳሪም ወደ አለመበዳደል ተቃረቡ ማለት ነው።

ምሳሌ አምና ወርቅ ዘጠኝ መቶ ብር ሆኖ ዘንድሮ አንድ ሺህ ብር ከሆነ፤ አምና አስር ሺህ ብር ያበደረን ሰው ማለት ፲፩ ግራም ወርቅ አበድሮናል ማለት ነው። ዘንድሮ ስንከፍለው ፲፩ ግራም ወርቅ በ፲ሺ ብር አብዝተን ብር ፲፩,፲ሺ መክፈል

አለብን ማለት ነው። ጭማሪዋ ብር ነ,ነነ0 ወለድ ሳትሆን የወረቀት ገንዘብ (የፊያት) ግሽበት ነው። ወርቅ ዋጋው ያው ከሆነም ብር ነ0,000 እንመልሳለን። ወርቅ 800 ብር ቢወርድ ብር 8,888.89 እንከፍላለን ማለት ነው። ይህ ማለት ፊያት ጠነከረ ማለት ነው እንጂ ወርቁማ ያው ነነ.ነነ ግራም ነው። ይህንን ብናደርግ ያለ አግባብ የምንበላላው ነገር ይቀራል። ተበዳሪዉም ቶሎ ለመመለስ ይጥራል።

የመጀመሪያ መጽሐፍ ከታተመ በኋላ (ታሕሳስ 2011 ኢት/አ) ጸሐፊው የወርቅ ዋጋ መመዝገብ ጀምሮ ነበር። በወቅቱ የጥፍጥፍ ወርቅ ዋጋ በግራም ነ,ነ00 ብር ገደማ ነበር። ልክ በሁለት ዓመቱ ታሕሳስ 2013 ግን 2,300 ብር ደረሰ። ከመቶ ፐርሰንት በላይ አደገ ወይም ፊያት ጋሸበ ማለት ነው። ከላይ የፊያት ገንዘብ አፈጣጠር ላይ እንዳየነው፤ የብሪተን ውድስ ስምምነት ወርቅን የመሰብሰብ ሒደት ነው። ምዕራባዊያን ወርቆችን በገፍ ሲሰበስቡ የቀራቸው የሴቶች ጌጣጌጥ ነው። እንደሚታወቀው በሁሉም ባሕል ወርቅ የጋብቻ ማሰሪያ ነው። ጥሎሽም በወርቅ ይከናወናል። ሚስት ባሏ ሲሞት ወይም ስትፈታ ወርቆቿን ሽጣ ክፉውን ወቅት ታልፋለች። ባሏ በሕይወት ኖሮ ኪሳራ ሲገጥመው ወርቆቿን ሽጣ ታቋቁመዋለች። አዛውንት እናቶች ለመቀበሪያዬ ብለው ያኖራሉ።

ኢትዮጵያ ለረጅም ዘመናት ወርቅ በኮንትሮባንድ ሲወጣባት ቆይቶ በ2013 የኢትዮጵያ በጀት ዓመት ልክ አሜሪካኖች በብሪተን ውድስ ያደረጉትን ዓይነት ነገር የኢትዮጲያ ብሔራዊ ባንክ ጀምሮ በዓመት የሚሰበስበው ወርቅ በወር ውስጥ መሰብሰብ ቻለ። ሀምሌ 2012 ላይ ብቻ ያለፈውን በጀት ዓመት በላይ ሰብስቧል። ከዓለም አቀፍ ዋጋ ላይ ከነ5 ፐርሰንት እስከ 20 ፐርሰንት እየጨመረ መግዛት መጀመሩ በርካታ ጠቀሜታዎች አሉት። አንደኛ የወርቅ ኮንትሮባንድ ሽሽትን መቆጣጠር ይችላል፤ አቅራቢዎች በሕጋዊ የግብይት መስመር ውስጥ እንዲገቡ

ያስችላል። ሁለተኛ ከወረቀት ይልቅ ዕውነተኛ ንብረት በመያዝ ዘርፈ-ብዙ ግልጋሎትን ማግኘት አስችሎታል (ለምሳሌ ሽያጭ፣ ከግሽበት ነጻ ወይም እዚህ ግባ በማይባል ግሽበት ወርቅን መያዝ ወይም ማከማቸት ወዘተ.)። ይህ ጉዳይ በመጀመሪያ እትም ወቅት ሲወጣ የእብደት ይመስል ነበር። መንግሥትም ወርቅን ከዋጋው በላይ መግዛት አምኖበት በኢ.አ. 2014 መጨረሻ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ከዓለም ዋጋ ላይ 35% ጨምሮ እንደሚገዛ በመገናኛ ብዙኃን ገለጠ።

ከዓለም አቀፍ ዋጋ ላይ ጨምሮ መግዛቱን በምሳሌ ለማስረዳት የዓለም ዋጋ 2,300 ብር ከሆነ ብሔራዊ ባንክ 3,000 ብር ሊገዛ ይችላል እንደማለት ነው። (ጭማሪው ግምታዊ ምሳሌ ነው)። አንድ ዜጋ ፣ ኪሎግራም ወርቅ ካመጣ 3 ሚሊዮን ብር የሚል ቁጥር ሒሳቡ ላይ ይገባል። ወርቅ ሰጥቶ ቁጥር ተቀበለ። መንግሥት ጉልበት ስላለው ንብረት ተቀብሎ ቁጥር ይሰጣል። ተቀባዩ ያንን ቁጥር ለሌላ ሰው ያስወነጭፈውና ቤት ወይም መኪና ይገዛል። ቤት የሸጠውም ቁጥር ይቀበልና ለሌላ ሰው ያስወነጭፈዋል። በኮምፒውተር ውስጥ ቁጥር ይዟዟራል። ከሀገር እስካልወጣ ድረስ ኢኮኖሚ ላይ የሚያመጣው ችግር የለም። ችግሩ የሚመጣው ጉልበተኛው የኢትዮጵያ መንግሥት ወይም ብሔራዊ ባንክ ከበላዩ ሌላ ጉልበተኛ ስላለበት እርሱም ዶላር የሚባል ቁጥር ይቀበልና ወርቁን ያስረክባል። እላይ ያሉ ጉልበተኞች ቁጥር ብቻ እየሰጡ ንብረት ይቀበላሉ። ይህንን የበደል እና የአራጣ ሲስተም ሀላል (ፍቁድ) አድርጎ የሸሪዓ ሕግ ሲያቆምበት ሊጣጣም አይችልም። ምክንያቱም የሸሪዓው መሠረት ባዶ ቁጥር ሳይሆን እስከ ጀነት ዋጋ ያለው ወርቅና ብር ነው። ሙስሊሙ ሸሪዓውን ካወቀ የሀብት ቁልፍ በእጁ ገብቷል። ካልሆነ ከሸሪዓውም ከሀብቱም ሳይሆን የአላህ ባሪያ ሳይሆን የሰው ባሪያና ገባር ሆኖ ይኖራል። የሆነውም ይኸው ነው። ይህ ሙስሊሙን ብቻ ሳይሆን ክርስቲያኖችንም አልማረም። ምክንያቱም በአራጣ ጉዳይ የኢስላምና የክርስቲያን ሕግ አንድ ናቸው። እንዲያውም

ጸሐፊው ባደረገው የሊትሬቸር ዳሰሳ የክርስትናው ጠና እንደሚል ተገንዝቧል። የክርስትና እምነት በአራጣ ላይ ያለው አቋም እጅግ ጠንካራ ነው። በክርስትና እምነት ባሕታዊነት አለ። አራጣ ቀርቶ መደበኛ ንግድና ዓለማዊ ድሎት እንኳ ብዙም አይወደድም። የባንኩ አራጣና የክርስትና አራጣ የተለያዩ ናቸውና ክርስቲያን አራጣ የሚበላና ሙስሊም የሚጸየፍ እንዳይመስለን። የባንክ ወለድ እንዴት ያለ ብይን ቢሰጡት ነው ብለን ቀሳውስቱን መጠየቅና መረዳት ይጠቅማል። የመጽሐፉ አጀንዳ ስላልሆነ ማቅረቡ ከአውድ ያስወጣናል።

ብድርን በወርቅ ማስላትና መመዘን አነሳን እንጂ ብዙ ጉዳዮች በወርቅ መመዘን ያስፈልጋቸዋል። በሕግ መጻሕፍት የወንጀለኛ መቀጫዎች በፊያት ተወስነው ይቀመጣሉ። አሁን በመሻሻል ላይ ያሉ የሀገራችን ሕጎች አብዛኞቹ በ1952 የወጡ ናቸው። ያኔ በገንዘብ የተቀመጠ የቅጣት ተመን እና የአገልግሎት ክፍያ አሁንም ያው ሆኖ ይስተዋላል። ያኔ ለአካል ማጉደል ወይም ለሕይወት ማጥፋት የተቀመጠ ተመን/ቅጣት ለስድሳ ዓመታት ተመሳሳይ ሆኖ ቆይቶ ሆኖ ከሆነ ያኔ 1952 ላይ መቀጫና መቀጣጫ ሲሆን 2012 ኢ.አ. ላይ ግን መገላገያ ሊሆን ይችላል። 1952 ላይ የሕይወት ካሳ 40,000 ነበር እንበል። ይህ ዋጋ በ60 ዓመታት 40 እጥፍ (4,000%) ጋሽቧል። በዚህ ግርድፋዊ ስሌት ለነፍስ ካሳ አንድ ነጥብ ስድስት ሚሊዮን ብር መሆኑ ነው። አሁን ማለትም 2012 ላይ የሰው ሕይወት ካሳ ሳይሆን 40,000 ብር የወይፈን ዋጋ ነው። ከተወሰነ ዓመታት በኋላ የበግ ሊሆን ይችላል። 2012 ኢ.አ. 1,600,000 ብር ብለን ብንወስነው ከቆይታ በኋላ የወይፈን ዋጋ ይሆናል። ይህና ሌሎች የሕግ ተመኖች በፊያት ገንዘብ ወስኖ መተው ወንጀልን ያባብሳል። ዛሬ መቀጫ ያልነው ከተወሰነ ዓመታት በኋላ ጭራሽ የወንጀል ማበረታቻ ሊሆን ይችላል። ሕጎች ሲወጡ ከግምት መግባት ካለባቸው ጉዳዮች አንዱ

መቀጫዎችና የአገልግሎት ክፍያዎች በፊያት መሆን እንደሌለባቸው ነው። ይህ ክፍል ብዙ የጥናት ርዕስ ይወጣዋል።

3.8. ኢስላማዊ የገበያ ሥርዓት መተግበር

ንግድና ሙስሊሞች አይነጣጠሉም። ሙስሊም ካለ ንግድ አለ። ንግድም ካለ ሙስሊም አለ። ነቢያችን ﷺ ከእረኝነት ቀጥሎ የሠሩት ሥራ ንግድ ነበር። ኢስላም ስለንግድ እጅግ ሰፊ እና ግልጽ ሕጎችን አስቀምጦአል። አሁን ያሉ ንግዶችን ስናይ የፊያት መገበያያን ተከትለው ወደ ሌላ አቅጣጫ ጦዘዋል። ኢስላማዊ የገበያ ሥርዓት አብሮ እየከሰመ ነው። ገንዘብና ንግድ የአንድ ሣንቲም ሁለት ገጽታዎች ስለሆኑ ሁለቱም ጎን ለጎን ወደ ተፈጥሮአቸው መመለስ ይገባቸዋል።

እዚህም ጋር ንግድ ተፈጥሮአዊ ነው። ሙስሊም ያልሆነው እርስ በርስም ከሙስሊሙም ጋር ይነግዳል። ነገር ግን አብሮ መናገድ እንዳለ ሆኖ ኢስላም ለንግድ ያስቀመጣቸው ሕግጋት አሉት። ያንን መከተል አለብን ለማለት ነው። እርስ በርስ ብቻ ሳይሆን ሙስሊም ካልሆነውም ጋር ምቹ የሆኑ ሕግጋት ናቸው። የሕጎቹ አብዛኞቹ ክፍሎች ማጭበርበርና ጥርጣሬን የሚያስወግዱ ነገሮች ላይ ያተኮረ ነው። ሕጉ ለሙስሊም ለክርስቲያን አይልም። ለምሳሌ "እጅ ላይ የሌለ ዕቃ አለመሸጥ" የሚለው ለማንም ምቹ ነው። በምዕራባዊው የገበያ ሥርዓት ከሄድን፣ ነገ ይህ ሊሆን ይችላል ብሎ በግምት መገበያየት ወይም "Speculation" የንግድ ሥርዓት አካል ነው። ወደ ኢስላማዊ ሕግጋት ስንመጣ ይህ ግብይትን ከሚያፈርሱ ነገሮች አንዱ ነው። ንግዶች ከጥርጣሬ መራቅ አለባቸው ይላል።

አንድ ምሳሌ ብንጨምር በሸሪዓው ብዙ ዓይነት የግብይት ሥርዓቶች አሉ። አንዱ ክፍት የገበያ ቦታ ነው። ሁሉም ሰው ሸቀጡን ይዞ ይወጣል። መንገድ ላይ

ማፈን ክልክል ነው። የግል የሚባል ግንብ መገንባት አይቻልም። ግንብ መገንባት ካስፈለገ የሚገነባው መንግሥት ወይም በጎ አድራጊ ነው። ወይም ነዋሪው ተባብሮ ይገነባዋል።

ነቢያችን ﷺ መዲና እንደወረዱ የሠሯቸው ሥራዎች መስጂድና የገበያ ቦታ ማቋቋም ነበር። የዚህን ገበያ ሥርዓት ሲናገሩ "ሱቆች ልክ የመስጂድ ሱና መከተል አለባቸው። አንድ ሰው ቀድሞ መጥቶ ቦታ ከያዘ የዕለቱን ግብይት ጨርሶ እቤቱ እስኪመለስ የመጠቀም መብት አለው"። (አል-ሂንዲ፣ ከንዙል ማል፣ ቅጽ 488፣ ቁ2688)

ኢብራሂም አልሙንዚር ከኢስሀቅ ኢብን ጃዕፈር ኢብን መሀመድ፣ ከዓብዱላህ ኢብን ጃዕፈር አልሚሰዋር፣ ከሹረይህ ኢብን ዓብዱላህ ኢብን አቢ ነሚር እንዳስተላለፈው፣ አጣእ ኢብን የሳር እንዳለው፣ ነቢያችን ﷺ መዲና እንደወረዱ የገበያ ቦታ ማቋቋም ፈለጉ። ወደ በኒቀይኑቃእ ነሳዎች የገበያ ቦታ ሄደው አዩ። ወደ መዲና ገበያ ተመልሰው በእግራቸው መሬቱን እንደ ማጎተም እርግጥ አደረጉና ይህ የገበያ ቦታችሁ ነው። መጥበብም የለበትም። ግብርም አይከፈልበትም አሉ። (ኢብንሺይባ፣ ታሪኽል መዲና አልሙነወራህ፣ 304)

ነጋዴው ወደ ገበያ ዕቃውን ይዞ ይወጣል። ልክ እንደ መስጂድ የሶላት ቦታ "የኔ ቦታ ነው ተነስልኝ" የሚባል የለም። ምናልባት "የዓይነት ተራዎች" ማለትም የዱቄት ተራ፣ የጎማ ተራ፣ የሸማ ተራ የሚባሉ ይኖራሉ። ገበያ በዋለበት ሸጦ/ገዝቶ ይገባል። የዕቃውን ዋጋ የሚወስነው ገበያው ነው። አምራች ከተጠቃሚ ጋር በቀጥታ ይገናኛል። በመሀል "መቀፈል"ና ዋጋ "ማበሻቀጥ" አይኖርም። በዚሁ በእኛው ዕድሜ በገጠር "ቅዳሜ ገበያ፣ ሐሙስ ገበያ" የሚሰኙ ግልጽ ገበያዎች ነበሩ። እየሳሱ ቢሆንም

አሁንም ድረስ አሉ። ነጋዴው ሸቀጡን ይዞ ይወጣል። ተገበያይቶ ይመለሳል። በየአቅራቢያ ስለሚኖሩ ብዙም አይቸግርም።እንደ ኒውዮርክ ስቶክ ኤክስቼንጅ ያሉ ዓለም አቀፍ የአክሲዮን ገበያዎች ውስጥ ተመሳሳይ አካሄድ ያላቸው አሉ። በእኛም ሀገር "የኢትዮጵያ ምርት ገበያ ድርጅት"ም ከዚህ ዓይነት የገበያ ሥርዓት ጋር የሚጋራው ነገር አለው።

አንድ ነገር ልጨምር። በዚሁ በኛው ዕድሜ መኖሪያ ቤትና ምግብ ያን ያህል አሳስቦ አያውቅም ነበር። ቤት ስትፈልግ ማኅበረሰቡ "በደቦ" ይሰራልሀል። አንተም ሄደህ በነጻ ትሠራለህ። የተኛ መሬት ስላለ የመሬት ችግር የለም። ካፒታሊዝም አወሳሰበው እንጂ አሁንም ቢሆን የመሬት ችግር የለም። ምግብ ከጓሮ ይቀጠፋል። ወይም ይዘመራል። የጎደለ ደግሞ ከገበያ ይገዛል። ይህንን ሁኔታ ምን ቀየረው የሚል ጥያቄ ካነሳን "በወረቀት መገበያያ ላይ የተመሠረተ ኑሮ" ኑሮዉን አነደደው። ሁሉም ነገር "ካሽ" ሆነ። ካሹ ደግሞ ፊያት ነው። በእጅ የተዘገነ ውሀ ማለት ነው። እያየኸው ተንጠባጥቦ ያልቃል። የገበያውን ሥርዓትም ጭምር "ነበር እንዴ" ወደሚያስብል ደረጃ አድርሶታል። ከፊያት ወጥተን ወደ ንብረት ገንዘብ ብንመለስ በመሀል ያሉ የድለላና የዘረፋ ሰንሰለቶች ስለሚቋረጡ ያኔ ሊገባን ይችላል። አሁንማ ኑሮና ገበያው እንደፊያት ዙሩ ከሮአል። ፈረንጆች በብላሽ የሚያጋብሱትን ሀብት አላህ ሚዛኑን እየጠበቀው ስለሚያድለው ሁሉም ሀገር ተጠቃሚ ይሆን ነበር። ኢትዮጵያ ባላት የተፈጥሮ ሀብት ያለማንም ጣልቃ ገብነት ከጎረቤት ሀገራት ዕቃ ማስገባትና መለዋወጥ ትችል ነበር። ይህ አሁን የምናየው ቴክኖሎጂም በማናስበው ሒደት ያድግ ነበር። ቴክኖሎጂውም ልክ እንደፊያቱ እና እንደ ንግዱ አንድ አቅጣጫ ስለተበጀለት የዓለም ሕዝብ ሁሉ ጅል፣ ነጮች ደግሞ ምሁር አድርገን እንድንስል ተገደናል።

ቴክኖሎጂው ንግድና ሀብትን፣ ሀብትና ንግድ ደግሞ ፈያትን ተከትለው ወደ አንድ አቅጣጫ እየሾሩ ነው። እዚህ ጋር የተጠቀሰው አንድ ምሳሌ ነው። ብዙ ዓይነት የንግድ ዓይነቶች ስላሉ እነሱን በጥልቀት ብናነብ "እንዴት" የሚለው ጥያቄ ግልጽ ይሆንልናል። ብዙ ቦታ ስላነሳነው ኢስላማዊ የንግድ ሥርዓት ምን እንደሚመስል በጨረፍታ እንዳስሰው።

የኢስላማዊ ንግድ ማዕዘናት እና ቅድመ ሁኔታዎች

ማዕዘናት፡- ሦስት ጥንድ ናቸው። (1) ገዢ እና ሻጭ፣ (2) ዋጋ እና ለሽያጭ የቀረበው (3) ሸጫለሁ እና ተቀብያለሁ። ከእነዚህ አንዱ ከጎደለ ግብይቱ ፉርሽ ነው።

1. ገዥና እና ሻጭ (ባዒእ / ሙሽተሪ)፡- ከሁለት አንዳቸው ቢገኙ ግብይቱ ተፈጻሚ አይሆንም። የሁለቱም መገኘት እና ማንነታቸውን ለመስካሪ መታወቅ አለበት። ማንነቱ ለማይታወቅ ሰው ማለትም ፊቱን ለሸፋፈነ ሰው መሸጥም፣ ከተሸፋፈነ ሰውም መግዛትም ለመስካሪ ስለሚያስቸግር ቢያንስ ግብይቱን ሲፈጸም መገለጥ አለባቸው። ለንግድ ሁለት ወገኖች በአንድ ወቅት መገኘት አለባቸው። በአንድ ወገን አቅራቢነት የሚካሄድ ነገር፤ ለምሳሌ ዕዳን መሰረዝ፣ ምጽዋት መስጠት እና ግዴታን መወጣት እንደ ንግድ ኮንትራት አይቆጠሩም።

2. ዋጋ እና ለሽያጭ የቀረበው (ሰመን / ሙስመን)፡-

    - ለሽያጭ የቀረበው ነገር ሀላል መሆን አለበት
    - በግብይት ወቅት የሚሸጠው ነገር እና ተከፋይ ገንዘቡ እጅ ላይ ያለ መሆን

- የሚሸጠው ነገር ጥራቱን፣ ብዛቱን፣ ልኬቱን፣ የተሠራበት ነገር፣ ወዘተ ለሁለቱም ወገኖች ግልጽ መሆን
- የሚከፈለው ዋጋ ቁርጥ ብሎ መታወቅ

3. ሸጫለሁ እና ገዝቻለሁ (ኢጃብ / ቀቡል)፡- ሻጩ መሸጡን በቃል ወይም በጽሑፍ ወይም በምልክት ማሳወቅ አለበት። ገዢም መግዛቱን ተቀብያለሁ ብሎ በቃል ወይም በጽሑፍ ወይም በምልክት ማረጋገጥ አለበት። ለትንሽ ለትልቁም ይባላል ወይስ አይባልም? በሊቃውንት መካከል ልዩነት አለ።

ቅድመ ሁኔታዎች (ሸርጦች)፡- ሰባት ሸርጦችን እንጠቁም።

1. ከአራጣ (ወለድ) የጸዳ መሆን (ከላይ በሀዲስ እንዳየነው ገበያ ውስጥ ሲሻሻጡ ገዢው እቤት እከፍልሀለሁ ማለት አራጣ መሆኑን አይተናል)።
2. ከቁማር መንጻት፡- በአጠቃላይ ቁማር ማለት በአንዱ ኪሳራ ሌላው የሚያተርፍበት ነው። ስለዚህ ንግዶችም አንዱ አትርፎ ሌላው የሚከስርባቸው ከሆኑ የንግድ ቅድመ ሁኔታን (ሸርጥን) ይጥሳሉ።
3. በጋራ ሲሠራ ትርፍን ቀድሞ አለመወሰን፡- በዚህ ሸርጥ መሠረት “ከዚህ ንግድ ይህንን ያህል ትርፍ ትከፍለኛለህ” አይባልም። (ለምሳሌ፡- እንደ ኢስላማዊ ባንኮቹ መበደር ማበደር ሊሆን ይችላል)። ነገር ግን ከትርፍና ኪሳራው “ይህንን ያህል መቶኛ ይደርሰናል/ይደርስብናል” ይባላል። ለምሳሌ ትርፍም ኪሳራም እኩል እንካፈላለን፣ ወይም ትርፍም ኪሳራም እንደመዋጮአችን ይሆናል፣ ትርፍና ኪሳራው እንደ ልፋታችን ይሆናል ሊባል ይችላል። ይህ ሲባል

ግን እያንዳንዱ ዝርዝር ጉዳይ በጥልቀት መጻፍ አለበት። ለጥርጣሬ የሚቀር ሸንቁር መኖር የለበትም።

4. ሥራው በሸሪዓው ሀላል የሆነ መሆን አለበት። (ለምሳሌ አስካሪ መጠጥ ሀራም በመሆኑ ይወድቃል ማለት ነው)።
5. ሥራው ቅድስና (በአላህ ፊት የሚያስመነዳ) እንደሆነ አድርጎ ማሰብ። (ንግድ ከአምልኮ ነው)።
6. ከጥርጣሬ የጸዳ መሆን (Speculation and risk) የሌለው መሆን አለበት። ንግዱም፣ ልውውጡም፣ መበዳደሩም፣ ወዘተ በተጨበጠ ነገር ላይ ብቻ መሆነ አለበት። ባልተጨበጡ ወይም በሚያወዛግቡና በሚያጠራጥሩ ነገሮች ላይ የሚደረጉ ልውውጦች ለጸብ በር ይከፍታሉ። ይህ ፊያት ዛሬ የደረሰበት ደረጃ ያሳያል።
7. የመገቢያያ ገንዘቦች መታወቅ እና ተገቢያዮቹ በእኩል መስማማት አለባቸው። (የሚቀጥለው 8 ቁጥር ከዚህኛው የቀጠለ አይደለም)

اللَّهُمَّ صَلِّ عَلَىٰ سَيِّدِنَا مُحَمَّدٍ وَعَلَىٰ آلِهِ وَصَحْبِهِ وَسَلِّمْ

3.9. “ኢስላማዊ ባንክ” ማቋቋም?

ኢስላማዊ የሚባል ባንክ አለ ወይ? ከተባለ የለም። “ኢስላማዊ” ወይም “የወለድ ነጻ” በመባል እየተጠራ ያለው ባንክ የእስልምና ኃይማኖት መጻሕፍት ዕውቅና አልሰጡትም። በእስልምና መጻሐፍት የሚታወቀው የገንዘብ ግምጃ ቤት እንጂ ባንክ አይደለም። በቲዎሪም በተግባርም “ኢስላማዊ ባንክ” ብሎ በድፍረት መናገር አይቻልም። ምክንያቱም የኃይማኖቱ መጻሕፍት ዕውቅና አልሰጡትም። ከስም አኳያ እንኳ ስምምነት ላይ አልተደረሰበትም። በተለያዩ ሀገራት ብዙ ስሞች ተሞክረዋል። “ግብረገባዊ ባንክ” ሲባል ሌሉቹ ባንኮች አይደሉም ወይ የሚባል ጥያቄ አስነሳ። “አካታች ባንክ” ሲባል በተመሳሳዩ ሌሎቹ አያካትቱም ወይ የሚል ጥያቄ አመጣ። አማራጭ ሲጠፋ “ከወለድ ነጻ” እየተባሉ ናቸው። ሆኖም ግን ከወለድ ነጻ መሆን አልቻሉም። በተግባር የታዩት የወለድ ምጣኔያቸው ከመደበኛው ይልቃል። ስለዚህ ምን ተብለው ይጠሩ ከተባለ ገና በስም ደረጃ መስማማት ላይ አልተደረሰም። ከስም አኳያ እንኳ ስምምነት ላይ ባለመደረሱ በዘርፉ ላይ ያጠኑ ምሁራን ኢስላማዊ ባንክ ከማለት ይልቅ “የኢስላማዊ የሸሪዓ ሕግጋትን መሠረት ያደረጉ የባንክ አሠራሮች” የሚለውን ይመርጣሉ።

ኢስላማዊ ባንክ ማለት ልክ እንደ ኢስላማዊ ሆቴል ነው ሲሉ ሊደመጥ ይችላል። የሙስሊም ሬስቶራንትና ሆቴሎች ወይም ሉኳንዳ ቤቶችን ከወሰድን የሙስሊም ያስባላቸው የእንስሳት አስተራረዱን የእስልምናን ሕግጋት የተከተለ በመሆኑ ነው። እስላማዊ በሬ ግን አይኖርም። በሬው ሀላል (ፍቁድ) በመሆኑና አስተራረዱ የኢስላም ሸሪዓ የጠበቀ በመሆኑ የሙስሊም ልኳንዳ ለመባል በቃ። ሆኖም ግን ኢስላማዊ የአሳማ ልኳንዳ ሊኖር አይችልም። ምክንያቱም አሳማን መመገብ ከመሠረቱ ተከልክሏል። ወደ ባንኩ ስናመጣው የገንዘብ ሥርዓቱ ከመሠረቱ

የተፋለሰና ከአሳማው ጋር የሚመሳል ነው። የአሳማ እርባታ ላይ ኢስላማዊ የአሳማ ልኳንዳ (አላህ ይጠብቀን) ቢቋቋም ብዙ የሚያመሳስላቸው ነገር ይኖራል። የገንዘብ ሥርዓቱ አይደለም እንዳንል ሙሉ ለሙሉ በአራጣ ሥርዓት ላይ ቆሞ ጥቂት ሀብታም እና ቢሊዮኖች ድሆችን ፈጥሯል። ነው እንዳንል መልካም ነገሮችም አሉት። የገንዘብ ሥርዓቱ በዚህ መሀል የሚዋልል ሲሆን በተለይ በሙስሊም ሊቃውንት በኩል በደንብ ተፈትሾ ብይን ሊሰጥበት ይገባል።

ከኢስላማዊ ባንክ ይልቅ ኢስላማዊ የፋይናንስ ሥርዓት ማለቱ የተሻለ እና ተገቢም ነው። ከኢስላማዊ ፋይናንስ ደግሞ ኢስላማዊ የግብይት ሥርዓት ይሰፋል። ምክንያቱም ከቁርአን እስከ ነቢያችን ﷺ ሀዲስ እንዲሁም የሊቃውንት ሥራዎች ላይ በስፋት አለ። ይህ ዘርፍ እጅግ በጣም ሰፊ እና ልንማረውና ልናውቀው የሚገባ ዘርፍ ነው። ኢስላማዊ ባንክ ብለን ማቅለል አይገባም።

ባንኮቹ እንዴት 'ኢስላማዊ' ወይም "የወለድ ነጻ" ተባሉ ከተባል መደበኛውን ባንክ የማይጠቀሙ በርካታ ሙስሊሞች በመኖራቸው ብቻ ለጆሮዋቸው የሚስማማ ስም እየተመረጠ ይሰየማል። በዚህ መጽሐፍ ለጆሮ በብዛት የተሰማና ባንኮች እየጠሩት ያለውን ስም መጠቀም ካልሆነ በስተቀር ጸሐፊው ትክልል ናቸውም አይደሉምም ብሎ አልወሰደም። ያለውን ዕውነታ እንዲሁም ተግባራዊና መሠረታዊ ችግሮቹን ለማሳየት ይሞክራል። ውሳኔው ለአንባቢ ተትቷል። በትዕምርተ ጥቅስ "" ነው የተቀመጡት።

የእስልምና ሸሪዓ ለኢኮኖሚው እጅግ ጥልቅ እና ሰፊ ትኩረት ችሯል። "ኢስላማዊ፣ የወለድ ነጻ' እየተባሉ የሚተዋወቁ ባንኮችና መስኮቶች ከፋቾችና ሠራተኞች ሁሉም ወይም አብዛኛው ሙስሊም ባልሆኑ ሰዎች የተጀመሩ ናቸው። የእስልምና ሕግጋትን ሊተገብሩ ቀርቶ በትክክል እንኳ ስም መጥራት አይችሉም።

ሸሪዓን ‘ሼሪያ’፣ ወዲዓን ‘ዋዲያት፣ ወዲያ፣ ዋዲያህ’ (ኧረዲያ ማለት ነው የቀራቸው)፣ ቀርድን ‘ቂረድ፣ ቃርዳ’፣ ሙራባሃን ‘መራባ፣ መርሃባ፣ ሙረባ’፣ ሙኧረባን ‘ሙዳ ረባ’ … እያሉ ይኮላተፉበታል። ያሳቅቃሉ። ሼሪያ ማለት ሸረኛ ማለት ይመስላል። ቂረድ ደግሞ ከርከሮ ነው። ቀርድ ማለት ብድርን ሲሆን ቂረድ ማለት ግን ዝንጅሮ ነው።

ሕዝቡ ላይ ማስታወቂያ ለመሥራት ለሆዳቸው ያደሩ የኃይማኖት መሳይ ሰዎችን ጂም ይከራያሉ። ለመስጂድ እና ለልጆቻችን ልንሰይማቸው የማንደፍራቸውን የኃይማኖቱ መሠረታዊ ስሞችን ለመስኩቶቻቸው ይሰይማሉ። ‘ኢኽላስ’ ማለት አላህን በፍጹማዊነት ማምለክ የሚል አገባብ ያለው ቃል ሲሆን አዋሽ ኢንተርናሽናል ባንክ ይጠቀመዋል። አቢሲንያ ባንክ ‘አሚን’ የሚለውን ቅጽል ይጠቀማል። አሚን ማለት ታማኝ ማለት ሲሆን የነቢዩ ሙሐመድ ﷺ ቅጽል ስም ሆኖ ያገለግላል። ፈጅር፣ ዙህር፣ መካ፣ መዲና፣ ዘምዘም፣ ሙዘደሊፋ፣ ሂጅራ፣ ረመዷን፣ ቂያሙ ለይል፣ ተሃጁድ፣ በይተል ማእሙር፣ በይተሏሂል አቲቅ፣ ሲዲቅ፣ ፋሩቅ፣ ዚኑረይን፣ ፋጢመቱ ዛህራእ፣ እያሉና ሙስሊሙ ለቅድስና የሚጠቀማቸው ስሞችን እየለጠፉ ከሙስሊሙ በብላሽ ገቢ ለመሰብሰብ ይሽቀዳደማሉ። የት ድረስ ይሄዳል ከተማለ ብዙም ዘላቂነት አይኖረውም.

3.9.1. “ኢስላማዊ ባንክ” ጥቅል ቲዎሪ (ጽንሰ-ሐሳብ)

ፊያትን ምንነት ከተረዳው በኋላ የተፈጥሮ ገንዘብስ ባንክ የለውም ወይ የሚል ጥያቄ እንደሚነሳ እሙን ነው። የተፈጥሮ ገንዘቦችን በመጠቀም ዘመናዊ የባንክ አገልግሎት የሚሰጡ ባንኮች ሸሪዓው ሊኖረው ይችላል። በእርግጥ በቁርአንም፣ በሀዲስም ይሁን በቀደምት ሊቃውንት እንዲህ ያለ የባንክ አሠራር አልነበረም ተባብለናል። በመጓጓዣ ምሳሌ ብንሄድ ግመልና ጀልባ እንጂ መኪናና አውሮፕላን

አልነበረም። (መሎኮታዊ መጓጓጉ ይኖራል)። ስለዚህ የግመልና የመርከብ (ጀልባ) አጠቃቀም ለመኪናና ለአውሮፕላን እንደሚውለው የሸሪዓው የንግድ ሕጎችም ለዘመናዊ ባንኮችም ለማመቻቸት የሞከሩ አሉ። ቲዎሪዎቹ ምን ያህል ትክክል ናቸው የሚለው ትግበራው ይፈትሻቸዋል።

እስካሁን በተግባር ባየነውና ባነበብነው ግን የ"ኢስላማዊ ባንክ" ቲዎሪና ተግባሩ የምሥራቅና ምዕራብ ያህል የተራራቁ ናቸው። ቲዎሪው እራሱ ልክ አለመሆን ሌላ ችግር ሆነ እያለ፤ ወደ ተግባር ሲመጣ ችግሩ ይብስ ታጥፏል። ምክንያቱም በፊያት ላይ ተግባራዊ ማድረግ አይቻልም። ገና ሲጀመር መሠረቱ ተበላሽቶአልና። ባንክ የሚባለው በራሱ ችግር ነው። አጠቃላይ ባንክ የሚባለው ክፍያን ማሳለጥና ማፍጠን ትልቅ በጎ ነገሮች እንዳሉት ሁሉ የቆመው በካፒታሊዝም ሥርዓት በመሆኑ ጥቂት ሀብታምና ብዙ ድሆችን ፈጥሯል። ይህንን እንዳለ ኢስላማዊ ማድረግ ሁለት ጥፋት አምጥቷል። (አንደኛው) መሠረቱ አራጣ የሆነ ሲስተም ውስጥ መቀላቀልና የግፉ አካል መሆን ሲሆን፤ (ሁለተኛው) አራጣን ሀላል (ፍቁድ) ማድረግና ኢስላምን ማሰደቡ ነው።

የዚህ መጽሐፍ አዘጋጅ መፍትሔ ሲያስቀምጥ ኢስላማዊ ከሚባሉ ባንኮች በፊት ሙስሊሙ መደበኛ ባንኮችን አስቀድሞ ቢያቋቁም ይሻላል ያለው፤ አሁን ባለው ስር የሰደደ የካፒታሊዝም ኢኮኖሚ ኢስላማዊ የተባለው መተግበር ስለሚያዳግት ነው። ሙስሊሙ በግሉም ይሁን በጋራ በኃይማኖቱ ሕግጋት መኖሩ አያደራድርም። ኢስላማዊ የሚባለው የባንክ አሠራር ብዙም ጥቅም አላመጣም። ኢስላም ከጊዜው ጋር ሁሉ ይሄዳል በሚል ስንነሳ ገንዘቡስ የወለዱን ሕግ ሲያመጡት የገንዘቡንም ሕግ ማየት ነበረባቸው። ትልቁ ችግራቸው ፊያትን ከእነችግሩ በወርቅ መተካታቸው ነው። ፊያት ማለት እንደ ወርቅ ነው ብለው ወስደው ተነሱ። ግሽበትን

ከእነጭራሹ ዘነጉት። ምክንያቱም ወርቅ ግሽበት የለውም። ከግሽበት የማይነጠለውን ፊያት ቀጥታ በወርቅ መተካትና እንዲሁም በወርቅና በስንዴ ላይ የተቀመጠ የአራጣ ሕግ በዶላርና በፓውንድ ማስቀመጥ አግባብ አልነበረም። ዶላርና ወርቅ አንድ ካልሆኑ የባንክ ወለድና የሸሪዓ አራጣ አንድ ሊሆኑ አይችሉም። ደግሞ አይደሉምም። ገና ከመነሻው ተፋልሷል። ከመነሻው የተፋለሰ የባንክ ነገር በሸንት ውዱእ እንደማድረግ ነው የሆነው።

ለደሀ ከማሰብ አኳያ በአንጻራዊነት ከኢስላማዊዎቹ ይልቅ መደበኞቹ (የምዕራባዊያን ባንኮች) ይሻላሉ። ኢስላማዊ የተሰኙት ከመኖራቸው አለመኖራቸው በእጅጉ የሚሻልበት ጊዜ ይበልጣል። ኢስላማዊ የሚባለው አሠራሩ እጅግ በጣም ጥንቃቄ የሚፈልግና ውስብስብ ነው። ያወሳሰበውም ኢስላማዊ ባንኮች ሥራቸው የተመሠረተው በአበዳሪ ተበዳሪ ሳይሆን በጋራ ጥቅም ላይ የተመሠረቱ ስለሆኑ ሁሉንም የማኅበረሰብ ክፍል ያሳትፋሉ። ባለቤትነታቸው ለሕዝቡ በአጠቃላይ ስለሆነ ባንኩን ማስተዳደር ማለት ሕዝብን እንደማስተዳደር ነው። በአሁን ወቅት ከመደበኛው ባንክ ጎን ለጎን ወይም ሥር የተከፈቱ "ከወለድ ነጻ" መስኮቶች እንዲሁም ኢስላማዊ የሚባሉ ባንኮች በቲዎሪ ከተጻፈው ኢስላማዊ ባንኮች ጋር ባናወዳድራቸው የተሻለ ነው። አሁን ሥራ ላይ ያሉ መስኮቶቹም ሆኑ ኢስላማዊ የተባሉ ባንኮች ብዙ መሠረታዊ ነገሮችን ይጥሳሉ። ለአብነት ያህል፡-

1. በፊያት መገበያያ የተቋቋሙ በመሆናቸው ከወለድ ነጻ ወይም ኢስላማዊ ሊሰኙ አይችሉም።
2. የ"ኢስላማዊ ባንክ" መሠረታዊ መቆሚያ ከሆኑት አንዱ የሆነውን "የኢንቨስተር -ወ- መተባበር" ግንኙነት ሳይሆን እንደ መደበኛ ባንኮች "የአበዳሪ ተበዳሪ" ግንኙነት ነው።


3. የ“ኢስላማዊ ባንክ” ሌላው መታወቂያ የሆነውን የትርፍ-ኪሳራ መጋራትን ተግባራዊ አያደርጉም። በተለይ “ሙሻረካ (መጋራት)” የሚባለው ሙስሊም ሀገራት እንኳ ብዙም አይደፍሩትም። ባብዛኛው የሚሠሩበት “ሙራበሀ (ዋጋ ሲደመር ትርፍ)” የተሰኘውን ነው። (አጠር ባለ ሁኔታ እናያቸዋለን)።
4. እራሳቸውን ከኪሳራ ሙሉ ለሙሉ ነጻ ለማድረግ መያዣ (collateral) ይይዛሉ። ተበዳሪው የሆነ እክል ቢገጥመው ኪሳራው ሙሉ ለሙሉ ተበዳሪው ላይ ይወድቃል። ባንኮቹ መያዣውን ይወርሳሉ።
5. አሠራሩ ላይ “ምኑ ነው ኢስላማዊ?” እስኪባል ድረስ ከመደበኛው ባንክ የከፉ ነገሮች አሉበት።
6. በሸሪዓ በሚተዳደር ሀገር ቢቋቋም እንኳ አስተዳዳሪዎቹ ማለትም የፊያት ተቆጣጣሪዎች ሙስሊም ያልሆኑ በተለይ ምዕራባዊያን ስለሆኑ “ከእጅ አይሻል ዶማ” የሚባል ዓይነት ነው የሚሆነው። ኢስላማዊ የሚባው ባንክ ከበላዩ በሸሪዓ የማይተዳደር ብሔራዊ ባንክ ይመራዋል። ብሔራዊ ባንክ ደግሞ ከበላዩ በሸሪዓ የማይተዳደሩ አይ.ኤም.ኤፍ. የመሳሰሉ ተቋማት አሉበት። ስለዚህ የእኛ የመንደር ውስጥ ባንክ የትም አይዘልቅም።
7. የአራጣ ዋነኛ ክልከላ በደልን ለማስወገድ ቢሆንም ኢስላማዊ የተሰኙት ግን ከመደበኛው ይከፋሉ። በተለይ የደሀን ድህነት ያባብሳሉ።

መሠረቱ ባልተስተካከለ ነገር ላይ የሚገነባ ቤት የአሸዋ ላይ ቤት ወይም የባሰ ነው። በሀራም (ክልክል) ላይ ሀላል (ፍቁድ) አይቆምም። ሙሉ በሙሉ ሙስሊሞች ቢያቋቁሙት እንኳ እዚያው በዚያው የሚቦካ ነው የሚሆነው። ምናልባት አሁን ያሉ መስኮቶችና ኢስላማዊ የተሰኙ ባንኮች ወደፊት ወደ ትክክለኛ ኢስላማዊ ባንኮች ለማምጣት ከመደበኞቹ ስለሚቀሉ መኖራቸው አይነቀፍም። አሁን ባለንበት ሁኔታ የወለድ ነጻ ባንኮች ብሔራዊ ባንክ ያወጣውን መመሪያ ቁጥር SBB/51/2011 በትክክል

ተግባራዊ ቢያደርጉት ሀገራዊ ዕድገታችን ላይ ብዙ አዎንታዊ ሚና ይጫወት ነበር። መደበኛ ባንክ እንከፈት እያልን ኢስላማዊ መስኮቶች አይኑሩ አይባልም። እዚህች ጋር ደግሞ የጸሐፊው መልዕክት ቢያንስ ብሔራዊ ባንክ ያወጣው መመሪያ ንግድ ባንኮች ይተግብሩት። እስቲ የኢስላማዊ ባንኮች ተግባራዊ ቢሆኑ ኖሮ ምን እንሚመስሉ እንመልከት።

اللَّهُمَّ صَلِّ عَلَىٰ سَيِّدِنَا مُحَمَّدٍ وَعَلَىٰ آلِهِ وَصَحْبِهِ وَسَلِّمْ

“የኢስላማዊ” ባንኮች አሠራር



ሰንጠረዡን ለመተንተን ያህል ከላይ የተቀባው ክፍል ወደ ጎን ብንመለከት ሦስት የአሠራር ሒደቶችን ያልፋል።

1. የፈንድ (ገንዘብ) ምንጭ
2. የፈንድ አስተዳደር
3. ትርፍና የትርፍ ክፍፍል

1. **የፈንድ (ገንዘብ) ምንጭ፡**-ሠንጠረዡ ላይ በዚህ ርዕስ ሥር ቁልቁል ሦስት ነጥቦች ይታያሉ።
   1.1. የባለአክሲዮኖች (የምሥረታ ወይም መነሻ) ካፒታል
   1.2. የአደራና የተንቀሳቃሽ ሒሳብ አካወንት እና
   1.3. የጠቅላላ (General) ኢንቨስትመንት እና ልዩ (Special) ኢንቨስትመንት አካውንት ናቸው።

እነዚህ ገንዘቦች ወደ ባንኩ ከገቡ በኋላ ወደ ሚከተለው ክፍል ማለትም ወደ "ፈንድ አስተዳደር" ይሰራጫሉ።

---

2. **የፈንድ አስተዳደር (ከላይ ወደ ጎን 2ኛ ላይ ተቀምጧል)፡**- ይህ ሁለት ክፍሎች አሉት።
   - የፈንድ ቋትና
   - የፈንድ ምደባ ናቸው።

   2.1. የፈንድ ቋት (Funds Pool)፡- ሦስት ምድቦች አሉት። እነርሱም
   - የአጠቃላይ ፈንድ ቋት
   - የልዩ ፈንድ ቋት እና
   - የባንክ ገቨ ፈንድ ቋት ናቸው።

   2.1.1. የአጠቃላይ ፈንድ ቋት (General Funds Pool)፡- ገቢ የሚያገኘው
   - ከመሥራች (መነሻ) ካፒታል (በከፊል)፣

- ከቁጠባ እና ተንቀሳቃሽ አካውንቶች (ሙሉውን ወደዚህ ይፈሳል)
- ከልዩ ኢንቨስትመንት አካውንት (በከፊል) ነው።

2.1.2. የልዩ ፈንድ ቋት (Special Fund Pool)፡- ገቢ የሚያገኘው

- ከልዩ ፈንድ አካውንት (በከፊል)

2.1.3. የባንክ ገዥ ፈንድ ቋት (Statutory Fund Pool)፡- ገቢ የሚያገኘው

- ከመሥራች (መነሻ) ካፒታል (በከፊል) ነው።

2.2. የፈንድ ምደባ፡- እዚሁ አጠገባችን ከፋፍለን በፈንድ ቋት (ፑል) የተመዳደቡት ገንዘቦች (ፈንዶች) የሚቀጥለው ሥርጭታቸው ማለት ነው። ሦስቱ ቋቶች ማለትም የጠቅላላ ፈንድ፣ የልዩ ኢንቨስትመንት ፈንድ እና የባንክ ገዥ ፈንድ ወደ አራት ቦታ ይከፋፈላሉ። በሌላ አነጋገር ወደ አራት ምድቦች ተከፋፍለው ለሥራ (ዳግም ኢንቨስትመንት) ይውላሉ።

- አጠቃላይ ብድር
- የንግድ ብድር
- ኢንቨስትመንትና
- የባንክ ገዥ ኢንቨስትመንቶች (ምርቶች) ናቸው።

2.2.1. ለአጠቃላይ ብድር (Generale Financing)፡- ፈንድ የሚያገኘው እላይ 1.1. ላይ የአጠቃላይ ፈንድ ቋት ካለው ምድብ ውስጥ ነው።

2.2.2. የንግድ ብድር፡- ገንዘብ የሚያገኘው፡- ከአጠቃላይ የፈንድ ቋት (1.1.) ነው።

2.2.3. ኢንቨስትመንት፡- ገንዘብ የሚያገኘው፡- ከልዩ የፈንድ ቋት (1.2.) ነው

2.2.4. የባንክ ገዥ ኢንቨስትመንቶች (ምርቶች)፡- ገንዘብ የሚያገኘው፡- ከባንክ ግዥ ፈንድ ቋት (1.3.) ነው።

3. ትርፍ፡- ትርፎች በሦስት ይጠራቀማሉ።

3.1. ከአጠቃላይ ብድርና ከንግድ ብድር የሚመጡ ለጠቅላላ አስቀማጭና ለባንክ ይከፋፈላሉ።

3.2. ከኢንቨስትመንት የሚገኙ ለልዩ ኢንቨስተሮች እና ለባንክ ይከፋፈላሉ።

3.3. ከባንክ ገዥ ምርቶች የሚገኙ ቀጥታ ወደ ባንክ ትርፍ ይዞራል።

በመጨረሻም የባንክ ድርሻዎች ደግሞ ለባንክ መሥራቾች “ዲቪደንድ” ሆነው ይከፋፈላሉ።

3.9.2. በተግባር የታየው “ኢስላማዊ ባንክ”ና ተፋልሶው

የ“ኢስላማዊ ባንክ” ትግበራ ከቲዎሪው ጋር የተጋጨ ወይም የተራራቀ ነው። ይህም የሆነበት ምክንያት ባንኩ ለመቆም ያሰበው በአራጣ ሲስተም በተመሠረተው የካፒታሊዝም ኢኮኖሚ ላይ ስለሆነ ነው። የፓኪስታን ሙፍቲ ሀቢቡላህ በ “A Juridical Rebuttal of Muhammad Taqi Uthmani” በሚለው ሥራቸው ውስጥ “ኢስላማዊ ባንክ” ማለት ካፒታሊዝምን ለማስለም በተደረገ ምኞት፤ ኢስላማዊ ሲስተም ሊያሳልፈው ያልቻለ የከሸፈ ሙከራ” ብለው ትልቅ ጥራዝ መጽሐፍ ጽፈዋል። ቲዎሪውን አንብቦ ተግባሩን ያየ ሰው “ኢስላማዊ ባንክ” ከተጀመረ ጀምሮ በዐርባ ዓመታት ውስጥ ለኢንደስትሪው ያበረከተው ነገር ቢኖር የዐረብኛ ቃላት

ማስተዋወቁ ብቻ ነው›› ብሎ ሊደመድም ይችላል።[66] ባንኩ ወይም ሲስተሙ ሊያስቆየው የቻለው ወይም የማይተቸው፤ መቅሰፍት ይወርድብናል ብለው ስለሚያስቡ፤ የባንኩ የጥቅም ተጋሪዎችም ሌላው ላይ መሰል ጫና ስለሚያሳድሩ፣ እና “ወለድ” የሚለውን ቃል እንደማስፈራሪያ ስለሚጠቀሙ ነው። ትግበራው በተለይ ገንዘባቸው (ፈያታቸው) በማሸበት ለሚዋዥቅ ሀገራት፤ ከመደበኛው ባንክ ምን ያህል እንደሚከፋ እናየዋለን።

በኢስላማዊ የባንክ አሠራር ባንኩና ተጠቃሚው የጋራ ባለቤትነት አሠራር ነው የሚኖራቸው ቢባልም፤ በቲዎሪ ደረጃ ካልሆነ በስተቀር ዓለም ላይ በተግባር ለመኖራቸው ያጠራጥራል። የሸሪዓው የንግድ አሠራር ትርፍና ኪሳራ መጋራት ላይ የተመሠረተ ነው። ለዚህም ሙሻረካ እና ሙዷረባ የሚባሉት ናቸው ሊሆኑ የሚችሉት። ሙራባሀ የሚባለው አይመከርም። ምክንያቱም ከአራጣ ጋር በጣም ይመሳሰላል። በተግባር ስናየው ደግሞ የአራጣዎች ሁሉ አራጣ ነው። በቲዎሪና በተግባር ምን እንደሚመስል ዋና ዋናዎቹን ለአብነት ያህል አንስተን እንይ።

አማና (በቲዎሪ)

በትርጉም ደረጃ ታማኝነት ማለት ነው። አንድ ሰው ንብረቱን የሚያምነው ሰው ጋር በአደራ ሊያስቀምጥ ይችላል። በአደራ የሚቀበለው ሰው ከአቅሙ በላይ በሆነ ሁኔታ ቢዘረፍ፣ ወይም እንዝህላል ሳይሆን አደራው ቢጠፋበት ወይም በአደጋ ቢወድም የመክፈል ግዴታ የለበትም። ታማኝ ያስባለውም እነዚህ ስለሌሉበት ነው። ታማኝ ሰው በአደራ የተቀበለውን ቀርቶ ከመንገድ ያነሳውን ንብረት እንኳ ባለቤቱ እስኪገኝ ድረስ ያራባለታል። ባለቤቱ ሲመጣ የረባውን ጭምር ይሰጣል። ምሳሌ

[66] Feysal Khan, How ‘Islamic’ is Islamic Banking, Journal of Economic Behavior & Organization 76 (2010) 805-820

አንድ ባለቤቷ ያልታወቀ ሴት ፍየል አገኘ እንበል። ከዚያ ፍየሏ ብትወልድ ወጪውን ቀንሶ ከእነግልገሎቿ ያስረክባል። በአደራ የተቀበለውንማ ከዚህም ይብሳል። ታማኝነትን ማርከስ እምነትን እንደማጥፋት ነው። አማና ሰማይም ምድርም ተራራም የፈሩት ከባድ ኃላፊነት እንደሆነ ቁርአን በ33፡72 ላይ ይገልጻል። ታማኝነት የእምነት ያህል ከባድ ነው። መጽሐፍ የሚወጣቸው የቁርአን እና ሀዲስ አንቀጾች አሉ። ዝርዝር ውስጥ አንገባም። የቀደምት ዘመናት ሙስሊሞች የአማናን ክብደት ስለሚፈሩ ወደ ብድር አስቀይረውና ተጠያቂነትን ወስደው ይቀበሉ ነበር። ብድር የራሱ ሕጎች ስላሉትና የንግድ ጸባይ ስለሚኖረው መበዳደሩ ይመረጣል። አንድ አማና ተቀባይ ሳይጠፋበት ጠፋብኝ ማለት ሌብነት ስለሆነ በሌብነት ሕግ ይታያል። ሆኖም ግን በትክክል ቢሰረቅ፣ በእሳት ወይም ሌላ አደጋ ቢወድም አስቀማጭ ይከስራል። ይህንን ኪሳራ ለመጋራት የብድር ስምምነት ይዋዋላሉ። ብድሩ የተለያዩ ሁኔታዎች ይኖሩታል። በአሁን ወቅት በሀገራችን ተግባር ላይ ያሉና “የሸሪዓን መርሆዎችን ሙሉ ለሙሉ እንፈጽማለን” የሚሉ ባንኮች እንዲህ ናቸው ወይ ካልን ግን አይደሉም፡፡ እዚሁ ከስር በተግባራዊ ተፋልሶ ርዕስ ውስጥ እናየዋለን፡፡

ቀርዶን ሀሰን (መልካም ብድር - በቲዎሪ)

ቀርዶን ሀሰን (ቀርደል ሀሰን በሚል የሰዋሰው አገበባብ ሊነበብ ይችላል) በቁርአን ውስጥ መልካም ብድር ስድስት ቦታ 2፡245፣ 5፡12፣ 57፡11፣ 57፡18፣ 64፡17 እና 73፡20 ላይ ተጠቅሷል። ስድስቱም ቦታዎች ላይ ሰዎች ለማይቸገረው አላህ የሚያበድሩት መልካም ብድሮች ናቸው። ትርጉሙም ለተቸገሩ ሰዎች ያለምንም ስስት ለአላህ ብለን ስንሰጥ ማለትም ችግራቸውን ስንቀርፍ ወይም ስናበድር ለአላህ እንዳበደርን ይቆጠራልና ነው። አላህም በብዙ እጥፍ ይመልስልናል። ለአላህ ማበደር ከአላህ ንብብር ትርፍ አለው።

ያ ለአላህ መልካም ብድርን የሚያበድርና ለእርሱ (አላህ) ብዙ እጥፎች አድርጎ የሚያነባብርለት ማነው? አላህም ይጨብጣል፤ ይዘረጋልም፤ ወደ እርሱም ትመለሳላችሁ። (ቁርአን 2:245)

መልካም ብድር ስናበድር ለአላህ ብለን ስለሚሆን ተበዳሪ መክፈል ባይችል፣ ወይም ለመክፈል ተጨማሪ ጊዜ ቢፈልግ ጊዜ ለመስጠት ወይም ምሕረት ለማድረግ ይመቻል። ለተበዳሪ ምሕረት ማድረግ ደግሞ እጅግ ተወዳጅ ሥራ ነው።

የድኽነት ባለቤት የኾነም (ባለዕዳ) ሰው ቢኖር እማግኘት ድረስ ማቆየት ነው። (በመማር) መመጽወታችሁም ለእናንተ በላጭ ነው። የምታውቁ ብትኾኑ (ትሠሩታላችሁ)። (ቁርአን 2:280)

ተበዳሪ የአበዳሪ ምርኮኛ ወይም እስረኛ ነው። እስኪያገኝ ድረስ ጊዜ መስጠት ያስፈልጋል። የሆነ ነገር ፈልገንበት ካበደርን አራጣ (ሪባ) ነው። አይራባም። ለአላህ ከሆነ ግን አላህ የአበዳሪውን ሀብት ያፋፋዋል። የሚያበድር ሰው አላህ የሚያበድረው ነገር አይከለከለውም። በሕይወታችን የምናየው ነው። አንድ ሰው ከብድሩ የሆነ ነገር ከፈለገ ወደ ንግድ ብድር ማዘዋወር ይሻለዋል። ተበዳሪም በብድሩ ይጠየቃል። አበዳሪም ከተበዳሪው ላይ ጥቅም ይካፈላል። ይህ እንግዲህ ወደ ሙደ̣ረባ (ትርፍ መከፋፈያ) ብድር ይመራናል። ስለሙደ̣ረባ ከማለፋችን በፊት ስለአጠቃላይ የብድር ስነሥርዓት ጥቂት እንግለጽ።

የአማና እና ቀርዶን-ሀሰን ተግባርና ተፋልሶው

ሕዝቦች ገንዘባቸውን በባንክ ብቻ ማስቀመጥና በባንክ ብቻ ማዘዋወር በመንግሥት ታዘዋል፤ ተገደዋል። ባንኮቹ የቆሙት ደግሞ በአራጣ ነው። አራጣ ክልክል በመሆኑ መሄጃ ያጣ ምእመን የዐረብኛ ቃላት በመጠቀም ይጎዱታል። ከላይ

በቲዎሪ ላይ እንዳየነው አማና (አደራ) ተቀባይ የተቀበለውን አደራ ሳይነካ ማስቀመጥ ሲገባው ለራሱ ሠርቶበት ገንዘቡ በግሽበት ተበልቶ ይመልስለታል። አንድ ቆጣቢ ገንዘቡን በአማና ሲያስቀምጥ የሀገሪቷ ግሽበት ሙሉ ለሙሉ ይነካዋል። በመደበኛው የባንክ አሠራር ግን ቢያንስ በዓመት 7% የግሽበት ማካካሻ (ትርፍ) ያገኝ ነበር። በተለይ ለተወሰኑ ዓመታት በውጭ ሀገራት የሚኖሩ (ዳያስፖራዎች) በከፍተኛ ሁኔታ ተጎጂ ናቸው። የሠሩበትን እየላኩ በኢትዮጵያ ብር እየተመነዘረ ይቀመጣል። በዓመት ብዙ ብር በግሽበት ይከስራሉ።

የዚህ መጽሐፍ የመጀመሪያው እትም አካባቢ ማለትም ዶክተር ዐብይ የኢሕአዴግ ሊቀመንበር የሆኑ ወቅት (2010 ኢጋማሽ) የአንድ የአሜሪካ ዶላር የባንክ ምንዛሪ 27 ብር ነበር። በሦስት ዓመት ውስጥ (2015) ግን 54 ብር ደረሰ። ያኔ 10 ሺህ ዶላር ልኮ ከወለድ ነጻ ያስቀመጠ ሰው 270,000 ብር አስቀምጦ ነበር። በሦስት ዓመት ውስጥ 10,000 ዶላሩን ለማግኘት፤ 540,000 ብር ያስፈልገዋል። 270,000 ብር ወይም 100% ጋሽቧል ማለት ነው። በሌላ አነጋገር ይህ ሰው 270,000 ብር ወይም 100% ወለድ ከፍሏል እንደማለት ነው። የፊያት መገበያያ "አደረ" ማለት አራጣ ፈጠረ ማለት ነው። የአራጣ ገንዘብ አላህ በረከቱን ይነሳዋል የሚለው የቁርአን አንቀጽ ከዚህ በላይ ተግባራዊ አስረጅ አይፈልግም። ይህንን ለማካካስ የግድ ወለድ መቀበል ያስፈልጋል። ምክንያቱም እኛ ባንፈልግም "የማዘግየት ወለድ - ሪበነሲአ" አለው። ጭማሪ ስንቀበል ይጣፋሉ። የወሰዱብንን መለሱልን ነው እንጂ አራጣ በላን አይባልም። ሲጀመር ፊያቱን ሸሪዓው እንደ ገንዘብ አልቆጠረውም።

ስለዚህ በዚህ ምሳሌ በውጭ ምንዛሪ ገንዘብ የሚልኩ ሰዎች በመደበኛው በ7% ቢያስቀምጡት ኖሮ 330 ሺህ ብር የመሆን ዕድል ነበረው። ቢያንስ 60 ሺህ ብር ያድኑ ነበር። ብልጥ ሰው ግን ከዚህ በተሻለ በጊዜ ገደብ የሚቀመጥ (Fixed time

deposit) ለምሳሌ 10% ትርፍ በሚባለው ቢቆጥቡ 360 ሺህ ብር የመሆን ዕድል ነበረው። የግሽበቱን ከግማሽ በላይ ማትረፍ ይችሉ ነበር። ጉዳዩ ሀራም (ውጉዝ) ሆኖ ቢሆን ኖሮ ችግር አልነበረውም። ገንዘብን ከሌባ ሲስተም ማስጣል ነው። ከላይ የተገለጸውን ለመድገም ያህል በዓመት በ20% የሚወስዱብንን በ7% ወይም በ10% መለሱልን እንደማለት ነው። ባንኮቹ ጋር ገና ጭማሪ ይቀረናል።

ባንኮቹ በመደበኛ ለሚያስቀምጥ ሰው 7% ሲከፍሉ ወጪያቸው ነው። በወለድ ነጻ በሚሉት "አማና/አደራ" ወይም "ቀርዶን ሀሰን/መልካም ብድር" ሲያደርጉት ግን ገቢ ይሆንላቸዋል። ውጤቱ እጥፍ ነው። ልብ በሉ! 7% ወጪ መሆን የነበረበት (ወለድ)፤ ባንኮቹ ወደራሳቸው ሲያዞሩት በእጥፍ 14% ሆነላቸው ማለት ነው። በየመገናኛ ብዙኃን የማስታወቂያ ጋጋታ የሚያደርጉት ለዚህ ነው። አሁን እንደምናስተውለው ከፍተኛ ሕገወጥ ሥራ እየሠሩ እንደሆነ የዚህ መጽሐፍ አዘጋጅ ተከታታይ ጥቆማዎች ይደርሱታል። መጀመሪያ ፈራ ተባ እያሉ የወለድ ነጻ መስኮት ከፈቱ። እየጠሉትም ቢሆን ጀመሩት። ሲገባቸው ግን ጭራሽ ነጻ ትርፍ ነው። ደንበኞቻቸውን ማባበል ውስጥ ገቡ። ከዚያ የኃይማኖቱን ሰዎችን ቀጠሩ። በእርግጥ መልካም የመሰላቸው ሰዎች አሉ። እንደውም በዚህ ገብተን እናሻሽላለን ያሉ የኃይማኖቱ ሰዎች ነበሩ። በተመሳሳይ ባንኮቹ ከወለድ ነጻ ብለው ስላስቀመጡት ገብተን ወደ ሥራ እንለውጠው ያሉም አሉ። ለአልኮል እና መሰል ፋብሪካ እንዳያበድሩት ላድርግ ያሉም አልጠፉም። ሆኖም ግን ያን ያህል የረባ ሥራ አልሠሩም። የእነዚህ ሸይኾች መልካም እሳቤያቸውን አላህ ይቁጠርላቸው። ሆኖም ግን ግፉን ከተረዱ በኋላ የግፈኞች መሳሪያ መሆናቸውና ለውጥ አለማምጣታቸው ጥፋት ነው።

ከወለድ ነጻ ማለት ለባንኩ “ከስጋት ነጻ ቁጠባ” ወይም ትርፍ የማይጠየቅበት ተቀማጭ ስለሆነ፤ የእስልምና ምልክት አድርጎ ባንክ የሚመጣን ሰው፤ የባንኮቹ ሠራተኞች ተገልጋዩን ከማሳፈር አልፎም በመገፋፋት “ከወለድ ነጻ” እስከማስከፈት ጀመሩ። ከወለድ ነፃ ሒሳቦች አከፋፈት ጋር በተያያዘ በመጽሐፉ ለመግለጽ የማይመቹ የተበላሹ አሰራሮች በተለያዩ ባንኮች እየተተገበሩ እንዳሉ በርካታ የሕዝብ ጥቆማዎች አሉ።

ትግበራው ላይ ከሸሪዓ ተጻራሪ ብቻ ሳይሆን ሆን ተብሎ እስልምናን የመዳፈር ሥራ ነው እየተካሄደ ያለው። ባንኮቹ ከተገልጋዩ በላይ ተቀማጭ ገንዘብ በግሽበት እንደሚቀንስ እያወቁ ገንዘብን በወለድ ነጻ ስም ከሙስሊሙ ማኅበረሰብ መሰብሰብ በአደራ ማስቀመጥ ሳይሆን አደራ መካድ ነው።

ብድርና የዱቤ ሽያጭ

የኢስላም ንግድ የእጅ በእጅ ልውውጥን ያስቀድማል። ወዲያው መክፈል ያልቻለ ሰው አልቻለምና የሰውን ገንዘብ በብድርና በዱቤ መልክ እንዳይወስድ ስነሥርዓት ተቀምጦለታል። ለዚህ ስነሥርዓት ቁርአን ለየትኛውም ኢስላማዊ ጉዳይ ያልሰጠውን ትኩረት ሰጥቶ የቁርአን ረጅሙ አንቀጽ በመባል የሚታወቀውን “አያቱል ሙዳየናህ” ወይም የመበዳደር አንቀጽ የሚሰኘውን መድቦለታል። ካፒታሊዝም እዚህ ጋር ማለትም የእጅ በእጅ ግብይት ተመናምኖ የዱቤ ሽያጭና ብድር እያየለ መጥቶ የመጻጻፍ ስነሥርዓት እየወረደ መምጣት ወይም ትኩረት ማጣት ላይ ነው የተመሠረተው። ንግዶች ከእጅ በእጅ (Cash base) ወደ ዱቤ እና የመተሳሰብ መደብ (accrual or credit or accounting base) ተቀየረ። ካፒታሊዝምና አራጣ፣ አራጣና ፊያት የአንድ ሳንቲም ሁለት ገጽታ ናቸው። አሁን ከእጅ በእጅ ሲስተም ርቀን ክሬዲትና ክሬዲት ካርድ ሲስተም ሰለገባን ያኛውን አናውቀውም ማለት

ይቻላል። የምንማረውም ይህንን ሲስተም ለማገልገል ወይም ጥሩ ባሪያ ስለመሆን እንጂ ሲስተሙን ስለመቀየር አይደለም።

ለአስተውሎት ያህል፡- እጅ በእጅ ግብይት ወቅት ሁሉም ነገር አንድ ቦታና በተመሳሳይ ሰዓት ያበቃለታል። ማሰብና መተሳሰብ አይኖርም። አራጣም ይሞታል። ልክ መዘግየትና ማደር ሲመጣ ግን አራጣ ተረግዞ መወለድ ይጀምራል። አራጣ የሚፈጠረው ሁለት ተገበያዮች አንደኛው ልዋጩን አዘግይቶ የመጀመሪያ እርምጃ እንደተራመደ አራጣ ይረገዛል። ሸይጧን ይከበዋል። ችግር ይጀመራል። ይህን ለመቅረፍ፤ እንዲሁም የእንቅስቃሴ በሮች ተዘጋግተው ሰዎች እንዳይጨናነቁ አላህ የመጻጻፍን በር ከፍቶልን እንድንጻጻፍ አስገድዶናል።

اللَّهُمَّ صَلِّ عَلَىٰ سَيِّدِنَا مُحَمَّدٍ وَعَلَىٰ آلِهِ وَصَحْبِهِ وَسَلِّمْ

ብድር የራሱ ቅደም ተከተሎች አሉት። በቁርአን ረጅሙ አንቀጽ የብድር አንቀጽ ነው። የብድር ሥነሥርዓትን በስፋት ተብራርቶበታል። ይህ አንቀጽ ከመዘንጋቱ ብዛት ለብዙ ነጋዴ እንግዳ ሲሆን ይታያል። የቁርአን ሱረቱል በቀራ 2፡282 ስለ ዕዳና ብድር እንይ። (በቅንፍ ያሉትና በትንንሹ የተጻፉት ከዕውቅ የቁርአን ትንታኔ መጻሕፍት የተወሰዱ የጸሐፊው ማብራሪያ ናቸው)

እናንተ ያመናችሁ ሆይ (ጥሪው አማኞችን ሲሆን፡- አስከትሎ ወይ ተግብሩ ሊል ነው፤ ወይ ተከልከሉ ሊል ነው)

እስከተወሰነ ጊዜ ድረስ (ብድር ወይም እዳ ወይም ተመላሽ ውለታ ወቅት በቀነ ገደብ due date መሆን እንዳለበት ያመለክታል)

በዕዳ በተዋዋላችሁ ጊዜ ጻፉት (ማንኛውም ዕዳ - የዱቤ ሽያጭንም ጨምሮ ጻፉት ይላል። “ፈክቱቡሁ” ሲል “ፈ” ፊደል ለማስገደድ ነው የመጣው)

ጸሐፊም በመካከላችሁ በትክክል ይጻፍ፤ (የውል ጽሑፍ ሙያተኛ፣ ሒሳብ ሰራተኛ፣ ወይም ጠበቃና የመሳሰሉ ሰዎች ሳያዳሉ በትክክል ይጻፉ)

ጸሐፊም አላህ እንደ አሳወቀው መጻፍን እንቢ አይበል፤ (ግዴታው የመጣው ዕውቀቱ የአላህ ስጦታ በመሆኑ አይኩራ)

ይጻፍም (ፈልየክቱብ - ስለዚህ የአላህ ግዴታ በመሆኑ የጽሑፍ ሰዎች ለተዋዋዮች ይጻፉ ብሎ ለማጥበቅ ትእዛዙን ደገመው)

ያም በርሱ ላይ ዕዳው ያለበት ሰው በቃሉ ያስጽፍ (የማስጻፍ ኃላፊነት የባለዕዳ ነው። በቃል የተባለበት ምክንያት ሲጻፍ ምስክሮች እንዲሰሙ ጭምር ነው። ወይም ከተጻፈ በኋላ ከመፈራረም በፊት ማንበብ ይቻላል)

አላህን ጌታውንም ይፍራ፤ ከርሱም (ካለበት ዕዳ) ምንንም አያጉድል (ድብቅ ነገር አይተው፣ አሻሚ ሐሳብ አያስገባ። ለአበዳሪ፣ ለተበዳሪና ለምስክር የተጣራ ውል መሆን አለበት)

ያም በርሱ ላይ ዕዳው ያለበት ቂል ወይም ደካማ (በሕግ ቋንቋ “insane and/or minor” የሚባሉ እንደ ሕጻን፣ ሽማግሌ፣ አዕምሮ የሳተ፣ ሕመሙ ወይም እርጅናው ለመዋዋል የማያስችለው)

ወይም በቃሉ ማስጣፍን የማይችል ቢኾን (ቂል እና/ወይም ደካማ ባይሆንም የማስጻፍ ልምድ የሌለው፣ ነገር የማያውቅ ወይም የሚዋዋሉበት ቋንቋ የማይችል ማለትም ተዋዋይና ምስክር የማይግባቡበት የተለያየ ቋንቋ ቢሆን እንደማለት ነው። ለዚህ በጣሊያንና በኢትዮጵያ መካከል የተካሄደው የውጫሌ ውል ውዝግብ ዓይነተኛ ምሳሌ ነው። ውሉ በጣሊያንኛና በአማርኛ ነበር፤ የጣሊያኖች ተዋዋዮች አማርኛን ሲችሉ፤ ነገር ግን የሐበሾቹ ተዋዋዮች ጋር አስተርጓሚ የነበሩት ግራዝማች ዮሴፍ የሚችሉት ፈረንሳይኛን ነበር። ጣሊያኖቹ በፈረንሳይኛ የተናገሩትን በአማርኛ ይሰፍር ነበር። ሆኖም ግን የጣሊያንኛ ጸሐፊ ሲጽፍ አንሻፈው ጽፈውት የታወቀው ወሉ ሥራ ላይ ሲውል ነበር። ወደ አድዋ ጦርነት አመራ። አጭበርባሪዎቹ ተሸነፉ)

ዋቢው በትክክል ያስጥፍለት፤ (የመግባቢያ ችግር ያለበት ወይም የአካል ጉዳት ወይም የዕድሜ አለመድረስ ያለበት ሰው ተወካይ እንደራሱ ሆኖ ተከታትሎና ተጠንቅቆ ያስጽፍ)

ከወንዶቻችሁም ሁለትን ምስክሮች አስመስክሩ (የብድር ውል መጻጻፍ ብቻ በቂ አይደለም። ሁለት የወንድ ምስክር ግዴታ ነው። ምክንያቱም ወንዶች፤ ሴቶች የማይገቡበት አደገኛ ቦታ ጭምር መግባት ይችላሉ)።

ሁለትም ወንዶች ባይኾኑ ከምስክሮች ሲኾኑ ከምትወዱዋቸው (ታማኝ የሆኑ ማለትም ምስክሮች በአጠቃላይ ታማኝ ሰው መምረጥ ያስፈልጋል)

አንድ ወንድና አንደኛዋ ስትረሳ አንደኛይቱ ሌላዋን ታስታውሳት ዘንድ ሁለት ሴቶች (ይመስክሩ)፤ (ሴቶች ሁለት ይሁኑ የተባለው፡- በተለይ ሴት በወር አበባ እና በወሊድ ወቅት ደም ስለሚፈሳት ሕመምና ራስ ምታት ይኖራል። ስለዚህ የማስታወስ ክኽሎትን ይቀንሳል። በዚህ ጊዜ የተፈጸመ ውል በክርክር ወቅት እንዲተዋወሱ ከአንድ ወንድ ጋር ተጨማሪ ሁለት ሴቶች ይፈቀዳል። የምስክር ወቅት መስቀለኛ ጥያቄ ላይ ሴቶቹ መተራረም ወይም መተጋገዝ ይችላሉ ማለት ነው። በወር አበባ ወቅት በነበራት ተፈጥሮ ምክንያት፤ ተጠያቂ መሆን የለባትም። አንድ ተጨማሪ ጥበብ ብንጠቅስ አንድ ወንድ እና አንድ ሴት ብቻ ሆኖ ቢሆን ኖሮ፤ ተዋዋዮቹ ቢጣሉ ምስክሮቹ በሚጠሩበት ወቅት ፍርድ ቤቱ ሩቅ ቦታ ቢሆን ባእድ የሆነ ወንድ እና ሴት ለጉዞ ያስቸግር ነበር፤ በተጨማሪም ሴቷ አንድ ከሆነችና ከወንዱ ጋር ወደ ፍቅርና ጋብቻ ቢያመሩ የምስክር ሥርዓቱን ሊያዛቡ ይችላሉ። በአንዴ ከሁለት ሴቶች በፍቅር መውደቅ ኢምንት ነው። አላህ በሁሉ ነገር ላይ ሙሉ አዋቂ ነው)

ምስክሮችም በተጠሩ ጊዜ እምቢ አይበሉ፤ (ሲዋዋሉም ይሁን ተጣልተው ሲከራከሩ ለምስክርነት መቅረብ ግዴታ ነው። አልመሰክርም ማለት አይቻልም። ሕግም ያስገድዳል)

(ዕዳው) ትንሽ ወይም ትልቅ ቢኾን እስከ ጊዜው ድረስ የምትጽፉ ከመኾን አትሰልቹ፤ (ትንሽ ነውና አያጣላም ተብሎ፤ ወይም ግዙፍ ስለሆነ አይሳትም ተብሎ ከመጻፍ አትወገዱ። የትኛው እንደሚያጣላ አይታወቅም። የውል ወረቀቱ ደግሞ ቢያንስ ዕዳው እስኪጠናቀቅና እስኪዘጋ ድረስ አስቀምጡት)

ይኻችሁ አላህ ዘንድ በጣም ትክክል፣ ለምስክርነትም አረጋጋጭ፣ ላለመጠራጠራችሁም በጣም ቅርብ ነው (ማንኛውም ብድር መጻፉ እንደ ኢስላም አላህ ዘንድ በጣም ትክክልና ኃይማኖታዊ፣ እተዋዋዮችም ዘንድ ሸይጧን

እንዳይጎተጉታቸው ተከላካይ፣ ከጊዜ ብዛት እንዳይረሳ፣ እንዳያጠራጥር፣ ለፍርድ ሒደትም የሚያረጋግጥ ነው)

ግን በመካከላችሁ እጅ በእጅ የምትቀባበሏት ንግድ ብትኾን ባትጽፉዋት በናንተ ላይ ኃጢአት የለባችሁም (የእጅ በእጅ ልውውጥ ላይ አለመጻጻፍ ኃጢአት የለበትም ማለት የዱቤ ሽያጭ ወይም ብድር ከሆነና ካልተጻፈ ኃጢአት አለበት ማለት ነው። ዱቤና ብድር አለመጻጻፍ ኃጢአተኝነት ነው። ምክንያቱም ሲውል ሲያድርና ነገሮች ሲለዋወጡ ሰዎችም ሊለዋወጡና የሸይጧን መጠቀሚያ እንዲሆኑ በር መክፈት ነው። እጅ በእጅ ስትሻሻጡ እንኳ ብትጽፉት የተሻለ ነው ማለት ነው)

በተሻሻጣችሁም ጊዜ አስመስክሩ (የእጅ በእጅም ቢሆን ባትጽፉትም ብትጻፉትም ግን አስመስክሩ። ይህ አሁን ላይ ምናልባት በደረሰኝ ሊተካ ይችላል። ስለዚህ ይህ አንቀጽ ተግባራዊ ቢደረግ “ደረሰኝ ካልተቀበሉ አይከፈሉ” ብሎ መጻፍ ሙስሊም ሱቅ ውስጥ ትርጉም አልባ ይሆን ነበር። ሦስቱም ወገኖች ማለትም ሻጭ፣ ገዥና ምስክር ፊታቸው በግልጽ መታየት አለበት። ይህ የግብይት መሠረቶች ውስጥ ነው። የተሸጠ ዕቃ የሚመለስበት አጋጣሚ ስለሚኖር ወይም ግብይቱ ችግር ኖሮበት ወደ ክርክር ቢያመሩ ሦስቱም በግልጽ የተያዩ መሆን ይጠበቅባቸዋል። በግልጽ ላልታየ ሰው መሸጥ፣ ካልታየም ሰው መግዛትና ምስክር መሆን ሕጉ ይከለክላል። መሸፈን ቢፈልጉ እንኳ ለግብይቱ ሲሉ በአግባቡ መገለጥ ሊኖር ነው)።

ጸሐፊም ምስክርም (ባለጉዳዩ ጋር) አይጎዳዱ (ጸሐፊ መጻፍ ግዴታው ነው ተብሎ በአላህ ተወስኖበታል። ግዴታህ ስለሆነ «ና ጻፍ ና መስክር» እያሉ በየቦታው ማስቆምና ማጓተት ተገቢ አይደለም። ስለዚህ ጸሐፊ የጻፈበትን ወይም ያዋዋለበትን ገንዘብ ቢቀበል አይኮነንም። ምስክርም ለመመስከር ሩቅ ቦታ ሲሄድ መንግሥት፣

ፍርድ ቤት ወይም ሁለቱም ተዋዋይ ወገኖች ወይም የሀገር ሽማግሌዎች የውሎ አበል ወይም መጓጓዣ ቢከፍሉዋቸው እንደ ጉቦ አይቆጠርም)

(ይህንን) ብትሰሩም (ሲጻፍም ይሁን ስትመሰክሩ ወይም ለሙያው ስትከፍሉ ወይም የሙያ ገንዘብ ስትጠይቁ ብትጎዳዱ)

በናንተ (የሚጠጋ) አመጥ ነው፤ አላህንም ፍሩ፤ አላህም ያሳውቃችኋል፤ አላህም ነገሩን ሁሉ ዐዋቂ ነው። (ወደ ጎጂው፣ አጭበርባሪው፣ ቅኔያዌ ቃላት አካታቹ፣ ጻፍ መስክር ሲባል እምቢተኛው ወዘተ. ዘንድ አመጽ ይጻፍባችኋል። ምክንያቱም ከአዋቂዎቹና ከብልጦቹ በላይ ውስጥ አዋቂ የሆነ አላህ እንዳለ ተገንዘቡ። (ቁርአን 2፡282)

ይህ የቁርአን ረጅሙ አንቀጽ በዚህ አያበቃም። ጸሐፊ እና/ወይም ምስክር ባይገኝ ምን ማድረግ ይቻላል ለሚለውም አስከትሎ ምላሽ ይሰጣል። ወደ ብድር ዋስትና ይወስደናል።

اللَّهُمَّ صَلِّ عَلَىٰ سَيِّدِنَا مُحَمَّدٍ وَعَلَىٰ آلِهِ وَصَحْبِهِ وَسَلِّمْ

የብድር ዋስትና

በኢስላም የብድር ዋስትና ተፈላጊ ነው። አንቀጹ ላይ የብድር ዋስትና ጸሐፊ ሳይኖር ወይም በጉዞ ወቅት ላይ የጠቀሰው፣ ሁሉም በተሟሉ ወቅት ጭምር ችግር ላለማባባስ ነው። ማስያዣ የሌለው ሰው ሊኖር ይችላል። የሚጽፍም የሚመሰክርም የሚያዝም የሌለበት ቦታ ቢሆን አበዳሪ ለአላህ ብሎ ይስጥ ወይም ያበድር። ምንዳውን ከአላህ ይፈልግ። በተቃራኒው ተጽፎም ምስክር ተቆጥሮም እያለ ማስያዣ አልተከለከለም። ምክንያቱም ተበዳሪ ሳይከፍል ቢሞት በዕዳ አይያዝም። ዕዳ ያለበት ሰው ላይ የሙት ሶላት (ሶላተል ጀናዛ) መስገድ ይጠላል። ቢያንስ ዕዳውን እኔ እሸከማለሁ የሚል ዘመድ ወይም ወራሽ መኖር አለበት። ስለዚህ ተበዳሪ አስይዞ ተበድሮ ሳይከፍል ቢሞት ተበዳሪ ብዙ አማራጭ አለው። ይቅር ብሎ ማስያዣውን መመለስ፣ ወራሽን ማስከፈል፣ ሽጦ ልዩነቱን ለወራሽ መስጠት ወይም ዕዳውን ማቻቻል ይችላል። ሟች ከዕዳ ነጻ ነው ማለት ነው።

በጉዞም ላይ ብትኾኑና ጸሐፊን ባታገኙ የተጨበጡ መተማመኛዎችን ያዙ። ከፊላችሁም ከፊሉን ቢያምን ያ የታመነው ሰው አደራውን ያድርስ። አላህንም ጌታውን ይፍራ። ምስክርነትንም አትደብቁ። የሚደብቃትም ሰው እርሱ ልቡ ኃጢአተኛ ነው። አላህም የምትሰሩትን ሁሉ አዋቂ ነው። (ቁርአን 2:283)

ይህ ሥርዓት የኢስላም ውብ ሥርዓቶች ውስጥ ነው። ቢተገበር ኖሮ በገንዘብ የሚጋጭ ሰው አይኖርም ነበር ማለት ያስችላል። ከዚህ ሲያልፍ ብድሮች አብሮ የሚያያዙ ኃላፊነትና ተጠያቂነት ይጎዳኛቸዋል። ተበዳሪ በብድሩ የሚጠየቅበት ወይም ኪሳራ የሚጋራበት ነው። እላይ የአራጣ ክፍል ላይ እንዳየነው ብድር ለአላህ ተብሎ ነው የሚሰጠው። ከዚያ ውጭ ግን የንግድ ብድር ነው። ወደ ባንኮች ሥርዓት ስንመጣ ድሆች ለባንኮች ሲያበድሩ (ማለትም ሲቆጥቡ) ለባንኩ አዝነውና ለአላህ

ብለው ነው የሚል አይኖርም። “ቀርድ፣ ቀርዶን ሀሰን” የሚሉ የባንኮች በማስታወቂያዎች እናያለን፣ እንሰማለን። ግራ አጋቢ ነው። ያለምንም ጥቅም ለሀብታም የሚሰጥ ብድር አይኖርም። ይህንን ከስር በትግበራ ክፍል ላይ እናየዋለን። አማና ስለሚያስቸግር ወደ ብድር፣ በባዶ አበዳሪ ሲጠፋ ወደ ትርፍን መጋራት ወይም ሙዷረባ (ፓርትነርሺፕ) አሠራር ይመራናል።

ሙዷረባ (በቲዎሪ)

በቲዎሪ ደረጃ የሙዷረባ አሠራር «ትርፍ ብቻ የመጋራት አሠራር» ሲሆን ገንዘብ ያለው ሰው፤ ገንዘብ ከሌለው ሰው ጋር ተቀናጅተው የሚሠሩበት ነው። ባንኮች በመጡበት ዘመን እንተርጉመው ካልን፤ ባንኮች ገንዘብ ስላላቸው የሥራ ብቃትና ክኽሎት ላላቸው ነገር ግን ለሥራው መከወኛ የሚሆን ገንዘብ ለሌላቸው ሰዎች ገንዘብ የማበደር ሥርዓት ነበር። አዲስ ተመራቂ፣ ከእስር ለተፈታ፣ አዲስ ሥራ ጀማሪ፣ ጥሩ የሥራ ጥናት ላቀረበ፣ ወዘተ ገንዘብ በማቅረብ የሚሠራበት የብድር ሥርዓት ቢሆንም ቅሉ፤ ባንኮቹ ለድሆቹ ማበደር ሲገባቸው ድሆች ለባንኮች ያበድሩና፤ ባንኮቹ ሠርተው «ትርፍ ብቻ» የሚያጋሩበት አሠራር ሆነና አረፈው። በሙዷረባ ኪሳራ ቢፈጠር ሙሉ ለሙሉ የገንዘብ አምጪው (ሀብታሙ) ይሆናል። ምክንያቱም ተበዳሪው ኪሳራ ኖሮ ሊያካክስ ቀርቶ ወትሮም ቢሆን ገንዘብ አልነበረውም። ስለዚህ ባለገንዘቡ ኪሳራውን ሲሸፍን ደሀው ጊዜና ጉልበት ይከስራል። ትርፍ ካለ ግን በቀዳማይ የውል ስምምነት መሠረት ይከፋፈላሉ። ልብ በሉ! መቶ ፐርሰንት ኪሳራ የገንዘብ አምጪ ሲሆን፤ ትርፍ ግን የጋራ ነው። ባንኮች በቲዎሪው መሠረት ሙዷረባን የማይደፍሩትና ተግባራዊ የማያደርጉት ተበዳሪው ቢከስር ኪሳራ ስለሚሸከሙ ነው። አሊያም በሁሉም ብድር ላይ እራሳቸው እንደ ባለቤት ከተበዳሪ ጋር እየተሯሯጡ ሊሠሩ ነው። ይህ ደግሞ አይቻልም። ስለዚህ ሕዝቡ ገንዘብ እንዲያመጣና እነርሱ እንዲሠሩበት አድርገው ገለበጡት። አበዳሪና

ተበዳሪ ተገላበጡ። ሸሪዓው ፈረሰ። ለዚህም ሁለት ዓይነት ስምምነቶች ሊኖሩ ይችላሉ። እነሱም ትግበራ በሚለው ቀጣይ ክፍል ላይ ይቀርባል።


የሙዷረባ ተግባርና ተፋልሶው (Reversed Muduarabah)

እላይ እንዳየነው ሙዷረባ የሚባለው ገንዘብ የሌለው ሰው ገንዘብ ካለው ሰው ጋር በጋራ የሚሠሩበት ነበር። ስለዚህ በዚህ አሠራር ቢሆን ኖሮ ባንኮች ገንዘብ ለሌላቸው ሰዎች ማበደር ነበረባቸው። ይህ ስለማይሆን ስሙን "ሙዷረባ" ብለውት ድሆች ለባንክ በሙዷረባ መልክ እንዲያስቀምጡ ያግባቡዋቸዋል። ወደዚህ ደረጃ የሚያድጉት ምእመናን ገንዘባቸውን ከወለድ ነጻ አስቀምጠው ከጉዳት ውጪ ምንም ትርፍ እንዳላገኙ ሲገነዘቡ ወደመደበኛ ሲቀይሩባቸው የሚያቀርቡት አማራጭ ነው። በሙዷረባ ኪሳራ ከመጣ ገንዘብ አምጪው ማለትም ቆጣቢው 100% ይሸፍናል። ትርፍ ከመጣ ግን በስምምነታቸው መሠረት ይካፈላሉ። አሠራሩ እንደሚከተለው ነው።

1. **ሙዷረባ ሙጥለቃ** (Unrestricted Mudarabah) የሚባለው አስቀማጩ (ኢንቨስተሩ፣ ባለሒሳቡ) ባንኩን "አምንሀለሁ፣ ጥሩ ስም አለህ። ስለዚህ ገንዘቤን በወደድከው እና አዋጭ ነው ባልከው ኢነቨስትመነት ላይ አውለው ሊል ይችላል። ሙሉ እምነት ለባንኩ ሰጥቶ የሚሆነውን መስማት ነው።
2. **ሙዷረባ ሙቀየዳ የሚባለው** (Restricted Mudarabah) አስቀማጩ፣ (ኢንቨስተሩ፣ ባለሒሳቡ) ባንኩ ከሚያቀርባቸው ኢንቨስትመንቶች ሊመርጥ ይችላል። ለምሳሌ ማዕድናት ወይም ከብት ማድለብ ላይ ወዘተ. ኢንቨስት አድርግልኝ። ከነገርኩህ ዘርፍ (ወይም ዘርፎች) ውጭ ገንዘቤ እንዳይውል ሊል ይችላል።

ስለአሠራሩ በአጭሩ ለመግለጽ

ሠንጠረዡን ስታነቡ ተራ ቁጥሮቹን ከ1 ቁጥር ጀምራችሁ ቀስቱን ተከታተሉት



ደንበኛው ወይም ኢንቨስተሩ (አስቀማጩ) ለምሳሌ ለአንድ ዓመት በሰባ፡ሠላሳ (70፡30) የትርፍ ክፍፍል የሆነ ገንዘብ ይዞ ባንኩ ጋር ይመጣል። ባንኩ በስምምነታቸው መሠረት ገንዘቡን ኢንቨስት ያደርገዋል። በትርፍ ክፍፍላቸው

መሠረት 70 በመቶው ወደ አስቀማጩ ሒሳብ ይገባና ባንኩ 30 በመቶ ትርፉን ይወስዳል። በሙዷረባ ወቅት ኪሳራ ቢፈጠር ኪሳራው ሙሉ ለሙሉ የሚወስደው ገንዘብ አምጪው ነው። ልክ በዚሁ ተመሳሳይ፤ ባንክ ለሥራ ፈጣሪ ሰው በሙዷረባ ሥርዓት ቢያበድር እና ኪሳራ ቢፈጠር ተበዳሪው (ሥራ ፈጣሪው) ድካሙን ሲከስር አበዳሪው (ባንኩ) ገንዘቡን ይከስራል። ገንዘብ አምጪ የሆነ ክፍል ኪሳራ ሙሉ ለሙሉ የሚወስደው ተበዳሪው (ሥራ ፈጣሪው) የአሠራር ግድፈትና ንዝህላልነት አለመፈጸሙ ከተረጋገጠ ነው።


በዚህ አሠራር እንኳ ባንኮች እሺ አይሉም። ምክንያቱም ብዙ ትርፍ ሊያካፍሉ ነው። 70% ሲያካፍሉ ብዙ ሊመስለን ይችላል። አንድ ሚሊዮን ብር ያስቀመጠ ሰው ባንኩ 40 ሺህ ብር ነው ያተረፍኩት ብሎ 28 ሺህ ብር ቢሰጠው ከመደበኛ ወለድ እጅግ በታች ነው። 2.8% ማለት ነው። ገንዘቡ ግሽበት ብዙም የማያጠቃው እንደ አሜሪካ ዶላር ቢሆን ጥሩ ነው እንል ነበር። 20% እየጋሸበ 3% ትርፍ በጣም አክሳሪ ነው። የባንኩ ሙዷረባ የሸሪዓውን ሙዷረባ በ180 ዲግሪ ገልብጠውና አቃርነውት ነው የሚተገብሩት። የዚህ መጽሐፍ አዘጋጅ ግልብጥ ሙዷረባ (Inverse Muduarabah) የሚል ስም የሰጠው ለዚህ ነው።

ሙሻረካ (በቲዎሪ)

የመጋራት አሠራር ማለት ነው። ይህኛው አሠራር የ"ኢስላማዊ ባንክ" ጽድት ያለ የአሠራር ዓይነት ነው። በዚህኛው አሠራር ትርፍና ኪሳራ ቀድሞ በተቀመጠ መቶኛ መሠረት ይከፋፈላሉ። የግድ ግን ባዋጡት ገንዘብ መሠረት ይሁን አይባልም። ሁለቱም ማለትም ባንኩና ገንዘብ አምጪው በኢንቨስትመንቱ አስተዳደር እና ኡዲት ላይ በጋራ ሊሳተፉ ይችላሉ። ሆኖም ግን ባንኩ በሥራው ላይ ከኋላ ሆኖ ነው በንቃት የሚከታተለው። ወይም ሁለቱም የጋራ አስተዳደር ሊያቋቁሙ ይችላሉ። ምክንያቱም

ትርፍና ኪሳራው የጋራ ነው። ኪሳራው ግን ባዋጡት ካፒታል ልክ ይሆናል። በተግባር ግን የሚደፍረው ሀገር ጠፍቷል። ዐረብ ኤሚሬት፣ ፓኪስታን፣ ማሌዥያና ባንግላዴሽ ጀምረውት አቅቷቸዋል።

(ቢሆን ኖሮ ብላችሁ ሠንጠረዡን ስታነቡ ተራ ቁጥሮቹን ከ ቁጥር ጀምራችሁ ተከታተሉት)



በሀገራችን ያሉ ባንኮች ንጹሕ የ"ኢስላማዊ ባንክ" ሊተገብሩ ይቅርና ኢስላማዊ ገበያና ገንዘብ በመጥፋቱ የሙስሊም ሀገሮችም ተቸግረውበታል። በሀገራችን ያለው

ሙስሊሙ “ያው ስሙ እንኳ ይኑር” በሚል ነው ገንዘቡን በወለድ ነጻ መስኮቶች እያስቀመጠ ያለው። የሚያሳዝነው ንግድ ባንኮች በስመ ዓረቢኛ ገንዘቦችን አስረው፤ መስኮቱ ከመኖሩ በፊት የባሰ ነገር እየሆነ ነው። ስለዚህ በፈንድ እጥረት ምክንያት ሥራ ፈትቶ እየተሰቃየ ላለው ዜጋ፤ ንግድ ባንኮች በታሰረው ብር ሥራ ሠርተው ሕዝቡን እንዲያሠሩ ይህ ጸሐፊ ብሔራዊ ባንክን አደራ ይላል። ኢስላማዊ የሚባሉ ባንኮች ለባንክ ኢንደስትሪ የጨመሩት ነገር ቢኖር ዐረብኛ ስምና ቃላት ከማስተዋወቅ አልዘለለም። በ“ኢስላማዊ ባንክ” ወይም ወለድ ነጻ ስም የሀገር ገንዘቦች ያለአግባብ ከሥራ ውጭ ሆነው መታሰር የለባቸውም።

ሙራባሀ በቲዎሪ እና የተግባር ተፋልሶው

ሙራባሀ በቲዎሪ፡- ቀላል ትርጉሙ አትርፎ መሸጥ ማለት ሲሆን ከብድር ጋር ወይም ገንዘብን ከማከራየት ጋር ግንኙነት የለውም። የሸሪዓው የግብይት ሕግ ለባንኮች የሚሠራ ከሆነ ሊተገበር ይችላል። ማለትም የባንኮቹ አሠራር ለሸሪዓው ሕግ ተጣጣሚ መሆን አለበት። ባንክ ይሁንም አይሁን የንግድ ሕግጋት ጋር የገጠሙ ግብይቶች ሁሉ ፍቁድ ናቸው። ዛሬ ያለውም ይሁን ነገ የሚመጣው የባንክ ሲስተም ከሸሪዓው ሕግ ጋር ከገጠመ ይወደዳል እንጂ አይኮነንም። ቴክኖሎጂ ብዙ አዳዲስ ነገሮችን ይዞ ሲመጣ ከቋሚ የግብይት ሕግጋት ጋር መፈተሽ ያስፈልጋል። የመጣውን ሁሉ እንዳለ መቀበል ወይም እንዳለ መቃወም ወይም እጅን አጣጥፎ መቀመጥ አግባብ አይደለም። “ኢስላማዊ ባንክ” የፈጠሩ ሰዎች ለሙራባሀ የንግድ ሕግን ለማስቀመጥ ሞክረዋል።

የ“ኢስላማዊ ባንክ” ፈጣሪዎች ለሙራባሀ ያስቀመጡት ቅድመ ሁኔታ

1. *የዕቃው ባለቤትነት የሻጯ (የባንኩ) መሆን አለበት።*
2. *ባንኩ የዕቃው ባለቤትነት ሰነድ በስሙ ማግኘት አለበት።*
3. *ዕቃው በሽያጭ ወቅት መገኘት አለበት። አየር ላይ ወይም ውጭ ሀገር ወይም በእርግዝና ላይ ማለትም ሆድ ውስጥ ያለ ጥጃ፣ ባሕር ውስጥ ያለ ዓሳ መሆን የለበትም። (ስለዚህ አየር በአየር ፕሮፎርማና ደረሰኝ መሸጥ አይሆንም ማለት ነው)።*
4. *የዕቃው ተጠያቂነትና ኃላፊነት የሻጯ መሆን አለበት። በሌላ አነጋገር ባንኩ በስሙ ገዝቶ መልሶ ለተበዳሪ እስኪሸጠው ማለትም እስኪያስተላልፈው ድረስ ሙሉ ኃላፊና ተጠያቂ መሆን አለበት።*
5. *በአንድ ግብይት ሁለት ግብይት በእነዚያው ተመሳሳይ ተገበያዮች መካከል መኖር የለበትም። በካሽ ግዛልኝና ወዲያው አትርፌ በዱቤ ልግዛህ መባል የለበትም። ሙራባሃ ከቲዎሪውና ትግበራው ጋር ያለውን ግጭት በነዚህ መፈተሽ እንችላለን።*

እንደሚታወቀው በኢስላም በየትኛውም ግብይት አራጣ ክልክል በመሆኑ ባንክም ላይ ይህንኑ የግብይት ሕግ ብቻ ነው የሚሠራው። ሽያጭ ላይ ክልክል (ሀራም) የሆኑ ሁሉ ሙራባሀም ላይ ክልክል ናቸው። ሙራባሀ ሀላል (ፍቁድ) የሚሆነው ሽያጭ እስከሆነ ድረስ ብቻ ነው። ሙራባሀን ለባንክ ስናመጣው የሸሪዓው የንግድ ሕግ በመሆኑ ለንግድ እንጂ አራጣን ሀላል (ፍቁድ) ለማድረግ ሊሆን አይችልም። ሆኖም ግን ይህንን ቅድመ ሁኔታ የባንኩ ፈጣሪዎችም አልቻሉትም። “ኢስላማዊ ባንክ”ን ከፈጠሩ ወይም ያዳበሩ ምሁራን ውስጥ ተቂ ዑስማኒ

"ሲጀመር ሙራባሀ የተወሰነ የሸያጭ ዓይነት እንጂ ገንዘብ ማበደር አይደለም። በሸሪዓ በደንብ የሚታወቁት ሙደረባና ሙሻረካ ናቸው። አሁን ባለው የኢኮኖሚ መዋቅር ሙደረባና ሙሻረካን መጠቀም አዳጋች ነው። በመሆኑም የዘመናችን የሸሪዓ ኤክስፐርቶች የተወሰኑ ቅድመ ሁኔታዎችን በማስቀመጥ አዘግይቶ ለመክፈል ሙራባሀን ፈቅደዋል። በዚህ አገባብ ሁለት ነገሮች የግድ መታወቅ አለባቸው። (አንደኛው) ሙራባሀ የተጣራው የሸሪዓ የግብይት ዓይነት አለመሆኑና ወለድን ለመሸሸ ጥቅም ላይ መዋሉን፣ (ሁለተኛው) ኢኮኖሚውን እስላማዊ ለማድረግ እንደ ድልድይ እንዲያገለግል ሲባል ብቻ ነው። ይህም የሚያገለግለው ሙደረባና ሙሻረካ ተግባራዊ በማይደረጉባቸው ሁኔታዎች ብቻ ነው።"[67]

ሙራባሀ በሊቃውንት የንግድ ሕግጋት (ፊቂሕ) ውስጥ ብዙም አይታወቅም። የ"ኢስላማዊ ባንክ" ጀማሪ ምሁራኑ ይህንን ሐቅ አልካዱም። ይህንን የካፒታሊዝም ሲስተም ለማምለጥ ብለው የፈጠሩት ነው ብለን በመልካም እንጠርጥራቸው። ሆኖም ግን ትግበራው ከድጡ ወደ ማጡ ሆኗል።

የሚከተለውን ቲዎሪያዊ የሙራባሀ ሞዴል እንመልከት። አንድ ገዢ የሚፈልገው ዕቃ ኖሮ ብር ሲያጥረው ሊከፍልለት የሚችል ድርጅት ወይም ሰው ወይም ባንክ ፈልጎ ይገዛለትና መልሶ ይሸጥለታል። ልድገመውና እርስዎ የሚፈልጉት ዕቃ ኖሮ ብር ሲያጥሮት ባንክ ይፈልጉና "ይህንን ዕቃ አንተ ግዛውና ሸጥልኝ" ይለዋል። እንዲህ የተደረገው ባንኩ ሲገዛው የዕቃው የመሰበር፣ የመበላሸትና የመሰረቅ ወዘተ. ስጋቶችን (ሪስኮችን) እንዲወስድ ነው። ባንኩ ስጋት መጋራቱ ብድር እንዳይሆንና የሸያጭ ሥርዓት እንዲይዝ ነው። ባንኩ ስጋት ካልተጋራና ባለቤትነት ካልያዘ ሸያጭ ሳይሆን


[67] Umar Ibrahim Vadillo, Fatawa on Bankig: The huse of Interest Received on Bank Deposits, 2006, Page 41.

ብድር ነው። ወይም አራጣን የመሸወጃ[68] መንገድ ነው። ከመደበኛው ባንክ አልተለየም ወይም ብሷል። ስጋት መጋራት የሚቻለው የዕቃው ሰነድ (Titles) በባንኩ ሲሆን ነው። ሰነዱ ማለትም ደረሰኙ በገጠው ስም (በእርስዎ) ሆኖ ለባንኩ "በካሽ[69] ክፈልልኝና እኔ በረጅም ጊዜ ልክፈልህ" ከተባለ አሁንም ከመደበኛው ጋር ምንም ልዩነት አይኖረውም። ልዩነቱ በመደበኛው የባንክ አሠራር ተበዳሪው ገንዘብ ተበድሮ እራሱ ሄዶ ሲከፍል በሙራባህ ባንኩ ሲከፍል ማለት ናቸው። ስለዚህ ከመደበኛው የባንክ አሠራር ለመሸሽ ባንኩ ዕቃውን በስሙ ገዝቶና ደረሰኝ አስቆርጦ ካበቃ በኋላ ባንኩ መልሶ ሻጭ ይሆናል። ዕቃውን ላስገዛው ሰው መልሶ ይሸጥለታል ማለት ነበር በቲዎሪ ደረጃ።

ይህም ቢሆን የሸሪዓ የግብይት ሥርዓት ያፋልሳል። በተግባር ሲመጣ ይህንንም ሀላል ማድረጊያ ቀጭን ቀዳዳ አይገኝም። በሀገራችን በተግባር እንደምናየው ተበዳሪዎች ዕቃውን ለባንኩ ወስደው እንኳ አያሳዩትም። ከሆነ ድርጅት ወይም ሱቅ የሚገዙትን ዕቃ ምንነት የሚገልጽ የዋጋ ማቅረቢያ (ፕሮፎርማ) ይዘው ባንኩ ጋር ይሄዳሉ። ባንኩ ለባለሱቁ ይከፍለዋል። እዚያው ባንኩ ቢሮ ውስጥ እንዳለ ገንዘቡን ያስተላልፍለታል። ባንኩ በፕሮፎርማው ዋጋ መሠረት ያስተላለፈውን ገንዘብ ወለድ (ትርፍ ይሉታል) ጨምሮ ወደ ብድርነት ያዞረዋል። በቲዎሪ ደረጃ ሆኖ እንኳ የሸሪዓ የሸያጭ ሕግጋትን ይጥሳል። በቲዎሪ ደረጃ የተቀረጸው የሙራባህ አሠራር በሚከተለው ሠንጠረዥ ቀርቧል።

[68] መሸወድ (Tricking the usury) የጽሑፍ ቋንቋ ባይሆንም የበለጠ ይገልጸዋል በሚል ነው።።
[69] ካሽ የሚለው ቃል እንግሊዝኛ ቢሆንም በስፋት ስለተለመደ ለመግባባት እንዳለ ተወስዷል።።

ሠንጠረዡን ስታነቡ ተራ ቁጥሮቹን ከ1 ቁጥር ጀምራችሁ ቀስቱን ተከታተሉት



ይህኛው አሠራር በተለይ ለምርት ወይም ለጥሬ ዕቃ ግዥ የሚያገለግል አሠራር ነው። የዓለም ኢስላማዊ የሚሰኙ ባንኮች ከ80 እስከ 90 ፐርሰንት አሠራራቸው ሙራባሀ ነው የሚሉ ብዙ ጥናቶች ያመለክታሉ። በሀገራችንም በቀላሉ አጠገባችን ያሉ ባንኮች ቅርንጫፎች ገብተን ብንጠይቅ የምናገኘው ብቸኛ አሠራር ነው ሊባል ይችላል።

የቲዎሪ ተፋልሶ፡- በቲዎሪ ደረጃ እንኳ የሸሪዓ ሕግጋትን ይጥሳል ያልነው፤

1. በቁርአን እና/ወይም በሀዲስ የጸና ድጋፍ አለመኖሩ
2. በአብዛኛው ሊቃውንት (ፉቀሐእ) ዘንድ የማይታወቅ እንግዳ በመሆኑ
3. የራስ ያልሆነን ዕቃ መሸጥ፡- ይህ ማለት ባንኩ ተደራድሮና እንደራሱ ሆኖ ገዝቶ አይሸጥም። ሰው ሊገዛ በተስማማው ዕቃ ላይ ተጠርቶ መጥቶ ከፍሎ ከዚያ አትርፎ በዱቤ መሸጥ ነው። በባንኮች የተለመደው አሠራር።
4. የሚሸጠው ነገር በሽያጭ ወቅት አለመገኘት ስላለ ነው። በተግባር እንደምናየው ገንዘብ ያጠረው ሰው ከባንክ ሊበደር ሲሄድ "ሪባ ነው" ብሎ ኢስላማዊ ወደተባሉት መስኮቶች "የሆነ የውሸት ፕሮፎርማ" ይዞ ይሄዳል። የዕውነትም ቢሆን ያው ነው። የሚታይ የሚዳሰስ ሳይሆን የሆነ ቦታ "አለ" የተባለ ዕቃ መግለጫ ነው።
5. የሚሸጠውን ዕቃ ኃላፊነት አለመውሰድ፡- የዕቃው ሙሉ ኃላፊነት የተበዳሪው ነው። የዕቃውን ደረሰኝ በገዢው ወይም በተበዳሪው ስም አድርጎ ባንኩን ገንዘብ ያስከፍላል። ቲዎሪው ላይ ቀድሞ ወደ ባንክ ዞሮ ከዚያ ወደ ተበዳሪው ይዞራል የሚለውን ይዘሉታል። ከምናዟዙር ቀጥታ ባንተ በተበዳሪው ስም ይሁን፣ የመኪና ሊብሬ ወይም የቤት ካርታም ከሆነ ባንተ በተበዳሪው ስም ይሠራና "እኛ ባንኩ" ዘንድ ይቀመጥ ይባባላሉ። ያው እንደ መደበኛው ማለት ነው።
6. በአንድ ሽያጭ ሁለት ሽያጭ ማካሄድ፡- ይህ ዕቃው ከመጀመሪያው ሻጭ ወደ ባንኩ ዞሮ እንደገና ከባንኩ ወደ ተበዳሪው ቢዞር ወይም በሌላ አነጋገር በገንዘብህ ግዛልኝና መልሼ በዱቤ ልግዛህ ማለት ክልክል ነው። ይህ ፉቀሐዎች "በይዓተይኒ ፊል በይዓ" ወይም "ሰፍቀተይኒ ፊል ሰፍቃ" ሲሉት የዘመኑ ኢኮኖሚስቶች **ዲቃላ ግብይት** (Hybrid Contract) ይሉታል።

በሀዲስ በግልጽ ክልክል ነው። ይህንን የተመለከቱ **አራት** (ዓይነት) ሀዲሶች አሉ።

ሀ. ሽያጭና ብድርን አንድ ላይ ማቀላቀል መከልከሉ

«ያህያ ከማሊክ ይዞ እንደነገረኝ፤ አንድ ሰው ለሌላ ሰው ይህንን ግመል በገንዘብህ ግዛውና ወዲያው ለእኔ በዱቤ ሸጥልኝ ሲለው ሰምተው ለዓብዱላህ ኢብን ዑመር (ረዲየሏሁ ዐንሁማ) ሲጠየቁ ክልክል እንደሆነ ነግረዋቸው ከለከሉዋቸው»። *(ሙዎጦእ ሀዲስ 657)*

ይህኛው አሠራር ኢስላማዊ ባንኮች እንዲሠሩበት የተቀረጸውን ቀጥታ የሚቃረን ነው። እዚህ ጋር የሚፈልገውን ዓይነት ግመል አግኝቶ ግን እጅ አጠረውና መክፈል የሚችል ሰው ጋር ሄዶ አንተ ግዛውና እኔ ደግሞ በዱቤ ልግዛህ አለው ማለት ነው። የሦስትዮሽ ግብይት ሲሆን ግብይቱ ግን ሁለት ነው። (1) ግመል ለመሸጥ የወጣው ሰውዬ፣ (2) ግመል ለመግዛት የፈለገው ሰውዬና (3) ብር ያለው ሰውዬ ናቸው። ግመል ለመሸጥ የወጣው ሰውዬ ማንም ይክፈለው አያገባውም። ችግር ያለው ግመል ለመግዛት የፈለገው ሰው ጋር ነው። ከባለ ብሩ ቀጥታ ብር ቢበደር ለምን ብሎ ሊጠይቀው ስለሆነ እንዲያምነው ግመል ሻጭ ይዞ መጣ። ግን ገና አልገዛውም። የግመሉ ባለቤት አልሆነም። እንዳይገዛ ደግሞ ብር የለውም። ብር ያለው ሰው ብር ከማበደር ይልቅ ግመል ሸጥኩ ሊል ነው። የካሽ ግብይት እና የዱቤ ሽያጭ በአንድ ወቅት ተያይዘው መጡ።

ለ. ሁለት ሽያጮችን (በይዐተይን ፊል በይዓ) አንድ ላይ ማጣመር መከልከሉ፡-

ያህያ ከማሊክ እንዳወራው፤ ነቢያችን ﷺ በአንድ ግብይት (ሽያጭ) ሁለት ግብይት (ሽያጭ) ከልክለዋል። (ሙዎጠእ 663)

ሐ. ሁለት የእጅ ምት በአንድ እጅ ምት ክልክል መሆኑ፡-

አንድ ሽያጭ የመከናወኑ ወይም ስምምነት ላይ የመደረሱ ማረጋገጫ ምልክት፤ ገዢና ሻጭ እጅ ሲመታቱ ወይም ሲጨባበጡ ነው። በሀገራችን ይህ ድርጊት በግና ፍየል ሻጮች ጋር ይገኛል። መኪና ሻጮችም ዘንድ አንዳንዴ ትስተዋላለች።

አቡሁረይራ ባወሩት ሀዲስ ነቢያችን ﷺ በአንድ ምት ሁለት ምት ክልክለዋል። (ሀዲስ ሙስነድ ኢማም አህመድ 1/398)

መ. በአንድ ግብይት ሁለት ቅድመ ሁኔታ ማስቀመጥ ክልክል መሆኑ፡-

ዐምር ኢብን ሹዓይብ ከአባቱና ከአያቱ ይዞ ነቢያችን ﷺ ብድርና ሽያጭ ማጣመርን፣ በአንድ ሽያጭ ሁለት ቅድመ ሁኔታዎችን ማስቀመጥና በእጅ የሌለን ነገር መሸጥን ከልክለዋል። (ሶሂህ አቡዳውድ 3504፣ አንነሳኢይ 4611፣ ቲርሚዚይ 1234፣ ኢብንማጃህ 2188፣ አህመድ 174 እና ሀኪም 17/2 ሀዲሱ በድምር ቡሉጉል መራም ኪታብ ውስጥ አለ።)

እዚህኛው ሀዲስ ላይ ሦስት ነገሮች ተካተዋል። ይህ ሀዲስ በብዙ ዘጋቢዎች የተዘገበ ከመሆኑም በላይ ብዙ ነገሮችን ይጠቀልላል። በተለይ የሙራባህ ግብይት ከዚህ ሀዲስ ውስጥ ይወድቃል። እላይ ከጠቀስናቸው በተጨማሪ በአንድ ግብይት

ሁለት ቅድመ ሁኔታ አይቀመጥም ላልነው ማስረጃ ነው። ምሳሌ፡- ይህንን ዕቃ የምሸጥልህ ለእገሌ ብቻ እንድትሸጥ ነው ማለት አይበቃም። ዕቃ ከተሸጠ በኋላ የማጓጓጥው በግልጽ መቀመጥ ይኖርበታል። ወይም የመረካከቢያ ቦታው የገዢ ሥፍራ መሆኑ በትክክል መስፈር አለበት። እንጨትም ሸጥልኝ፣ ወስደህም ፍለጥልኝ ቢባል ሁለት ቅድመ ሁኔታ በመሆኑ በኋላ ውዝግብ ስለሚፈጥር ቁርጥ ያለ መሆን አለበት። መሸጥ፣ ማድረስ እና መፍለጥ መካጣጠል አለባቸው።

ሙራባሀ በቲዎሪ ደረጃ እንኳ ሸሪዓዊ ድጋፍ የለውም። ለዚህም ነው የፊቅሕ (የሸሪዐ ሕግጋት) መጻሕፍት ውስጥ የማይታየው። የአራጣ ባሕሪው ከፍ ያለና የተለያዩ አሻሚና አወዛጋቢ ነገሮች ስላሉት ሊቃውንቱ ፍቁድ የግብይት ዓይነት አድርገው ዕውቅና አልሰጡትም። አሁን ላይ ደግሞ ከካፒታሊስት የግብይት ሥርዓትም የባሰ በዳይነት አለው። በቲዎሪ ደረጃ ተቃርኖ ካመጣ በካፒታሊስት የኢኮኖሚ ሥርዓት ሲተገበር ምን ሊሆን እንደሚችል መገመት ይቻላል። በቀጣይ ተግባራዊ ተቃርኖውን እንመለከታለን።

የሙራባሀ ተግባርና ተፋልሶው፡-

ከላይ በሳጥን ውስጥ ያለው የሙራባሀ ማሳያ ስዕላዊ መግለጫ በምሳሌ ለማስረዳት ያህል፡- የባንኮች ተግባራዊ አሠራር ስናይ ጋሽ አብራር መኪና መግዛት ፈልገው ወደ ወይዘሮ ሰውዳ የመኪና መሸጫ ሱቅ ሄደው በ ነ,000,000 ብር ቢስማሙ፤ ጋሽ አብራር ደግሞ ገንዘቡን መክፈል ስላልቻሉ መኪናውን ለባንክ በነ,200,000 ብር ሊብሬውን ወይም (ሰነዱን) ሸጠው መልሰው በሁለት ዓመት ለመክፈል ይስማሙና ከፍለው ሲጨርሱ ሰነዱን ቢገዙ፤ ማለትም የይዞታ ማረጋገጫ ሊብሬውን ወደ ስማቸው ቢያዞሩ ማለት ነው። ጋሽ አብራር ለባንክ ሸጥኩልህ ይሉና መልሰው ገዛሁህ ብለው ሀላል (ፍቁድ) እናስመስለው እንደማለት ነው። ከአራጣ

ብድር የተለየው ዕቃው ቀድሞ ስለታወቀ ኢስላማዊ ነው ብለው የሚሞግቱት። በመደበኛ ቢሆን ገንዘቡን ወስደው ካሻቸው ቦታ ያሻቸውን ዕቃ መግዛት ሲችሉ፣ ኢስላማዊ የተባለው የሚገዙትን ዕቃ ለባንክ ነግረውና የዋጋ ማቅረቢያ አምጥተው ባንኩ እንዲከፍል ማድረግ ነው።

እዚህ ጋር የተጠቀሰው የጋሽ አብራርና የወይዘሮ ሰውዳ ምሳሌ በቲዎሪው መሠረት ብንሄድ ነው። ትግበራውማ ከዚህም የባሰ ከድጡ ወደ ማጡ ነው። ምክንያቱም ባንኮች የንግድ ሥራ እንዲሠሩ አይፈቀድላቸውም። የንግድ ዕቃ በስማቸው ገዝተው መሸጥ አይችሉም። ይህ ከሆነ ከሕዝብ ላይ በቁጠባ በተሰበሰበን ብር መልሶ ከቆጣቢው ጋር ያልተገባ የንግድ ውድድር ያስገባል። የባንክ ሥራ ፋይናንስን ወይም ፊያትን ማሳለጥ፤ ማለትም ከቆጣቢ የተሰበሰበን ገቢ ለአምራችና አገልግሎት ሰጭ ድርጅቶች ማበደር እና የመሳሰሉት ላይ የተገደበ ነው። ትልቁ የተፋልሶ ነጥብ ያለው እዚህ ጋር ነው። ፋይናንስ ከማሳለጥ በስተቀር ዕቃ እየገዙ መሸጥ በማይችል የባንክ ተቋም ውስጥ ይህንን አገልግሎት እሰጣለሁ ማለት ጋር አለተጣጣመም። ይህንን ለማለፍና “ኢስላማዊ” ለማድረግ የሚደረጉ ግብግቦች ወይም ጨዋታዎች አንዳንዴ አላህን ለማታለል አንዳንዴ አማኙን ለማታለል የሚደረጉ የሚመስሉ የጅል ጨዋታዎች ናቸው። አብዛኞቹ ተዋናዮች ሙስሊሞች ካለመሆናቸው ጋር ሲዳመር እጅግ አሳቃቂ ነው።

አላህንና እነዚያን ያመኑትን (ሰዎች) ያታልላሉ፤ የማያውቁ ሲኾኑ ነፍሶቻቸውን እንጅ ሌላን አያታልሉም። (ቁርአን 2፡9)

እንደ ሙስሊም ሐቂቃውን መናገር ነው። መዋሸትም ይሁን ማታለል ከአራጣው የከፋ ለከሀደት እና ለንፍቅና የቀረበ በሽታ ነው። በቁርአን ክህደትና ውሸት ተቆራኝተው ይቀርባሉ። በፍጹም የአማኝ ባሕሪይ ሊሆኑ አይችሉም።

ሀ. የቃላት ጨዋታ

በመደበኛው አሠራር ‹‹ወለድ›› እና በኢስላማዊው አሠራር ‹‹ትርፍ›› የሚሰላው ከዋናው ገንዘብ በመነሳት ነው። ሁለቱንም የሚወስነው የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ነው። ኢስላማዊ ልንለው የምንችለው ባንክና ጋሽ አብራር የገበያ ዋጋ ቢያስማማቸው ነበር። ማለትም ባንኩ መኪና አቅርቦ በካሽ ይህንን ያህል፣ በዱቤ ከሆነ ደግሞ ይህንን ያህል ቢል የተሻለ ይሆን ነበር። ባንክ በካሽ የሚሸጠው ዕቃ የለውም። ካሹን ወይም ገንዘቡን ነው የሚያከራየው። ጋሽ አብራር ከባንክ የተከራዩትን አንድ ሚሊዮን ብር በአንድ ዓመት መክፈል ከቻሉ አንድ መቶ ሺህ ብር ጭማሪ (ወለድ/ትርፍ/Mark-ups) ወይም 10% ይከፍላሉ። ይህንኑ አንድ ሚሊዮን ብር በሁለት ዓመት ከሆነ ሁለት መቶ ሺህ ወይም 20% ይዋዋላሉ። በአምስት ዓመት ከሆነ 500ሺህ ብር ወይም 50% ይጠበቅባቸዋል። አጠገባችሁ ያለ ማንኛውም ባንክ ገብታችሁ ሙራባሀ የሚሰኘውን አሠራር ዝርዝር ብትጠይቁ ይህንን ነው የሚመስለው። በአማርኛ “ወለድ” ብለን የተደናበርንበትን በእንግሊዝኛ ስም ቀይሮ “Mark-up” ነው የተባለው።

ለ. በቁጥር ማታለል[70]


ምንድን ነው ልዩነቱ ብትሉዋቸው የመደበኛው 16% ሲሆን የኢስላማዊው ወይም የወለድ ነጻው 10% ነው ብለው ለመሸወድ ይሞክራሉ። ትንሽ ዐቅል ያለው ሰው “እሳት ካየው ምን ለየው” ይላል። ትንሽ ሻል ያለ ዐቅል ያለው ከሆነ ‹‹ሙስሊም ያልሆኑ ሰዎች በከፈቱዋቸው ባንኮች ለራሳቸው እና ለወገኖቻቸው ሰዎች በ16% እየተበደሩና እያበደሩ፤ ለሙስሊሙ በምን ሒሳብ ነው በ10% የሚያበድሩት?›› ብሎ

[70] ቃሉ ለመጽሐፍ ባይመጥንም በታላቅ የገንዘብ ተቋማት መሪነት በታላቅ ኃይማኖት ላይ የሚፈጸም በመሆኑ ጸሐፊው ቃሉ የተጋነነ አይደለም የሚል ግምት አለው።

ይጠይቃል። ሌላው ግን ማሰብም ላይፈልግ ይችላል። የቁጥር ጨዋታው በወለድ ስሌት (Discounting amortization) 16% እና 9%፤ አንድ ወይም ተቀራራቢ ናቸው። እንዴት?

በመደበኛው ባንክ ለ12 ወራት ገንዘብ ብትበደሩ ልክ አንድ ወር ሲያልፍ የወለድ ስሌቱ የብድር ገንዘብ 1/12ኛ ነው። የሁለተኛውን ወር ወለድ፤ ቀሪ ገንዘብ ለቀጣይ 12 ወራት ቢቆይ፣ ሦስት ወር ሲያልፍም ልክ እንደዚሁ ለቀጣይ 12 ወራት ቢቆይ እየተባለ ይሰላል። በአጭሩ ስሌት ወለዱ ቀሪ ገንዘብ ላይ ነው የሚሰላው። የከፈላችሁት ገንዘብ ወለድ ስለታሰበበት በቀጣዩ ላይ አይካተትም። እነዚህ ቅንስናሾች ሲደማመሩ ጠቅላላ ውጤቱ ከ16% ወደ 9% ይወርዳል። ሙሉ 16% የሚሆነው ግን አሥራ ሁለቱም ወር ምንም ብድር ሳይከፈል ገንዘቡ እጃችሁ ላይ ቢቆይ በሚለው ነው። መስከረም 1 ላይ ተበድራችሁ ነሐሴ 30 ላይ ብድሩን ብትመልሱ ሙሉ 16% ይሆናል። በየወሩ የምትከፍሉ ከሆነ ግን ማባዣው እየተቀናነሰ ይሄዳል። ብድሩ እየተቆረሰ በሄደ ቁጥር ወለድ መታሰቢያ ብሩም እየቀነሰ ይሄዳል። እርሷን አስልተው ነው 9% ወይም 10% የሚሉዋችሁ።

ምሳሌ፡- 100 ብር ከመደበኛ ባንክ ለአንድ ዓመት፣ በ16.22% ወለድ ብትበደሩና በየወሩ ለመክፈል ብትስማሙ ወርሃዊ ወለድ ምጣኔ (16.22%/12 1.35%) ይመጣል። በዚህ ስሌት መሠረት በአቆልቋይ (Declining amortization) ስሌት ጠቅላላ ዓመታዊ ወለድ 9 ብር ይሆናል ማለት ነው። (ምልክቱን የ “$” ምልክት ቢሆንም ብር እንደሆነ አስቡት)።




ይህኛው የወለድ ስሌት ሶፍትዌር ከባንኮች ድረ-ገጽ የተወሰደ ነው። ገበታችሁ መሞከር ትችላላችሁ። በዘመኑ ሞባይል Apple store ወይም Google play ላይ ማውረድ ትችላላችሁ። በዌብሳይቶች ላይ “Loan Calculator” ብላችሁ ፈልጉት።

በ**16.22%** የወለድ ስሌት በወርሐዊ ክፍያ ሲሠራ “አሞርታይዝ” የሆነ ወለዱ **$9.00** ብር ወይም **9%** ይመጣል ማለት ነው። ይህ ሆኖ ሳለ ውሸትን ልክ ኃይማኖትን መለወጥ (ኩፍርን) ጋር አንድ አድርጎ በሚያይ እስልምና ስም ቀርቶ ለየትኛውም ባሕል የማይመጥን ውሸት በባንኮቹ ሲሠራ ይስተዋላል። ኢስላማዊ የሚባሉ ባንኮች ልዩ የሚያደርጋቸው “በአራጣ” ላይ የጭንቅላት ጨዋታ (ትሪክ) ማካተታቸው ነው። እንደ መደበኛው ባንክ ሐቁን ተናግረው ከኃይማኖቱ ሊቃውንት (ዑለሞች) መፍትሔ መሻት ይሻላል። ባንኮቹ ግን የእስልምና ሊቃውንትን ሲሸሹ ይስተዋላል። ማብራሪያዎች ከስር ተያይዘዋል።

የሙራባሀ እና የመደበኛ ባንክ የብድር እና ወለድ ስሌት ሰንጠረዥ

ሀ. ብድሩ በዓመት አንዴ ተመላሽ ቢደረግ

የመደበኛ ባንክ አሠራር		
ዋና ብድር	$ 100.00	
ዓመታዊ የወለድ ፐርሰንት	16.22%	ብድሩ ለ12 ወራት እጁ ላይ ስለቆየ ሙሉ ወለድ ይከፍላል።
የብድር ዘመን (ዓመት)	1 ዓመት	
የብድር መነሻ ቀን	መስከ /1/2012	
የብድር ማለቂያ ቀን	ነሐሴ 30/2012	
ወርሐዊ ጠቅላላ ክፍያ	የለም	
የክፍያ ክፍልፋይ ጊዜ	1 ጊዜ	
ጠቅላላ ወለድ	$ 16.22	
ጠቅላላ ብር ከነወለዱ	**$ 116.22**	



ይህ አሠራር ለአንባቢ ግንዛቤ ያህል እንጂ የሀገራችን የባንክ ብድር በየሦስት ወሩ ወይም በየወሩ ተመላሽ ይደረጋል። ባንኮች አበድረው (ፋይናንስ አድርገው) 12 ወራት ቁጭ ብለው አይጠብቁም።

ለ. ብድሩ በየሦስት ወሩ ተመላሽ ቢደረግ

ይህ አሠራር በባንክ የተለመደ የብድር አመላለስ ሥርዓት ነው። የሚከተለውን ሰንጠረዥ ተመልከቱ። የ "$" ምልክቱን ገንዘብ ለማመለከት ብቻ ነው የገባው እንጂ ዶላርን ለማመላከት አይደለም።

የመደበኛ ባንክ አሠራር

ዋና ብድር	$ 100.00	
ዓመታዊ የወለድ ፐርሰንት	16.22%	ወለዱ ከ 16.22% ወደ 10.34% ይወርዳል።
የብድር ዘመን (ዓመት)	1 ዓመት	
የብድር መነሻ ቀን	መስከ/1/2012	
የብድር ማለቂያ ቀን	ነሐሴ 30/2012	
የየሦስት ወራት ብድር + ወለድ ክፍያ	$ 27.59	✓ ዓመታዊ ጠቅላላ ወለድ 10.34 ብር
የክፍያ ክፍለፋይ ጊዜ - በየ 3 ወራት	4 ጊዜ	
ትክክለኛ ወለድ (Actual interest) (10.34%)	$ 10.34	✓ መነሻ ብድር 100 ብር
ጠቅላላ ብድር ከነወለዱ	$ 110.34	ስለዚህ፦ 10.34 ሲካፈል ለ100 = 10.34%

Loan Calculator

Amortized Loan: Paying Back a Fixed Amount Periodically


Use this calculator for basic calculations of common loan types such as mortgages, auto loans, student loans, or personal loans, or click the links for more detail on each.

Loan Amount	$100
Loan Term	1 years 0 months
Interest Rate	16.22 %
Compound	Quarterly
Pay Back	Every Quarter

Calculate Clear

Results:

Payment Every Quarter	**$27.58**
Total of 4 Payments	**$110.34**
Total Interest	**$10.34**



View Amortization Table

Amortization Schedule

	Beginning Balance	Interest	Principal	Ending Balance
1	$100.00	$4.06	$23.53	$76.47
2	$76.47	$3.10	$24.48	$51.99
3	$51.99	$2.11	$25.48	$26.51
4	$26.51	$1.07	$26.51	-$0.00
		Year #1 End		

ጠቅላላ ወለዱ ከ $16.22 ወደ $10.34 ለምን ወረደ?

100 ብሩ (ዶላሩ) ዓመቱን ሙሉ እጁ ላይ አላቆየውም። በተበደረ በሦስተኛው ወር ብድር መመለስ ጀመረ። ወለዱ ሕዳር 30 ላይ በ$100 ተሰልቶ ለ4 ሩብ ዓመት ሲካፈል $4.06 መጣ። ከዋና ብድር መመለስ ያለበት $23.53 ነው። አሁንም ወለድ የሚታሰበው ባልከፈለው በመሆኑ $23.53 ከስሌት ይወጣና $76.47 ለቀጣይ ይዞራል። ሰንጠረዡን ስናይ ይበልጥ ግልጽ ይሆናል።

ተ.ቁ.	የክፍያ ቀናት	የየ3 ወር የብድር መነሻ	ወለድና ብድር ተመላሽ	ከብድር ተመላሽ	ከወለድ ተመላሽ	ለቀጣይ ስሌት ተሻጋሪ
1	ሕዳር 30	$ 100	$ 27.59	23.53	$ 4.06	$ 76.47
2	የካቲት 30	$ 76.47	$ 27.59	24.48	$ 3.10	$ 51.99
3	ግንቦት 30	$ 51.99	$ 27.59	25.48	$ 2.11	$ 26.51
4	ነሐሴ 30	$ 26.51	$ 27.59	26.51	$ 1.07	0.00
	ድምር		$ 110.34	$ 100	10.34	

ባንኩ በ16.22% የወለድ ምጣኔ ቢያበድርም ወለዱ ግን ወደ 10.34% ወርዷል። ምክንያቱም ተበዳሪው ብድሩን ዓመቱን ሙሉ እጁ ላይ አቆይቶ አልሠራበትም። አራት ጊዜ በየሦስት ወሩ ከፍሏል። ወለዶችን ስንደምራቸው $10.34 ሆኗል። እላይ ካሳለፍነው ከዓመታዊው ጋር ስናነጻጽረው በየሩብ ዓመቱ በመክፈሉ $ 5.88 ወለድ አድኗል። ግን መሥሪያ ገንዘቡ (Working capital) እጁ ላይ አልቆየም። አሠራሩ Declining interest amortization (አቆልቋይ የወለድ ስሌት) ይሰኛል።

የሙራባሃ የቁጥር ጨዋታ - (በሩብ ዓመት)

ይህንን አሠራር ወደ "ወለድ ነጻ" በሚለው አሠራር ሲቀይሩት የባንኩ ትርፍ $ 10.34 የነበረውን "Mark-up" ብለው ስም ቀይረው ይይዙታል። በ 10.34% ፐርሰንት ያስፈርሟችኋል። ልዩነቱ ባንኩ በ16.22% አበድሮ በ Declining interest amortization (አቆልቋይ የወለድ ስሌት) አስልቶ በዓመቱ የሚያገኘውንና መቼም

ቢሆን የማያጣውን እርግጠኛ ወለድ ማስፈረሙ ነው። ዞሮ ዞሮ በሁለቱም መስኮት የተበደሩ ተበዳሪዎች እኩል ነው የሚከፍሉት። ልዩነቱ 16.22% አቆልቋይ መባሉና 10.34% ቀጥታ መባሉ ነው። ሁለቱም ተበዳሪዎች የክፍያ ወቅታቸው በየሦስት ወሩ ነው። ከወለድ ነጻ ስለተባለ የተለየ የጊዜ ስሌት የለውም። በሁለቱም መስኮቶች በየሦስት ወሩ ለመክፈል የተዋዋለ ተበዳሪ ቢያዘገይ በመደኛ የተበደረው የወለድ ስሌቱ በቀሪው ላይ በመሆኑ ወለዱ በቆየው ቀን ልክ (Recalculate) ተደርጎ ከፍ ይላል። ከወለድ ነጻ በሚባለው መስኮት ወይም ባንክ ተበድሮ በተዋዋሉበት የየሦስት ወራት ጊዜ ያዘገየ ሰው፤ በመደበኛ ባንክ በቆጠረው ጭማሪ ወለድ ልክ ተሰልቶ ይከፍላል። ባይሆን ስሙ 'ወለድ' ሳይሆን 'ቅጣት' ይባላል። ፔፕሲን በዐረብኛ "ቤብሲ" እንደማለት ነው። ደንበኛ ለመሳብ ወይም ከባንኮቹ ጋር ካላችሁ የቢዝነስ ቅርርብ ቅጣቱን ከተውላችሁ ሌላ ጉዳይ ነው።

ሐ. ብድሩ በየወሩ ተመላሽ ቢደረግ

ያለፉት ሁለቱ አሠራሮችን ልዩነት፤ የመክፈያ ጊዜ አንዴ በዓመት ወይም አራቴ በየሦስት ወሩ መሆን ነበር። ይህንኑ የአንድ ዓመት ብድር ክፍያውን በየወሩ ማለትም አስራ ሁለቴ ቢሆንስ በሚለው እንየው። ይህኛውም የተለመደ የባንክ አሠራር ነው። ጠቅላላ ወለዱ ካለፉት ከሁለቱም ይቀንሳል። ምክንያቱም በተበደራችሁ ገና በወሩ መክፈል ጀምራችኋል። መስከረም ፣ ተበድራችሁ በወሩ መስከረም 30 ወይም ጥቅምት ፣ ስትከፍሉ፤ የመለሳችሁት ብድር ከቀጣይ ስሌት ይቀነሳል። $100 ተበድራችሁ በወሩ $10 ብትመልሱ ለቀጣዩ ወለድ የሚታሰበው በ$90 ነው። በ$70፣ በ$60፣ በ$50 ... እያለ ይሄዳል። አሠራሩ በቀጣይ ሰንጠረዦች ተመልከቱ። ከባንክና ፋይናንስ ውጭ አንባቢያን ለማስመቸት ሲባል ተተርጉሟል።

Loan Calculator

Amortized Loan: Paying Back a Fixed Amount Periodically


Use this calculator for basic calculations of common loan types such as mortgages, auto loans, student loans, or personal loans, or click the links for more detail on each.

Loan Amount	$100
Loan Term	1 years 0 months
Interest Rate	16.22 %
Compound	Monthly (APR)
Pay Back	Every Month

Calculate Clear

Results:

Payment Every Month	**$9.08**
Total of 12 Payments	**$109.00**
Total Interest	**$9.00**



View Amortization Table

Amortization Schedule

	Beginning Balance	Interest	Principal	Ending Balance
1	$100.00	$1.35	$7.73	$92.27
2	$92.27	$1.25	$7.84	$84.43
3	$84.43	$1.14	$7.94	$76.49
4	$76.49	$1.03	$8.05	$68.44
5	$68.44	$0.93	$8.16	$60.28
6	$60.28	$0.81	$8.27	$52.01
7	$52.01	$0.70	$8.38	$43.63
8	$43.63	$0.59	$8.49	$35.14
9	$35.14	$0.47	$8.61	$26.53
10	$26.53	$0.36	$8.72	$17.81
11	$17.81	$0.24	$8.84	$8.96
12	$8.96	$0.12	$8.96	$0.00
Year #1 End				

በሶፍትዌር የተሠራውን እላይ እንዳደረረግነው ወደ አማርኛ ከስር ተመልሷል። ለባንክና ለፋይናንስ ሩቅ ለሆኑ አንባቢያን ሲባል ነው የተደጋገመው።

የመደበኛ ባንክ አሠራር		
ዋና ብድር	$ 100.00	
ዓመታዊ የወለድ ፐርሰንት	16.22%	ወለዱ ከ 16.22% ወደ 9% ይወርዳል።
የብድር ዘመን (ዓመት)	1 ዓመት	
የብድር መነሻ ቀን	መስከ/1/2012	
የብድር ማለቂያ ቀን	ነሐሴ 30/2012	✓ ዓመታዊ ጠቅላላ ወለድ 9.00 ብር
የየወሩ ጠቅላላ ክፍያ	$ 9.08	
የክፍያ ክፍልፋይ ጊዜ - በየወሩ	12 ጊዜ	✓ መነሻ ብድር 100 ብር
ትክክለኛ ወለድ (Actual interest) (9%)	$ 9.00	
ጠቅላላ ብድር ከነወለዱ	**$ 109.00**	ስለዚህ 9/100 = 9%

$100 ነበር የተበደራችሁት። የብድሩ ወለድ በ16.22% ተባዝቶ ለ360 ቀናት ይካፈላል። የሥላሳ ቀናት ወይም የወሩ ወለድ $ 1.35 ይሆናል። የተበደራችሁትም 12 ቦታ ማካፈል ነው። ለ12 ወራት እንደማለት ነው። ከዋናው ብድር ላይ ለዚያ ወር $7.73 ስትከፍሉ $92.27 ይቀራል። ከብደሩ $7.73 ሲደመር ከወለዱ $1.35 ስትደምሯቸው $9.08 ይሰጠናል። የቀጣይ ወር ስሌት መነሻ ይህ ($92.27) ነው። ይህንንም በ16.22% ተባዝቶ ለ360 ይካፈላል። ለምን 30 ቀናት ተቀንሶ ለ330 ቀናት አልሆነም? ከተባለ እጁ ላይ አንድ ዓመት ቢቆይስ? ተብሎ ይታሰባል። የሦስተኛውም ወር ልክ እንደዚው ነው። ቀሪ ክፍያ ሲባዛ በ16.22% ሲካፈል ለ360 ቀናት እያለ

ይቀጥላል። ወርሃዊ የብድር ተመላሽ እየጨመረ ሲሄድ ወለዱ ደግሞ እየቀነሰ ይሄዳል። የወሩ ክፍያ ግን ያው ነው። የሚከተለውን ሰንጠረዥ ተመልከቱ።

ተ.ቁ.	የክፍያ ቀናት	ወርሐዊ መነሻ	የየወሩ ክፍያ	ከብድር በየወሩ ተመላሽ	ወርሐዊ ወለድ በ16.22%	ወርሐዊ ቀሪ
1	መስከረም 30	$ 100.00	$ 9.08	$ 7.73	$ 1.35	$ 92.27
2	ጥቅምት 30	$ 92.27	$ 9.08	$ 7.84	$ 1.25	$ 84.43
3	ሕዳር 30	$ 84.43	$ 9.08	$ 7.94	$ 1.14	$ 76.49
4	ታሕሳስ 30	$ 76.49	$ 9.08	$ 8.05	$ 1.03	$ 68.44
5	ጥር 30	$ 68.44	$ 9.08	$ 8.16	$ 0.93	$ 60.28
6	የካቲት 30	$ 60.28	$ 9.08	$ 8.27	$ 0.81	$ 52.01
7	መጋቢት 30	$ 52.01	$ 9.08	$ 8.38	$ 0.70	$ 43.63
8	ሚያዝያ 30	$ 43.63	$ 9.08	$ 8.49	$ 0.59	$ 35.14
9	ግንቦት 30	$ 35.14	$ 9.08	$ 8.61	$ 0.47	$ 26.53
10	ሰኔ 30	$ 26.53	$ 9.08	$ 8.72	$ 0.36	$ 17.81
11	ሐምሌ 30	$ 17.81	$ 9.08	$ 8.84	$ 0.24	$ 8.96
12	ነሐሴ 30	$ 8.96	$ 9.08	$ 8.96	$ 0.12	$ 0.00
		ድምር	**$ 109.00**	**$ 100.00**	**$ 9.00**	

የሙራባሃ የቁጥር ጨዋታ - በወርሃዊ ስሌት ላይ

በመደበኛ መስኩት በ16.22% አቆልቋይ (Declining) የተበደረም በ9% ቀጥታ (Flat) የተበደረም የመጨረሻ ክፍያው ያው ነው። $100 በ16.22% የተበደረ ሰው

በየወሩ ብድሩን ቢመልስ በአጠቃላይ የሚከፍለው ወለድ ወደ 9% ይወርዳል። የወለድ ነጻ የሚባለው አቆልቁሎ ሲጨርስ ያለው ነው።

ሐ. ያልተጠቀሙበትን መክፈል

የሙራባሀ ክፋት ከባንክ ጋር ስምምነት ውስጥ ከገባችሁ ወዲያ፤ በበነጋታው ገንዘብ ብታገኙና ብድሩን ለመዝጋት ብትወስኑ የሁሉንም ዓመት ወለድ ለመክፈል ትገደዳላችሁ። የሃያ ዓመት ብድር ውስጥ ብትገቡና በዓመቱ ለመዝጋት ብታስቡ፤ የቀሪ 19 ዓመታት ወለድ (ማርከአፕ) መክፈል አለባችሁ። ስምምነቱን ኢስላማዊ ለማስመሰል ብድር ሳይሆን ሽያጭ ስለሚባል ነው። ምክንያቱም ብር ሳይሆን የተሰጦት ከሌላ ድርጅት ዕቃ ነው የተገዛሎት። የተሸጠ ዕቃ ደግሞ አይመለስም። ዕቃው ከሌላ ድርጅት ነው የተገዛውና። ሙሉ ሒሳብ ለዚያኛው ተከፍሎታል።

“ኢስላማዊ ባንኩ” ከመደበኛ ባንክ ጋር ለመወዳደር እና ደንበኛ እንዳይሄድበት ብዙ መንገድ ሲፈጥር ይስተዋላል። መደበኞቹ ያበደሩትን ብድር ከውሉ በፊት ተበዳሪው ሲከፍል በቀሪ የውል ጊዜ ያለውን ወለድ በአብዛኛው ጊዜ ስለማያስከፍሉ ደንበኞች ይህንን ጥቅም ለማግኘት ኢስላማዊ ከሚሰኘው ባንክ ወደ መደበኛው ሊሄዱ ይችላሉ። ምክንያቱም ኢስላማዊ የሚባል ስም ይሰጠው እንጂ ሁሉ ነገሩ ተመሳሳይ ሆኖ ግን ጉዳቱ ከፍ እስካለ ድረስ ደንበኞች ሊመርጡት አይችሉም። ምንም ወይም የረባ መንፈሳዊ ጥቅም ላያገኙበት አይከስሩም።

ለትርፍ ነበር እንጂ ጎራውን መዞሬ

ወንዙን መሻገሬ

ለመሳ መሳማ ምን አለኝ ሀገሬ

እንዳለው ጌቴ አንለይ ማለት ነው። ውጭ ሄዶ ኑሮው ከሀገር ቤት የማይሻል ሲሆንበት የገጠመው ነው። የመደበኛው ባንክ ወለድ የቁርአኑ ዓይነት “ሪባ” ቢሆን ኖሮ እኔም ጫፉን አልነካውም ነበር። መሳ ለመሳም ቢሆኑም የወለድ ነጻ የተባለው እንመርጥ ነበር ይሆናል። ግን በወለድም በመምከንም የወለድ ነጻው ይብሳል። የምሥራቅና ምዕራብ ያህል ይራራቃሉ። ወደ ርዕሱ ስንመልሰው ኢስላማዊ የተባሉ ባንኮች ሲያበድሩ ወለዱን “ትርፍ” ብለው መዝግበውታል። ታዲያ “ትርፍ መልሻለሁ” ሊሉ ነው ወይስ “ትርፍ ትቻለሁ” ሊሉ ነው? ምክንያቱም በሒሳብ መዝገብ አያያዝ ሁለቱም አገባባቸው ይለያል።

የመደበኛው ማቋረጥ ብትፈልጉ ያልተጠቀማችሁበትን የቀሪ ዓመት ወለድ አትጠየቁም። ግልጽ ሕግና ውል አለው። በመሆኑም ውል ማፍረሻ “Early settlement” ቅጣት ሊያስከፍሉ ይችላሉ። የብድር ውሉ ላይ አለ። ቁርጥ ብሎ ተቀምጧል። ከኢስላማዊ የውል ሕግጋት አንዱ ሁለቱ ተዋዋዮች በውል ወቅት ሁሉንም ነገር በግልጽ ማወቅ አለባቸው። አሁን ላይ የእኛ ሀገራት ባንኮች የወለድ ነጻ መስኮቶች ደንበኞች ወደ መደበኛው ሲሄዱባቸው ቶሎ ለሚከፍሉ ተበዳሪዎች (Mark-ups) በራሳቸው በባንኩቹ ፍላጎት እየቀነሱ ናቸው። 100 ብር “በወለድ ነጻ” መስኮት ለሦስት ዓመት በ27% ማርክአፕ ተበድራችሁ አንድ ዓመት ተጠቅማችሁ ሙሉውን ስትዘጉ የሁለት ዓመት ማለትም 18% ጨምራችሁ መክፈል የግድ ነው። በየዓመቱ 9% ሲሆን የሦስት ዓመት 27% ይመጣል። ልክ እንደ መደበኛው ቀሪ ወለድ (ማለትም Mark-ups) መተው ግን የተበዳሪዎች መብት ሳይሆን በባንኮች መልካም ፈቃድ ላይ የተመሠረተ ነው። አሁን ላይ አንዳንድ ባንኮች “ቀድሞ ለከፈለ በባንኩ መልካም ፈቃድ ትርፋችንን (Mark-ups) አስበን ልንተው እንችላለን” የሚል አንቀጽ ማስገባት ጀምረዋል። ማማለያ ነው።

መ. የታክስ ጉዳት፡-

ከታክስ አኳያ ስንመጣ ሙራባሀ ሦስቴ ታክስ ይከፈልበታል (Triple tax disadvantage) አለው። ይህ እራሱን የቻለ ሰፊ ርዕስ ቢሆንም በአጭሩ ለመዳሰስ ያህል፡-

7. ከ"ኢስላማዊ ባንክ" የተበደረ ሰው ወለድ ቢከፍልም፤ ወለድ ተብሎ ስለማይመዘገብ ግብር ጋር እንደ ወጪ ይዞ ማወራረድ አይችልም። ምክንያቱም ከሌላ ድርጅት ዕቃ ተገዝቶ ተሸጦለታል። ወለድ የሚባል ነገር የለም። ሆኖም ግን ይህንን ለማካካስ ወለዱን "ኮሚሽን፣ የአገልግሎት ክፍያ" የሚል ስም ሲሰጠው ይስተዋላል። እዚህ ጋር ከመደበኛው ጋር ሲነጻጸር አንድ ከፍተኛ ጉዳት አለ። በተግባር ይህ ይፋለሳል። ከባንክ ጋር በመሞዳሞድ መደበኛ ብድር የሚያስመስሉ አሉ። ለቤተሰብ "ከኢስላማዊ ተበደርኩ። ለገቢዎች ደግሞ ከመደበኛ ተበደርኩ" ብለው ለማምለጥ ይጥራሉ።
8. ባንኩ የሚጨምረው ትርፍ የዕቃ ዋጋ ሆኖ ስለሚመዘገብ እንደ ዕቃ ዋጋ (Cost of Goods Sold) ስለሚያዝ ዞሮ ዞሮ አያከስርም የሚል የሒሳብ (አካውንቲንግ) መከራከሪያ ሊቀርብ ይችላል። በኢትዮጵያ የታክስ አሠራር ለየዘርፉ የትርፍ መቶኛ ተቀምጧል። አንድ ዘርፍ ካስመዘገበው የዕቃ ዋጋ ላይ በመመርኮዝ ግብር ይጣልበታል። 100 ብር በመደበኛ የተበደረ ሰው በዓመት 9 ብር ወለድ ቢከፍል፤ 100 ብሩ የዕቃ ዋጋ ጋር ይገባና 9 ብሩ እንደ ዓመታዊ ወጪ ይያዛል። ግብር ሲሰላ በ100 ብር ተመርኩዞ ነው። "በኢስላማዊው" ግን 9 ብሩ "ትርፍ" ተብሎ ዋና ብድሩ ላይ ተደምሮ፤ የዕቃው ዋጋ 109 ብር ይሆናል። ግብር የሚሰላው በ109 ብር ነው። (ነጋዴ ለሆነ ሰው በጣም ግልጽ ነው)። በአጭሩ ከመደበኛ የተበደረው ግብር የሚሰላበት ዋጋ 100 ብር ሲሆን፤

ከ"ኢስላማዊ ባንክ" የተበደረ ሰው ግብር የሚሰላበት በ109 ብር ነው። ሁለተኛ ጉዳት።

9. ሦስተኛው ደግሞ ከ"ኢስላማዊ ባንክ" የሚበደር ሰው ዋና ዓላማው ብር ማግኘት ነው። ወለድ የሚለውን ቃል ሸሽት ነው ወደዚህ ያስገባው። በመሆኑም ፕሮፎርማ (የሽያጭ ስምምነት) የሚያቀርብለት ድርጅት ያግባባል። ያ ድርጅት የራሱን ትርፍና ቫት ጨምሮ ለባንኩ ሸጦ ባንኩ መልሶ በብድር መልክ ይሸጥለታል። ሲሸጥለት ባንኩ የተጨማሪ እሴት ታክስ (ቫት) ተመዝጋቢ ባለመሆኑ ተበዳሪው አያወራርደውም። ወይም የተጨማሪ እሴት ታክስ ግብአት አይኖረውም። ሙስሊም ተበዳሪ ነጋዴ መሆኑ ቀርቶ የመጨረሻ ተጠቃሚ (Consumer) ይሆናል ማለት ነው። ይህ ቲዎሪውን ተከትለው ከሄዱ ነው። ባለፕሮፎርማው ትርፍና ቫት ጨምሮ ይሰጠዋል። ምክንያቱም ደረሰኝ ስለሚያቀርብ የግድ ሽያጭ ተብሎ ለገቢዎች ሪፖርት ይደረጋል። የሒሳብ ሪፖርትና ንግድ በዘመነበት ሀገር ባዶ ደረሰኝ መሸጥ ብዙም ላይኖር ይችላል። በእኛ ሀገር ያለው ሁኔታ ግን ደረሰኝ መሸጥ ይበዛል። (ጸሐፊው ነጋዴና የፋይናንስ አማካሪ በመሆኑ ከሚያስተውለው ነው)።

ሠ. ቀድሞ የተወሰነ ትርፍ

በቲዎሪ ደረጃ ተበዳሪው እና ባንኩ የትርፍ ክፍፍላቸውን ይስማማሉ ይባላል። ምክንያቱም የትርፍ ፐርሰንት እንጂ "ይህንን ያህል ቁርጥ ትርፍ ተሰጠኝለህ" አይባልም። ትርፍ ገበያ ይወስን እንጂ አበዳሪ አይወስንም። ሆኖም ግን ትርፉን የሚወስነው የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ነው እንጂ ገበያው አይደለም። የመደበኛ ባንክ ወለድ ስሌት ጋር አቻ ወይም ተቀራራቢ አድርጎ ያስቀምጠዋል። በቲዎሪው መሠረት ቢሆን ኖሮ በስምምነታቸው መሠረት ባንኩ ዕቃውን ከአቅራቢው ገዝቶ ትርፉን የባንኩ ንብረት ሆኖ፤ ባንኩ ትፉን (Mark-up) ጨምሮ እንዲሁም ለተበዳሪ

ደንበኛው ተጨማሪ የመክፈያ ጊዜ ሰጥቶ ይሸጥለታል። ችግሩ የባንክ ሥራ ፋይናንስ ማቅረብ እንጂ በሕዝብ ብር እቃ እየገዙ አትርፎ መሸጥ አይደለም። በሙራባሀ ሽያጭ መንገድ ላይ ችግር ቢገጥም ወይም መርከቡ ቢሰምጥ ኪሳራው የባንኩ ይሆናል። ለምሳሌ የርክክብ ቦታ ስምምነታቸው እስከ ጉምሩክ ወደብ ድረስ ሊሆን ይችላል። በተግባር ግን ባንኮቹ እንደመደበኛው ተጨማሪ ዋስትና ይይዛሉ። እቃ በስማቸው ገዝተው አያስረክቡም። ተበዳሪው ጨርሶ ላመጣውና ላለቀለት ነገር ብቻ ብር ያቀርባሉ።

ረ. ሰዶ ማሳደድ

ባንክ የሄዳችሁት ብድር ፈልጋችሁ ሆኖ ሳለ፤ ሽያጭ ለማስመሰል ገንዘቡ ወደ ሆነ ሰው አካውንት ይገባል። ምሳሌ 10 ሚሊዮን ብር ፈልጋችሁ ባንኩ የሚፈልግባችሁን ሰነድ በሙሉ ታሟላለችሁ። ካርታ ያለው ቤት ታስይዛላችሁ። ብሩ የሚገባው ግን በእናንተ ስምና አካውንት አይደለም። “እኛ ዕቃ ገንዘተን ነው እንጂ የምንሰጠው፤ ብር አንሰጥም” ይላችኋል ባንኩ። እሺ ታዲያ ስትሉ፤ ዕቃ የሚሸጥላችሁን ሰው ጋር ሄዳችሁ “ፕሮፎርማ” አምጡ ይላችኋል። እንደሚታወቀው ብዙ ሰው ብር ፍለጋ ነው ባንክ የሚሄደው እንጂ “የምገዛውን ዕቃ አግኝቻለሁና ክፈሉልኝ” ለማለት አይደለም። ባንኩስ ብሩን ከየት አመጣው ካልን ከሕዝብ በነጻ የሰበሰበውን ነው። እና ቤት አስይዛችሁ የተበደራችሁት ብር ወደ ሌላ ሰው ሒሳብ ይገባል። ሰውየው ዕቃ ሸጦላችሁ ከሆነ ደግ። ድናችኋል። ካልሆነ ግን ነገ፣ ዛሬ እያለ ያጉላላችኋል።

የዚህ መጽሐፍ ጸሐፊ ብዙ አሳዛኝ ነገር የገጠማቸውን ያውቃል። አንዱ ወንድም እህቶቹን አስማምቶ ቤታቸውን አስይዞ 8 ሚሊዮን ብር ጠየቀ። ፕሮፎርማ ሲሉት አንድ ጓደኛው ጋር ሄዶ አመጣ። ገንዘቡ በባለፕሮፎርማው አካውንት ተላለፈ። ሁለት ሚሊዮን ብር ቆንጥሮ ሰጥቶት ስልኩን ዘጋ። አንድ ሳምንት ከተጠፋፉ በኋላ የሰሜኑ

ኢትዮጵያ ጦርነት ተነሳ። ስድስት ሚሊዮን ብሩን ሳይቀበል ጦርነቱ ተሟሟቀና አጠቃላይ ስልክ ተዘጋ። ይህ መጽሐፍ ማተሚያ ቤት እስኪገባበት ድረስ የስልክ ኔትወርክ እንደተዘጋ ነው። ባንኩ ግን ብድሬን መልስልኝ እያለ ወጥሮ ይዞት ለምክር ደወለልኝ። በእርግጥ መጀመሪያ አካባቢ በማኅበራዊ ሚዲያ ከሚሳደቡት ወይም ከሚያላግጡት ጋር ነበር። ስለው ከነበረው ጋር ተፋጠጠ። በራሱ ደረሰ። እንዲህ ያሉ በርካታ ገጠመኞች አሉ። ከባንክ ካርታ አስይዛችሁ ገንዘቡን ምንም ካርታ ላላስያዘ ሰው ሒሳብ ማስገባት እንዴት ኢስላማዊ እንደሚሆን እስልምና ያስተማርዋችሁ ሰዎችን ጠይቁ። አሠራሩ ከመደበኛው ስለተወሳሰበና ወለዱ ስለጨመረ ብቻ "ከወለድ ነጻ" እንዴት ይባላል?

ሰ. በበደል ገንዘብ መነገድ

አራጣ የተከለከለው ሰዎች እንዳይበደሉ ነበር። የሙራባሀ እና ባጠቃላይ የ"ኢስላማዊ ባንክ" ትልቁ ጥፋት በሰዎች ገንዘብ እየሠሩ ለባለገንዘቦቹ ምንም ጥቅም አለማካፈል ነው። ገንዘብ እንዲቆጥቡ እንጂ እንዲጠቀሙ አይደረግም። በካፒታሊዝም እንኳ ያልታየ ጭካኔና በደል ነው። መደበኛ ባንኮች ለአስቀማጭ ትርፍ ሲያካፍሉ "ኢስላማዊ ባንኮች" ግን ይህንንም ይነፍጋሉ። ስለዚህ የሙራባሀ ተጠቃሚዎች የሚበደሩት ገንዘብ የበደል ገንዘብ ነው። የሚያስይዘው ንብረት እና ትርፋማ ሥራ የሌለው ደሀ ይህንን ላሟሉ ሰዎች ይቆጥብላቸዋል። መበደር ላልቻለ ለደሀው ግን ምንም አይሰጡም። 20 ሀብታሞች ባንክ መክፈት ይችላሉ። ከዚያ ሕዝቡ ገንዘቡን በቤቱ ማስቀመጥ፣ ከሀብታሞቹ ባንኮች ውጭ መክፈል፣ መቀበል፣ ማዘዋወር አይችልም። በብሩ እነርሱ ይነግዱበታል። ሊበደር ቢሄድ ትርፋማ ሥራና ካርታ ያለው ማስያዣ ይጠይቁታል። ከሁለት አንዱ ከጎደለው ድርሻው እየፈጋ ለእነትሱ መቆጠብ ነው። በአጸፋው ካተረፉት ላይ ብሔራዊ ባንክ ባስቀመጠው የትርፍ መቶኛ እንዲከፍሉ ያስገድዳል። ምሳሌ 7% ሊሆን ይችላል። ይህ መበደር

ያልቻሉ ቆጣቢ ደሃዎች የሚያገኙት ትርፍ ነው። ይህንን ትርፍ መንፈግ “ከወለድ ነጻ”፣ በአንዳንድ ደፋሮች ደግሞ “ኢስላማዊ” ይባላል። ይህ የእስልምና የሪባ ሕግጋትን የሚጻረር ጸረ-ኢስላም አሠራር ነው። ዘካን ለደሃ እንዲከፈል የኃይማኖት ማቆሚያ ያደረገ፣ የሪባ አንቀጾችን ሲደመድም “አትበድሉም፤ አትበደሉምም” ካለው ጋር ይቃረናል።

ሸ. እንደ ማጠቃለያ ያለው ጉዳትና ተቃርኖ

“ኪራይ ሰብሳቢ (Rent seeker) አሠራር” የሚወቀስበት ምክንያቶች፡-

- ምንም ሳይሠራ ሰዎች ከወለድ ነጻ በቆጠቡት ገንዘብ ሥራ ይዘው ለመጡ ሰዎች ያበድርና ቁጭ ብሎ ትርፍ (ወለድ) መሰብሰብ ነው።
- አሠራሩ ከመደበኛው አሠራር የተቀዳ ሆኖ ግን የከፋ ነው።
- ቲዎሪው እና ተግባሩ ለየቅል ናቸው።
- ደንበኛው መግዛት የፈለገውን ዕቃ አጥንቶ እና ከአቅራቢው ጋር ተስማምቶ ለባንኩ አቅርቦ ከባንኩ ጋር ያስተሳስረዋል። ይህኛው አሠራር በሀዲስ በግልጽ የተወገዘ መሆኑን ከላይ አይተነዋል።
- ቢያንስ ባንክ ንብረት ተከራክሮ ገዝቶ ለሌላ ሰው መሸጥ ነበረበት እንጂ ሌላው በለፋው ላይ፤ ባንኩ የሕዝብ ገንዘብ ሰብስቦ ሲያበቃ ዞሮ ትርፍ አስቦ «ሸጥኩኝ» ማለት በሸሪዓ መቀለድ ነው።
- ከመደበኛው ባንክ ይብሳል እንጂ አይሻልም። ሙራባሀ የሚባለው በትክክል ቢተገበር እንኳ ከወለድ የተለየ አይደለም በሚል ብዙ ምሁራን አይቀበሉትም። እንደው ሙሻረካና ሙዷረባ ሲጠፉ ብቻ ለቢቸግር የሚባል ነው። ሆኖም ግን ባንኮች ለሸሪዓው የሚቀርቡትን ሙዳራባህና ሙሻረካህን ችላ ብለው ለኪሳራ የማያጋልጣቸውን ሙራበሀን ነው የሚጠቀሙት።

- ሙራባሀው ወይም ትርፉ የሚታሰበው ልክ እንደ መደበኛ ብድር ከዋጋው ላይ ነው። ምሳሌ፡- መደበኛ ብድር አንድ ሚሊዮን ብር የተበደረ ሰው ወለዱ የሚታሰበው ከአንድ ሚሊዮን ብሩ ላይ ነው። ሙራባሀም ከአንድ ሚሊዮን ብር ዋጋ ላይ ነው።

ልክ እንደ መደበኛው ባንክ ብድር ዓመት ከጨመረ፤ በጨመረው ዓመት ይባዛል። የነ ዓመት ከሆነ በአንድ፣ የ2 ዓመት ከሆነ በሁለት ይባዛል።

የዚህ ንዑስ ርዕስ ማጠቃለያ፡- የዓለም አቀፍ የፋይናንስ እና ኢኮኖሚ ሴክተሩ ብዙ አብዮቶች፣ ጦርነቶች፣ ውድቀቶችና መፍትሔዎች ማስተናገዱ አይቀርም። አሁንም ለሦስተኛ የዓለም ጦርነት ጫፍ ላይ ያለን እስኪመስል ሀገራት ለሀገራት ተፋጠዋል። አሁን ያለው የፋይናንስና የኢኮኖሚ ሚዛን መዛባት በተለይ ሙስሊሙን ክፉኛ ጎድቶታል። ጦርነቶቹና ፍጥጫዎቹ አሁንም ሙስሊሙን በቀዳሚነት መጉዳታቸው አይቀርም። "ኢስላማዊ፣ ከወለድ ነጻ" የተሰኙትም መፍትሔ ከመሆን ይልቅ ችግር ሆነዋል ማለት ይቻላል። እነርሱንም ማስተካከል ግን ይቻላል። መስተካከል የሚችሉት ደግሞ በዘርፉ ምሁራንና በኃይማኖት ሊቃውን ነው። የሪባ (አራጣና ወለድ) መሠረቱ በደል ነው። መበዳደል የሌለበት ወይም ላለመበዳደል የቀረበ ቀመሮች (Formulas) የእስልምና ሕጉ (ሸሪዓው) አለው። ዘርፉን ለምሁራንና ፉቀሐዎች ክፍት ማድረግ ወይም የዘርፉ ምሁራንና ፉቀሐዎች በንቃት መሳተፍ አለባቸው። የዚህ ክፍል መግቢያ አካባቢ ያሰመርኩበትን ለመድገም ያህል፤ ኢስላማዊ ባንክ ከምንል ኢስላማዊ ሸሪዓን መሠረት ያደረገ ባንክ ቢባል ስሜት ይሰጣል። ሙስሊሞች የባንክ ተጠቃሚ ሳይሆኑ

ለዘመናት ቆይተዋል። ሌሎች በከፈቷቸው ባንኮች ቀርቶ የወለድ ነጻ ብለው በሚሰጧቸው መስኮቶች እንኳ በአግባቡ አይስተናገዱም። ብድር ሲጠይቁ እንኳ ይታሻሉ። ስለዚህ ሙስሊሞች ተሰባስበው ቢከፍቱና በሸሪዓው መሠረት በፍትሕ ቢንቀሳቀሱ ለወገናቸው መድረስና ለውጥ ማምጣት ይችላሉ። በዚህ ከሚያግዙት ነኝ። አድሎአዊነት ግን የትም ቢሆን ውጉዝ ነው።

اللَّهُمَّ صَلِّ عَلَىٰ سَيِّدِنَا مُحَمَّدٍ وَعَلَىٰ آلِهِ وَصَحْبِهِ وَسَلِّمْ

“ኢስላማዊ ባንክ” ለመክፈት ከማሰብ በፊት መመለስ ያለባቸው ጥያቄዎች

(ጥያቄዎቹ ባንኮች ከመከፈታቸው በፊት የተጠየቁ ናቸው)

1. “ኢስላማዊ ባንክ” ካለ ኢስላማዊ ገንዘብ እንዴት አይኖርም?
2. ኢስላማዊ ገንዘብ ከሌለ “ኢስላማዊ ባንክ” ከየት መጣ? ኢስላማዊ ገንዘብ ካለስ የት ነው መገኛው?
3. ኢስላማዊ ገንዘብ አለ ከተባለ መለኪያው ምንድን ነው?
4. “ኢስላማዊ ባንክ” ፊያት ላይ መቆም ይችላል?
5. ወይስ ፊያት ኢስላማዊ ገንዘብ ነውን? በምን መስፈርት?
6. ፊያት ኢስላማዊ ገንዘብን ተክቷል የሚባል ነገር ሲሰማ ይስተዋላል። ታዲያ ፊያት እንዴት እና በምን የሸሪዓ መረጃ ኢስላማዊ ገንዘብን ተካ?
7. ኢስላም ግሽበትን እንዴት ይመለከተዋል?
8. ግሽበት እና ወለድ አንድነትና ልዩነታቸው ምንድነው?
9. ወለድ (interest)፣ አራጣ (usury) እና ሪባ አንድነትና ልዩነት ታይቷል?

10. የባንክ ወለድን “ሪባ” የተባለበት የሀገራችን የዑለማ ስምምነት አለ ወይስ “ወለድ” በሚል ስም ብቻ ነው የበረገግነው?
11. ገንዘባቸው ከዶላር ጋር ብዙም የማይዋዥቅ ሀገራት ፈትዋ በግሽበት ለምንሰቃይ ለእኛ ሀገር ሥርዓት ይሠራልን?
12. ባንኮች በሕግ ፋይናንስን ከማሳለጥ (intermediary) ከመሆን ውጭ ዕቃ ገዝተው መሸጥ ይችላሉ?
13. በብዙ ጥናቶች እንደሚታየው የዓለም ባንኮች ከ80% እስከ 90%ቱ ለምን ሙራባሀን መረጡ?
14. በCost ላይ Mark-ups ማስላት ሀላል መሆኑ ከቁርአን እና ከሀዲስ መረጃ አለ?
15. መደበኛው ብድር ወለዱ በብድሩ ላይ ይሰላል። የሙራባሀውም ትርፉ ልክ እንደ መደበኛው በዋጋው ላይ በፐርሰንት እያሰሉ በዓረቢኛ "ሙራባሃ" ማለት ብቻ ሀላል ያደርገዋል?
16. የመደበኛው Principal እና የሙራባሃ Cost እንዲሁም የመደበኛው interest እና የሙራባሃ markups ምንም ልዩነት ከሌላቸው ወይም እጅግ እየተመሳሰሉ አንዱ ሀራም እንዱ ሀላል እንዴት ሆነ?
17. የመደበኛው የወለድ ምጣኔ እና የሙራባሃ markups ብዙ ባንኮች ጋር ሲወዳደር የሙራባሀው ይጨምራል። ለምን?
18. የሙራበሃ Markup መነሻ የሃገሪቱ ወለድ ምጣኔ ለምን ሆነ?
19. የተበደሩት የሙራባሃው ብድር ሁለት ዓመት ከሆነ በ2፣ አምስት ዓመትም ከሆነ በ5 ማብዛት ከየት የመጣ ነው? ከመደበኛው ጋር ያው መንትያ ነው። ለምን?

20. መደበኞቹ ወለድ የሚያሰሉት በቀሪው ብድር እና በቀሪው ጊዜ እየተቀናነሰ ሲሆን ሙራባሃው ግን እየተከፈለም ወለዱ ያው ለምን ሆነ?
21. በመደበኛው ብድር ላይ ኮንትራቱ ድንገት ቢቋረጥ ለቀሪው ጊዜ ወለድ አይታሰብም። ምናልባት ለቀሪው ብድር፤ ከነጻ እስከ 5% ቅጣት ሲከፈል እናያለን። በሙራባሃው ግን ብድሩ ዛሬም ቢመለስ ሙሉ ወለዱን (markups) የማስከፈል ጉዳትስ?
22. በመደበኛው ብድር ከኮንትራት ዘመን ሲሻገር ማለትም ተበዳሪው መክፈል ባይችል ወለዱ እየተነባበረ ይሻገራል። በኢስላማዊው ግን አይሻገርም ቢባልም ግን ቅጣት አለ። የኢስላማዊው ቅጣት እና የመደበኛው ተነባባሪ ወለድ አንድ ናቸው? ልዩነቱ በቃላት ስያሜ ብቻ ነው?
23. በሀዲስ በአንድ ግብይት ሁለት ግብይት ማለትም አንተ በካሽ ግዛልኝና እኔ በዱቤ ጨምሬ ልክፈልህ የሚለው ተከልክሎ እያለ በሙራባሃው ግን በቀጥታ ይህ ይፈጸማል። ይህ ማለት በሦስት የፈታኋትን ሚስት አግብተህ ፍታልኝ ጋር ተመሳሳይ ነው። “በይዓተይን ፊል በይዓ” የሚከለክለውን ሀዲስ በምን ይታረቃል?
24. መደበኛ ንግድ ባንኮች ሲያበድሩ ብቻ ሳይሆን በቁጠባ ገንዘብ ሲያስቀምጡ ሠሩም አልሠሩም ለአስቀማጩ ትርፍ (ወለድ) ይከፍላሉ። ይህንን ሀዘኔታ “ኢስላማዊዮች” እንዴት አጡት? (ትርፍ ማጋራት ለማለት ነው)።
25. መደበኞቹ ገንዘብ ሲያስቀምጡ እንደ ብድር ሲቆጥሩት የኢስላማዊዎቹ "ወዲኽል አማናህ" የሚሉት ዕውነት አማና ይጠብቃሉ? (በአመዘጋገብ ያው ብድር ቢሆንም)

26. መደበኞቹ የግሽበት ማካካሻ ለቆጣቢው ሲከፍሉ “ኢስላማዊዮቹ” ግን ምንም አያካክሱም። ለምን? (ኪሳራ ማካካስን የተመለከተ ነው። ከጥያቄ ቁጥር 23 ጋር እንዳያምታታ)።
27. በአማና ሲባል ገንዘቡ ሳይጎድል ማስረከብ ነው። ሆኖም ግን በግሽበት አስበልቶ መስጠት ሸሪዓን መሠረት ያደረገ እንዴት ይሆናል?
28. Collateral ወይም ማስያዣ የ“ኢስላማዊ ባንክ” መታወቂያው ነው። በኢስላም የማስያዣ መርኾዎች አሉ። ከዚህ ጋር ለማየት የተዘረጋ ሥርዓት አለ ወይስ የመደበኛው ባንክ አሠራር በቂ እና ሀላል ነው?
29. በብላሽ የሚያስቀምጥ ደህ ማስያዣ ስለሌለው አይበደርም። ከደህው እየወሰዱ ማስያዣ ላለው ሀብታም ማበደር እንዴት ሸሪዓዊ ይሆናል?
30. ሙዷረባ ጋር ስንመጣ “ኢስላማዊ ባንክ” ለሌጣ ደህ አያበድርም። ባይሆን ደህውን << በሙዷረባ አስቀምጥ። ካተረፍን ትርፍ ትጋራለህ። ከከሰርን በሙዷረባ ሕግ፤ ኪሳራ የገንዘብ አምጪ ስለሆነ ገንዘብህን ትከስራለህ >> ይባላል። ደህ ቆጣቢ ለሀብታም ባንክ ማበደሩ ሸሪዓዊ ነውን?
31. ሙሻረካ (ትርፍና ኪሳራ መጋራት) መቼም ስለማናስበው እንለፈው። ግን አንድ ጥያቄ ብናነሳ፤ ዋነኛውን የባንኩ አሠራር ትቶ እንዴት ኢስላማዊ ይሆናል?
32. ትርፍና ኪሳራ መጋራት ያለው መደበኛው ባንክ ላይ ነው ማለት ይቻላል። ምክንያቱም ኢስላማዊው ኪሳራን መሸሽ ወይም ከትርፍ አለማካፈል ከወዲኽል አማና (በነጻ ማስቀመጥ) ይጀምራል። መደበኛው ግን ለቆጠበለት ሰው ባንኩ ሠራም አልሠራም አሁን ባለው 7% ይከፍላል። ኢስላማዊው ግን ገንዘብ ተቀብሎ ሠርቶበት በባዶ ለቆጣቢው ይመልሳል። በበነጋታው አንድ ብር አበድሩኝ ቢባል አያበድርም። ይህ እንዴት ኢስላማዊ ይሆናል?

33. በመደበኛው የተከፈለው ወለድ ለታክስ ማቀናነሻ ወጪነት ተይዞ፤ ቢያንስ የወለዱ 30% ከዓመታዊ ታክስ ላይ ሲቀናነስ የኢስላማዊው markups ግን እንደ ዕቃው ዋጋ ይያዛል። ይህ double taxation እንዴት አልተስተዋለም?
34. የቋሚ ዕቃ (ምሳሌ የግንባታ፣ ማሽን ግዢ) ዋጋ አድርገን በእርጅና ቅናሽ depreciation እናካክሰዋለን ሊባል ይችል ይሆናል። ገዝተን በምንሸጠው ሸቀጣሸቀጥም ዋጋ ላይም ጨምረነው "Cost of goods sold"ን ከፍ ስለሚያደርግ ትርፍ (Gross Profit)ን ዝቅ ስለሚያደርግ እንደ ወጪ ተይዟል የሚባል መከራከሪያ ከሒሳብ ባለሙያ ሊሰነዘር ይችል ይሆናል። ሆኖም ግን በኢትዮጵያ የግብር አሰባሰብ መሠረት የዘርፍ የትርፍ ሕዳግን ከፍ ያደርገዋል። ማለትም ለየዘርፉ አንድ ነጋዴ ማትረፍ አለበት ተብሎ የተቀመጠ ፐርሰንት አለ። ነጋዴው ባቀረበው ዋጋ ላይ የማትረፊያ ፐርሰንቱ ይባዛል። የኢስላማዊው ወለዱ የዕቃው ዋጋ "Cost of goods sold" ስለሚሆን ከፍ ባለ ዋጋ ላይ ይሰላል ማለት ነው። በዚህም ሙስሊሙ መንግሥት እንኳ ክፈሉኝ ያላለ አላስፈላጊ ታክስ ይከፍላል። ለምን?
35. ነጋዴው ገንዘብ ተበድሮ ሄዶ ዕቃ ገዝቶ የተጨማሪ እሴት ታክስ (ቫት) ሲያወራርድ በሙራባሃም ይሁን ሌሎች ግብይቶች ላይ ግን ቫቱ አይወራረድም። ጭራሽ የብድር አካል ይሆናል። ይህ ሦስተኛ የታክስ ጉዳት (Triple taxation) እንዴት አልታየም? በሌላ አነጋገር ሙስሊም ተበዳሪ ዕቃ ተገዝቶ ስለሚሰጠው ልክ እንደ መጨረሻ ተጠቃሚ (End consumer) ሆነ ማለት ነው። ይህ ወሳኝ ጥያቄ እንዴት አልታየም?
36. ኢስላማዊ፣ ከወለድ ነፃ፣ ሸሪዓን መሠረት ያደረገ ሲባል ከመጅሊሱ የዑለማ ጉባዔ በኩል ውይይት ተደርጎበት ለምን አልተጀመረም?

37. ጉዳዩ ኃይማኖታዊ እንደመሆኑ ለወደፊቱስ ኢስላማዊ የተሰኙ ባንኮች በማዕከላዊነት ማን ነው የሚቆጣጠራቸው?
38. በባንኩ ዙሪያ ለሚፈጠሩ ክርክሮች የት ነው የሚዳኙት?
39. በመደበኛው ፍርድ ቤት ከሆነ የሸሪዓው ዕውቀት አላቸው?
40. የሸሪዓ ዕውቀት ቢኖራቸው እንኳ ክርስቲያኖች በሸሪዓ ሊፈርዱን ይችላሉ?
41. ለሸሪዓ ፍርድ ቤቶች ቢሠጣቸው ሥልጣን አላቸው?
42. ሸሪዓ ፍርድ ቤቶቻችን በባለሙያ ዕጥረት እየተሰቃዩ የጋብቻና ፍች ጉዳይ እንኳ በክርስቲያኖች ዕርዳታ ነው የሚፈጽሙት። ይህንንስ የማየት ብቃት (Efficiency) አላቸው?
43. ከሌላቸው ስለ Capacity building ምን ታስቧል?
44. የብዙ ሙስሊም ሀገራት የሸሪዓ ፍርድ ቤቶች ሳይቀር በኢስላማዊ ሊቃውንት (ፉቀሐእ) መለያየት ይቸገራሉ። ለዚህም አንዱን መዝሀብ ብቻ ይከተላሉ። ኢትዮጵያ ውስጥ ከሁለት መዝሀብ በላይ ተግባር ላይ አለ። ስለዚህ በየትኛው መዝሃብ ነው የሚዳኙት?
45. የታክስና የንግድ ሕጎች ብቻ ሳይሆኑ የፍትሐብሔር እና የወንጀለኛ መቅጫ ሕጎችም መሻሻል ሊኖርባቸው ነው። ስንት ዓመት ይወስዳል?
46. እነዚህን ሕግጋትን ስናሻሽል የሌላው ማኅበረሰብ አመለካከት ምን ያህል ነው?
47. የሀገር ውስጥ ሕጎች የዓለም አቀፍ በተለይም የምዕራባዊያን ሕጎችና መጻሕፍትን ነው የምንጠቀመው። አገር ውስጥ ያሻሻልነው ሕግ ከሀገር ሲወጣ አይስማማም። ሌሎች መደበኛ ባንኮች ግን በዓለም አቀፍ ቅኝት ነው የተቋቋሙት። ይህንን ከባድ ፈተና በምን ይታለፋል?
48. በንግድ ባንኮች የወለድ ነፃ ሲጀምሩ ከገጠር እንደጀመሩት፤ ኢስላማዊ ብለው የጀመሩ ጅምር ባንኮች እንዳየነው ከከተማና ከተማረው ሰው ሳይሆን

ከገበሬው ለመጀመር ለምን መረጡ? የገበያ ስትራተጂ ነው ሊባል ይቻል ይሆናል። ለገበሬና ለገጠሬው ቶሎ ይደርስለታል?

49. 2ኛ ደረጃ የአክሲዮን ገበያ (Stock market) በሌለበት ሀገር አክሲዮን ወደ ካሽ እጅግ የማይቀየር (illiquid) ንብረት ነው። ሙስሊሙ ደግሞ ለዚህ ዘርፍ እጅግ ገና ነው። ደሀም ጭምር በመገፋፋት አክሲዮን ሲሸጥ ታይቷል። ደሀውን ከመጥቀም አኳያ ምን የተወጠነ ነገር አለ። ይህ ጥያቄ ለወደፊት ለሚቋቋሙ ባንኮችና አክሲዮኖች ይሠራል።
50. 2ኛ ደረጃ የአክሲዮን ገበያ ኖረም አልኖረም ትርፍ ክፍፍል በዓመት አንዴ ነው። እሱም ትርፍ ከተገኘ ነው። ታዲያ በድህነት ወለል ላይ እና እጅግ በታች ለሆነ ሰው በዓመት አንዴ ትርፍ አግኝቶ ኑሮውን እንዴት ይገፋል? እንዲታሰብበት ያህል ነው።
51. ትልልቅ አክሲዮን የሚያደራጁት ሀብታሞችና በዘርፉ ላይ ዕውቀት ያላቸው ሰዎች ናቸው። ምክንያቱም ከፍተኛ ዕውቀት እና ገንዘብ ስለሚጠይቅ ነው። ስናይ ግን ከሙያው ውጭ የሆኑ ሰዎች ይበዛሉ። እንዴት ውጤታማ ሊሆን ነው?
52. የአደራጅ ገንዘብ (5%) ሰብስቡ የሚል ሕግ ሳይኖር ብሎም ክልክል ሆኖ ሳለ መሰብሰብ ከሕግ አኳያ እንዴት ታስቦ ነው? ይህ በአጠቃላይ የሀገሪቱ አክሲዮኖች የሚታይ ክፍተት ሆኖ ቆይቷል።
53. በቅርበት እንዳስተዋልነው በሙያው ላይ ዕውቀት የሌላቸው ዑለሞችን ከፊት በማሰለፍ አክሲዮን መሸጥ ማታለል ከመሆኑም በላይ ችግር ቢፈጠር በሕግ እንደሚጠየቁ አታውቁም?

54. የባንኮቹ አክሲዮኖች ለሁሉም ክፍት እንደመሆናቸው ክርስቲያኖችም ይገዛሉ። የአክሲዮኑ አብላጫ ድምፅ (30% እና በላይ) ከያዙ በሸሪዓ አናስተዳድረውም እንዲሁም አንተዳደርም ካሉስ?
55. ነባር ንግድ ባንኮች የሰኪዩላር ንግድ ሕጉን ተጠቅመው አክሲዮን ገዝተው overtake ቢያደርጉትስ?
56. መደበኛ ንግድ ባንኮች ኢስላማዊ ለሚሰኘው ባንክ ዝግጅታቸውን ጨርሰዋል። (ይህ መጽሐፍ በሚታተምበት ገደማ በቅርንጫፍ ደረጃ ከፍተዋል)። በአሠራር ቅልጥፍናና ልምድ የተሻሉ በመሆናቸው ከእነርሱ የተለየ ምን ዓይነት አሠራር ሊመጣ ነው? ውድድሩን እንዴት ይቻላል?
57. አክሲዮን የገዙ ሰዎች ባንኩ ሥራ እስኪጀምር ዘካቸንን ማን ሊያወጣልን ነው? የሚል ጥያቄ ያነሳሉ። የአክሲዮን ካፒታል እና ዘካ ማብራሪያ ለምን አልተሰጠም? ሥራ ከጀመረ በኋላ ባንኩ በብሔራዊ ባንክ ስር የሚተዳደር በመሆኑና የዘካ ሕግ ስለሌለው የዘካ ጉዳይ እንዴት ሊሆን ነው?
58. ሙስሊምና ክርስቲያን ተቀላቅሎ በሚያቋቁመው ባንክ ውስጥ የዘካ እጣ ፈንታ ምንድን ነው?
59. ክርስቲያኖች በሚያስተዳድሯቸው ባንኮች ውስጥ ያሉ ኢስላማዊ ባንኮች ወይም ቅርንጫፎች ዘካ እንዴት ሊሆን ነው? ክርስቲያን ዘካ የመክፈል ግዴታ አለበት?
60. የዘካ መክፈያ Point of Zakkah የቱ ጋር ነው? የአክሲዮን ገንዘቡ ላይ ወይስ የአክሲዮን ማኅበሩ የጋራ ትርፍ ላይ ወይስ የተከፋፈለ ትርፍ (ዲቪደንድ) ላይ ወይስ ከዲቪደንድ ታክስ በኋላ?
61. ሕዝባችን እጅግ ደሀ ሆኖ እያለ ማይክሮፋይናንስ ለምን ችላ ተባለ?

62. ባንኮቹ እስኪቋቋሙ ማለትም ሕብረተሰብ ጋር ለመድረስ እጅግ ረጅም ዓመት እንደሚወስዱ ይታወቃል። እስከዚያስ ሕዝቡ ምን ያድርግ?
63. ማይክሮፋይናንስ እና ሌሎች የመንግሥት የገንዘብ ተቋማት ከመንግሥት ዕድሎች ጋር ለምሳሌ ከመሬት እና ከሥራ መሥሪያ ቦታ ዕድለኝነት ጋር የተያያዙ ናቸው። ይህንን ትልቅ ዕድል ማስመለጥስ እንዴት ታየ?
64. የታክስ እና የንግድ ሕጎችን ተስማሚነት ላይ ማስቀደም ባይቻል እንኳ ጎን ለጎን ማስኬድ ለምን አልተሞከረም?
65. ተግተልትሎ ለመመሥረት ተገብቶ ያለንን ውሱን ካፒታል፣ የተማረ ኃይልና ደንበኛ መከፋፈልስ ለምን ተፈለገ? ይህ ጉዳይ ገና ከጅምር የታየ ችግር ነበር። በቀጣይ ለሚከፈቱም ይሁን በተከፈቱ ባንኮች ላይ ችግሩ ላለመዝለቁ ምን ዋስትና አለ?
66. ምእመኑን በኢስላማዊ አመለካከት አቧድኖ ባንክ መጀመር የባንኩም የምእመኑም የወደፊት ዕጣ ፈንታ ላይ ችግር አይፈጥርም? ይህ ጉዳይ ጥናት ቢፈልግም መቦዳደኑ ግን መራራ ዕውነታ ነው። በአስቸኳይ መቅረፍም ይፈልጋል።71
67. ባንክ ያለ ኢንሹራንስ ሊሠራ አይችልም። ስለዚህ ኢስላማዊ ባንኩ የሚጠቀመው መደበኛ የኢንሹራንስ ኩባንያዎችን ነው?
68. ኢስላማዊ ኢንሹራንስ (ተካፉል) የሚባል ሌላ ፍልስፍና አለ። ፍልስፍና እንደየዘመኑ ሊነሳ ይችላል። ይህኛው ፍልስፍና ምን ያህል ታይቷል? ወይስ በሒደት ይግባን?

[71] የብሔር መቦዳደንም እንዳይኖር ጥንቃቄ ይፈልጋል። በመደበኛ ባንኮች ዘንድ ይህ የብሔር ቡድን አለ። እዚህም እየተንጸባረቀ ነው። ከኃይማኖት የአንጃ ክፍፍል ጋር ከተዳቀለ ባንኮቹን ያሽመደምዳል።

69. ተካፋል እንደ ባንክ፣ ወለድ (ሪባ) ብቻ ሳይሆን ቁማር እና ገረር (Speculation) ጭምር ስላለው ከኢትዮጵያ የንግድ ሕግ ጋር ከፍተኛ ምርምር ይፈልጋል። ኢንሹራንስ ላይ ሪባ እና ቁማር መሰል ኮንትራቶች ስላሉ ከሸሪዓችን ጋር መናበብ ይኖርበታል። ይህም በሒደት ይግባን ወይስ የጥናት ምርምር ተቋም ይቅደም?
70. ከፍ ብሎ የጠቀስኳቸው ሁለቱ ነጥቦች ቢኖሩን ብለን አስበን እንኳ ኢንሹራንሱ (ተካፋሉ) የታለ? ከፈረሱ ጋሪው የቀደመ ይመስላል።
71. በቅደም ተከተል ኢንሹራንሱ ከማይክሮፋይናንስም መቅደም ነበረበት። ትኩረት ለምን ተነፈገው?
72. ኢስላማዊ ባንኩ ገንዘብ ቢቸገር ከየት ነው የሚበደረው? ከመደበኛ ባንኮች? በመደበኛ ወለድ?
73. የኢኮኖሚ ሥርዓትን ከሚወስኑ ነገሮች አንዱ የፖለቲካ ጥንካሬ ነው። የፖለቲካ ጥንካሬ በሌለበት ሀገር ውስጥ ኢስላማዊ የተሰኙ ባንኮች ከእነስማቸው የሲስተሙ ተቃራኒ ሆነው ሲመጡ የፖለቲከኞችን ፈተና እንዴት ነው የሚቋቋሙት?
74. የኢስላማዊ ባንኮች አንዱ ፈተና ተለይቶ መመታት ነው። ሀገሪቷ 15 ባንኮች ቢኖራት ለሁሉም ተመሳሳይ ሕግ ታወጣለች። ለብቻ የሚጠቃ ወይም የሚጠቀም ባንክ ላይኖር ይችላል። ኢስላማዊዎቹ ግን ሕግ የሚወጣላቸው ለብቻ ነው። ወይም ችላ ይባላሉ። ሁሌ ወደ ማለቃቀስ መሄዱ ለቀጣይ ትውልድ ለቅሶ ማውረስ አይሆንም?
75. የኢስላማዊ ባንኮች ትልቁ ፈተና የውጭ ሀገራት Correspondent bank ናቸው። ከምዕራባውያኑ Hard currency ባንኮች ጋር ምን የተጀመረ እንቅስቃሴ አለ?

76. የጸረ-ሽብር ሕግጋት በተለይም ሙስሊምና ሙስሊም ሀገራት ላይ ያነጣጠረ በመሆኑ በኮረስፖንደንት ባንክ (Vostro/nostro) አካውት ላይ ብዙ ጊዜ እግድ ይጣላል። ስለዚህ እዚህ የሚቋቋሙት ባንኮች ምን ያህል ጥንቃቄ ተደርጎባቸዋል?
77. በካፒታሊስታዊ የኢኮኖሚ ሲስተም ንግድ ባንኮች ከመንደር ተነስተው እስከ ምዕራባዊያን መሪዎች ድረስ ሰንሰለት አለው። ምክንያቱም ሲስተሙ ያግዘዋል። የኛ የሙስሊሞቹ ሰንሰለት ጥንካሬ ግን ከዚሁ ከብሔራዊ ባንክ አያልፍም። ምናልባትም አይደርስም። ታዲያ ሙስሊሙን እንዲህ ያለ ሸለቆ ውስጥ ለመክተት ለምን አስፈለገ?
78. ሙስሊሙን "በወለድ ነጻ" ወይም በ"ኢስላማዊ ባንክ"" ስም ለብቻ በአንድ ቅርጫት መመዝገብ ወይም መሰብሰብ ያለው አደጋ እንዴት አልተስተዋለም?
79. ባንኮቹ የቅርብ ዘመናት ዕድሜ ያለው ቲዎሪ እንደማያስኬድ ከገባቸው ለመቀየር ምን ያህል ዝግጁ ናቸው?
80. ኢስላማዊ ባንኮች ላይ ያሉ ባለሙያዎች ዕውነታውን ቢያውቁትም የሕዝቡ አለመንቃት ወይም "ወለድ፣ ባንክ" ለሚለው ስም ያለው አመለካከት ከፍተኛ በመሆኑ በማይፈልጉት መንገድ እየሄዱ እንደሆነ ይናገራሉ። ይህንን የተንሻፈፈ አረዳድ ለመቀየር ምን የተዘጋጁት ነገር አለ?
81. የሸሪዓ የፋይናንስ ስታንዳርድ ተዘጋጅቷል?
82. የሸሪዓ አዲትስ ተቋቁሟል?
83. የኡዲት ስታንዳርድስ አል?
84. ማዕከላዊ የሸሪዓ መማክርት ተዘጋጅቷል?
85. እነዚህንና መሰል ጥያቄዎችን ለመመለስ ምን ያህል ቁርጠኛ ነን?

اللَّهُمَّ صَلِّ عَلَىٰ سَيِّدِنَا مُحَمَّدٍ وَعَلَىٰ آلِهِ وَصَحْبِهِ وَسَلِّمْ

ምዕራፍ አራት

ኃላፊነት መስጠት

የፊያት መገበያያና የሸሪዓ አቋም

የኢስላማዊ ሕግ ጭፍን ተከታይነትን ያወግዛል። ለንቁ ትግል ያበረታታል። ካመንንና ከታገልን አላህ ድል እንደሚሰጠን በቁርአንም በሀዲስም ተምረናል። በተለይ ሀራም ሲነግስ፣ ነገሮች ሲወሳሰቡ፣ ችግሮች እግር ከአንገት ሲይዙ፣ በዚያው ተይዞ መቅረት ወይም "አላህ ይብቃን" ብሎ መቀመጥ "ልግመኝነት" ነው። ("ልግመኝነት" የሚለውን ቃል ለጽሑፍ እንደሚጎረብጥ እረዳለሁ። ለመውቀስና ለማውገዝ ሳይሆን መጠነኛ ቁንጥጫ ነው። ለቃሉ ይቅርታ)። ምክንያቱም የነቢ ሙሳ (ዐሰ) ሕዝቦች ከፈርአን ባርነት ነጻ ወጥተው፣ የተቀደሰችዋ ምድር ክልል አካባቢ ደርሰው፣ በውስጧ መጥፎ ሕዝቦች ስላሉ ተዋግታችሁ አውጡ፤ አላህ ድል ይሰጣችኋል ተባሉ።

"ሙሳ ሆይ! በርስዋ ውስጥ ኃያላን ሕዝቦች አሉ። ከርስዋም እስከሚወጡ ድረስ እኛ ፈጽሞ አንገባትም። ከርስዋም ቢወጡ እኛ ገቢዎች ነን አሉ። ከእነዚያ (አላህን) ከሚፈሩትና አላህ በእነርሱ ላይ ከለገሰላቸው የኾኑት ሁለት ሰዎች "በእነርሱ (በኃያሎቹ) ላይ በሩን ግቡ። በገባችሁትም ጊዜ እናንተ አሸናፊዎች ናችሁ። ምእመናንም እንደኾናችሁ በአላህ ላይ ተመኩ" አሉ። "ሙሳ ሆይ! በውስጧ እስካሉ ድረስ እኛ ፈጽሞ አንገባትም። ስለዚህ ሺድ አንተና ጌታህ ተጋደሉም፤ እኛ እዚህ ተቀማጮች ነን" አሉ። ቁርአን 5:22-24

እንዲህ በማለታቸው አላህ ለአርባ ዓመታት እንዳይገቡ እርም አድርጎባቸው እዚያው በዚያው የሚዳክሩ አደረጋቸው። ስለዚህ እኛም እንደነሱ እንዳንሆን ተጠንቅቀን ለሥራ መንቀሳቀስ ነው። የፈለገውን ያህል ጊዜ ሊፈጅ ይችላል። የኛ ድርሻ መንቀሳቀስ ሲሆን ድል መስጠት ግን የአላህ ነው።

ብዙዎቻችንን ሸብባ የያዘችን "ዶሩራ" የምትሰኝ ቃል አለች። "ዶሩራ" ማለት "አስፈላጊ ችግር" ወይም "አስቸጋሪ ፍላጎት" የሚሉት ቃላት ሊቀርቡት ይችላሉ። በምሳሌ ብናስረዳው ምግብ በአቅራቢያ በማይገኝበት አስቸጋሪ ቦታ የአሳማ ሥጋ መብላት ልንገደድ እንችላለን። ሀራሙን የምንበላው ካለንበት ረሀብ ሀላል ምግብ ወዳለበት ቦታ ለመውጣት ነው። ነገር ግን እንደ ዳቦ ከጣመን እና የምግብ ባለሙያ ቀጥረን የምናሸሞነሙነው ከሆነ ግን "ዶሩራ" አይደለም። (ዓለም ሁሉ የዓሳማ ሥጋ ቅንብር ውጤት ቢሆንስ ከተባለ ይህ ባንኮችን በምናይበት አተያይ እናየዋለን)። የአሳማ ሥጋ በየትኛውም ችግር ሀላል (ፍቁድ) አይሆንም። ሊሆን የሚችለው ከችግር መሻገሪያ ግዴታ ነው። **ችግር ሀራሞችን (ክልክሎችን) ፍቁድ አያደርግም። ባይሆን መወጣጫ ግዴታ ነው የሚያደርጋቸው።** ምክንያቱም ከተገደድን ለመቀየር እንታገላለን። ሀላል ካደረግነው ግን ክልክሉ ላይ ተመቻችተን እንቀመጣለን።

በተመሳሳይ ወለድም ተመችቶን ከተቀመጥን እያጣጣምነው ነው ማለት ነው። በወርቅ ገንዘብ ቢሆን እንኳ ወለድ የምንበላበት ሁኔታ ሊከሰት ይችላል። ሆኖም ግን ለመውጣት መዘጋጀት ያስፈልጋል። አሁን የሪባ ሥርዓት ከእግር እስካንገት ወሮናል። ይህንን «ኢስላማዊ» እያሉ ማሸሞንሞን አሳማውን ከማሸሞንሞን ተለይቶ አይታይም። ሀላል ወለድ እየበሉ ዝንተ ዓለም ሊንኖር አይቻልም። ከዶሩራ (ችግር) መውጣት አለመፈለግ ወይም ችግሩ ከደላን ውስጣችን የባሰ ከባድ ችግር አለ ማለት ነው። ጤነኛ አእምሮ ለችግር መውጫ መንገድ ይፈልጋል። በአላህ መንገድ ላይ

በጽናት ይታገላል። ከመንገዶች ሁሉ ቀናው መንገድ “አላህን መፍራት ነው”። አላህን ፈርተን ከታገልን አላህ መውጫ መንገድ ያበጅልናል። “እጅ አጣጥፈን ከተቀመጥን” ግን የኢስራኢል ልጆች ከፊርአውን ባርነት ነጻ ወጥተው ሲለግሙ አላህ በረሀ ለበረሀ እንዳንከራተታቸው “ልግመኞች” እንዳንሆን ያስፈልጋል። የፊያት አውዳሚነት ከቀትር ጸሐይ ወይም በጠራ ሰማይ ላይ ከ14ኛው ሌሊት ጨረቃ በላይ ግልጽ ነው። ስለዚህ “የግድ መወገድ ያለበት ችግር ነው”።

የባንኩ ወለድ “ሪባ” ካልሆስ የሚል ነገር የሚያስብ አይጠፋም። የባንኩ ወለድ የቆመው የባሰ ወለድ “ፊያት” ላይ ነው። ተበደርንም አልተበደርንም ይበላናል። ከሁሉም ድቅቅ የሚሉት ለአቅመ-ብድር ያልደረሱት ናቸው። ምክንያቱም ወለዱ ቀድሞ በሕትመት ወይም በጅት ወቅት ተፈጥሯል። የተበደሩት ይከላከሉታል። ከባንክ በወሰዱት ብድር ንብረት ይገዙና ወለዱን ለማይበደሩት በግሽበትና በተጨማሪ እሴት ታክስ (ቫት) መልክ ይረጩታል።

ፊያት ሌሎች ገንዘቦችን ሁሉ ተክቶ መሥራት?

ይህ አባባል ብዙ ቦታ ልትሰሙት ትችላላችሁ። ግን ዕውን ተክቷል? ይህንን መጽሐፍ ጨርሶ ያነበበ ሌላ ባይጨምር እንኳ ደፍሮ ተክቷል ሊል አይችልም ብሎ በድፍረት መናገር ይቻላል። ምክንያቱም የተፈጥሮ ገንዘቦች ምንነትና የፊያትን ምንነት ግንዛቤ ይኖረዋል። ሌላ አስረጅ ለመጥቀስ ባንደከም እንኳ በሎጂክ ወይም ንጹሕ አእምሮ መመለስ ወይም ማስረዳት ይቻላል። በእርግጥ የትክክለኛ ገንዘቦቻችን መረጃ ከቁርአንና ሀዲስ እንዲሁም ከኢኮኖሚክስ አሳልፈናል። ለተወጣጠረ አእምሮ የተወሰኑ ሎጂኮችን እናክልና ዘና ብለን መጽሐፉን እናሳርገው።

አንድ ነገር በመጥፋቱ ወይም በመወገዱ ወይም በሌላ ነገር መተካቱ የመጀመሪያውን ሆኖ ሊያገለግል አይችልም። አባት ቢሞት እናት፤ ያው እናት እንጂ አባት አትሆንም። ለልጆቿ የአባትንም ቦታ ተክታ መሸፈን ትችላለች እንጂ አባትነት መቼም አይገኝም። ይህ ከጥቂት ልዩነት ውጭ በሁሉም ቦታና ሁኔታ ይሠራል። ሌላው ቀርቶ ቴክኖሎጂ ቢያሻሽላቸው እንኳ ከኢስላማዊ መሠረት መልቀቅ የለብንም። የጊዜ መቁጠሪያ "ካላንደር" ስለመጣ ኢስላማዊ ቆጠራዎች በጨረቃ መከታተል አይቀርም። የረመዷን ጾም መጀመርም መጨረስም ያለብን በጨረቃ ነው። ካላንደሩ ከገጠመ እሰየው፣ ካልገጠመም የጨረቃው ትክክል ነው የሚሆነው። ሰዓት ስለመጣ የሶላት ወቅት የፀሐይን አቅጣጫና ጥላ እያዩ መስገድን አያስቀርም። ሰዓቱ መግጠም ያለበት ከተፈጥሮአዊ መለኪያ ጋር ነው። የድምጽ ማጉሊያ በመምጣቱ ሶላት ሲሰገድ የኢማሙን ድምጽ የሚያስተጋባ መኖር አለበት። ይህ ነገር ከመካና መዲና መስጂዶች ውጭ በሌሎች መስጂዶች አይታይም። በድምጽ ማጉሊያ እየተሰገደ ድንገት መብራት ሲጠፋ ሶላተል-ጀማዓው (የስግደት ስብስቡ) ይፋለሳል። በተለይ የሴቶች መስጂድ፣ በወንዶቹ ደግሞ ከመስጂዱ ውጭና በረንዳ አካባቢ የሚሰግዱት ከኢማሙ (ከመሪው) ይገነጠላሉ። የነዚህ ችግር መሠረትን ትቶ፤ ሸሪዓውን "ሊጠፉ በሚችሉ" ሰው ሰራሽ ነገሮች መተካት የፈጠራቸ ግድፈቶች ናቸው።

ትንሽ ዘና ለማድረግ ያህል፡- አዲስ አበባ ፒያሳ ኑር መስጂድ ላይ የጁምዓ (ዓርብ) ሶላት እየተሰገደ ነው። ሶላቱ ሊያበቃ የመጨረሻ ተሸሁድ (ማሳረጊያ መቀማመጥ) ላይ ኢማሙ የሶላት ማብቂየ ዓረፍተ ነገር (አሰላሙ ዓለይኩም ወራህመቱላህ) የሚባለውን ከመናገራቸው በፊት መብራት ይጠፋል። ኢማሙ መብራት ጠፋም አልጠፋም ማለታቸው አይቀርምና ብለው አሰግደው ጨርሰው ሌላ ሶላት ጀምረዋል። ሶላቱ "ሶላተል ጋኢብ" ይሰኛል። አንድ የሚታወቅ ሙስሊም ከዚያ

መስጂድ ርቆ ሞቶ ዱዓ ለማድረግ የሚሰገድ ነው። አስከሬን አጠገብ ከሚሰገደው ጋር አንድ ዓይነት ነው። ተቁሞ ነው የሚሰገደው። ማጎንበስም ይሁን መሬት መውረድ የለውም። የጁምዓ ሶላት አካል አይደለም። የፈለገ ይሰግዳል፤ የፈለገ ይሄዳል። ይህ ስግደት አራት ጊዜ "አላሁ አክበር" አለው። በዚሁ ተመሳሳይ አራት ጊዜ "አላሁ አክበር" የሚባል ያለው አለ። ምን መሰላችሁ የእርሳቻ ሱጁድ ወይም እርማት ይሰኛል። በማንኛውም ሶላት ውስጥ ግዴታ ያልሆነ ነገር ከተረሳ በመጨረሻ ላይ ለማሟያ አራት ጊዜ ተክቢራ ይደረጋል። ሁለት ወደ መሬት መደፋት (ሱጁድ) አለው።

ውስጥ ያሉ ሰዎች የጁምዓ ሶላት ጨርሰው እኩሎቹ ይህንን ሶላተል ጋኢብን ለመጀመር ቆመዋል። እኩሎቹ እየወጡ ናቸው። መብራት በመጥፋቱ ውጭ ያሉት ግን የጁምዓ ሶላቱ አብቅቶ መሰላመቱን አላወቁም። ልክ ኢማሙ የሙት ሶላት ሊጀምሩ ሲሉ መብራቱ መጣ። ኢማሙ "አላሁ አክበር" ሲሉ ውስጥም ውጭም ተሰምቷል። የውስጠኞቹ በቆሙበት የሙት ሶላቱን ጀምረዋል። የውጪዎቹ በተቀመጡበት "የእርሳቻ ማስተካከያ" ሱጁድ ወደ መሬት ተደፍተዋል። ሶላተል ጋኢብ እና ሰጅደተ ሰህው ተቀላቀሉ። ኢማሙ አላሁ አክበር ሲሉ በአንድ መስጂድና በአንድ ኢማም ሁለት የተለያየ ሶላት ተሰገደ ማለት ነው። ችግር የተፈጠረው የሙት ሶላት ግዴታ ስላልሆነ ለጉዳይ ቸኩለው የሚወጡት በረንዳ ላይ በፈጠሩት ጫጫታ ነው። ያኔ የተፈጠረው ግርታ የነበረ ሰው መቼም አይረሳውም። ለዚህ ምንም ዓይነት ሸሪዓዊ ብያኔ የለውም። መፍትሔው ከኢስላማዊ መሠረት አለመልቀቅና መብራት ኖረም አልኖረም በየርቀቱ ከኢማሙ እየተቀበለ ወደኋላ የሚያሰማ ሰው ማቆም ነው። ይህ በመካና በመዲና መስጂድ ተግባራዊ ሲደረግ ሌሎች መስጂዶች ላይ አይስተዋልም።

ሌላ ምሳሌ ለመጨመር ያህል የፊያት መገበያያ እና የቴሌቪዥን ምስል ይመሳሰላሉ። ቴሌቪዥን መልዕክት ማስተላለፊያ እንጂ ተቀርጸው የሚናገሩ ሰዎች የተፈጥሮ ሰዎች ናቸው ብለን አንወስድም። ፊያትም ኮምፒውተር ውስጥ እንደሚቀመጠው ምስሎቹም ኮምፒውተር ውስጥ ይቀመጣሉ። ሁለቱም አገልግሎታቸው መልዕክት ማስተላለፊያ ናቸው። የተፈጥሮው ሰውዬ ሞቶ ቪዲዮው ሊጫወት ይችላል። ተመስሎም ይሠራል። የቪዲዮው ሰውዬ አይከስም፣ አይከሰስም፣ ምስክር መሆንም አይችልም። እንደ ጽሑፍ መረጃ መሆን ግን ይችላል። የፊያት መገበያያም ተመሳሳይ ነው።

ፊያት ወርቅን ስለተካና የዓለም ሕዝብ ስለተቀበለው እኛም እንቀበለው የሚባል መከራከሪያ ሲቀርብ ለሚያቀርብ ሰው ቪዲዮም ሰውየው ቀን ተቀርጾ ማታ መልዕክት ያስተላልፋል። የዓለም ሕዝብ በሙሉ መልዕክቱን ሊያምነው ይችላል። ግን የተፈጥሮው ሰውዬ ነው ማለት አይቻልም። ፊያትም ተመሳሳይ ነው። የግብይት ቋንቋ እንጂ የፊያት አስተናባሪዎችና ኢኮኖሚክሱም፣ ፋይናንሱም ጭምር ገንዘብ ነው አይለውም። ኖት፣ ቢል እያለ ይጠራዋል። ባለ 50 ብር ኖት፣ ባለ 100 ብር ኖት ሲባል እንደምንሰማው። ባለፉት ምዕራፎች እንዳሳለፍነው በሸሪዓውም በኢኮኖሚክሱም ገንዘብ ካልተባለ፤ ጭራሽ እራሱ የአራጣ ሆኖ ሸሪዓዊ አራጣ ሊሰላበት ብቁ አይሆንም። የሚፈጥረው ትርምስ ልክ በቪዲዮ ወይም ቴሌቪዥን እንደሚፈጠሩ ትርምሶች ልንዳኘው እንችላለን። ሰው በካሜራ ተቀርጾ ከተፈጥሮ ሰው በላይ ሊበጠብጥ እንደሚችለው፣ የፊያት መገበያያም በኮምፒውተር ገብቶ ከተፈጥሮ ገንዘብ በላይ ሊያምስ ይችላል። ይህንን ከአራጣ ጋር አያይዘን ብይን መስጠት ወይ ሸሪዓውን ወይ ፋይናንሱን አለማወቅ ነው። ገንዘብ ተብሎ ሊወሰድ አይችልም። በተለምዶ ልንጠራው እንችላለን።

ወርቅን ወይም ስንዴን ተክቷል በሚለው ብንስማማ፤ ወርቅ በወርቅ፣ ስንዴ በስንዴ እኩል በእኩል፣ እጅ በእጅ መገበያየት እንጂ ማበላለጥም ማዘግየትም እንደማይቻል እላይ አሳልፈነዋል። ዶላርም ፣ ግራም ወረቀት፣ ሪያልም ፣ ግራም ወረቀት፣ ፍራንክም ፣ ግራም ወረቀት ናቸው። ታዲያ ለምን ልውውጣቸው ተለያየ? ለአሜሪካ ለብቻ የወረደ የቁርአን አንቀጽ አለ እንዴ? ፎቶዎቹ ስለተለያዩ ምንዛሪውም ይለያያል? የፈረንጅ ፎቶ ያለበት ወረቀት የአፍሪካዊ ፎቶ ባለበት 50 ወረቀት ይለወጣል እንዴ? እኛ አሜሪካ ሄድን በ1 ዶላር 50 ቀርቶ 500 ብር ብንሰጣቸው አይቀበሉም። ምክንያቱም ድንበር ተሻጋሪ መገበያያዎች ስድስት ሲሆኑ ሌሎች ከድንበር አይወጡም። ወርቅ ግን ድንበር የለውም።

አስባችሁታል ቁርአንና ሀዲስ “እናንተ ጥቂቁሮች ሆይ በስድስት የተፈጥሮ ገንዘቦች ምትክ የስድስት ፈረንጆችን ፎቶ ተክታችሁ ተጠቀሙ” ሲል። የአንዳንዶች ማንቀላፋት የአሜሪካን ዶላር ማለት ወርቅ፣ ጠገራ ብር ማለት ዩሮ፣ ተምር ማለት ፓውንድ ስተርሊንግ፣ ስንዴ ማለት የጃፓን የን፣ ገብስ ማለት የስዊዝ ፍራንክ ሲሆን ጨው ደግሞ የካናዳ ዶላር ሆኗል የሚል ፈትዋ ወይም የቁርአን አንቀጽ የያዙ ይመስላሉ። ስድስቱ የእሴት ወይም የተፈጥሮ የሸሪዓ ገንዘቦችን በስድስቱ የፈረንጅ ፊያቶች እንደተተኩ ተደላድላችሁ የተቀመጣችሁ ምእመናን ተጠየቁ። የየሀገራት ፊያቶች ክብደታቸው ተመሳሳይ ነው። የፈረንጆቹ ፎቶ ላይ የጸጉር እና የአፍንጫ ቅርጽ ካልሆነ ወይም ወይም ፊያቱ ላይ የተሳለው ጥንቸል እና ድኩላ ወይም ጋሻና ጦር ካልተለያየ በስተቀር ተመሳሳይ ናቸው። ወይስ ዶላር ማለት ወርቅ ነው። ስለዚህ በጃፓን የን (ስንዴ) ቢቀየር ችግር የለውም ልትሉ ይሆን? ይህን ነጥብ እንዴት ነው የምታስታርቁት? ይህንን እንደ ጨዋታ እዚህ ተነሳ እንጂ ፊያት ወርቅን “ተክቷል” ብላችሁ ከተቀበላችሁ ከዚህኛውም የባሱ ጥያቄዎች ጋር ትፋጠጣላችሁ። (ዝርዝሮቹ መ-ገንዘብ መጽሐፍ ላይ ታትመዋል)።

ይድረስ ለዑለማእ (ሊቃውንት) እና ኡመራእ (አስተዳዳሪዎች)

ከዚህ በፊት የፊያት መገበያያ መጠቀምን የሚፈቅዱ ብዙ ፈትዋዎች (ኢስላማዊ ብይኖች) ተላልፈዋል። ፈትዋዎች መሠረት አድርገው የነበረው የፊያት መገበያያ ሰፊ ተቀባይነት ስላለውና ከዚህ ውጭ መሆን ስለማንችል በሚል ነበር። ፈትዋዎቹ የተሰጡት (ALMUNAWWAR 2013)

1. ሀይአል ኪባረል ዑለማእ (ስዑዲ፣ 1979)
2. ለጅና አልፈታዋ (ኩወይት፣ 1979)
3. አልመጅማዕ አልፊቅሂ አልኢስሚ (ስዑዲ፣ 1985)
4. አልመጅማዕ አልፊቅሂ አልኢስላሚ አልዱወሊ (ኦአይሲ፣ 1986)
5. ነድዋቱል ፊቅህ (ኩወይት በይቱል ማል፣ 1987)

ይህ የመጨረሻው ፈትዋ ከተላለፈበት 30 ዓመታት ወይም የመጀመሪያው ፈትዋ ከወጣበት 40 ዓመታት ገደማ ነው ያለነው። ነገሮች ተገለባብጠው ችግሮች ከእግር እስከ አንገት አንቆ ይዞናል። እያንዳንዱ ሰው "ምንድን ነው እየሆነ ያለው" ብሎ እስኪገረም ድረስ ችግሩ በየቤታችን ገብቶአል። የሚያስተኛ አይደለም። ሊቃውንት ቀበቶአችሁ አጥብቃችሁ ተነሱ።

የተፈጥሮ የአላህ ገንዘብ እጃችን ላይ አለ። ለምንድን ነው ከአየር የቀጠነ የሌባና የጠላት ገንዘብ የምንጠቀመው? ወደ ተፈጥሮአችንና ወደ ፍትሐችን ለመመለስ የሚያስችሉ እጅግ በርካታ መንገዶች አሉ። ሀራምን (ክልክልን) ማስወገድ ብቻው በቂ አይደለም። በቦታው ሀላል (ንጹሕ-ወ-ፍቁድ) ነገር መተካት የግድ ነው።

ከላይ የጠቀስናቸው ፈትዋዎችን ስናጤን የፊያት መገበያያ የተፈቀደባቸው ምክንያቶች "አልረዋጅ (ሰፊ ቅቡልነት)" እና "አልሀጃ (የግድ አስፈላጊነት)" የሚሉትን

በአግባቡ እንዳልተፈተሹ ያሳያል። መተካት ሲባል ወረቀት ወርቅን ሊተካ ቀርቶ መዳብ ነሀስን፣ ስንዴ ማሽላን ሊተካ ይችላልን? እላይ እንዳየነው በበደል ላይ የተመሠረተ ቁጥር ወርቅን ሊተካ ቀርቶ ጭራሽ አውዳሚ በደል ነው። የዓለም ሀብት ሁሉ አስር በማይሞሉ ሀብታሞች ስር የሚጥል የቁጥር ሰንሰለት እንጂ ሕዝቡ ወዶና ፈቅዶ የሚኖረው፣ የሚያጠራቅመው፣ የሚያዘወትረው አይደለም። ምን እየሆነ እንደሆነ እንኳ የሚያውቅበት ነገር የለውም። ከስር ሆኖ ወደ ሰማይ የተቀጣጠለና ምሥጢራዊ የቁጥር ጨዋታ ነው። ወደ ሸሪዓ ብናመጣው ተከቷል ለማለት የምንችለው በሸሪዓ መዝነነው ነው። ቁጥሩ ወይም የታተመው ወረቀቱ ባንኮች እንኳ ‹‹ኖት፣ ቢል›› እያሉ ነው የሚጠሩት እንጂ ገንዘብም አይሉትም። ሸሪዓውም ሳይለው፣ ሳይንሱም ሳይጠራው በዘልማድና በስሚ ስሚ ተነስቶ ሀላል/ሀራም መበየን ከኢስላማዊ መርሆ ጋር በጽኑእ ይጋጫል።

በኢስላማዊ ሊቃውንት መካከል በስፋት የሚታወቅ መርህ አለ። “ዶሩራ (አስፈላጊ ችግር) ለማስወገድና ወደ ሀላል ለመቀየር ጥረት ሳይደረግ ተመቻችቶ መጠቀም አይቻልም” ይላሉ። የዑለማዎች ጥረት እምን ድረስ ነው? የሚታይ ነገር አለ? በእርግጥ ጉዳዩ እጅግ ውስብስብ እና ግዙፍ በመሆኑ የአንድ ጀንበር ሥራ አይደለም። በርካታ ዓመታት የሚፈጅ ሥራ ነው። በአንዴ ከፊያት ወደ ወርቅ የምንገባበት ቀላል ሥራ አይደለም። ወደ ተፈጥሮአችን እስክንመለስ ዘካችንን በፊያት መግበያያ እየከፈልን መቀጠል የግድ እንደሆነው ሁሉ በፊያት መገበያያ አየተጠቀምን ቀስ በቀስ መቀየርም የግድ ነው። አውቀነው እና “ኒያችንን (እሳቤያችንን)” አስተካክለን ማድረግና በድንቁርና መከተል የተለያዩ ነገሮች ናቸው።

ዶሩራ (አስፈላጊ ችግር) የመጀመሪያውን የኢስላማዊውን ሕግ አይሽርም። ሕጉ እንዳለ ነው። ስለተቸገርን ከችግሩ እስክንወጣ ብቻ ነው የምንጠቀመው።

አስፈላጊነቱም ቢሆን የማይካድ ነው። ሆኖም ግን ፈልገን ሳይሆን ተገደን ነው። ሙስሊም ግን ነጻ አእምሮ ነው ያለው። ባርነቱ ለአላህ ነው እንጂ ለፍጡራን አይደለም። ነጻነቱን ሁል ጊዜ ይፈልገዋል። ነጻነት ግን በነጻ አይገኝም። ትግል ይፈልጋል።

በመጨረሻም ሊቃውንትና መሪዎች አላህ ፊት ሊያስጠይቃችሁ የሚችል፣ እንቅልፍ የማያስተኛ፣ ከራስ ጸጉር እስከ እግር ጥፍር ጠፍሮ የያዘን፣ ነፍሳችንም ጭምር የወሰደብን፣ አእምሮአችንን ባተሌ ያደረገብን፣ ነጻ ፍጡርን በባርነት ቀንበር ሥር ያሳደረ ጉዳይ ጋር ተጋፍጠናል። ታሪኮቹን በደንብ ፈትሹ። ያለፉ ፈትዋዎችን አጢኗቸው። እጃችሁ ላይ መፈተሻ ኢስላማዊ ዕውቀት አለ። ይህ አነስተኛ ጽሑፍ ሲዘጋጅ እንደመፍትሔ ለመቁጠር ሳይሆን ለዑለማው ጥያቄ ለማቅረብ ነው። ምን እናድርግ? ሕዝቡ እናንተን እየጠበቀ ነው። **ጥያቄው ወደ እናንተ ተሻግሮአል። ጽሑፉ ተጀመረ እንጂ አልተፈጸመም።**

ኤፒሎግ፡- የእጅ ሥራ ትምህርት እና ፋይናንሻል ኢምፔሪያሊዝም

(የዓለም የገንዘብ ስሪት ምንነት የሚገልጽ ጥሩ ምሳሌ)

በ1970ዎቹ በገጠር የአንደኛና መለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ስንማር ለእጅ ሥራ ትምህርት ማሟያና ለወላጆች በዓል ቀን (ሰኔ 30) የሚሸጥ ዕቃ ሠርተን እናቀርብ እና ለልፋታችን ከመቶ የሚያዝ ማርክ ይጻፍልን ነበር።

አንደኛ ደረጃ ትምህርት በነበርንበት ወቅት ሴቶች ተማሪዎች ዳንቴል ሲሠሩ ወንዶች ተማሪዎች ደግሞ የሹራብ ኮፍያ እንሠራ ነበር። ድህነት በገጠር እጅግ የከፋ በመሆኑ ክር በግዢ ለማግኘት ስለማይታሰብ አሮጌ ሹራብ ካገኘን እሱን እንቀራመታለን። አማራጭ ያጣ ተማሪ የተሰጣ ሹራብ ሊሰርቅ ይችላል። ይልቅ ከከፋ ግን የለበስነውን ሹራብ ከታች ከጉልበታችን ወይም እንደርዝመቱ ከጭናችን በኩል ጀምረን እስካስኬደን ድረስ እስከእምብርትም እስከደረትም እንፈታው ነበር።

ትዝ ይለኛል አንዴ “በአዝመራ የልማት ዘመቻ” ምክንያት ለነኛ ሴሚስተር ፈተና አጣድፈውን ማርክ ላለማጣት ሹራቤን እስከ እምብርቴ ተልትዬ ፈትቼ ኮፍያ ሠርቼ አስረክቤያለሁ። በ1978 ኢ.አ. የ4ኛ ክፍል የውጤት ካርዴ ላይ “የእጅ ሥራ” የሚለው ላይ አንደኛ ሴሚስተር 50 ከመቶ ሁለተኛ ሴሚስተር 45 ከመቶ ይላል። የሚገርመው ግን የክፍል ደረጃዬ 1ኛ ይላል። በሁለተኛ ሴሚስተር ወደ 3ኛ ጎትቶኝ በአማካይ ውጤት 2ኛ ወጥቻለሁ። የእጅ ሥራ ከፍተኛ ያገኘሁት በ1980 6ኛ ክፍል ሆኜ ነው። እሱም 76 እና 70 ከመቶ አምጥቻለሁ። ደረጃዬ እንደተለመደው ከነኛ እስከ ሦስተኛ በታች አይወርድም። እጅሥራ ግን ሁል ጊዜ እንደጎተተኝ ነበር። እነዚህን ማርኮች የማገኘው ሹራቤን እየተለተልኩም ጭምር ነበር። ያው ልጆች ስለነበርን ሀፍረታችን ታየ አልታየ ብዙም አሳሳቢ አይደለም።ምናልባት የኔ ወላጆች

አዲስ አበባ ነዋሪ ስለነበሩ ባለኪስ ቁምጣ የምለብሰው እኔ ብቻ ሳልሆን አልቀርም። ቢታይ እንብርቴን ነው ብዬ ተልትያለሁ።

የሹራብና ዳንቴል መሥሪያ የብረት ኪሮሽ (በጉራጊኛ "ወሌምባ") ያየሁት የከተማ አራድነቴ በገጠር ግዞት ተሰርዞ "ፎርማት" ሆኖ "ጥርብ ፋራ" ሆኜ አዲሳባ ስመጣ ነበር። የኛ የገጠር ኪሮሻችን የጃርት እሾህ ነበር። "ፉጋ" የሚባሉ አዳኞች ጃርት ሲገድሉ፤ ለኪሮሽ የሚሆን የጃርት ልብስ (ሾህ) ነቅለው ይሰጡን ነበር። አንዳንዴም የተነቀለ "ወሌምባ" ጫካ ውስጥ እናገኛለን። ጫፉን በእሳት እናሞቀውና ቆልመም ስናደርገው ኪሮሽ ይሆንና ኮፊያም ይሁን ዳንቴል እንሠራበት ነበር። የወሌምባውን ጫፍ በመቆልመም እና ኪሮሽ መሥራት የሚያክለኝ አልነበረም።

የኮፊያና የዳንቴል ተፈላጊነት ሲቀንስ ትምህርት ቤቶች ከዘንባባ የሚሠራ ኬሻ ምንጣፍ፣ ዘንቢልና ባርኔጣ ማሠራት ጀመሩ። ለግብዓት የሚሆነውን የዘንባባ ዝንጣፊ የምንጠቀመው የዘንባባው ውስጠኛው ሙሽራውን ነበር። ይህንን ለማግኘት እና ለመቁረጥ ከጃርት እሾኽ ያልተናነሱ የዘንባባ እሾኾቹን ማቋረጥ ይጠይቃል። እጆቻችችን ተወጋግተው ፈንጣጣ የያዘው ፊት ይመስል ነበር።አንድ ጊዜ አያቴ በቅርብ "ከጉማጅ የመኪና ባሌስትራ" አስቀጥቅጠው ያሰሩትን ምርጥ ማጭዳቸውን ደብቄ ይዤ ለእጅ ሥራ ትምህርት ዘንባባ ለመቁረጥ አስፈሪ እና ያልተነካ ጫካ ውስጥ ገባን። አሪፍ ዘንባባ አግኝተን እየቆረጥን እያለ በታሪኬ አይቸው የማላውቀው ግዙፍ እባብ እየተምዘገዘገ እና በዘንባባው የተፈጥሮ ዳስ እየተንሻለለ ወደምቆርጠው ዘንባባ ሲገባ ማጭዱን ትቼ "ዋአአአይ" ብዬ እራሴን እስክስት ሮጫለሁ።

አባባ (አያቴ) በጣም ስለሚያምኑኝ እና ከልጆቻቸውም በላይ ስለሚወዱኝ ማጭዳቸውን የእባቦች ጫካ ውስጥ ትቼው እቤት መምጣትና ፊታቸውን ማየት

ከበደኝ። ስናጠፋ ከሚጋረፈው አባቴ ይልቅ የማይገርፉኝ አያቴን ነበር የምፈራውና የማከብረው። ወደ ጫካው ተመልሼ መግባት ሁሉ ፈራሁ። ልጅ ነኝና አልቅሼ ጓደኞቼን ለምኜ ተመልሰን ገባን። ስንገባ እባቡ እራሱ ይሁን ሌላ አላውቅም ገብቶ አላለቀም። በርቀት ቆመን ገብቶ ሲያልቅ በረጅም እንጨት ማጭዱን ለማውጣት ሞከርን። የባሰ ወደ ውስጥ ለመውደቅ ተመቻቸ። እንደምንም ተባብረን ትንሽ አፈናጥረን ወደ ውጭ አድርገን በእንጨት ለማውጣት የማይሞች ሲሆን ጓደኞቼ "የራስህ ጉዳይ" ብለው እብቡን ፈርተው ሮጡ።

እባብ ያየህ ቀን ክር ሲነካህ እባብ የነካህ ይመስልሀል። እኔ የአባባን ፊት ከማየት የሚሻለኝን ሳሰላስል የአእዋፍ ድምጽ መስሚያ ፋታ አገኘሁ መሰለኝ ይብስ ተረበሸኩ። ለካ ጫካ ውስጥ ነኝ። ጫካው ደግሞ የአቦሸማኔና አነር መዋያ ነው። ምን አቅብጦን እንደገባንም አላውቅም። እነሱን ሳስብ እባቡን ረሳሁት። አሁን የቆምኩበት ቦታ መቸም ቢሆን ተመልሼ እንደማልገባ እርግጠኛ ሆንኩ። ከዚህ በላይ ለማሰብና ለማሰላሰል ሰኮንዶች መቆየት አልችልም። ጅልነት ይሁን ልጅነቴ ይዞኝ አላውቅም፤ እጄን ሰድጄ ማጭዱን ይገፍ ከቅድሙ ባልተናነሰ ሮጥኩኝ። ውጪ ተረጋግቼ ሳየው እጄና እግሬ በዘንባባ እሾህ ክፉኛ ደምቶአል። ልቤ የሚመታ ሳይሆን እንደ ሞተር የሚሾር ነው የሚመስለው። ልብ በኃይል ሲመታ አንደበት እንደሚታፈን እና ዓይን እንደሚፈጥ ያኔ ነው የተረዳሁት።

በዚህ ስቃይ የቆረጥነውን እንዲደርቅ የቤት ጣራ ላይ እንሰቅለዋለን። እነሱ ደግሞ "የሳር ቤት ክዳን ትበሱብኛላችሁ" በሚል ከወላጆች ጋር ጸብ ነው። ከአጥር ይልቅ ጣራ ሚመረጠው ቶሎ ለመድረቅ ብቻ ሳይሆን ለሌባ አይመችም። በአጥርም በጣራም ለወር ያህል ከደረቀ በኋላ የተወሰነውን ቀለም እንነክራለን። ቀለም የምንነክረው እናቶች ሩቅ ገበያ በሄዱበት ሰዓት ድስት ሰርቀን ነው። ድስቱን በማገዶ

እንጨት ጥደን ዘንባባውን እንጨምርና እንቀቅለዋለን። ከድርቀቱ ለዘብ ሲል ቀለም ጨምረን ከድነን ቀለሙ ሲይዝ አውጥተን ምንም እንዳልሠራን ነገር ድስቱን አጥበን በቦታው ላይ እንሰቅላለን። ወንዝ ወርደን ጣቶቻችንን በሳሙናም ይሁን በእንዶድ ፈትገን እናጥባለን። ብዙ ጊዜ እንደ ምርጫ ቀለም እስከሳምንትም አይለቅም። ብቻ ልፋቱ አንድ መጽሐፍ ያጽፋል።እጅግ አሳዛኝ እና ዘግናኝ በሆነ ልፋት የእጅ ሥራ ከሠራን በኋላ ስናስረክብ መምህራኖቹ ካልጣማቸው እጅሥራውንም እኛንም በካልቾ ይጠልዙናል። በቀኝ እግር እኛን "ቺ" በግራ ዘንቢሉን! እያለቀስን ወደቤት! ከዚያ እቤት ዘንቢል ከገበያ ግዙልን ብለን እዬዬ። በኮፍያ ዘመን በሹራባችን መቀደድ፤ በንዘቢል ዘመናት ደግሞ ከብቶቻችንን ትተን ለዘንባባ በተሰማራንበት ከብቶቹ ከሰው ማሳ ገብተው እህል ያበለሻሹና ይታሠራሉ። ወላጆች ደግሞ "ስትጫወቱ ሂደውባችሁ ነው" ብለው ይገርፉናል። ደግነቱ እኔ ከማይጋረፉ አያቴ ጋር ስላደግኩ አልተመታሁም እንጂ!

የዕጅ ሥራው ተቀባይነት ካገኘ እንደመምህሩ ሙድ 50ም 70ም ማርክ ሰርተፊኬታችን ላይ ይጻፍልናል። በቃ! ይኸው ነው። ከዚያም ምርጥ ምርጡን የእጅ ሥራዎች መምህራን ይወስዱታል።የተወሰነውን ለወላጆች በዓል ቀን ለትምህርት ቤቱ "ገቢ" ይሸጣል።የራሳችንን ዘንቢልም ይሁን ዳንቴል፣ ኮፍያም ይሁን ኬሻ በገንዘባችን ብናገኝ በስንት ጣእሙ። ያው እንግዲህ ለልፋታችን የቁጥር ማርክ ተጽፎልናል።

===== ~~~ ፋይናንሻል ኢምፔሪያሊዝም ~~ =====

የዓለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅቶች አሠራር ልክ እንደዚህ ነው።ስንት ሰው ሞቶበት የተቆፈረ ማዕድንና ነዳጅ ኢምፔሪያሊስቶቹና ባንከሮቹ ለባለማዕድኖቹ ለልፋታቸው ውጤት ባንክ ላይ ቁጥር ይጽፉላቸዋል። ወይም ቁጥርና ፎቶ ያለበትን

ወረቀት ይሠጧቸዋል። “ገንዘብ” ብለውታል። ለፊው ይለፋል። የፋይናንሻል ኢምፔሪያሊስቶች ሥራ ግን ወረቀት አትሞ መስጠት ነው።

ይህ ችግር ላይኖረው ይችል ነበር የሚባለው ዶላር አታሚዎች በተመረተ ምርት ልክ የሚጨበጥ ነገር ቢያንስ ወርቅ እንኳ በባንክ በአደራ ቢያስቀምጡ ጥሩ ነበር። ከ1971 በፊት ዶላር የሚታተመው በተቀመጠ ወርቅ ልክ ነበር። ዶላር ይዞ ለሄደ ሪዘርቭ ባንኮቹ ወርቅ የመክፈል ግዴታ ነበረባቸው። ግን ጉልበት ወርቅን ተካ።

አሁን እኛ በጥቃቅን አጀንዳዎች እንታኮስ ይሆናል። ግን አንኳሩን ጉዳይ ስናየው ያመረትነውን ምርት ለኢምፔሪያሊስት ወረቀት ነው የምንገብረው። የኢኮኖሚውንም የፈትዋዉንም (ብይኑን) አቅጣጫ አዙረውታል። ትንሽ እንኳ እንዳንንቀሳቀስ ወረቀቱም ወለድ አለው ብለው ሸባ አድርገው አስቀምጠውናል። ቁርአንና ሀዲሱን ትተን ከሆነ ሀገር የሚመጣ ፈትዋም እንደ ቁርአንና ሀዲስ እንወስዳለን። ዓለመል ኢስላም እምጥ የሆነ ስምጥ ውስጥ ገባ።

አሜሪካንን ያሳደገው የስዑዲ ፔትሮዶላር ነው።በአሜሪካ ወርቅ ድጋፍ ሲንቀሳቀስ የነበረው ዶላር በስዑዲ ነዳጅ ድጋፍ እንደገና አንሰራራ። እኛን ሙስሊሞቹ ግን የቁልቁለት መንገድ ተያያዝነው። ኢምፔሪያሊስትና ሽይጧን ጠላቶቻቸው ላይ ምንም ርህራሄ የላቸውም። ይኸውነው። ታሪክ ሳይሆን በዓይናችን በብረቱ የምናየው ዕለታዊ ክስተት ነው።ቢረፍድም ግን ዳግም መነሳት እንችላለን። እንታገላለን። ድል ግን በአላህ እጅ ነው።

መደምደሚያ፡-

የኢስላማዊ የኢኮኖሚ ሲስተም የራሱ የሆኑ መነሻ፣ ማካሔጃና ውጤት አላቸው። ከሌሎች ኃይማኖቶችና አስተሳሰቦች ብዙ የሚጋሩት ነገሮች እንዳሉት ሁሉ የሚለዩበትም አላቸው። በእስልምና ንግድ የተቀደሰና ከአምልኮዎች ውስጥ የሚመደብ ተግባር ነው። መንፈሳዊ ምንዳ ያስገኝ ዘንድ በንጽሕና መከወን ይኖርበታል። ንጽሕና ሲባል ከአራጣ፣ ከስርቆት፣ ከማታለል፣ ከማጭበርበር፣ ያልተገባ ትርፍና ውድድር ውስጥ ከመግባት፣ በተለይ የምግብ ዘሮችን በመጋዘን ከመከዘን፣ ከጉቦ፣ በሌላ ሰው ግብይት ላይ አጉል ጣልቃ ገብቶ ደርቦ ከመገበያየት፣ ከምቀኝነት፣ ከመሃላና ንግድን ሊያቆሽሹ ከሚችሉ ነገሮች አጽድቶ መገበያየት ያስፈልጋል

ነቢዩ ሙሐመድ ﷺ ካስተማሩት ውስጥ የሚከተለውን ሀዲስ እንይ፡-

“ዕውነተኛና ታማኝ ነጋዴ ምድቡ ከነቢያት፣ ከሲዲቆች (ዕውነተኞች) እና ሰማዕታት ጋር ነው። (ሱነን ቲርሚዚይ)

عَنْ أَبِي سَعِيدٍ عَنْ النَّبِيِّ صَلَّى اللَّهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ قَالَ

التَّاجِرُ الصَّدُوقُ الْأَمِينُ مَعَ النَّبِيِّينَ وَالصِّدِّيقِينَ وَالشُّهَدَاءِ

سنن الترمذي كتاب البيوع باب ما جاء في التجار وتسمية النبي صلى الله عليه وسلم

በመጨረሻም፡- እንኳንስ ይህ በተሳሳች ተራ ግለሰብ የተጻፈ መጽሐፍ ቀርቶ የሁሉንም ነገር ፈጣሪ በሆነው አላህ የተወረደው ቁርአን እንኳ መመሪያነቱ ለፈራሂያን ነው ይላል። መፍራትን ለከጀሉ ይመራል። መጥመምን ለፈለጉ አይመራም። የቅናቻ እንጂ የጥሜት መጽሐፍ አይደለም እንደማለት ነው። ምሳሌውን እዚህ ሳመጣው አገላለጽ አጥሮኝ ቢያስረዳልኝ በሚል ነው። ይህ መጽሐፍ የተዘጋጀው የማውቀውን ለማሳወቅ እና አላህ ዘንድ ከጥየቃ ለመዳን በመከጀል፣ እንዲሁም ሰዎችን ለመጥቀም በማሰብ ብቻ ነው። ከእኔ በተሻለ የሚገልጹ ሰዎች እንዲያስፋፉት፣ ከእኔ በዕውቀት የበለጡ ሰዎች በርዕሱ ላይ ብዙ እንዲጽፉ ምኞቴ ነው። አንብበው ከሚጠቀሙ ያድርገን።

=== ተፈጸመ ===

الحمد لله رب العالمين

اَللَّهُمَّ صَلِّ وَسَلِّمْ وَبارِكْ عَلىَ سَيِّدِنا وَمَوْلاَنا مُحَمَّدٍ شَجَرَةِ اْلاَصْلِ النُّوْرَانِيَّةِ، وَلَمْعَةِ الْقَبْضَةِ الرَّحْمَانِيَّةِ، وَاَفْضَلِ الْخَلِيْقَةِ اْلاِنْسَانِيَّةِ، وَأَشْرَفِ الصُّوْرَةِ الْجِسْمَانِيَّةِ، وَمَعْدِنِ اْلاَسْرَارِ الرَبَّانِيّةِ، وَخَزَائِنِ الْعُلُوْمِ اْلاِصْطِفَائِيَّةِ، صَاحِبِ الْقَبْضَةِ اْلاَصْلِيَّةِ، وَالْبَهْجَةِ السَّنِيَّةِ، وَالرُّتْبَةِ الْعَلِيَّةِ، مَنِ انْدَرَجَتِ النَّبِيُّوْنَ تَحْتَ لِوَائِهِ، فَهُمْ مِنْهُ وَاِلَيْهِ، وَصَلِّ وَسَلِّمْ وَبارِكْ عَلَيْهِ وَعَلىَ آلِهِ وَصَحْبِهِ عَدَدَ مَاخَلَقْتَ، وَرَزَقْتَ وَأَمَتَّ وَأَحْيَيْتَ اِلَى يَوْمِ تَبْعَثُ مَنْ أَفْنَيْتَ، وَسَلِّمْ تَسْلِيْماً كَثِيْراً وَالْحَمْدُ لِلهِ رَبِّ الْعَالَمِيْنَ

አሚን

ዋና ዋና ዋቢ መጻሕፍት

1. *A PREMIER ON ISLAMIC FINANCE; Bala Shanmugam, Zaha Rina Zahari; The Research Foundation of CFA Institute; December 2009. (ለምዕራፍ ሦስት የ"ኢስላማዊ ባንክ" ቀጥተኛ ምንጭ)*
2. *B. M. ANDERSON; JR., PH.D, THE VALUE OF MONEY, THE MACMILLAN COMPANY, New York, 1917*
3. *Cai Tianxin, Perfect Numbers and Fibonacci Sequences, Zhejiang University, China, 1963, Translated by Tyler Ross New York, World Scientific Publishing Co. Pte. Ltd., USA, 2022. ISBN 9789811244070 (hardcover)*
4. *CHARLES A. LINDBERGH, Banking and Currency and The Money Trust, C.A. LINDBERGH, LITTLE FALLS, MINNESOTA, 1917.*
5. *David Orrell and Roman Chlupatý; The evolution of money; New York Columbia University Press; 2016; Page 45; ISBN 978-0-231-54167-1*
6. *David Park, The Grand Contraption: The World as Myth, Number, and Chance, Princeton University Press, 2007, ISBN: 9780691130538*
7. *Edward B. Burger, Zero to Infinity; A History of Numbers, The Teaching Company, 2007, ISBN: 9781598033762.*
8. *Fred Moseley, Marx's Theory of Money: Modern Appraisals, PALGRAVE MACMILLAN Houndmills, Basingstoke, Hampshire RG21 6XS and 175 Fifth Avenue, New York, N.Y., 2005, ISBN 1–4039–3641–2*
9. *INTEREST, Maulana Syed Abul a'la Mawdudi, Translated to English by: Dr. Maaz Amjad and Arshad Shaikh, Markazi Maktaba Islami Publishers, New Delhi, December 2015. (የካፒታሊዝም፣ የሶሺያሊዝምና የኢስላም የኢኮኖሚ አይዲዮሎጂዎችን ለማነጻጸር እንድ ምንጭ አገለግሏል)*

10. James Buchan, Frozen Desire: The Meaning of Money, Farrar Straus & Giroux, New York, 1997, ISBN: 1-56649-180-0.
11. John Smithin, What is Money?, Routledge International Studies in Money and Banking, Routledge, Year: 1999, ISBN: 0-415-20690-1 (Print Edition)
12. National Bank of Ethiopia Annual bulletin 30 June 2022
13. Sisay Debebe, Endale Gebre, and Tadesse Kuma, Yield Gaps and Technical Inefficiency Factors for Major Cereal Crops in Ethiopia: Panel Stochastic Frontier Approach, Ethiopian Journal of Economics, Volume 31 Number.
14. Solomon Tsehay, Zewdie Adane and Adem Feto (2022), Agriculture-Industry Linkages for Employment and Economic Transformation in Ethiopia, Ethiopian Journal of Economics, Volume 31 Number.
15. Stefano Battilossi, Youssef Cassis, Kazuhiko Yago; Handbook of the History of Money and Currency; Origins of Money and Interest: Palatial Credit, Not Barter, ISBN 978-981-13-0595-5
16. THE DAZZLING PROOF FOR THE RETURN OF OUR PURE MONEY, Asatizah of Almunawwar (Ustaz Muhammad Deros (Al-Azhar University, Ustaz Amiruddin bin Muhammad Zain (Al-Azhar University, Ustaz Muhammad Faisal Bin Muhammad Ayub (National University of Malaysia); 2013 Pdf (የምዕራፍ አንድ ቀጥተኛ ምንጭ)
17. THE END OF ECONOMICS, Umar Vadillo, Madinah Press, 1991. (ለአንደኛው ምንጭ ማጠናከሪያ)
18. THE RETURN OF THE GOLD DINAR, Umar Ibrahim Vadillo, Bookwork Press, United Kingdom, December 1996. (ለአንደኛው ምንጭ ማጠናከሪያ)
19. UNDERSTANDING ISLAMIC FINANCE; Muhammed Ayub; John Wily & Sons Ltd; 2007. (ለአራተኛው ምንጭ ማጠናከሪያ)

20. ቅዱስ ቁርአን የአማርኛ ትርጉም፣ ሸኽ ሲይድ ሙሐመድ ሳዲቅ እና ሐጂ ሙሐመድ ሳኒ ሐቢብ፣ ነጃሺ አሳታሚ ድርጅት፣ ሁለተኛ እትም 1997. (የቁርአን ትርጎሞች ብቸኛ ምንጭ)

21. ዓብዱልቃዲር ኑረዲን፣ መ-ገንዘብ፡ ከዘ-ፍጥረት እስከ ዘመናችን፣ 3ኤስ ማተሚያ ቤት፣ 2015 ኢ.አ.

22. እስልምናና ተግባራቱ፣ ሀጂ ሰዒድ ዩሱፍ መንሱር፣ መርዋ አሳታሚ ድርጅት፣ 2003 (የኢስላማዊ ገበያ ሥርዓት ማጠናከሪ ምንጭ)

23. የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የኢንዱስትሪ ልማት ስትራቴጂ፣ በማስታወቂያ ሚኒስቴር የፐሬስና ኡዲዮቪዝዋል መምሪያ፣ ሜጋ አሳታሚ፣ 1994. (ለመጽሐፉ ሐገራዊ ማዕቀፎች ቀጥተኛ ያልሆነ ምንጭ)

24. የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የደሕንነትና የውጭ ጉዳይ ስትራተጅ፣ በማስታወቂያ ሚኒስቴር የፐሬስና ኡዲዮቪዝዋል መምሪያ፣ ሜጋ አሳታሚ፣ 1994. (ለመጽሐፉ ሐገራዊ ማዕቀፎች ቀጥተኛ ያልሆነ ምንጭ)

ከመ-ገንዘብ፡ ከዘ-ፍጥረት ኣሰከ ዘ-መናቸን መጽሐፍ የተወሰደ የነፃ የግል ባንኮች የብድር ሁኔታ በየዘርፉ ለማብርና የተመደበው ብድር ነው።

PRIVATE COMMERCIAL BANKS (ETH)

SUMMARY BY LOAN (FINANCING)

AS OF 30 JUNE 2021

#	NAME OF BANKS	OTHERS	Agro.	HOTEL	Transp.	Staff	Personal	IFB	IMPORT	Const.	Bldg &	Manuf.	EXPORT	Trade	Domestic	TOTAL OUTSTNDG
1	Abay Bank S.C.		124,166	436,466	1,127,024				4,277,587	3,274,453	1,588,643	4,277,587	5,056,475	20,162,400		
2	Addis International Bank		4,885		29,490	29,197	19,350		292,627	844,673	543,431	1,849,762	919,649	4,533,064		
3	Awash International Bank		338,670		2,250,100	2,708,137	6,244,374	2,120,280	10,190,725	18,091,986	10,470,171	17,625,711	17,499,132	87,539,286		
4	Bank of Abyssinia		2,742,179		1,516,613		2,019,007	392,738	4,065,756	8,504,387	13,928,759	27,156,717	16,260,503	76,576,659		
5	Berhan International Bank		69,493	417,496	365,516	1,202,324	1,364,992		1,366,483	4,047,912	2,008,330	1,137,112	5,843,370	17,822,028		
6	Bunna International Bank		60,604		664,619	844,193			4,804,385	3,148,266	946,595	4,804,385	3,019,178	18,292,224		
7	Cooperative Bank of Oromia		505,233			1,928,373		7,816,229	1,930,830	2,124,341	9,088,737	11,927,928	19,181,708	54,503,379		
8	Dashen Bank	1,105,763	381,071	415,388	1,518,366	2,860,817	4,186,537	2,256,056	2,404,352	8,366,417	14,452,596	8,355,219	17,945,763	64,248,345		
9	Debub Global Bank		20,717		96,404	258,203	86,239		782,833	958,687	659,223	3,179,395	2,334,426	8,376,127		
10	Enat Bank		98,441		521,480	289,977	65,439		774,530	1,749,696	1,443,020	2,873,081	1,266,482	9,082,146		
11	Hibret Bank		106,432	1,335,571	883,722	1,458,619	336,010	1,012,511	7,337,514	4,662,611	7,038,842	5,523,635	6,187,134	35,882,601		
12	Lion International Bank		139,787	913,075	272,276	373,144			4,287,199	2,016,651	1,218,920	8,268,772	5,438,175	22,927,999		
13	Nib International Bank	212,192	186,990	4,232,510	755,075		665,752	-	3,912,069	6,367,280	5,919,780	6,160,726	6,072,472	34,484,846		
14	Oromia International Bank	92,273	290,130	1,415,178	320,102	2,149,051	134,808	3,542,349	1,839,061	1,752,911	2,429,502	4,684,710	7,101,806	25,751,881		
15	Wegagen Bank			1,109,082	1,185,967			361,866	3,542,099	3,921,198	4,009,083	7,756,109	5,406,287	27,291,691		
16	Zemen Bank		196,522	2,023,316	132,475	490,185	779,448		1,102,619	1,174,283	3,217,011	2,349,766	2,791,463	14,257,088		
	TOTAL	1,410,228	5,265,320	11,189,000	11,562,344	15,778,187	15,901,956	17,492,029	52,910,668	71,005,752	78,962,643	117,930,614	122,323,023	521,731,764		
	PERCENTAGE	0.27%	1.01%	2.14%	2.22%	3.02%	3.05%	3.35%	10.14%	13.61%	15.13%	22.60%	23.45%	100%		

Figure 2.1 (source): Translated from Amharic book "Ma-genzeb from Genesis to Today" (Abdulkarir Nureddin (2023)